ወዲያው ወንሳ ወንድ ልጅ ወሰደች ፤ 14 የኰረ
ቤትም ሴቶች ናዖሚን እንዲህ አሉአት ፦
"የሚጦርሽን የልጅ ልጅ ሰሰ ሰጠሽ እግዚአ
ብሔር የተመሰገነ ይሁን ፤ እግዚአብሔር
ይሁን ልጅ በእስራኤል ዝነኛ ያድርገው ።
15 ምራትሽ በጣም ትወድሻሰች ፤ ሰባት ልጆች
ከሚያደርጉልሽ የበለጠ አድርጋልሻሰች ፤
አሁን ደግሞ ሕይወትሽን የሚያድሰልሽና በአ
ርጅናሽ ወራት የሚጦርሽን ወንድ ልጅ ወል
ዳልሻሰች ።"
16 ናዖሚም ይሁን ሕፃን ልጅዋ አድርጋ ዘመ
ቀበል አቀፈችው ፤ ተከባከባም አሳደገችው ።

17 የኰረቤት ሴቶች ልጁን "ኢዮቤድ"
ብሰው ስም አወጡሰት ፤ "ሰናዖሚ ወንድ ልጅ
ተወሰደሳት!" እያሱም ሰሰው ሁሱ አወሩ ።
የንጉሥ ዳዊት አባት የሆነውን እሴይን የወ
ሰደ ይኸው ኢዮቤድ ነው ።
18-22 ከፋሬስ እንሥቶ እስከ ዳዊት ያሰው
የትውልድ ሐረግ የሚከተሰው ነው ፤ ፋሬስ
ሔጽሮንን ወሰደ ፤ ሔጽሮን አራምን ወሰደ ፤
አራም ወሚናዳብን ወሰደ ፤ ሠሚናዳብ ነአሶንን
ወሰደ ፤ ነአሶን ሳልሞንን ወሰደ ፤ ሳልሞን ቦዔ
ዝን ወሰደ ፤ ቦዔዝ ኢዮቤድን ወሰደ ፤ ኢዮቤድ
እሴይን ወሰደ ፤ እሴይም ዳዊትን ወሰደ ።

መጽሐፈ ሳሙኤል

ክፍል አንድ

መግቢያ

መጽሐፈ ሳሙኤል ክፍል አንድ ፣ እስራኤል ከመሳፍንት አገዛዝ ወደ ንጉሣዊ መንግሥት የተሸጋገረችበትን ሁኔታ ይገልጣል ፤ ይህ ለውጥ በእስራኤል ብሔር አቀፍ ሕይወት ውስዋ ሊካ ሄድ የቻለው አብዛኛውን በሦስት ሰዎች ምክንያት ነው ፤ እነርሱም ፦ አንደኛው ከመጨረሻ ዎቹ ታሳላቅ መሳፍንት አንዱ የነበረው ሳሙኤል ሲሆን ፣ ሁስተኛው የእስራኤል የመጀመሪያ ንጉሥ የነበረው ሳኦል ነው ፤ ሦስተኛው ደግሞ ወደ ሥልጣን ከመውጣቱ በፊት የነበረው የመ ጀመሪያ ታሪኩ ከሳሙኤልና ከሳኦል ታሪክ ጋር የተጣመረው ዳዊት ነው ።

የዚህ መጽሐፍ ዋና መልእክት በብሎይ ከዳን እንደሚገኙት እንደ ሌሎቹ የታሪክ መጻሕ ፍት ሁሉ ፣ ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን በረከትንና የኑሮ መሳካትን እንደሚያስከትል ፣ ያስ መታዘዝም ውድቀትንና ጥፋትን እንደሚያመጣ ያሳያል ። ይህም እግዚአብሔር ለካህኑ ለዔሊ ፦ "እኔ የሚያከብሩኝን አከብራለሁ ፤ የሚንቁኝንም አዋርዳለሁ" በማለት በተናገረው ቃል ግልጥ ሆኖ ይታያል (2 ፡30) ።

ይህ መጽሐፍ ስለ ንጉሣዊ መንግሥት አመሠራረት የነበረውን የተለያየ ሰሜት ይገልጣል ፤ ቀደም ሲል የእስራኤል አውነተኛ ንጉሥ እንደሆነ የሚታወቀው ራሱ እግዚአብሔር ነበር ፤ ነገር ግን ዘሃያት ብሎ ከሕዝቡ በተነሣው ጥያቄ መሠረት ፣ እግዚአብሔር ለእነርሱ ንጉሥ መረ ጠላቸው ። ያም ሆነ ይህ ዋናው ቁምነገር ፤ ንጉሡም ሆነ ፣ የእስራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር የበላይነትና ፈራጅነት ሥር መገኘታቸው ነው (2 ፡7-10) ። ይህም በእግዚአብሔር ሕግ ሥር ሀብታሞችም ሆኑ ድኾች የሰዎች መብት በትክክል መከበር እንዳለበት የሚያመለክት ነው ።

ምዕራፍ 1

ሕልቃናና ቤተሰቡ በሴሎ

1 በኩረብታማው በኤፍሬም አገር ራማ ተብሳ
በምትጠራ ትንሽ ከተማ የሚኖር ትውልዱ ከኤ
ፍሬም ነገድ የሆነ ፣ ሕልቃና ተብሎ የሚጠራ
አንድ ሰው ነበር ፤ የአርሱም አባት ይሮሐም
ተብሎ የሚጠራ የኤሊሁ ልጅ ሲሆን ፣ ከጹፍ
ጐሳ ክፍል የቶሔ ቤተሰብ ነበር ፤ 2 ሕልቃናም
ሐናና ፈኒና ተብለው የሚጠሩ ሁሰት ሚስቶች
ነበሩት ፤ ፈኒና ልጆች ነበሩአት ፤ ሐና ግን አን
ድም ልጅ አልነበራትም ፤ 3 ሕልቃና በየዓመቱ
ሁሱን ጆይ ሰሆነው አምላክ ሰመስገድና መሥዋ
ዕት ሰማቅረብ ከራማ ወደ ሴሎ ይሄድ ነበር ፤
በዚያም ዘመን ሖፍኒና ፊንሐስ ተብሰው የሚጠ
ሩት የዔሊ ልጆች የእግዚአብሔር ካህናት ሆነው
በሴሎ ያገሰግሱ ነበር ። 4 ሕልቃና መሥዋዕቱን
በሚያቀርብበትም ጊዜ ሁሱ ከመሥዋዕቱ ሥጋ
አንድ ድርሻ ሰፈኒና ይሰጣል ፤ አንዲሁም ሰወን
ዶችና ሰቤቶች ልጆችዋ ሰእያንዳንዳቸው አንዳ
ንድ ድርሻ ያድሳል ፤ 5 ሐናን ይወዳት ስለነበር
እጥፍ ድርሻ ይሰጣት ነበር ፤ ቢሆንም እግዚአብ
ሔር ልጅ ነሥቶአት መኻን ነበረች ፤ 6 እግዚአብ
ሔርም ልጅ ሰለነሣት ጣውንትዋ ፈኒና ሐናን

የሚያሰቈጣ ነገር በመፈለግ ታበሳጫት ነበር ፤ 7 ይህም ሳይቋረጥ በየዓመቱ የሚደጋገም ነገር ነበር ፤ ይኸውም ወደ እግዚአብሔር ቤት በሄዱ ቍጥር ሐና እያለቀሰች ምግብ ለመብላት እምቢ እስከምትል ድረስ ፈኒና በብርቱ ታበሳጫት ነበር ። 8 ከዚህም የተነሣ ባልዋ ሕልቃና “ሐና ሆይ! ለምን ታለቅሻለሽ? ለምንስ አትመገቢም? ለምንስ በውትር ይህን ያህል ታዝኚአለሽ? ከሰባር ልጆች ይልቅ እኔ አልበልጥብሽ ምን?” ይላት ነበር ።

ሐና ወደ እግዚአብሔር ያቀረበችው ጸሎት

9-10 አንድ ቀን በሴሎ በሚገኘው ለእግዚአብሔር ቤት በልተው ጠጥተው ካበቁ በኋላ ሐና ተነሣች ፥ ክባድ ሐዘን ይሰማት ስለነበር በመረረ ሁኔታ እያለቀሰች ወደ እግዚአብሔር ትጸልይ ነበር ፤ በዚህን ጊዜ ካህኑ ዔሊ በበሩ አጠገብ በወንበሩ ላይ ተቀምጦ ነበር ፤ 11 ሐናም እንዲህ ስትል ስእለት ተሳለች ፥ “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሆይ! እኔን አገልጋይህን ተመልከችኝ ፥ መከራዬንም በማየት አስበኝ ፥ አትርሳኝም ፥ አንድ ወንድ ልጅ ብትለጠኝ በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ለአንተ የተለየ እንዲሆን አደርገዋለሁ ፥ ጠጕሩም ከቶ አይላጭም ።”

12 ሐና በዚህ ዐይነት ጸሎትዋን በማስረዘም ብዙ ጊዜ ስለቆየች ፥ ዔሊ አፍዋን ይመለከት ነበር ፤ 13 ሐና ምንም ድምፅ ሳታሰማ ከንፈር ዋን እያንቀሳቀሰች በልብዋ በመናገር ትጸልይ ነበር ፤ ከዚህም የተነሣ ዔሊ በመጠጥ የሰከረች ስለመሰለችው ፥ 14 “እንዲህ ሰክረሽ የምትቆ ይው እስከ መቼ ነው? ይህን ሰክርሽን ወዲያ አስወግደሽ ጤናማ ሰው ሁኚ” አላት ።

15 እርስዋም እንዲህ ስትል መለሰችለት ፥ “ጌታዬ አኔ እኮ አልሰከርሁም ፥ ምንም ዐይነት የሚያሰክር መጠጥ አልጠጣሁም ፤ ነገር ግን እኔ ተስፋ ስለቈረጥሁ ኑፍሴን በማስጨነቅ ችግ ሬን ለእግዚአብሔር በማቅረብ ጸለይሁ ፤ 16 አኔን አገልጋይህን እንደማትረባ ሰካራም ሴት አድርገህ አትቍጠረኝ ፤ ይህን ያህል በማስረዘም የጸለይሁት መከራ የበዛብኝ ችግረኛ በመሆኔ ነው ።”

17 ዔሊም “በሰላም ሂጂ! የእሰራኤል አም ልክ የለመንሽውን ይሰጥሽ” አላት ።

18 እርስዋም “እኔን አገልጋይህን ዘወትር በበጎ መንፈስ አስበኝ” አለችው ፤ ከዚያም ተነ ሥታ በመሄድ ምግብ ተመገበች ፤ ሐዘንዋንም አቆመች ።

የሳሙኤል መወለድና ለእግዚአብሔር መሰጠቱ

19 በማግሥቱም ሕልቃናና ቤተሰቡ በማለዳ ተነሡ ፤ ለእግዚአብሔር ከሰገዱም በኋላ በራማ ወደሚገኘው ቤታቸው ሄዱ ፤ ሕልቃናም ከሚ ስቱ ከሐና ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገ ፤ እግዚአብሔርም ለጸሎትዋ መልስ ሰጣት ፤ 20 ስለዚህም ዘጎሳ የርግዝናዋ ወራት ካለፈ በኋላ ወንድ ልጅ ወለደች ፤ እርስዋም “ከእግዚአብ ሔር ለምኜ ያገኘሁት ነው” ስትል ስሙን “ሳሙኤል” አለችው ።

21 ሕልቃና ከቤተሰቡ ጋር ዓመታዊ መሥዋ ዕትና በተለይም ቃል የገባበትን የስእለት መሥ ዋዕት ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ አንደገና ወደ ሴሎ የሚወጣበት ጊዜ ደረሰ ፤ 22 ነገር ግን ሐና በዚህ ጊዜ አብራ አልወጣችም ፤ ምክንያ ቱም “ልጂ ጡት በሚተውበት ጊዜ እስክ ሕይ ወቱ ፍጻሜ ወደማናርበት ወደ እግዚአብሔር ቤት ወዲያውኑ አወስደዋለሁ” ብላ ለባልዋ ነግ ራው ስለነበር ነው ።

23 ሕልቃናም “ጥሩ ነው ፤ መልካም መሰሎ የታየሽን አድርጊ ፤ ጡት እስክታስጥዮውም ድረስ በቤት መቆየት ትችያለሽ ፤ እግዚአብሔር የሰጠሽን የተስፋ ቃል ይፈጽምልሽ” ሲል መለ ሰላት ፤ ስለዚህም ሐና በቤት ተቀምጣ ልጂን ታሳድግ ጀመር ።

24 ጡት ካስጣለችውም በኋላ ወደ ሴሎ ይዛው ወጣች ፤ ከእርሱም ጋር የሦስት ዓመት ኮርማ ፥ ዐሥር ኪሎ ዱቄትና አንድ አቁማዳ ሙሉ የወይን ጠጅ ይዛ ሄደች ፤ ሳሙኤልንም ገና በልጅነቱ በሴሎ ወደሚገኘው ወደ እግዚአ ብሔር ቤት ወሰደችው ፤ 25 ኮርማውንም ካረዱ በኋላ ሕፃኑን ወደ ዔሊ አቀረቡት ፤ 26 ሐናም ዔሊን እንዲህ አለችው ፥ “ጌታዬ ይቅርታ አድ ርግልኝ ፤ እኔን ታስታውሰኛለህን? እኔ እኮ አንድ ጊዜ እዚህ በፊትህ ቆሜ ወደ እግዚአብ ሔር ስጸልይ ያየኸኝ ሴት ነኝ ፤ 27 የጸለይሁ ትም እግዚአብሔር ይህን ልጅ እንዲሰጠኝ ነበር ፤ እግዚአብሔርም በጠየቅሁት መሠረት ይህን ወንድ ልጅ ሰጠኝ ። 28 እኔም ደግሞ እር ሱን ለእግዚአብሔር የተለየ ስጦታ እዲሆን አድ ርጌአለሁ ፤ ስለዚህም በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ለእ ግዚአብሔር የተሰጠ ይሆናል ።” ከዚያም በኋላ በዚያ ለእግዚአብሔር ሰገዱ ።

ምዕራፍ 2

የሐና ጸሎት

1 ሐናም እንዲህ ብላ ጸለየች ፥
“ልቡ በእግዚአብሔር ደስ ይሰኛል ፤
ክብሬም በእግዚአብሔር ከፍ ከፍ
ብሎአል ፤
እኔ በጠላቶቼ ላይ እስቃለሁ ፤
ምክንያቱም እግዚአብሔር ስለረዳኝ
እኔ እጅግ ተደስቻለሁ ።

1፡11 ፦ ዘኍ. 6፡5 ። 2፡1-10 ፦ ሉቃ. 1፡46-55 ።

2 “እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለም ፤
እርሱንም የሚመስለው ከቶ የለም ፤
እምላካችንን የሚመስልም መጠጊያ
ምሽግ የለም ፤
3 እስቲ በመታበይ አትጓደዱ ፤
የትምክሕት ንግግራችሁንም
አስወግዱ ፤
እግዚአብሔር አምላክ ሁሉን ያውቃል ፤
ሕዝብ የሚሠራውንም ሁሉ በፍርድ
ይመዝናል ።
4 የኀያላን ጦረኞች ቀስቶቻቸው ተሰበሩ ፤
ደካሞች ግን ብርታት አግኝተው
ጠነከሩ ፤
5 ቀድሞ ጠግበው የነበሩ ሕዝብ
ተርበዋል ፤
እነሆ ዛሬ ራሳቸውን ለምግብ
አሳልፈው አስከ መሸጥ ደርሰዋል ፤
ተርበው የነበሩ ግን ጠግበዋል ፤
መኻን የነበረችው ሴት
እነሆ የሰባት ልጆች እናት ሆነች ፤
የብዙዎች ልጆች እናት የነበረችው
ሴት ግን መከነች ።
6 እግዚአብሔር ይገድላል ፥ እግዚአብሔር
ያድናል ፤
ወደ ሙታን ዓለም እንዲወርዱ
ያደርጋል ፤
ከሙታንም ዓለም መልሶ ሊያወጣቸው
ይችላል ።
7 እርሱ ማደኸየትም ሆነ ማበልጸግ
ይቻለዋል ፤
እርሱ እንዱን ከፍ ፥ ሌላውን ዝቅ
ያደርጋል ።
8 እርሱ ድኾችን ከትቢያ ያስነሣቸዋል ፤
ከችግር ላይ ያነሣል ፤
ወደ ልዑላንም ደረጃ ከፍ ከፍ
ያደርጋቸዋል ፤
በክብር ቦታም ያኖራቸዋል ፤
የምድርን መሠረቶች የሠራ እግዚአብሔር
ነው ፤
በእነርሱም ላይ ዓለምን የፈጠረ እርሱ
ነው ።

9 “የሚታመኑበት ሕዝብ ሁሉ በእርሱ
ተጠብቀው ይኖራሉ ፤
ክፉ አድራጊዎች ግን በጨለማ ውስጥ
ይጣላሉ ፤
ማንም ሰው ኀይል ያለው ቢመስለውም
በራሱ ብርታት ድልን አያገኝም ።
10 እግዚአብሔርን የሚጠሉ ሁሉ ይጠፋሉ ፤
ምክንያቱም እግዚአብሔር በሰማይ
ሆኖ ያንጐዳጕዳቸዋል ፤
እግዚአብሔር በዓለም ሁሉ ይፈርዳል ፤
ለንጉሡም ኀይልን ይሰጣል ፤
የመረጠውንም ንጉሥ ድልን
አንዲቀዳጅ ያደርጋል ።”
11 ከዚህ በኋላ ሕልቃና በራማ ወደሚገኘው
መኖሪያ ቤቱ ተመልሶ ሄደ ፤ ሕፃኑ ሳሙኤል
ግን በሴሎ ቀረ ፤ በካህኑ ዔሊ ሥር ሆኖም እግ
ዚአብሔርን ያገለግል ነበር ።

የዔሊ ልጆች ክፉ አድራጎት

12 የዔሊ ልጆች ምንም የማይረቡ ክፉዎች
ነበሩ ፤ እግዚአብሔርንም አያከብሩም ነበር ፤
13 ካህናቱ ከሕዝቡ ሰለሚጠይቁትም ሰጦታ የተ
ወሰነውን ሥርዓት አይጠብቁም ነበር ፤ ይኸ
ውም አንድ ሰው መሥዋዕት በሚያቀርብበት
ጊዜ የካህኑ ተላላኪ ሦስት ጣት ያለው የብረት
ሜንጦ ይዞ ይመጣ ነበር ፤ ሥጋውን ገና ሳይበ
ስል ፥ 14 በሚቀቀልበት ታላቅ አፍላል ውስጥ
እስገብቶ ፥ ሜንጦ ይዞ የሚያወጣውን ማንኛው
ንም ዐይነት ሥጋ ወሰዶ ለካህኑ ይሰጠው
ነበር ። መሥዋዕት ለመሠዋት ወደ ሴሎ የሚ
መጡ እሰራኤላውያን ሁሉ ልክ በዚህ ዐይነት
ይበዘበዙ ነበር ፤ 15 ከዚህም በቀር የመሥዋዕቱ
ሥጋ ገና ጥሬ ሳለ ፥ ስቡ ሳይጤስ የካህኑ ተላ
ላኪ መሥዋዕት ወደሚያቀርበው በው ዘንድ
ይመጣና ሥርዓት በጐደለው አነጋገር “ለካህኑ
የምጠብስለት ሥጋ ስጠኝ ፤ ምክንያቱም ካህኑ
የሚፈልገው ጥሬ ሥጋ እንጂ የአንተን ቅቅል
ሥጋ መብላት አይፈልግም” ይለዋል ።
16 ስውየውም ሲመልስ “በሕጉ መሠረት
በመጀመሪያ ሰቡ ይጢስ ፤ ከዚያም በኋላ የምት
ፈልገውን መርጠህ ትወሰዳለህ” ያለው እንደ
ሆን ፥ የካህኑ ተላላኪ “አልፈልግም ፤ እስከዚ
ያም አልቆይም ፤ ይልቅስ አሁን ስጠኝ ፤ እምቢ
ካልህ በኀይል ነጥቂ እወስድብሃለሁ” ይለዋል ።
17 ይህም የዔሊ ልጆች ኃጢአት በእግዚአብ
ሔር ፊት እጅግ አስከፊ ሆኖ ነበር ፤ ምክንያ
ቱም ለእግዚአብሔር በሚቀርበው መሥዋዕት
ላይ ይህን የመሰለ ሥነ ምግባር የጐደለውን አቀ
ባበል ያደርጉበት ነበር ።

ሳሙኤል በሴሎ

18 ይህም በዚህ እንዳለ ሳሙኤል ገና በልጅ
ነቱ ከበፍታ የተሠራ ኤፉድ ለብሶ በእግዚአብ
ሔር ፊት ያገለግል ነበር ፤ 19 እናቱም በየዓመቱ
ባልዋን ተከትላ ዓመታዊውን መሥዋዕት ለማቅ
ረብ በሚወጡበት ጊዜ ሁሉ ታናሽ መደረቢያ
ካባ እየሠራች ታመጣለት ነበር ። 20 ዔሊም
ሕልቃናን ከሚስቱ ከሐና ጋር በሚመርቅበት
ጊዜ ፥ ሕልቃናን “ለእግዚአብሔር የተለየ አድ
ርጋችሁ በሰጣችሁት በዚህ ልጅ ፈንታ ከዚህች
ሴት ሌሎችን ልጆች ይስጥህ” ይለው ነበር ።
ከዚያን በኋላ ወደ ቤታቸው ይመለሱ ነበር ።
21 በእርግጥም እግዚአብሔር ሐናን ባረካት ፤
ስለዚህም በተጨማሪ ሦስት ወንዶችና ሁለት

ሴቶች ልጆችን ወለደች ፤ ወጣቱ ሳሙኤልም
አግዚአብሔርን እያገለገለ አደገ ።

ዔሊና ሁለቱ ልጆቹ

22 እነሆ ዔሊ በዕድሜው እርጅት ነበር ፤
ልጆቹም በእስራኤላውያን ላይ የሚያደርጉት
ከፉ ነገርና በተሰይም አግዚአብሔር በሚመሰክ
በት ድንኳን ክሚያገለግሉት ሴቶች ጋር የግብረ
ሥጋ ሩካቤ መፈጸማቸውን ሁሉ ይሰማ ነበር ።
23 ስለዚህም እንዲህ አላቸው ፥ "ስለምን ይህን
ከፉ ነገር ታደርጋላችሁ? የምታደርጉትን ከፉ
ነገር ሁሉ ከእያንዳንዱ ሰው ስምቼዋለሁ ፤
24 ልጆቼ! እንዲህ ያለው ከፉ ነገር ይቅርባ
ችሁ ፤ የአግዚአብሔር ሕዝብ ሰለ እናንተ የሚነ
ግሩኝ ሁሉ አጅግ አሳፋሪ ነው ፤ 25 አንድ ሰው
ሌላውን ሰው ቢበድል ፥ አግዚአብሔር በመታ
ደግ ሊያድነው ይችላል ፤ ነገር ግን አግዚአብሔ
ርን የሚበድል ሰው ማን ሊያማልደው ይች
ላል?"

ይህም ሁሉ ሆኖ አግዚአብሔር ሊያጠፋ
ቸው ቍርጥ ውሳኔ ስላደረገ የዔሊ ልጆች የአባ
ታቸውን ምክር ሰሰሙ አልወደዱም ።

26 ወጣቱ ሳሙኤል ግን በቁመት እያደገ ፥
በአግዚአብሔርና በሰውም ዘንድ ጸጋና ሞገስን
አያገኘ ሄደ ።

በዔሊ ቤተሰብ ላይ የተነገረ ትንቢት

27 ከአግዚአብሔር የተላከ አንድ ነቢይ ወደ
ዔሊ መጣ ፤ ለእርሱም ከአግዚአብሔር የተሰ
ጠው መልእክት አንዲህ የሚል ነበር ፥ "ዔሊ
ሆይ! የቀድሞ አባትህ አሮንና ቤተሰቡ ፥ የግ
ብጽ ንጉሥ አገልጋዮች በነበሩበት ጊዜ እኔ ለአ
ሮን ራሴን ገለጥሁለት ፤ 28 የእኔ ካህናት ሆነው
በመሠዊያዬ ላይ ዕጣን በማጠን ፥ ከእኔ ዘንድ
ምክር የሚጠይቁበትን ኤፉድ በመልበስ ያገለግ
ሉኝ ዘንድ የአሮንን ቤተሰብ ከሌሎቹ የእስራ
ኤል ነገዶች ሁሉ መካከል ሰይቼ መረጥሁ ፤
በመሠዊያዬ ላይ ከሚቃጠለው መሥዋዕትም
ሰእነርሱ ድርሻ የማግኘት መብት እንዲኖራ
ቸው አደረግሁ ። 29 ታዲያ በትእዛዜ መሠረት
ከሕዝቤ የሚቀርበልኝን መሥዋዕትና ስጦታ
ሁሉ ስለምን በስስት ዐይን ተመለከትህ? አንተ
ዔሊ! ኧረ ልጆችህን ከእኔ አብልጠህ የምታከብ
ርበት ምክንያት ምንድን ነው? ሕዝቤ ለእኔ
ከሚያቀርቡልኝ መሥዋዕት ሁሉ ምርጥ የሆነ
ውን ክፍል እየተቀበሉ በመብላት ራሳቸውን
ያወፍሩ ዘንድ የፈቀድህላቸውስ ስለምንድን
ነው? 30 የእስራኤል አምላክ የሆንሁ እኔ አግዚ
አብሔር የአንተን ቤተሰብና ጐሳ ሰዘላለሙ ያገ
ለግልኛል ብዬ ተስፋ ሰጥቼ ነበር ፤ አሁን ግን
ይህን የተሰፋ ቃል ላጸናልህ አልፈልግም ፤ ምክ
ንያቱም እኔ የሚያከብሩኝን አከብራለሁ ፤ የሚ
ንቁኝንም አዋርዳለሁ ፤ 31 እንግዲህ አድምጥ ፤
እነሆ እኔ በአንተ ቤተሰብና በጐሳህ ውስጥ የሚ
ገኙትን ወጣቶች ወንዶች ሁሉ በሞት የምቀጣ
በት ጊዜ ደርሶአል ፤ ስለዚህም በአንተ ቤተሰብ
ውስጥ ረዥም ዕድሜ የሚያገኝ አይኖርም ፤
32 እነሆ ገና ብዙ መከራ ይገጥምሃል ፤ እኔ ለሴ
ሎቹ የእስራኤል ሕዝብ በምሰጠው በረከት አስ
ቀናሃለሁ ፤* ነገር ግን ከአንተ ቤተሰብ ውስጥ
ረዥም ዕድሜ የሚኖረው አይገኝም ። 33 ይሁን
እንጂ ከአንተ ዘሮች መካከል ተርፎ በከሀንት
የሚያገለግለኝ ሰው ዐይንህን በእንባ ያፈዛል ፤
ነፍስህንም ያሳዝናል ፤ ሌሎቹ ዘሮችህ ግን በአደ
ገኛ ሁኔታ ይሞታሉ ፤ 34 ሁለቱ ልጆችህ ሖፍኒ
ንና ፊንሐስ በአንድ ቀን በሚሞቱበት ጊዜ ይህ
አኔ የተናገርሁት ቃል ሁሉ እውነት ሆኖ መፈ
ጸሙን ታረጋግጣለህ ። 35 ለእኔም በእንተ ምትክ
ታማኝ የሆነና እኔ የምወደውን ሁሉ የሚያደ
ርግ ሌላ ካህን እመርጣለሁ ፤ ለእርሱም እኔ
በምመርጠው ንጉሥ ፊት ካህናት ሆነው የሚያ
ገለግሉ ዘሮችን እሰጠዋለሁ ። 36 ከአንተ ዘሮች
መካከል በሕይወት የሚተርፍ ቢኖር እንኳ ወደ
ዚያ ካህን ዘንድ እየሄደ ሰጥ ብሎ እጅ በመን
ሣት ከእርሱ ገንዘብና ምግብ ይጠይቃል ፤ የሰ
ለት ምግብ ብቻ ሰማግኘትም ሲል ካህናትን
በረዳትነት ማገልገል እንዲፈቀድለት ይለም
ናል ።"

ምዕራፍ 3

አግዚአብሔር ለሳሙኤል ተገለጠለት

1 ወጣቱ ሳሙኤል በዔሊ የአመራር ሥልጣን
ሥር ሆኖ አግዚአብሔርን ያገለግል ነበር ፤ በዚ
ያን ጊዜ ከአግዚአብሔር የሚነገር የትንቢት
ቃልም ሆነ ወይም ከእርሱ የሚገሰጥ ራእይ አየ
ታማ በመሄዱ ብርቅ ሆኖ ነበር ። 2 በእርጅና
ምክንያት ዐይኖቹ ፈዝዘው የነበሩት ዔሊ ከዕለ
ታት በአንደኛው ቀን ሌሊት በመኝታ ክፍሉ
ተኝቶ ነበር ። 3 ሳሙኤልም የተቀደሰው የቃል
ኪዳን ታቦት ባለበት መቅደስ ውስጥ ተኝቶ
ነበር ፤ ሌሊቱም ከመንጋቱ አስቀድሞ ገና መብ
ራቱ ላይጠፋ ፥ 4 እግዚአብሔር ሳሙኤልን
ጠራው ፤ ሳሙኤልም "እነሆ አለሁ ጌታዬ!"
አለ ። 5 ፈጥኖም ወደ ዔሊ ዘንድ በመሄድ "ሰለ
ጠራኸኝ እነሆ መጥቻለሁ" አለ ።

ዔሊ ግን "እኔ አልጠራሁህም ፤ ተመልስህ
ሂድና ተኛ" አለው ፤ ሳሙኤልም ተመልሶ
ተኛ ።

6-7 አግዚአብሔርም እንደገና ሳሙኤልን
ጠራው ፤ ወጣቱ ሳሙኤል ይጠራው የነበረው

1* 2፥32 አስቀናሃለሁ ፤- ወይም "በማደሪያዬ ጠላትህን ታያለህ ።"

2፥26 ፦- ሉቃ. 2፥52 ። 2፥28 ፦- ዘጸ. 28፥1-4 ፤ ዘሌ. 7፥35-36 ። 2፥34 ፦- 1ሳሙ. 4፥11 ።

እግዚአብሔር መሆኑን አላመቀም ፤ ምክንያቱም ከዚያ በፊት እግዚአብሔር ተናግሮት አያውቅም ነበር ፤ ስለዚህም ተነሥቶ ወደ ዔሊ በመሄድ “እነሆ ስለጠራኸኝ መጥቻለሁ” አለው ።

ዔሊ ግን “ልጄ ! እኔ አልጠራሁህም ወደ መኝታህ ተመልሰህ ሂድ” አለው ።

[8]እግዚአብሔርም እንደገና ለሦስተኛ ጊዜ ሳሙኤልን ጠራው ፤ ሳሙኤልም ተነሥቶ ወደ ዔሊ በመሄድ “እነሆ ስለጠራኸኝ መጥቻለሁ” አለው ።

ከዚህም በኋላ ሳሙኤልን ይጠራው የነበረው እግዚአብሔር መሆኑን ዔሊ ተገነዘበ ፤ [9]ስለዚህም “ወደ መኝታህ ተመልሰህ ሂድ ፤ እንደገናም የጠራህ እንደሆን ‘ጌታ ሆይ ! እነሆ እኔ አገልጋይህ እስማሰሁና ተናገር’ በለው” ሲል ሳሙኤልን መከረው ። ሳሙኤልም ተመልሶ ወደ መኝታው ሄደ ።

[10]እግዚአብሔርም መጥቶ በዚያ ቆመ ፤ ከዚያም በፊት ያደርግ በነበረው ዐይነት “ሳሙኤል ! ሳሙኤል !” ብሎ ጠራው ።

ሳሙኤልም “ጌታ ሆይ ! እነሆ አገልጋይህ እስማሰሁና ተናገር” አለው ።

[11]እግዚአብሔር እንዲህ አለው ፥ “እነሆ እኔ በእስራኤል ላይ እጅግ አሠቃቂ የሆነ እንድ ነገር የማደርግበት ቀን ተቃርቦአል ፤ ያንን አሠቃቂ ነገር የሚሰማውም ሁሉ በድንጋጤ ራሱ ይዞራል ፤ [12]በዚያም ቀን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ በዓሊና በቤተሰቡ ላይ አሰቀ ድሜ የተናገርሁትን ብርቱ የማስጠንቀቂያ ቃል ሁሉ በተግባር እፈጽማለሁ ፤ [13]ቤተሰቡን ስዘላለም ለመቅጣት መዘጋጀቴንም አሰቀድሜ ነግሬ ዋለሁ ፤ ምክንያቱም ልጆቹ በእኔ ላይ ክፉ ቃል ተናግረዋል ፤ ዔሊም ይህን ሁሉ እንደሚያደርጉ ያውቅ ነበር ፤ ነገር ግን በመገሠጽ አልከለከላቸውም ፤ [14]ስለዚህ ምንም ዐይነት መሥዋዕትም ሆነ ቊርባን ቢቀርብ እንኳ ይህን የመሰለውን እሠቃቂ ኃጢአት ከዔሊ ቤተሰብ ማሰወገድ ስዘላለም እንደማይቻል በመሐላ አስታውቄ አለሁ ።”

[15]ሳሙኤልም እስኪነጋ ድረስ ተኝቶ ቆየ ፤ በነጋም ጊዜ ተነሥቶ የእግዚአብሔርን ቤት በሮች ከፈተ ፤ ያየውንም ራእይ ስዔሊ ለመንገር ፈራ ፤ [16]ዔሊ ግን ሳሙኤልን “ልጄ ! ሳሙኤል” ሲል ጠራው ።

ሳሙኤልም “እነሆ አለሁ ጌታዬ !” ሲል መለሰ ።

[17]ዔሊም “እግዚአብሔር የነገረህ ቃል ምን ድን ነው ? ከእኔ ምንም ነገር እንዳትሰውር ፤ እርሱ የነገረህን ሁሉ ለእኔ ባትነግረኝ ፥ እግዚአብሔር በእንተ ላይ ብርቱ ቅጣት ያመጣብሃል” አለው ። [18]ከዚህም በኋላ ሳሙኤል ሁሉንም ነገር ለዔሊ አሰረዳው ፤ ሰውር ያሰቀረው ምንም ነገር አልነበረም ፤ ዔሊም “እርሱ እግዚአብሔር ነው ፤ ስለዚህም መልካም መሰሎ የታየውን ነገር ያድርግ” አለ ።

[19]ሳሙኤል እያደገ ሄደ ፤ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ሰለነበር ሳሙኤል የሚናገረውን ቃል ሁሉ ይፈጽምሰት ነበር ፤ [20]ከዚህም የተነሣ በሀገሩቱ ዳር እሰከ ዳር የሚኖሩ እስራኤላውያን ሁሉ ሳሙኤል የእግዚአብሔር ነቢይ መሆኑን ዐወቁ ፤ [21]እግዚአብሔርም ከዚህ በፊት ባደረገው ዐይነት ሰሳሙኤል በሴሎ እየተገለጠለት ማነጋገሩን ቀጠለ ፤ ሳሙኤልም በሚናገርበት ጊዜ በመላው እስራኤል ተደማጭነትን አገኘ ።

ምዕራፍ 4

የቃል ኪዳኑ ታቦት መማረክ

[1]በዚያን ጊዜ እስራኤላውያን ፍልስጥኤማውያንን ሰመውጋት ወጡ ፤ ስለዚህም እስራኤላውያን ኤቤንዔዜር ተብሎ በሚጠራ ስፍራ ሰፈሩ ፥ ፍልስጥኤማውያንም አፌቅ ተብሎ በሚጠራ ስፍራ ሰፈሩ ፤ [2]ፍልስጥኤማውያንም አደጋ መጣል ጀመሩ ፤ ከከባድ ሙርነት በኋላ እስራኤላውያንን ድል በመንሣት በሙር ሜዳ አራት ሺ ሰው ገደሉባቸው ፤ [3]ከሠርነት ተርፈው ያመስጡት መደ ሰፈራቸው በተመለሱ ጊዜ የእስራኤል መሪዎች እንዲህ አሉ ፥ “ዛሬ ፍልስጥኤማውያን እኛን ድል ያደርጉ ዘንድ እግዚአብሔር ስለምን ፈቀደላቸው ? ከእኛ ጋር በመሄድ ከጠላቶቻችን እጅ ያድነን ዘንድ እንግዲህ እንሂድና የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ከሴሎ እና ምጣ ።” [4]ስለዚህም ወደ ሴሎ መልእክተኞች ልከው ዙፋኑን በታቦቱ ላይ ባሉ ኪሩቤል ያደረገ ፥ ሁሉን ቻይ የሆነ እግዚአብሔር ማርማውን የሚገልጥበትን የቃል ኪዳኑን ታቦት አስመጡ ፤ ሁሰቱ የዔሰ ልጆች ሖፍኒንና ፊንሐስም የቃል ኪዳኑን ታቦት አጅበው መጡ ።

[5]የቃል ኪዳኑም ታቦት በዚያ ሀታ በደረሰ ጊዜ እስራኤላውያን ምድር እሰከትናወዋ ድረስ ታላቅ የእልልታና የሆታ ድምፅ አሰሙ ። [6]ፍልስጥኤማውያንም ያንን የእልልታ ድምፅ ሰምተው “በዕብራውያን ሰፈር የምንሰማው ይህ ታላቅ የእልልታ ድምፅ ምን ይሆን ?” ተባባሉ ፤ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ዕብራውያን ሰፈር መምጣቱንም ባወቁ ጊዜ ፥ [7]ፈርተው እንዲህ አሉ ፥ “ባለማልክት እንዱ ወደ እነርሱ ሰፈር መጥቶአል ፤ እንግዲህ መጥ ፉታችን ነው ! ከዚህ በፊት እንዲህ ያስ ሁኔታ ደርሶብን አያውቅም ! [8]ኀያላን ከሆኑ ከእነዚህ አማልክትሰ ማን ሲያድነን ይችላል ? ቀድሞ

ግብጻውያንን በበረሓ የደመሰሱ እነዚሁ አማል
ክት ናቸው! 9 ፍልስጥኤማውያን ሆይ! እንግ
ዲህ በርቱ! በወንድነትም ተዋጉ፤ ይህ ካልሆነ
ቀድሞ እነርሱ የእኛ ባሪያዎች እንደነበሩ ሁሉ
እኛም ደግሞ የዕብራውያን ባሮች ሆነን መቅረ
ታችን ነው፤ ስለዚህ በወንድነት ጠንክራችሁ
ተዋጉ!”
10 ፍልስጥኤማውያንም በብርቱ ተዋግተው
እስራኤላውያንን ድል ነሡ፤ እስራኤላውያንም
ወደየድንኳናቸው ሸሹ፤ ታላቅ እልቂት ሆኖ
ሠላሳ ሺ እስራኤላውያን ወታደሮች ተገደሉ፤
11 የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦትም ተማ
ረከ፤ ሁለቱ የዔሊ ልጆች ሐፍኒንና ፊንሐስም
ተገደሉ።

የዔሊ መሞት

12 ነገሩ ከብንያም ወገን የሆነ አንድ ሰው
ከሦር ሜዳ ተነሥቶ በመሥጣሥ በዚያኑ ዕለት
ሴሎ ደረሰ፤ ሐዘኑንም ለማሳወቅ ልብሱን ቀዶ
በራሱ ላይ ትቢያ ነስንሶ ነበር፤ 13 ዔሊም ስለ
ቃል ኪዳኑ ታቦት በአሳብ በመጨነቅ እላፊ እግዳ
ሚውን ማየት በሚችልበት መንገድ ዳር በተዘጋ
ጀስት ወንበር ላይ ተቀምጦ ነበር፤ ያም ሰው ወሬ
ውን በየመንደሩ ሲነዛው የሰማ ሰው ሁሉ ከፍር
ኃት የተነሣ በመሸበር መጮኽ ጀመረ። 14 ዔሊም
የጩኸቱን ድምፅ ሰምቶ “ይህ ሁሉ ጩኸት ምን
ድን ነው?” ብሎ ጠየቀ፤ ያም ሰው ወሬውን
ለዔሊ ለመንገር ቸኩሎ ሄደ፤ 15 በዚያን ዘመን
ዔሊ የዘጠና ስምንት ዓመት ሽማግሌ ነበር፤ ዐይ
ኑም ሊጠፋ ተቃርቦ ነበር። 16 ሰውየውም ቀርቦ
“እኔ ከሦርነቱ እምልጡ መጣሁ፤ ዛሬም ከዚህ
የደረስሁት በብርቱ ሩጫ ነው” አለ።
ዔሊም “ልጄ ሆይ! ታዲያ እንዴት ሆነ?”
አለው።
17 መልእክተኛውም “እስራኤላውያን ድል
ሆነው ከፍልስጥኤማውያን ፊት ሸሹ፤ ይህም
ሽንፈት በእኛ ላይ መድረሱ እጅግ እሠቃቂ
ነው! ከዚህም ሁሉ ጋር ልጆችህ ሐፍኒንና ፊን
ሐስ ተገደሉ፤ የእግዚአብሔርም የቃል ኪዳን
ታቦት ተማረከ” ሲል መለሰለት።
18 መልእክተኛው የቃል ኪዳኑን ታቦት
መማረክ ባወሳ ጊዜ ዔሊ በቅጽሩ በር አጠገብ
ከተቀመጠበት ወንበር ላይ ተገልብጦ ወደ
ኋላው ወደቀ፤ እርሱም ሽማግሌ ከመሆኑም
በላይ በውፍረቱ ግዙፍ ስለነበር ከአወዳደቁ የተ
ነሣ እንገቱ ተሰብሮ ሞተ፤ ዔሊም በእስራኤል
መሪ ሆኖ የቆየበት ዘመን አርባ ዓመት ነበር።

የሚቹ ፊንሐስ ሚስት እሚሚት

19 የፊንሐስ ሚስት የነበረችው የዔሊ ምራት
ነፍሰ ጡር ነበረች፤ የምትወልድበትም ጊዜ
ተቃርቦ ነበር፤ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን
ታቦት መማረኩን፥ ሀማቷና ባልዋ መሞታቸ
ውን በሰማች ጊዜ በድንገተኛ ምጥ ተያዛ ወለ
ደች፤ 20 እርስዋም ስመሞት በምታጣጥርበት
ጊዜ በማዋለድ የምትረዳት ሴት “እያዘንሽ
በርቺ! ወንድ ልጅ ወልደሻል” አለቻት፤ ነገር
ግን አዳምጣ መልስ አልሰጠቻትም፤ 21 ሆኖም
በቀስታ ድምፅ “የእግዚአብሔር ክብር ከእስራ
ኤል ተሰየ” ስትል ስዚያ ልጅ “ኢካቦድ”[29]
የሚል ስም አወጣችለት፤ ይህም አባባል የቃል
ኪዳኑን ታቦት መማረክ፥ የአማትዋንና የባልዋ
ንም መሞት የሚያመለክት ነበር። 22 ቀጥላም
“የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት በመማረኩ
ምክንያት የእግዚአብሔር ክብር ከእስራኤል
ተሰየ” አለች።

ምዕራፍ 5

የቃል ኪዳኑ ታቦት በፍልስጥኤማውያን መካከል መገኘት

1 ፍልስጥኤማውያን የቃል ኪዳኑን ታቦት
ከማረኩ በኋላ ከኤቤንዔዜር እሽዶድ ተብላ ወደ
ምትጠራ ከተማቸው ወሰደው፥ 2 ዳጎን ተብሎ
ወደሚጠራው አምላካቸው ቤተ መቅደስ አስገ
ቡት፤ ከምስሉም ሐውልት ጐን አቆሙት።
3 በማግሥቱም ማለዳ የአሽዶድ ሕዝብ ተነሥ
ተው ሲመለከቱ የዳጎን ምስል ሐውልት በእግዚ
አብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ፊት በግንባሩ
መሬት ላይ ተደፍቶ አዩት፤ ከዚያም አንሥ
ተው ቀድሞ በነበረበት ስፍራ አቆሙት፤ 4 በተ
ከታዩም ቀን ማለዳ ተነሥተው ሲመለከቱ የም
ስሉ ሐውልት በቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት እንደ
ገና ወድቆ አዩት፤ በዚህ ጊዜ ራሱና ሁለት
እጆቹ ተሰባብረው በመግቢያው መድረክ ላይ
ወድቀው ሌላው አካሉ ብቻ ቀርቶ ነበር።
5 ዛሬም እንኳ ቢሆን የዳጎን ካህናትና በአሽዶድ
እርሱን የሚያመልኩት ሁሉ ያን የመግቢያ
መድረክ በእግራቸው ሳይረግጡ ተራምደው
የሚሄዱበት ምክንያት ይኸው ነው።
6 እግዚአብሔርም የአሽዶድን ሕዝብ በብ
ርቱ ቀጥቶ አስጨነቃቸው፤ እነርሱንና በዙሪያ
ቸው ያሉትን ሕዝብ ሁሉ በእባጭ መቅሠፍት
ቀጣቸው። 7 የሆነውንም ነገር ሁሉ ባዩ ጊዜ
“የእስራኤል አምላክ እኛንና አምላክችንን ዳጎ
ንን በመቅጣት ላይ ነው፤ ስለዚህም ከእንግዲህ
ወዲህ የቃል ኪዳኑን ታቦት በዚህ እንዲቆይ
ማድረግ እንችልም” አሉ፤ 8 በዚህም ምክንያት
ወደ እምስቱም የፍልስጥኤማውያን ነገሥታት
መልእክተኞች ልከው በማስጠራት “ስለ እስራ
ኤል አምላክ የቃል ኪዳን ታቦት ምን እናድ
ርግ” ብለው ጠየቁአቸው።

---

[29] 4፥21 ኢካቦድ ፡- በዕብራይስጥ “ያለ ክብር” ማለት ነው።

እነርሱም “ወደ ጋት ውሰዱት” ብለው መለሱላቸው ፤ ስለዚህም ጋት ተብላ ወደምትጠራው ወደ ሌላይቱ የፍልስጥኤማውያን ከተማ ወሰዱት ፤ 9 ነገር ግን የቃል ኪዳኑ ታቦት እዚያ ከደረሰ በኋላ እግዚአብሔር ያችንም ከተማ ጭምር ቀጣ ፤ ሕዝብዋንም በብርቱ አስጨነቀ ። ሕዝቡንም ሽማግሌውንም ሳይለይ ሕዝቡን ሁሉ በእንድኅት በእብጠት በሽታ ቀጣቸው ፤ 10 ስለ ዚህም የቃል ኪዳኑ ታቦት ዔቅሮን ተብላ ወደ ምትጠራው ወደ ሌላይቱ የፍልስጥኤማውያን ከተማ እንዲወስድ እደረጉ ፤ ነገር ግን እዚያ በደረሰ ጊዜ ሕዝቡ እየጮኹ በማልቀስ “የእስ ራኤልን አምላክ የቃል ኪዳን ታቦት ወደዚህ ያመጡብን እኛን ሁላችንን ለመፍጀት አስበው ነው” አሉ ። 11 ስለዚህም እንደገና ወደ ፍልስ ጥኤማውያን ነገሥታት ሁሉ መልእክተኞች ልከው “እኛንና ቤተሰባችንን ሁሉ ከመፍጀቱ በፊት የእስራኤልን የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ስፍራው መልሳችሁ ላኩ” አሉ ፤ እግዚአብሔር በብርቱ ስለቀጣቸው በመላ ከተማይቱ የሚያስ ጨንቅ የሞት ድንጋጤ ነበር ፤ 12 ከሞት የተረፉ ትም የአባጩ በሽታ በርትቶባቸው ስሰንበር ሕዝቡ ዕርዳታ ለማግኘት ወደ አማልክቶቻቸው በማልቀስ ጮኹ ።

ምዕራፍ 6

የቃል ኪዳኑ ታቦት መመለስ

1 የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት በፍል ስጥኤም ስባት ወር ከቆየ በኋላ ፥ 2 ሕዝቡ ካህና ቶቻቸውንና አስማተኞቻቸውን ጠርተው እን ዲህ ሲሉ ጠየቁአቸው ፥ “ስለ እግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ምን ማድረግ የሚኖሰን ይመስላችኋል? ወደ ስፍራው እንዲመለስ ብና ደርግ በምን ዐይነት ሁኔታ እንላከው? ዘዴውን ንገሩን” አሉአቸው ።

3 እነርሱም እንዲህ ሲሉ መለሱላቸው ፥ “የእስራኤልን አምላክ የቃል ኪዳን ታቦት መልሳችሁ ለመላክ ብትፈልጉ ፥ ስለ በደላችሁ የሚከፈል ስጦታ አብራችሁ መላክ ይገ ባችኋል ፤ የቃል ኪዳኑ ታቦት ያለ ምንም ስጦታ ተመልሶ መሄድ የለበትም ፤ በዚህም ዐይ ነት ሁኔታ እናንተ ከሕመማችሁ ትፈወሳለ ችሁ ፤ እርሱ እናንተን በብርቱ የቀጣበትንም ምክንያት ልታውቁ ትችላላችሁ ።” 4 ሕዝቡም “ስሰ በደል የሚከፈል ይሆን ዘንድ ከምን ዐይ ነት ስጦታ ጋር እንላከው?” ሲሉ ጠየቁ ።

እነርሱም እንዲህ ሲሉ መለሱላቸው ፥ “በእ ባጩ አምላል የተሠራ አምስት የወርቅ ጕልቻ ፥ እንደ ፍልስጥኤማውያን ንጉሦች ብዛት በእይዋ አምላል የተሠራ አምስት የወርቅ ጕልቻ መሆን አለበት ፤ ምክንያቱም በእናንተ ሁሉና በእምስቱ ነገሥታቶቻችሁ ላይ የተላከው መቅሠፍት አንድ ዐይነት ነው ። 5 አገራችሁን ሰማጥፋት በተላኩት እይጦችና እባጮች እም ሳል እነዚህን ስጦታዎች ሠርታችሁ ለእስራኤል እምላክ ክብር መስጠት አለባችሁ ፤ ይህን ብታ ደርጉ ምናልባት እናንተን ፥ አማልክቶቻችሁ ንና ምድራችሁን የሚቀጣበትን መቅሠፍት ይገታ ይሆናል ፤ 6 የግብጽ ንጉሥና ግብጻውያን እንዳደረጉት ሰሰምን ልባችሁን ታደነድናላ ችሁ? አሰራኤላውያን የግብጽን ምድር ለቅቀው የወጡት ፥ እግዚአብሔር ግብጻውያንን በብርቱ ከቀጣቸው በኋላ እልነበረምን? 7 ስለዚህ አዲስ ሠረገላና ቀንበር ያልተጫነባቸው ሁለት ላሞች እዘጋጁ ፤ ላሞቹን ጠምዳችሁ ሠረገላው የሚሳ ብበትን ጫፍ በቀንበሩ ላይ አሰሩት ፤ እንቦሶች ቸውንም ወደ በረት መልሱ ፤ 8 የእግዚአብሔር ንም የቃል ኪዳን ታቦት ወስዳችሁ በሠረገላው ላይ እኑሩ ፤ ስለበደላችሁም እንዲከፈል ከእርሱ ጋር ለመላክ የሠራችሁትን ልዩ ልዩ ወርቅ በሣ ጥን ውስጥ አስገብታችሁ በታቦቱ ጐን አስቀ ምጡ ፤ ሠረገላውንም መንገድ አስይዛችሁ በራሱ ጎይል እንዲንቀሳቀስ ተዉት ። 9 ከዚህም በኋላ አካሄዱን ተመልከቱት ፤ አቅጣጫው ወደ ቤትሼሜሽ ከተማ ያመራ እንደሆነ ይህን አሠ ቃቂ መቅሠፍት በእኛ ላይ የላከብን የእስራኤል አምላክ መሆኑን ያመለከታል ፤ ወደዚያ አቅ ጣጫ ባያመራ ግን መቅሠፍቱ የመጣብን በእጋ ጣሚ እንጂ እግዚአብሔር የላከብን አለመሆኑን እንገነዘባለን ።”

10 እነርሱም እንደተነገራቸው አደረጉ ፤ ሁለት ላሞች ወስደው ሠረገላ በታሰረበት ቀን በር ጠመዱአቸው ፤ እንቦሶቻቸውንም ወደ በረት መልሰው ዘጉባቸው ። 11 የቃል ኪዳኑን ንም ታቦት ወስደው በእይጦችና በእባጮች እምሳል የተሠራ ወርቅ ከተሞላበት ሣጥን ጋር በሠረገላው ላይ አስቀመጡ ፤ 12 ላሞቹም መንገ ዱን ሳይለቁና ወደ ግራም ወደ ቀኝም ሳያዘነ ብሉ በቀጥታ ወደ ቤትሼሜሽ በማምራት ጉዞአ ቸውን ቀጠሉ ፤ በሚሄዱበትም ጊዜ እምቧ ይሉ ነበር ፤ እምስቱም የፍልስጥኤም ነገሥታት እስከ ቤትሼሜሽ ድንበር ድረስ በመከተል ሸኙ አቸው ።

13 የቤትሼሜሽም ሰዎች በሸለቆው ውስጥ ስንዴ ያጭዱ ነበር ፤ ቀና ብለው በተመለከቱም ጊዜ የቃል ኪዳኑን ታቦት አዩ ፤ ያንንም በማየ ታቸው እጅግ ደስ አላቸው ። 14 ሠረገላውም በቤትሼሜሽ ወደሚኖር ኢያሱ ተብሎ ወደሚ ጠራው ሰው እርሻ መጥቶ በትልቅ ቋጥኝ አጠ ገብ ሲደርስ ቆመ ። ሕዝቡም የሠረገላውን እን ጨት ፈለጡ ፤ ላሞቹንም ዐርደው ለእግዚአብ ሔር የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገው አቀረቡ አቸው ። 15 ሌዋውያንም የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦትና ከእርሱ ጋር የነበረውን ወርቅ የሞላበት ሣጥን አንሥተው በታላቁ ቋጥኝ ላይ አስቀመጡ ፤ የቤትሼሜሽም ሰዎች

የሚቃጠልና ሌሳውንም መሥዋዕት ሁሉ ለእግዚአብሔር አቀረቡ፤ 16አምስቱም የፍልስጥኤም ነገሥታት ይህን ሁሉ ሲመለከቱ ቆይተው በዚያው ቀን ወደ ዔቅሮን ተመለሱ።

17ስለ በደላቸው የሚከፈሉ ስጦታዎች ይሆኑ ዘንድ ፍልስጥኤማውያን ለእግዚአብሔር የላኩአቸው በእባጮች አምሳል የተሠሩ አምስት የወርቅ ጕልቻዎች አሽዶድ፥ ጋዛ፥ አስቀሎና፥ ጋትና ዔቅሮን ተብለው በሚጠሩት ከተሞቻቸው ስም የተላኩ ነበሩ፤ 18እንዲሁም በተመሸጉ ከተሞችና ቅጽር ባልተሠሩላቸው መንደሮች ሆነው አምስቱ የፍልስጥኤም ነገሥታት በሚያስተዳድሩት በእያንዳንዱ ከተማ ስም በአያጥ አምሳል የተሠሩ አምስት የወርቅ ጕልቻዎች ሳኩ። በቤትሼሚሽ በሚኖረው በኢያሱ እርሻ ውስጥ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ያኖሩበትም ታላቅ ቋጥኝ ለዚህ ለተደረገው ነገር ሁሉ ምስክር ሆኖ እስከ አሁን ይገኛል።

19የታቦቱን ውስጣዊ ክፍል በመመልከታቸው እግዚአብሔር ተቈጥቶ ከጎምላ ሺ የቤት ሼሚሽ ሕዝብ መካከል ሰባ ሰዎችን ገደለ፤ እግዚአብሔርም ይህን ሁሉ እልቂት በመካከላቸው በማድረጉ ሕዝቡ በማዘን አለቀሱ።

የቃል ኪዳኑ ታቦት በቂርያትይዓሪም

20ስለዚህም የቤትሼሚሽ ሕዝብ "በዚህ ቅዱስ አምላክ ፊት ማን ይፍሮ ይቆማል? ከእኛስ ወደ ሌላ እንዲሄድልን ወዴት ልንልከው እንችላለን?" አሉ። 21በቂርያትይዓሪም ወደሚኖሩትም ሕዝብ መልእክተኞችን ልከው "ፍልስጥኤማውያን የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ወደ እኛ እምጥተዋልና መጥታችሁ ውሰዱት" አሉ።

ምዕራፍ 7

1የቂርያትይዓሪም ሕዝብም የቃል ኪዳኑን ታቦት ወስደው በኮረብታ ላይ ወደሚኖረው አቢናዳብ ተብሎ ወደሚጠራው ሰው ቤት አስገቡት፤ የቃል ኪዳኑንም ታቦት ቊጥጥራት ይጠብቅ ዘንድ ልጁን ኤልዓዛርን ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተለየ እንዲሆን አደረጉ።

ሳሙኤል የእስራኤል መሪ ሆነ

2የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ሰረ ዅም ጊዜ በቂርያትይዓሪም ኖረ፤ ይኸውም ሃያ ዓመት ያህል ነበር፤ በዚህን ጊዜ እስራኤላውያን ሁሉ እንዲረዳቸው ፈልገው ወደ እግዚአብሔር ጮኹ።

3ሳሙኤልም ስለ እስራኤል ሕዝብ እንዲህ አለ፥ "በሙሉ ልባችሁ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ከፈለጋችሁ ባዕዳን አማልክትን ሁሉ በተለይም ዐስታሮት ተብላ የምትጠራውን የሴት አምላክ ምስል አስወግዱ፥ ራሳችሁንም ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር በማስረከብ እርሱን ብቻ አምልኩ፤ እርሱም ከፍልስጥኤማውያን እጅ በመታደግ ያድናችኋል።" 4ስለዚህም እስራኤላውያን ያመልኩአቸው የነበሩትን የባዓልንና የዐስታሮትን ጣዖቶች አስወግደው እግዚአብሔርን ብቻ አመለኩ።

5ከዚህም በኋላ ሳሙኤል "እኔ በዚያ ለእናንተ ወደ እግዚአብሔር ስለምጸልይላችሁ በምጽጳ ተሰብሰቡ" ብሎ ለእስራኤላውያን ሁሉ ጥሪ አደረገ። 6እነርሱም በአንድነት በምጽጳ ተሰበሰቡ፤ ውሃም ቀድተው ለእግዚአብሔር መባ አድርገው በማፍሰስ በዚያን ዕለት ቀኑን ሙሉ ጾሙ፤ "እኛ እግዚአብሔርን በድለናል" ብለውም ተናገሩ፤ ሳሙኤል በእስራኤላውያን መካከል የነበረውን ጠብና ክርክር በዳኝነት የሚወስነውም በዚህች በምጽጳ ነበር።

7እስራኤል በምጽጳ መሰብሰባቸውንም ፍልስጥኤማውያን ሰሙ፤ ስለዚህም አምስቱ የፍልስጥኤም ነገሥታት አደጋ ሊጥሉባቸው በመፈለግ የጦር ሰዎቻቸውን አስከትለው ዘመቱ፤ እስራኤላውያንም ይህን በሰሙ ጊዜ ፈርተው፥ 8ሳሙኤልን "ከፍልስጥኤማውያን እጅ ያድነን ዘንድ ወደ አምላካችን ወደ እግዚአብሔር መጸለይን አታቋርጥ" አሉት። 9ሳሙኤልም ገና ጡት ያልተወ ትንሽ ጥቦት ወርዶ በሙሉ የሚቃጠል መሥዋዕት በማድረግ ለእግዚአብሔር አቀረበው፤ ከዚህም በኋላ እስራኤላውያንን ይረዳ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ እግዚአብሔርም ጸሎቱን ሰማለት፤ 10ሳሙኤል መሥዋዕት በሚያቀርብበት ጊዜ ፍልስጥኤማውያን አደጋ ለመጣል ወደፊት በመግፋት ላይ ነበሩ። ነገር ግን በዚያኑ ጊዜ እግዚአብሔር ከሰማይ የነጐድጓድ ድምፅ አሰማቸው፤ እነርሱም በፍጹም ታውከው በመሸበር ከእስራኤላውያን ፊት ሸሹ። 11እስራኤላውያንም ከምጽጳ ተነሥተው በመገሥገሥ በሸሸት ላይ የነበሩትን ፍልስጥኤማውያን እስከ ቤትካር በታች እያሳደዱ በየመንገዱ ገደሉአቸው።

12ሳሙኤልም ድንጋይ ወስዶ በምጽጳና በሼን መካከል በማቆም "እግዚአብሔር እስከ አሁን ረድቶናል" አለ፥ ስለዚህም ያንን ድንጋይ የዕርዳታ አለት መሆኑን ለመግለጥ "ኤቤን ዔዜር" ብሎ ጠራው። 13በዚህም ዐይነት ሁኔታ ፍልስጥኤማውያን ድል ሆኑ፥ እግዚአብሔርም ሳሙኤል ባለበት ዘመን ሁሉ በእስራኤል ግዛት ላይ ወረራ እንዳይፈጽሙ ከለከላቸው። 14ፍልስጥኤማውያን የያዙአቸው በዔቅሮንና በጋት መካከል የነበሩትም ከተሞች ሁሉ

7፥1 ፡- 2ሳሙ. 6፥2-4፤ 1ዜ.መ. 13፥5-7።

ስእስራኤላውያን ተመለሱላቸው ፤ ስለዚህም የእ
ስራኤል ሕዝብ ተይዞባቸው የነበረውን ግዛት
ሁሉ እንደገና አገኙ ፤ በእስራኤላውያንና በከነዓ
ናውያንም መካከል ሰላም ሰፍኖ ነበር ።

15 ሳሙኤል በነበረበት ዘመን ሁሉ የእስራኤ
ልን ሕዝብ መራ ፤ 16 በየዓመቱም ወደ ቤት
ኤል ፥ ጌልገላና ምጽጳ እየሄደ በእነዚህ ሰፍራ
ዎች የሚነግረውን ክርክር ሁሉ በዳኝነት ይወ
ሰን ነበር ። 17 ከዚያም በራማ ወደሚገኘው
መኖሪያ ቤቱ እየተመለሰ እዚያም የዳኝነት
ሥራ ይሠራ ነበር ፤ በዚህም በራማ ስእግዚአብ
ሔር መሠዊያ ሠራ ።

ምዕራፍ 8

ንጉሥ ስለማንገሥ የእስራኤል ሕዝብ ያቀረቡት ጥያቄ

1 ሳሙኤል በሸመገለ ጊዜ ሁለቱን ልጆቹን
በእስራኤል ፈራጆች አድርጎ ሾሞአቸው ነበር ፤
2 የበኵር ልጁ ዩኤል ፥ ታናሽ ልጁ አቢያ ተብ
ለው የሚጠሩ ሲሆኑ በቤርሳቤህ ዳኞች ሆነው
ተሾመው ነበር ፤ 3 ነገር ግን የአባታቸውን መል
ካም አርአያነት አልተከተሉም ፤ ይህን በማድ
ረግ ፈንታ የጥቅም ፈላጊዎች ሆነው
ጉቦ እየተቀበሉ ፍርድን ያጣምሙ ነበር ።

4 ከዚህ በኋላ የእስራኤል ማኅበር መሪዎች
በአንድነት በመሰብሰብ ሳሙኤል ወደሚገኝበት
ወደ ራማ ሙዮተው እንዲህ አሉ ፥ 5 “ተመል
ከት ፥ እነሆ አንተ በእርጅና ላይ ነህ ፤ ልጆች
ህም የአንተን መልካም አርአያነት አልተከተ
ሉም ፤ ሰሰዚህ በሌሎች አገሮች እንደሚደረገው
እኛን የሚመራን ንጉሥ አንግሥልን ።”
6 ንጉሥ ያነግሥላቸው ዘንድ በመጠየቃቸውም
ሳሙኤል አዘኖ ወደ እግዚአብሔር ጸሰየ ፤
7 እግዚአብሔርም ሳሙኤልን እንዲህ አለው ፥
“ሕዝቡ የሚሉህን ነገር ሁሉ ተቀበል ፤ እነርሱ
የናቁት አንተን አይደለም ፤ በእነርሱ ላይ ነግሼ
እንዳልኖር ፥ እነርሱ የናቁት እኔን ነው ። 8 እኔ
እነርሱን ከግብጽ ካወጣሁበት ጊዜ ጀምሮ ፌታ
ቸውን መልሰው ከእኔ በመራቅ ባዕዳን አማልከ
ትን ቢያመልኩ ኖረዋል ፤ እንግዲህ በእኔ ላይ
ሲያደርጉት የነበረውን ሁሉ እነሆ በእንተም
ላይ መፈጸም ጀምረዋል ፤ 9 ሰሰዚህ ከእንግዲህ
ወዲህ የሚሉህን ተቀበል ፤ ነገር ግን ነገሥታቶ
ቻቸው ወደ ፌት በእነርሱ ላይ የሚፈጽሙባቸ
ውን ነገር ሁሉ በመግለጥ በብርቱ አሰጠንቅቃ
ቸው ።”

10 ሳሙኤልም ንጉሥ እንዲያነግሥላቸው
ስጠየቁት ሕዝብ እግዚአብሔር የነገረውን ሁሉ
አሰረዳቸው ፤ 11 እንዲህም ሲል ገሰጠላቸው ፥
“ንጉሣችሁ የሚያደርግባችሁ ነገር ይህ ነው ፦
ልጆቻችሁን ወሰዶ ሞፍሮች ያደርጋቸዋል ፤
ከእነርሱም አንዳንዶቹን የጦር ሠረገላ ነጂ
ዎች ፥ አንዳንዶቹን ፈረሰኞች ፥ አንዳንዶቹንም
በሠረገላ ፌት የሚሮጡ ያደርጋቸዋል ፤ 12 ከእነ
ርሱም አንዳንዶቹን የሺ አለቆችና የነምሳ አስ
ቆች አድርጎ ይሾማል ፤ ወንዶቹ ልጆቻችሁ የን
ጉሡ ኩዳድ አራሽዎችና መከር ሰብሳቢዎች
ይሆናሉ ፤ ሴቶችም የጦር መሣሪያና የሠረገላ
ዕቃ ሠራተኞዎች ይሆናሉ ። 13 ሴቶች ልጆቻች
ሁም ለእርሱ ሽቶ አዘጋጅዎች ፥ ወጥ ሠሪዎችና
አንጀራ ጋጋሪዎች ይሆናሉ ። 14 ምርጥ የሆነ
ውን የእርሻ መሬታችሁን ፥ የወይን ተከል ቦታ
ችሁንና የወይራ ተከላችሁን ሁሉ ወሰዶ ሰመኳ
ንቶቹ ይሰጥባችኋል ። 15 ከእህላችሁና ከወይናች
ሁም ከዐሥር አንዱን አጅ ወስዶ ለቤተ መንግ
ሥቱ ባለሟሎችና ሰሌሎቹም ሹማምንት ይሰጥ
ባችኋል ። 16 የወንድና የሴት አገልጋዮቻችሁን ፥
ምርጥ ከብቶቻችሁንና አህዮቻችሁን ወሰዶ
ሰራሱ መጠቀሚያ ያደርጋቸዋል ። 17 ከበግና
ከፍየል መንጋዎቻችሁ ከዐሥር አንዱን ይወሰ
ዳል ፤ እናንተም የእርሱ ባሪያዎች ትሆናላ
ችሁ ፤ 18 ያ ዘመን በደረሰ ጊዜ የመረጣችሁት
ንጉሥ ሰሰሚፈጽሞባችሁ በደል በመረረ ሁኔታ
ማጕረምረም ትጀምራላችሁ ፤ እግዚአብሔር
ግን እቤቱታችሁን አያዳምጥም ።”

19 ይሁን እንጂ ሕዝቡ ሳሙኤል ሰነገራቸው
ቃል ሁሉ ዋጋ አልሰጡትም ፤ ይልቁንም “እን
ደዚህ አይደሰም ! እኛ ንጉሥ እንዲኖረን እንፈ
ልጋለን ፤ 20 በዚህም ዐይነት ሌሎች ሕዝቦች
እንደሚያደርጉት እኛን የሚያሰተዳድርና ከጠላ
ቶቻችንም ጋር በምንዋጋበት ጊዜ ወደ ጦር
ሜዳ የሚመራን ንጉሥ ይኖረናል ።” 21 ሳሙኤ
ልም እነርሱ ያሉትን ሁሉ አዳመጠ ፤ ከዚያም
ሄዶ ለእግዚአብሔር ነገረ ፤ 22 እግዚአብሔርም
“እነርሱ በጠየቁህ መሠረት ፥ ንጉሥ አንግሥላ
ቸው” አለው ፤ ከዚያም በኋላ ወደየቤታቸው
እንዲሄዱ ሳሙኤል ሕዝቡን አሰናበተ ።

ምዕራፍ 9

ሳኦልና ሳሙኤል

1 ከብንያም ነገድ ቂሰ ተብሎ የሚጠራ ታዋ
ቂነት ያለው አንድ ባለጸጋ ሰው ነበር ፤ እርሱም
የአቢኤል ልጅ ፥ የጸሮር የልጅ ልጅ ሲሆን ከአ
ፊሐ ጐሳ ወገን የበኩራት ቤተሰብ ነበር ።
2 ቂሰም ሰመልከ ቀናነቱ ተወዳዳሪ የማይገኝሰት
ሳኦል ተብሎ የሚጠራ ልጅ ነበረው ፤ ሳኦል
በቁመት ከሕዝቡ ሁሉ ይልቅ ረዥም ነበር ፤
በመልከቀናነቱም ከሁሉ ይበልጥ ነበር ።

3 ቂሰ የራሱ ንብረት የሆኑ አህዮች ጠፍተው
በት ነበር ፤ ሰሰዚህም ልጁን ሳኦልን “ከአገልጋ
ዮች አንዱን ይዘህ ሂድና የጠፉትን አህዮች

ፈልግ” ብሎ አዘዘው። 4ሳኦልና አገልጋዩም ተነሥተው በተራራማው የኤፍሬም አገርና በሻሊሻ ምድር በኩል አልፈው አህዮቹን መፈለግ ጀመሩ፤ ነገር ግን አህዮቹን ማግኘት አልቻሉም፤ ከዚያም በሻዕሊም ምድር በኩል አልፈው ሳያገኙአቸው ቀሩ፤ እንደገናም በብንያም ግዛት በኩል አለፉ፤ ይሁን እንጂ አሁንም አህዮቹን ማግኘት አልቻሉም። 5ወደ ጹፍ ምድር በደረሱም ጊዜ ሳኦል ከእርሱ ጋር የነበረውን አገልጋይ “አሁንስ ወደቤት እንመለስ፤ ምክንያቱም አባቴ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ አህዮቹ ማሰቡ ቀርቶ ስለ እኛ መጨነቅ ይጀምራል” አለው።

6አገልጋዩም “ቆይ አስቲ! በዚህች ከተማ በጣም የተከበረ አንድ የእግዚአብሔር ሰው አለ፤ እርሱ የሚናገረው ቃል ሁሉ በትክክል ይፈጸማል፤ ስለዚህም ወደ እርሱ እንሂድ፤ ምናልባትም አህዮቹን የት ማግኘት እንደምንችል እርሱ ሊነግረን ይችል ይሆናል” ሲል መለሰለት።

7ሳኦልም “መሄዱንስ እንሂድ፤ ነገር ግን ለዚያ ሰውዬ ምን ዐይነት ስጦታ ልናበረክትለት እንችላለን? ስንቃችንም አንኳ ከስል ቻችን አልቆአል፤ ታዲያ ሌላ የምንሰጠው ነገር አለ እንዴ?” አለው።

8አገልጋዩም “እነሆ እኔ የአንድ ጥሬ ብር አንድ አራተኛው እጅ አለችኝ፤ እርስዋን አሰጠዋለሁ፤ እርሱም አህዮቹን የት ማግኘት እንደ ምንችል ይነግረናል” ሲል መለሰ።

9-11ሳኦልም “መልካም አሳብ ነው! እንግዲ ያውስ እንሂድ” አለው፤ ስለዚህም የእግዚአብ ሔር ሰው ወደሚገኝበት ከተማ ሄዱ፤ ወደ ከተ ማይቱም ለመድረስ ዳገት በመውጣት ላይ ሳሉ ውሃ ለመቅዳት የወጡ ልጃገረዶችን አገኙ፤ “ባለ ራእዩ ሰው በዚህች ከተማ ይገኛልን?” ሲሉ ልጃገረዶቹን ጠየቁአቸው።

በዚያን ዘመን ነቢይ ሁሉ “ባለ ራእይ” እየ ተባለ ይጠራ ስለነበር፥ ከእግዚአብሔር አንድ ነገር ጠይቆ ማግኘት የሚፈልግ ሰው ሁሉ “ወደ ባለ ራእዩ እንሂድ” ይል ነበር።

12-13ልጃገረዶቹም እንዲህ ሲሉ መለሱላ ቸው፥ “አዎን ባለ ራእዩ አለ! እንዳያውም በፊታችሁ እየሄደ ስለሆነ ፈጠን ብላችሁ ብት ወጡ ትደርሱበታላችሁ፤ ወደ ከተማይቱ ስት ገቡ ወዲያውኑ ታገኙታላችሁ፤ እርሱ ዛሬ ወደ ከተማይቱ መጥቶአል፤ ምክንያቱም ሕዝቡ በከ ረብታው ላይ በሚገኘው መሠዊያ መሥዋዕት ለማቅረብ ተዘጋጅተዋል፤ እርሱ በመጀመሪያ መሥዋዕቱን መባረክ አለበት፤ የተጋበዙትም ስዎች ሁሉ እርሱ ከመምጣቱ በፊት ምንም ነገር አይቀምሱም፤ ስለዚህም አሁን ብትወጡ እርሱ ለመመገብ ወደ ኮረብታው ከመውጣቱ በፊት ታገኙታላችሁ።” 14ከዚያም በኋላ ሳኦ ልና አገልጋዩ ወደ ከተማይቱ ወጡ፤ ወደ ከተ ማይቱም በመግባት ላይ ሳሉ ሳሙኤል ወደ ማምለኪያው ስፍራ ለማለፍ ወደ እነርሱ አቅ ጣጫ ሲመጣ አዩት።

15ከዚያም ቀን በፊት እግዚአብሔር ሰሳ ሙኤል እንዲህ ሲል ነግሮት ነበር፥ 16“ነገ በዚህ ስዓት ከብንያም ነገድ አንድ ሰው ወደ አንተ አልክለሁ፤ እርሱንም የሕዝቤ የእስራ ኤል መሪ አድርገህ ቀባው፤ እርሱም አነርሱን ከፍልስጥኤማውያን እጅ በመታደግ ያድናቸ ዋል፤ ምክንያቱም እኔ የሕዝቤን ሥቃይ ተመልክቻለሁ፤ ወደ እኔ ያቀረቡትንም ጩኸት ሰምቻለሁ።”

17ሳሙኤልም ሳኦልን ባየው ጊዜ፥ እግዚአ ብሔር ሳሙኤልን “ያ የነገርሁህ ሰው እነሆ ይህ ነው፤ እርሱ ለሕዝቤ መሪ ይሆናል” አለው። 18ሳኦልም በቅጽሩ በር አጠገብ ወደነ በረው ወደ ሳሙኤል ቀረብ ብሎ “ባለ ራእዩ የት እንደሚኖር አባክህን ንገረኝ” አለው።

19ሳሙኤል አንዲህ ሲል መለሰለት፥ “ባለ ራእዩ እኔ ነኝ፤ ከእኔ ቀድመህ ወደ ማምለኪ ያው ስፍራ ሂድ፤ ሁለታችሁም ዛሬ ከእኔ ጋር አብራችሁ ትመገባላችሁ፤ ነገ ጠዋትም ለዋያቄ ዎችህ ሁሉ መልስ ስጥቼ አሰናብትሃና መንገድ ህን ትቀጥላለህ፤ 20ከሦስት ቀን በፊት የጠፉት አህዮችህ ተገኝተዋልና ስለ እነርሱ አትጨነቅ፥ ነገር ግን የእስራኤል ሕዝብ ምኞት ማንን ለማ ግኘት ይመስልሃል? እነርሱ የሚፈልጉት አንተ ንና የአባትህን ቤተሰብ አይደለምን?”

21ሳኦልም “እኔ ከእስራኤል ነገዶች መካ ከል በተለይ ታናሽ የሆነው የብንያም ነገድ ተወላጅ ነኝ፤ በዚሁም ነገድ ውስጥ እንኳ የእኔ ቤተሰብ በጣም አነስተኛ ነው፤ ታዲያ እንዲህ ያለውን ጕዳይ ለእኔ ስለምን ትነግረኛ ለህ?” ሲል መለሰለት።

22ከዚህ በኋላ ሳኦልንና አገልጋዩን እየመራ ወደ ታሳቁ አዳራሽ አስገብቶ ብዛታቸው ሠላሳ የሚሆኑ እንግዶች በተቀመጡበት ገበታ ከሁሉ በላይ የሆነውን የክብር ቦታ ስጣቸው። 23ሳሙ ኤልም የወጥ ቤቱን ሠራተኛ ጠርቶ “ስብቅው አስቀምጥ ብዬ የስጠሁህን ብልት ሥጋ አምጣ!” አለው፤ 24ስለዚህም የወጥቤቱ ሠራ ተኛ ምርጥ የሆነውን የታናሽ ብልት ሥጋ አም ጥቶ በሳኦል ፊት አስቀመጠ፤ ሳሙኤልም ሳኦ ልን “ተመልከት፥ ይህ ለአንተ ተለይቶ የተቀ መጠልህ ምርጥ ሥጋ ነው፤ እኔ ከጋበዝሁአ ቸው እንግዶች ጋር ሆነህ እንድትበላ ያስቀመ ጡልህ ስለሆነ አርሱን ተመገብ” አለው።

ስለዚህም በዚያ ቀን ሳኦል ከሳሙኤል ጋር አብሮ ተመገበ፤ 25ከማምለኪያውም ስፍራ ወር ደው ወደ ከተማይቱ በገቡ ጊዜ ሳኦል የሚተኛ በትን አልጋ በሰገነት ላይ አዘጋጀለት፤ እርሱም እዚያ ተኝቶ አደረ።

ሳሙኤል ሳኦልን ቀብቶ አነገሠው

26 በነጋም ጊዜ ማለዳ ሳሙኤል ከሰገነቱ ላይ
ሳኦልን ጠርቶ "እንግዲህ ተነሥ! ልሸኝህና
መንገድህን ቅጥል" አለው፤ ሳኦልም ከመኝ
ታው ተነሣ፤ እርሱና ሳሙኤልም አብረው ወደ
መንገዱ ሄዱ፤ 27 ወደ ከተማይቱም ዳርቻ በደ
ረሱ ጊዜ ሳሙኤል ሳኦልን "አገልጋይህ ቀድ
ሞን ወደ ፊት እንዲሄድ ንገረው" አለው፤ አገ
ልጋዩም ቀድሞ ከሄደ በኋላ ሳሙኤል ሳኦልን
እንደገና "አንተ አዚህ ትንሽ ቆይ፤ እኔም እግ
ዚአብሔር ያለውን ሁሉ እነግርሃለሁ" አለው።

ምዕራፍ 10

1 ሳሙኤል የወይራ ዘይት መያዣውን ቀንድ
ወሰዶ በሳኦል ራስ ላይ አፈሰሰው፤ ከሳመውም
በኋላ እንዲህ አለው፤ "እግዚአብሔር የሕዝቡ
የእስራኤል መሪ እንድትሆን ቀብቶሃል፤ አን
ተም ሕዝቡን በመምራት ከጠላቶቻቸው ሁሉ
ትጠብቃቸዋለህ፤ የሕዝቡ መሪ እንድትሆን እግ
ዚአብሔር አንተን ስለመምረጡ ማስረጃ የሚሆ
ንህ ምልክት ይህ ነው፤ 2 ዛሬ ከእኔ ተለይተህ
በምትሄድበት ጊዜ፥ በብንያም ግዛት በሚገ
ኘው ዜልጻሕ ተብሎ በሚጠራው ሰፍራ ባለው
በራሔል መቃብር አጠገብ ሁለት ሰዎች ታገኛ
ለህ፤ እነርሱም ስትፈልጋቸው የነበሩ አህዮች
መገኘታቸውንና አባትህም ስለ እነርሱ ማበቡን
ትቶ ስለ አንተ በመጨነቅ 'እንግዲህ ስለ ልጄ
ምን ላድርግ' እያለ በመጠየቅ ላይ መሆኑን ይነ
ግሩሃል። 3 ከዚያም አልፈህ በታቦር ወደሚገ
ኘው ወደ አንድ የተቀደሰ ዛፍ ትደርሳለህ፤
እዚያም በቤትኤል ለእግዚአብሔር መሥዋዕት
ለማቅረብ የሚሄዱ ሦስት ሰዎችን ታገኛለህ፤
ከእነርሱ አንዱ ሦስት የፍየል ጥቦችን እየሳበ
የሚሄድ ሲሆን ሁለተኛው ሰው ሦስት ጎብዝት
የተሸከመ ነው፤ ሦስተኛውም የወይን ጠጅ የተ
ምላበት አቁማዳ የተሸከመ ይሆናል፤ 4 እነር
ሱም ሰላምታ ከሰጡህ በኋላ ከጎብስቶቹ ሁለቱን
ይሰጡሃል፤ አንተም መቀበል ይገባሃል፤ 5 ከዚ
ያም አልፈህ የፍልስጥኤማውያን ጦር ሰፈር
ወደሚገኝበት ጊብዓ ተብሎ ወደሚጠራው ወደ
እግዚአብሔር ኮረብታ ትመጣለህ፤ ወደ ከተማ
ይቱም መግቢያ በር በምትደርስበትም ጊዜ በኮ
ረብታው ላይ መሥዋዕት እድርገው የሚመለሱ
የነቢያትን ጉባኤ ታገኛለህ፤ እነርሱም በገና
እየደረደሩ፥ ከበሮ እየመቱ፥ ዋሽንት እየነፉ፥
በመበንቆ ዜማ ሲዘምሩ ትሰማለህ፤ እነርሱም
እያሸበሸቡ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ትን
ቢት በሚናገሩበት ጊዜ፥ 6 በድንገት የእግዚአብ
ሔር መንፈስ በኀይል በአንተ ላይ ይወርዳል፤
ከእነርሱም ጋር እያሸበሸብህ ድምፅህን ከፍ
አድርገህ ትንቢት መናገር ትጀምራለህ፤ ልዩ
ለውም ትሆናለህ፤ 7 እነዚህም ምልክቶች በተፈ
ጸሙ ጊዜ እግዚአብሔር ከእንተ ጋር ስለሆነ
ልታደርገው የሚገባህን ሁሉ ፈጽም፤ 8 የሚታ
ጠለውንና ስደኅንነት የሚሆነውንም የኅብረት
መሥዋዕት ስማቅረብ እንተን ወደማገኝበት ወደ
ጌልገላ ቀድመኸኝ ትሄዳለህ፤ እኔ መጥቼ ምን
ማድረግ እንደሚገባህ እስከነግርህ ድረስ ሰሰባት
ቀን በዚያው ቆይ።"

9 ሳኦልም ከሳሙኤል ተለይቶ በሄደ ጊዜ እግ
ዚአብሔር የሳኦልን ልብ በመሰወጥ አዲስ ሕይ
ወት ሰጠው፤ ሳሙኤል በምልክት የነገረውም
ሁሉ በዚያን ቀን ተፈጸመ። 10 ሳኦልና አገል
ጋዩ ጊብዓ በደረሱ ጊዜ የነቢያት ጉባኤ ከሳኦል
ጋር ተገናኘ፤ በድንገት የእግዚአብሔር መንፈስ
ቡኃይል በሳኦል ላይ ወረደ፤ በዚያን ጊዜም
እርሱ ከእነርሱ ጋር ማሸብሸብና ድምፁን ከፍ
አድርጎ ትንቢት መናገር ጀመረ። 11 ከዚያ
በፊት እርሱን የሚያውቁትም ሰዎች ይህን ሲያ
ደርግ በተመለከቱ ጊዜ "የቂስን ልጅ ምን
ነካው? ሳኦል ከነቢያት እንደ አንዱ ሆኖ ተቈ
ጥሮአልን?" በማለት እርስ በርሳቸው ተጠያ
የቁ። 12 በዚያም የሚኖር አንድ ሰው "የእነዚ
ህስ የሌሎቹ ነቢያት ሁኔታ እንዴት ነው? አባ
ቶቻቸውስ እነማን ናቸው?" ሲል ጠየቀ፤
"ሳኦልም ደግሞ ከነቢያት አንዱ ሆኖ ተቈጠረ
እንዴ?" የሚል የምሳሌ አነጋገር የመነጨውም
ከዚህ ነው። 13 ሳኦልም እያሸበሸበ ድምፁን
ከፍ አድርጎ ትንቢት መናገሩን ከፈጸመ በኋላ
በኮረብታው ላይ ወደሚገኘው መሠዊያ ወጣ።

14 የሳኦል አጐት ሳኦልንና አገልጋዩን አይቶ
"የት ነበራችሁ?" ሲል ጠየቃቸው።

ሳኦልም "አህዮች ልንፈልግ ሄደን ልናገኛ
ቸው ስላልቻልን ሳሙኤልን ስመጠየቅ ነራ
ብስን ነበር" ሲል መለሰለት።

15 አጐትየውም "እርሱስ ምን አላችሁ?"
ሲል ጠየቀ።

16 ሳኦልም "የአህዮቹን መገኘት ነግሮናል"
ሲል መለሰለት፤ ነገር ግን ንጉሥ ስለመሆኑ ሳሙ
ኤል የነገረውን ሁሉ ለእጐቱ አላወራለትም።

ሳኦል ንጉሥ መሆኑ በይፋ ተነገረ

17 ሳሙኤል በምጽጳ መንፈሳዊ ስብሰባ ያደ
ርጉ ዘንድ ሕዝቡን ሁሉ በእንድነት ጠራ፤
18 እንዲህም አላቸው፥ "የእስራኤል አምላክ
የሆነ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ 'እኔ እኔ
ከግብጽ ምድር አወጣኋችሁ፤ ከግብጻውያንና
ከሚጨቍኑአችሁ ከሌሎች ሕዝቦች ሁሉ በመ
ታደግ አዳንሁአችሁ፤ 19 ከመከራችሁና ከችግራ
ችሁ ሁሉ በመታደግ የማድናችሁ እኔ አምላክ
ችሁ ነኝ፤ አሁን ግን እኔን ከድታችሁ ንጉሥ

10:12 ፡- 1ሳሙ. 19:23-24።

እንዳነግሥሳችሁ ጠይቃችኋል ፤ መልካም ነው ! በሉ እንግዲህ በየነገዳችሁና በየጐሳችሁ በእግዚ አብሔር ፊት ተሰብሰቡ ።’’’

20ከዚህ በኋላ ሳሙኤል እያንዳንዱ ነገድ ወደ ፊት እንዲቀርብ እደረገ ፤ እግዚአብሔርም የብንያምን ነገድ መረጠ ፤ 21እንደገናም ሳሙ ኤል ፥ የብንያም ነገድ ቤተሰቦች ሁሉ ወደፊት እንዲቀርቡ እደረገ ፤ ከነዚያም የማጥሪ ቤተሰብ ተመረጠ ፤ የማጥሪ ቤተሰብ የሆኑ ወንዶችም ወደፊት እንዲቀርቡ ተደርጎ ከእነርሱ መካከል የቂስ ልጅ ሳኦል ተመረጠ ፤ እነርሱም በፊስ ጉት ጊዜ ሊያገኙት አልቻሉም ፤ 22ሰለዚህም እነርሱ “ሌላ የቀረ ይኖር ይሆን ?’’ ሲሉ እግዚ አብሔርን ጠየቁ ።

እግዚአብሔርም “ሳኦል እነሆ በስንቅ ጓዝ መካከል ተደብቆ ይገኛል’’ ሲል መለሰላቸው ።

23ስልዚህም እነርሱ ፈጠን ብለው በመሄድ ከተሸሸገበት እውጥተው ወደ ሕዝቡ እመ ጡት ፤ ሕዝቡም ሳኦል በቁመት ከሁሉ የሚበ ልጥ መሆኑን ተመለከቱ ፤ 24ሳሙኤልም ሕዝ ቡን “እግዚአብሔር የመረጠው ሰው እነሆ ይህ ነው ! ከእኛም መካከል እርሱን የሚስተካከለው የለም’’ አለ ።

ሕዝቡም ሁሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው “ንጉሡ ለዘላለም ይኑር !’’ አሉ ።

25ሳሙኤልም ለሕዝቡ ፥ ለእንደ ንጉሥ ሊደረግለት የሚገባውን ወግና ሥርዓት አስረዳ ቸው ፤ ያንንም በመጽሐፍ ጽፎ በእግዚአብሔር ፊት በተቀደሰ ስፍራ አስቀመጠው ፤ ከዚያም በኋላ ሕዝቡን ሁሉ ወደየቤቱ አሰናበተ ፤ 26ሳኦልም በጊብዓ ወደሚገኘው ቤቱ ተመልሶ ሄደ ፤ በእግዚአብሔር ፍቅር የተሞሉ ጎያላን ጦረኞች ሳኦልን ተከትለው ሄዱ ፤ 27ነገር ግን እንዳንድ የማይረቡ ሥርዓት አልባዎች “አሁን ይህ ሰው እኛን ለመዳን ምን ሊጠቅመን ይች ላል ?’’ ተባባሉ ፤ እርሱንም በመናቅ ምንም ዐይነት ገጸ በረከት ሳያመጡለት ቀሩ ።

ምዕራፍ 11

ሳኦል ዐሞናውያንን ድል አደረገ

1ከእንድ ወር በኋላ የዐሞን ንጉሥ ናዖስ በገ ለዓድ ግዛት በምትገኘው በያቤሽ ከተማ ላይ ሠራዊቱን በማዝመት ከበባት ፤ የያቤሽም ሰዎች ናዖስን “ከእኛ ጋር የውል ስምምነት አድርግ ፤ እኛም የእንተ አገልጋዮች እንሆናለን’’ አሉት ።

2ናዖስም “ከእናንተ ጋር የውል ስምምነት ማድረግ የምችልበት እንደ ዐይነት ግዴታ አለ ፤ ይኸውም የእያንዳንዱን ሰው ቀኝ ዐይን በማውጣት በእስራኤላውያን ላይ አሰፋሪ ውር ደት አመጣለሁ’’ ሲል መለሰላቸው ።

3የያቤሽ መሪዎችም “ወደ መላይቱ የእስራ ኤል ምድር መልእክተኞች እስክንልክ ድረስ የሰባት ቀን ጊዜ ስጠን ፤ እኛን የሚታደገን ካጣን ለእንተ እጃችንን እንሰጣለን’’ አሉት ።

4መልእክተኞቹም ሳኦል ወዳለበት ወደ ጊብዓ ደረሱ ፤ ወሬውንም በተናገሩ ጊዜ ሕዝቡ ተሰፋ በመቊረጥ እየጮኸ ማልቀስ ጀመሩ ፤ 5ሳኦል ስዚህ ጊዜ ጥንድ በሬዎቹን ይዞ ከዋል በት እርሻ በመመለስ ላይ ነበር ፤ እርሱም “ምንድን ነው ነገሩ ? ሰው ሁሉ የሚያለቅሰው ስለምንድን ነው ?’’ ሲል ጠየቀ ፤ እነርሱም ከያ ቤሽ የመጡ መልእክተኞች የሚሉትን ወሬ ነገ ሩት ። 6ሳኦልም ይህን በሰማ ጊዜ የእግዚአብ ሔር መንፈስ በእርሱ ላይ በኀይል ወረደ ፤ የሳኦ ልም ቊጣ እጅግ ተቃጠለ ። 7ጥንዱንም በሬ ዎች ወስዶ ቈራረጣቸው ፤ የሥጋውንም ቊራጭ ሁሉ እስይዞ “ሳኦልንና ሳሙኤልን ተከትሎ ወደ ጦርነት የማይወጣ ሰው ቢኖር በሬዎቹ እንደዚህ ይቈራረጡበታል’’ ከሚል ማሰጠንቀቂያ ጋር መልእክተኞችን ወደ መላው የእሰራኤል ምድር ላከ ።

የእሰራኤልም ሕዝብ እግዚአብሔር ስለሚያደ ርገው ነገር ፈርተው እንድም ሰው ሳይቀር ሁሉም በእንድነት ወጡ ፤ 8ሳኦልም ቤዜቅ በተ ባለ ሰፍራ ሰበሰባቸው ፤ የቊጥራቸውም ብዛት ከእሰራኤል የመጡት ሦስት መቶ ሺ ሲሆን ከይ ሁዳ የመጡት ሠላሳ ሺ ነበር ። 9ከያቤሽ የመጡ ትንም መልእክተኞች “ነገ ከቀትር በፊት በመታ ደግ የምናድናቸው መሆኑን ለሕዝባችሁ ንገሩ’’ አሉአቸው ። የያቤሽም ሕዝብ ይህን መልእክት በተቀበሉ ጊዜ እጅግ ተደሰቱ ። 10ናዖስንም “ነገ እጃችንን ለእንተ እንሰጣለን ፤ እንተም በእኛ ላይ ደስ ያለህን ሁሉ ማድረግ ትችላለህ’’ አሉት ።

11በማግሥቱም ማልድ ብሎ በመነሣት ሳኦል ሠራዊቱን ከሦስት ከፈለው ፤ ገና ሲነጋም ገሥግሦው ወደ ጠላት ጦር ሰፈር በመግባት በዐ ሞናውያን ላይ አደጋ ጣሉባቸው ፤ ቀትር እስኪ ሆንም ዐሞናውያንን ፈጁ ፤ ከእልቂት የተረፉ ትም ለየብቻቸው በመሮጥ ተበታተኑ ።

12ከዚህ በኋላ የእስራኤል ሕዝብ ሳሙኤልን “ሳኦል በእኛ ላይ እይነግሥብንም ያሉት ሰዎች የት አሉ ፤ እነርሱን አሳልፈህ ስጠንና እንግደላቸው’’ አሉት ።

13ሳኦል ግን “በዛሬ ዕለት ማንም ሰው እይገ ደልም ፤ ምክንያቱም የዛሬው ዕለት እግዚአብ ሔር እስራኤልን በመታደግ ያዳነበት ቀን ነው’’ አለ ። 14ሳሙኤልም “ሁላችንም ወደ ጌልገላ እንሂድና ሳኦል ንጉሣችን መሆኑን እንደገና ለይፋ እናስታውቅ’’ አላቸው ።

15ስስዚህም ሁሉም ወደ ጌልገላ ሄዱ ፤ እዚ ያም በተቀደሰው ስፍራ ሳኦል ንጉሥ መሆኑን በይፋ አስታወቁ ፤ በዚያም ስደኅንነት የሚሆኑ ውን የኅብረት መሥዋዕት አቀረቡ ፤ ሳኦልና የእ ስራኤል ሕዝብ ሁሉ የዚያን ድል በዓል በደ ስታ አከበሩ ።

ምዕራፍ 12

ሳሙኤል የተናገረው የመሰናበቻ ቃል

1 ከዚህ በኋላ ሳሙኤል ለእስራኤል ሕዝብ
እንዲህ አለ፥ “ጥያቄአችሁን ሁሉ ተቀብዬ
ንጉሥ አንግሼላችኋለሁ፤ 2 ከእንግዲህ ወዲህ
እነሆ የሚመራችሁ ንጉሥ አማኝታችኋል፤ እኔ
ግን ዕድሜዬ ስለገፋ ሽምግያለሁ፤ ልጆቼም
ከእናንተው ጋር አሉ፤ ከወጣትነት ጊዜዬ
ጀምሮ እስከ እሁን ድረስ የእናንተ መሪ ሆኜ
ቆይቼአለሁ። 3 እነሆ እሁን በፊታችሁ እገኛ
ለሁ፤ የበደልሁት ነገር አለ እንደሆን፥ እነሆ
በእግዚአብሔርና እርሱ በመረጠው ንጉሥ ፊት
ልትከሱኝ ትችላላችሁ፤ ከቶ እኔ ላም ወይም
አህያ የወሰድሁበት ሰው ይገኛልን? ያታለልሁ
ትና የጨቈንሁትስ ሰው አለን? ከማንም ሰው
ጉቦ የተቀበልሁበት ጊዜ አለን? ከእነዚህ ሁሉ
ነገሮች አንዱን እንኳ እድርጌ ከሆነሁ የወሰድ
ሁትን ለመመለስ ዝግጁ ነኝ።”

4 ሕዝቡም “ከቶ አላታለልኸንም፤ አልጨቈ
ንከንም፤ ከማንም ሰው ምንም ነገር አልወሰድ
ህም” ሲሉ መለሱለት።

5 ሳሙኤልም “እንግዲህ ዛሬ በፊታችሁ
ንጹሕ ሆኜ ሰለመገኘቴ እግዚአብሔርና እርሱ
የመረጠው ንጉሥ ምስክሮች ናቸው” አለ።

ሕዝቡም “አዎ! እግዚአብሔር ምስክራችን
ነው” ሲሉ መለሱለት።

6 ሳሙኤልም የሚናገረውን ቃል በመቀጠል
እንዲህ አለ፥ “ሙሴንና አሮንን የመረጠ፥ የቀ
ድሞ አባቶቻችሁንም ከግብጽ ምድር ያወጣ
እግዚአብሔር ነው፤ 7 እንግዲህ ተነሥታችሁ
ባላችሁበት ቁሙ፤ የቀድሞ አባቶቻችሁንና እና
ንተን ለማዳን እግዚአብሔር ያደረገላቸውን
ድንቅ ሥራዎች ሁሉ በማስታወሰ እነሆ እኔ
በእግዚአብሔር ፊት አከሳችኋለሁ፤ 8 ያዕቆብና
ቤተሰቡ ወደ ግብጽ መርደው በዚያ ሲኖሩ ግብ
ጻውያን የጭቆና ቀንበር ጫኑባቸው፤ የቀድሞ
አባቶቻቸውም ዕርዳታ ለማግኘት ወደ እግዚአ
ብሔር ጮኹ፤ እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን
ላከላቸው፤ እነርሱም ከግብጽ መርተው በማው
ጣት በዚህች ምድር እንዲሰፍሩ አደረጉአ
ቸው፤ 9 ነገር ግን ሕዝቡ አምላካቸውን እግዚአ
ብሔርን ረሱ፤ ስለዚህም እግዚአብሔር ፍልሰጥ
ኤማውያንና የሞአብ ንጉሥ፥ እንዲሁም የሐ
ጸር ከተማ ሠራዊት አዛዥ የነበረው ሲሣራ በቀ
ድሞ አባቶቻቸው ላይ በጠሳትነት ተነሥተው
በመውረር ድል እንዲነሡአቸው አደረገ።
10 ከዚያም በኋላ ዕርዳታ ለማግኘት እንዲህ
ሲሉ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፥ ‘እግዚአብ
ሔር ሆይ! ከአንተ ርቀን ባዓልና ዐስታሮት
ተብሎ ስሚጠሩት የባዕዳን አማልክት ምስሎች
በመሰገዳችን ምክንያት እነሆ በደል ሠርተናል፤
አባክህ ከጠላቶቻችን እጅ በመታደግ አድነን፤
እኛም አንተን እናመልካለን።’ 11 እግዚአብሔ
ርም መጀመሪያ ጌዴዎንን፥ ከዚያም በኋላ ባራ
ቅንና ዮፍታሔን፥ በመጨረሻም እኔን ላከ፤
እኛም እያንዳንዳችን እናንተን ከጠላቶቻችሁ
እጅ በመታደግ አድነን በሰላም እንድትኖሩ አደ
ረግን፤ 12 እናንተ ግን የዐሞን ንጉሥ ናዖስ
አደጋ ሊጥልባችሁ መነሣቱን ባያችሁ ጊዜ
ንጉሣችሁ የነበረውን እግዚአብሔርን ከድታ
ችሁ ‘የሚመራን ንጉሥ አንግሥልን’ ሰትሉ
ጠየቃችሁኝ።

13 “እንግዲህ የመረጣችሁት ንጉሥ እነሆ!
በጠየቃችሁት መሠረት እግዚአብሔር አርሱን
ሰጥቶአችኋል፤ 14 እምላካችሁን እግዚአብሔርን
ብታከብሩትና ብታገለግሉት፥ ቃሉን ብትሰ
ሙና ትእዛዙቱንም ብትጠብቁ፥ እናንተና ንጉ
ሣችሁም እርሱን ብትከተሉት ሁሉ ነገር ይሰም
ርላችኋል፤ 15 ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል
ባትሰሙ፥ ትእዛዛቱንም ባትፈጽሙ፥ እርሱ
ራሱ በጠላትነት ይነሣባችኋል፤ 16 ስለዚህ ባላች
ሁበት ጸንታችሁ ቁሙ፤ እግዚአብሔር የሚያደ
ርገውንም ድንቅ ነገር ታያላችሁ፤ 17 እነሆ
አሁን እንደምታውቁት የዐሐይ ትኩሳት የበዛ
በት የመከር ወራት ነው፤ ነገር ግን እኔ አሁን
እጸልያለሁ፤ እግዚአብሔርም ነጐድጓድና
ዝናም ይልክል፤ ይህም በሚሆንበት ጊዜ
ንጉሥ እንዲያነግሥላችሁ በመጠየቃችሁ ምነን
ያት በደል በመሥራት እግዚአብሔርን ያሳዘና
ችሁ መሆናችሁን ታረጋግጣላችሁ።”

18 ከዚህም በኋላ ሳሙኤል ጸሰየ፤ እግዚአብ
ሔርም በዚያኑ ዕለት ነጐድጓድና ዝናም ላከ፤
ከዚህም የተነሣ ሕዝቡ እግዚአብሔርንና ሳሙ
ኤልን እጅግ ፈሩ፤ 19 ሳሙኤልንም እንዲህ
አሉት፥ “እንዳንሞት እባክህ ወደ አምላክህ
ወደ እግዚአብሔር ጸልይልን፤ ሌላውን ኃጢ
አት ሁሉ ክመሥራት አልፈን ንጉሥ እንዲያነግ
ሥልን በመጠየቃችን በደለኞች መሆናችንን
አሁን ተገንዝበናል።”

20 ሳሙኤልም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፥
“አይዞአችሁ አትፍሩ፤ ይህን የመሰለ ክፉ ነገር
ያደረጋችሁ ብትሆኑ እንኳ በሙሉ ልባችሁ
እርሱን አገልግሉት እንጂ ፈቃችሁን ከእግዚአ
ብሔር ወደ ሌላ አትመልሱ። 21 ሐሰተኞች
አማልክትን አትከተሉ፤ እነርሱ እውነተኞች
ስላልሆኑ ምንም ሊረዱአችሁም ሆነ ሊያድኑአ
ችሁ አይችሉም፤ 22 እግዚአብሔር ፍጹም
ተሰፋ ስለሰጣችሁ እይተዋችሁም፤ ምክንያቱም
እርሱ የራሱ ወገን ሊያደርጋችሁ አስቀድሞ

12:6 ፡- ዘጸ. 6:26 ። 12:8 ፡- ዘጸ. 2:23 ። 12:9 ፡- መሳ. 3:12 ፤ 4:2 ፤ 13:1 ። 12:10 ፡- መሳ. 10:10-15 ።
12:11 ፡- ፩ሳሙ. 3:20 ፡ መሳ. 4:6 ፤ 7:1 ፤ 11:29 ። 12:12 ፡- ፩ሳሙ. 8:19 ።

ወስኖአል፤ 23 እኔ በበኩሌ ስለ አናንተ መጸለይ
ይን በማቋረጥ እግዚአብሔርን የምበድል ሆኜ
እንዳልገኝ እርሱ ይጠብቀኝ፤ ይልቅስ ስለእና
ንተ መጸለይን በማቋረጥ ፈንታ ልታደርጉት
የሚገባችሁን መልካምና ቅን ነገር አስተም
ራችኋለሁ። 24 ስለዚህ ስእግዚአብሔር ታዘዙ፤
በሙሉ ልባችሁም በታማኝነት አገልግሉት፤
እርሱ ለእናንተ ያደረገላችሁን ድንቅ ነገሮች
ሁሉ አስታውሱ፤ 25 ነጢአት በመሥራት ብት
ጸኑ ግን እናንተም ንጉሣችሁም ትጠፋላ
ችሁ።"

ምዕራፍ 13

በፍልስጥኤማውያን ላይ የተደረገ ጦርነት

1 ሳኦል በነገሠ በሁለተኛው ዓመት፤ 2 ሳኦል
ከእስራኤል ሕዝብ መካከል የተውጣጡ ሦስት
ሺ ሰዎችን መርጦ፥ ከእነርሱ መካከል ሁለቱን
ሺ በሚክማስና በቤትኤል በሚገኘው ኮረብታማ
አገር ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ መደበ፥ አንዱን ሺ
ሰዎች ደግሞ ከልጁ ከዮናታን ጋር በማሰለፍ
በብንያም ነገድ ግዛት ውስጥ ጊብዓ ተብሎ ወደ
ሚጠራው ኮረብታማ አገር ላከ፤ ከዚህ የተረፉ
ትን ሌሎች ሰዎች ግን ወደየቤታቸው አሰና
በተ።

3 ዮናታን ጌባዕ ተብሎ በሚጠራው ሰፍራ
በፍልስጥኤማውያን ላይ አደጋ ጣለ፤ ፍልስጥኤ
ማውያንም ሁሉ ይዘን ወሬ ሰሙ፤ ሳኦልም
መልእክተኞች ልኮ በመላ አገሪቱ መለከት በማ
ስነፋት ዕብራውያንን ሁሉ ስመርኔት ጠራ።
4 ሳኦል የፍልስጥኤማውያንን የጦር አዛዥ መግ
ደሉና ከዚህም የተነሣ ፍልስጥኤማውያን በእስ
ራኤላውያን ላይ ብርቱ ጥላቻ ያደረባቸው
መሆኑ ለመላው እስራኤላውያን ተንሚሶአቸው
ነበር፤ ስለዚህም ሕዝቡ በጊልገላ ከሳኦል ጋር
የሚሰለፉ መሆናቸውን በመገለጥ መልሰ ሰጡ።
5 ፍልስጥኤማውያንም እስራኤላውያንን ስመ
ውጋት ተሰበሰቡ፤ አነርሱም ከሠላሳ ሺ የጦር
ሠረገላዎችና ከስድስት ሺ ፈረሰኞች ጋር ብዛቱ
እንደ ባሕር ዳር አሸዋ ሊቈጠር የማይችል ሠራ
ዊት ነበራቸው፤ ሄደውም በቤትአዌን በስተም
ሥራቅ ሚክማስ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ
መሸጉ፤ 6 እዚያም ሆነው በሚዋጉት ብርቱ
አደጋ አስራኤላውያንን ማርበትበት ጀመሩ፤
ከዚህም የተነሣ ከእስራኤላውያን አንዳንዶቹ
በየዋሻውና በየጉድጓዱ፥ እንዲሁም በተሰነ
ጣጠቁ አለቶችና በተሰረጉሱ ጕድጓዶች ተሸሸ
ገው ነበር፤ 7 ሌሎቹ ደግሞ የዮርዳኖስን ወንዝ
ተሻግረው ወደ ጋድና ወደ ገለዓድ ግዛቶች
ሄዱ።

ሳኦል ግን አስከዚህ ጊዜ ድረስ በጊልገላ
ነበር፤ ከእርሱም ጋር የነበሩ ሕዝብ ከመፍራታ
ቸው የተነሣ ይንቀጠቀጡ ነበር፤ 8 ሳኦልም
አሰከ ሰባት ቀን ድረስ የሳሙኤልን መምጣት
ሲጠብቅ ቆየ፤ ምክንያቱም እንዲሁ ያደርግ
ዘንድ ሳሙኤል ሳኦልን አዝዞት ነበር፤ ይሁን
እንጂ አስከዚያ ጊዜ ድረስ ሳሙኤል ወደ ጌል
ገላ አልመጣም ነበር፤ ከዚህም የተነሣ ሕዝቡ
ሳኦልን በመክዳት ማፈግፈግ ጀመሩ፤ 9 ስለዚ
ህም ሳኦል ሕዝቡን "የሚቃጠለውንና እንዲ
ሁም ስደኅንነት የሚሆነውን የኅብረት መሥዋ
ዕት አምጡልኝ" ብሎ በማዘዝ የሚቃጠለውን
መሥዋዕት አቀረበ። 10 ይሆንንም መሥዋዕት
የማቅረቡን ሥርዓት እንደፈጸመ ወዲያውኑ
ሳሙኤል ደረሰ፤ ሳኦልም ወጥቶ አቀባበል አደ
ረገለት፤ 11 ሳሙኤል ግን "ያደረግኸው ነገር
ምንድን ነው?" ሲል ጠየቀው።

ሳኦልም እንዲህ ሲል መለሰለት፥ "ሕዝቡ
ሊክዱኝ ተቃርበው ነበር፤ አንተም በቀጠርከኝ
ሰዓት ሳትመጣ ቀረህ፤ ከዚህም በላይ ፍልስጥኤ
ማውያን መጥተው በሚክማስ ተሰሰፉ፤ 12 ስለዚ
ህም 'ፍልስጥኤማውያን ገና በጌልገላ ሳለሁ
አደጋ ሊጥሉብኝ ነው፤ የእግዚአብሔርንም ዕር
ዳታ ስማግኘት አልተዘጋጀሁም' ብዬ አሰብሁ፤
መሥዋዕት ማቅረብ እንደሚገባኝም ተረዳሁ።"

13 ሳሙኤልም ሲመልስለት እንዲህ አለው፥
"ይዘ የሞኝነት አመራር ነው፤ አምላክህ አግዚ
አብሔር የሰጠህን ትእዛዝ አልፈጸምህም፤ ትእዛ
ዙን ብትፈጽም ኖሮ አንተና ዘሮችህ በአስራ
ኤል ላይ ስዘላለም እንድትነግሡ ሃሳ መንግሥ
ትህን ባጸናልህ ነበር፤ 14 አሁን ግን መንግሥ
ትህ ወደ ፊት የሚቀጥል እንደማይሆን ዕወቅ፤
ምክንያቱም ለአግዚአብሔር ታዛዥ ሆነህ አል
ተገኘህም፤ ስለዚህም እግዚአብሔር የሚፈቅደ
ውን ሰው መርጦ ለሕዝቡ በእስራኤል ላይ ያነ
ግሣል።"

15 ሳሙኤልም ከጌልገላ ተነሥቶ ሄደ፤ ሳኦ
ልም ከወታደሮቹ ጋር ለመደባለቅ ሲሄድ የቀ
ሩት ሕዝብ ተከተሉት፤ ከጌልገላም ተነሥተው
በብንያም ግዛት ወደምትገኘው ወደ ጊብዓ
ሄዱ፤ ሳኦልም ሠራዊቱን በቈጠረ ጊዜ ብዛታ
ቸው ስድስት መቶ ሆኖ ተገኘ፤ 16 ሳኦል፥
ልጁ ዮናታንና ሠራዊታቸው በብንያም ግዛት
ውስጥ ጌባዕ ተብላ በምትጠራው ሰፍራ
መሸጉ፤ የፍልስጥኤማውያን ወታደሮችም
ምሽግ በሚኽማስ ነበር፤ 17 የፍልስጥኤማውያን
ወታደሮች በሦስት ክፍል ተከፍለው ወረራ ስግ
ድረግ ከምሽጋቸው ወጡ፤ አንዱ ቡድን በሹ
ዓል ግዛት ወደሚገኘው ወደ ያፍራ አቅጣጫ
አመራ፤ 18 ሁለተኛው ቡድን ወደ ቤትሖሮን
ሲሄድ፥ ሦስተኛው ቡድን ከጸቦዓም ሸለቆና
ከምድረበዳው ፊት ለፊት ወደሚገኘው ጠረፍ
አለፈ።

13:8 ፦ 10:8። 13:14 ፦ ሐሥ. 13:22።

19 በዚያን ዘመን በእስራኤል ብረት አቅል
ጠው የሚሠሩ ጠቢባን አልነበሩም ፤ ምክንያ
ቱም ዕብራውያን ሰይፍና ጦር እንዳይሠሩ ፍል
ስጥኤማውያን ቍጥጥር ያደርጉባቸው ነበር ፤
20 እንዱውም እስራኤላውያን ማረሻቸውንና
ዶማቸውን ለማሾል ፥ መጥረቢያቸውንና ማሄዴ
ቸውን ለማሳል ወደ ፍልስጥኤማውያን መው
ረድ ነበረባቸው ፤ 21 መጥረቢያ ለማሳልና የበሬ
መንጃ ለማሾል የሚከፈለው ዋጋ እራት ግራም
ያህል የሚመዝን ጥሬ ብር ነበር ፤ ማረሻና ዶማ
ለማሾልም የሚከፈለው ዋጋ የዚሁ እጥፍ
ነበር ። 22 ከዚህም የተነሣ በጦርነቱ ቀን ከሳእ
ልና ከልጁ ከዮናታን በቀር በእስራኤላውያን
ወታደሮች መካከል ሰይፍና ጦር የያዘ እልነበ
ሩም ።

23 ፍልስጥኤማውያን የሚክማስን መተላለ
ፊያ የሚከላከል እንድ የጦር ቡድን ላኩ ።

ምዕራፍ 14

ዮናታን በፍልስጥኤማውያን ላይ በቈራጥነት የጣለው አደጋ

1 እንድ ቀን ዮናታን የጦር መሣሪያ የሚሸከ
ምለትን ወጣት ጋሻ ጃግሬውን "ወደ ፍልስጥኤ
ማውያን የጦር ሰፈር እንሻገር" አለው ። ነገር
ግን ዮናታን ይህን ጉዳይ ለአባቱ ለሳኦል እንኳ
አልነገረውም ፤ 2 በዚህ ጊዜ ሳኦል ከጊብዓ
በጣም ላይርቅ በሚግሮን በእንድ የሮማን ዛፍ
ሥር ሰፍሮ ነበር ፤ ከእርሱም ጋር ስድስት መቶ
ጭፍሮች ነበሩ ፤ 3 ኤፉድ በመልበስ ከእርሱ
ጋር የነበረው ካህን የኢካቦድ ወንድም የአሒ
ጡብ ልጅ አኪያ ነበር ፤ እኪያም ከፊንሐስ የተ
ወለደው ፥ በሴሎም የእግዚአብሔር እገልጋይ
የነበረው የካህኑ የዔሊ የልጅ ልጅ ነበር ፤ ከሳ
እል ጋር የነበሩትም ጭፍሮች ዮናታን ወዴት
እንደሄደ እላወቁም ነበር ።

4 ዮናታን ወደ ፍልስጥኤማውያን ሰፈር ለመ
ድረስ በሚከማስ መተላለፊያ መውጣት ነበረ
በት ፤ በመተላለፊያውም ከግራና ከቀኝ ሁለት
ሾጣጣ አለቶች ሲኖሩ የእንደኛው አለት ስም
ቦዼጽ ፥ የሁለተኛውም ሰም ሴኔ ተብሎ ይጠ
ራል ፤ 5 ከአለቶቹም አንዱ ከመተላለፊያው
በስተ ሰሜን ዘኩል በሚከማስ ፊት ለፊት የሚገ
ኘው ሲሆን ፥ ሁለተኛውም በስተደቡብ በኩል
በጌባዕ ፊት ለፊት ይገኛ ነበር ።

6 ዮናታን ጋሻ ጃግሬ የሆነውን ወጣት "ወደ
ነዚያ ወደ አረማውያን ጦር ሰፈር እንሻገር ፤
ምናልባትም እግዚአብሔር ይረዳን ይሆናል ፤
እኛ የቱንም ያህል ጥቂቶች ብንሆን እግዚአብ
ሔር ከፈቀደ ለእኛ ድልን ከማቀዳጀት የሚገ
ታው ኀይል የለም እሰው ።"

7 ወጣቱም ጋሻጃግሬ "የምትፈቅደውን ነገር
ሁሉ እድርግ ፤ እኔ ከእንተ አልለይም ፤ በሙሉ
ልቤም ከእንተ ጋር ነኝ" አለው ።

8 ዮናታንም እንዲህ አለው ፥ "እሺ እንግዲያ
ውስ ወደ ማዶ እንሻገርና ለፍልስጥኤማውያን
ፊት ለፊት እንታያቸው ፤ 9 እነርሱም 'ወደ እና
ንተ እስከንመጣ ድረስ በዚያ ጠብቁን' ቢሉን ፥
ባለንበት እንቆያለን ፤ 10 ነገር ግን 'ወደ እኛ ኑ'
ቢሉን ፥ ወደ እነርሱ እንሄዳለን ፤ እግዚአብሔር
በፍልስጥኤማውያን ላይ ድልን ሊያቀዳጀን ለለ
መፍቀዱ ይህ ራሱ ምልክት ይሆናል ።"

11 እነርሱም ወጣ ብለው ለፍልስጥኤማው
ያን ታዩአቸው ፤ ፍልስጥኤማውያንም "ተመል
ከቱ! እንዳንድ ዕብራውያን ከተሸሸጉበት
ጉድጓድ በመውጣት ላይ ናቸው!" ተባባሉ ፤
12 ከዚህ በኋላ ፍልስጥኤማውያን ዮናታንና ጋሻ
ጃግሬውን ጠርተው "የምንነግራችሁ ጉዳይ ሰላ
ሰን ወደዚህ እኛ ወዳለንበት ኑ" አሉአቸው ።

ዮናታንም ጋሻጃግሬውን "እንግዲህ ተከተ
ለኝ! እግዚአብሔር ለእስራኤል በፍልስጥኤማ
ውያን ላይ ድልን በጥቶአል" አለው ፤ 13 ዮናታ
ንም በእጁና በጕልበቱ እየዳኸ ወደ አፋፉ
ወጣ ፤ ጋሻጃግሬውም ተከተለው ፤ ዮናታንም
በፍልስጥኤማውያን ላይ ድንገተኛ እደጋ በመ
ጣል ድባቅ መታቸው ፤ እርሱ የጣላቸውንም
ጋሻጃግሬው ገደላቸው ። 14 በመጀመሪያውም
ግድያ በእንድ የእርሻ ከልል ላይ ሃያ ያህል
ሰዎችን ገደሉ ፤ 15 በገጠር የነበሩ ፍልስጥኤማ
ውያንም ሁሉ ተሸበሩ ፤ እደጋ ጣዮችና በሰፈር
የነበሩ ወታደሮችም ሁሉ በፍርሃት ተንቀጠ
ቀጡ ፤ እግዚአብሔር በላከባቸውም እስጨናቂ
ሽብር መሬት ተንቀጠቀጠች ።

ፍልስጥኤማውያን ተሸነፉ

16 የሳኦል ወታደሮች የብንያም ግዛት በሆነ
ችው በጊብዓ መሸገው ሁኔታውን ሁሉ በመጠባ
በቅ ላይ ሳሉ በመታወክ የሚሸሹትን ፍልስጥኤ
ማውያን አዩ ። 17 ስለዚህም ሳኦል "እስቲ ወታ
ደሮችን ቍጠሩና ከእኛ መካከል የጐደሉ እን
ዳሉ እረጋግጡ" ብሎ እዘዘ ፤ በትእዛዙም መሠ
ረት ሠራዊቱን በቈጠሩ ጊዜ ዮናታንና ጋሻጃግ
ሬው አለመኖራቸው ታወቀ ። 18 ሳኦልም ካህ
ኑን እኪያን "ኤፉዱን ይዘህ ና" አለው ። በዚ
ያን ቀን ካህኑ እኪያ ኤፉድ ለብሶ በእስራኤል
ሕዝብ ፊት ነበር ፤ 19 ሳኦል ከካህኑ ጋር በመነ
ጋገር ላይ ሳለ ፥ በፍልስጥኤማውያን ሰፈር የተነ
ሣው ሁከትና ሽብር እየባሰበት ሄደ ፤ ሳኦልም
ካህኑን "እግዚአብሔርን ለመጠየቅ አሁን ጊዜ
የለንም!" አለው ። 20 ከዚህ በኋላ ሳኦልና ወታ
ደሮቹ ካሉበት በመንቀሳቀስ በሽብርና ሁከት
እርሰ በርሳቸው መፋጀት በጀመሩት ፍልስጥኤ
ማውያን ላይ ዘመቱባቸው ። 21 ከፍልስጥኤማው
ያን ጋር በመተባበር ወደ ጦሩ ሰፈር ሄደው የነ
በሩ እንዳንድ ዕብራውያንም ፍልስጥኤማውያ
ንን ከድተው ከሳኦልና ከዮናታን ጋር ተባበሩ ።
22 በኤፍሬም ኮረብታዎች ተደብቀው የነበሩ

ሌሎች እስራኤላውያንም ፍልስጥኤማውያን በሽ
ሽት ላይ መሆናቸውን ሰሙ ፤ ስለዚህም ከወገን
ጦር ጋር ተባብረው በፍልስጥኤማውያን ላይ
አደጋ በመጣል ፥ 23 እስከ ቤትአዌን ከተማ ማዶ
ባለው መንገድ ሁሉ ተከታትለው ወጉአቸው ፤
እግዚአብሔርም በዚያን ቀን እስራኤልን በመታ
ደግ እዳነ ።

ከሞርነቱ በኋላ የተፈጸሙ ድርጊቶች

24 በዚያን ቀን እስራኤላውያን በረሀብ
ደከሙ ፤ ምክንያቱም ሳኦል “ጠላቶቼን እስክበ
ቀል ድረስ ዛሬ እህል ውሃ የሚቀምስ ማናቸ
ውም ሰው የተረገመ ይሁን” ብሎ በመማል
ማንም ሰው እህል ውሃ እንዳይቀምስ ትእዛዝ
ሰጥቶ ነበር ። ከዚህም የተነሣ ሁሉም ምንም
ነገር ሳይቀምሱ ቀኑን ሙሉ ዋሉ ። 25 ጫካ
ወደበዛበትም ቦታ በመጡም ጊዜ በየስፍራው
ማር አግኝተው ነበር ፤ 26 ዛፉ ሁሉ ማር የሞላ
በት ቢሆንም የሳኦልን እርግማን በመፍራት
ከማሩ የቀመሰ ማንም አልነበረም ፤ 27 ዮናታን
ግን አባቱ ሕዝቡን በእርግማን ማስፈራራቱን
ሰሳልሰማ ፥ የያዘውን በትር በመዘርጋት ወለላ
ውን እየሳበ ጥቂት ማር በላ ፥ ወዲያውኑ ብር
ታት አግኝቶ ዐይኑ በራ ፤ 28 ነገር ግን ከወታደ
ሮቹ አንዱ “እኛ ሁላችን በረሀብ ደክመን ዝል
ናል ፤ አባትህ ግን ‘በዛሬው ዕለት ምንም ዐይ
ነት ምግብ የሚመገብ ሰው የተረገመ ይሁን’
ሲል በብርቱ አስጠንቅቆናል” አለው ። 29 ዮና
ታንም እንዲህ ሲል መለሰ ፥ “አባቴ በሕዝባችን
ላይ የፈጠረው ችግር ምን ያህል ከባድ ነው!
ትንሽ ማር አግኝቼ በመብላት ብርታት አግኝቼ
ዐይኔ እንደበራ ተመልከት! 30 ታዲያ ዛሬ ሕዝ
ባችን ጠላትን ድል መትቶ ከምርኮ የሚያገኘ
ውን ምግብ ቢመገብ ኖሮ እንዲት በተሻለው
ነበር ፤ የሚገድሉአቸው ፍልስጥኤማውያን
ቊጥር ምን ያህል ይበዛ እንደነበር አስቲ
ንምት!”

31 በዚያን ቀን እስራኤላውያን ከሚክማስ
እስከ አያሎን ባለው መንገድ ሁሉ እያሳደዱ
በመውጋት ፍልስጥኤማውያንን ድል መቱ ፤
በዚህም ጊዜ እስራኤላውያን ሰለተራቡ በመድ
ከም ዝለው ነበር ። 32 ስለዚህም ከጠላት ባገኙት
ምርኮ ላይ እየተረባረቡ በጎችንና የቀንድ ከብቶ
ችን ባገኙበት ቦታ እያረዱ ሥጋውን ከነደሙ
መብላት ጀመሩ ፤ 33 ሳኦልም “ተመልከት!
ሕዝቡ ደም ያለበትን ሥጋ በመብላታቸው በእ
ግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ሠርተዋል” የሚል
ወሬ ደረሰው ።

ሳኦልም “እናንተ ከዳተኞች! እንድ ትልቅ
ድንጋይ አንከባልላችሁ ወደዚህ አምጡልኝ”
ሲል ጮኽባቸው ። 34 ከዚህም በኋላ ሌላ ትእ
ዛዝ እንዲህ ሲል አስተላለፈ ፥ “ወደ ሕዝቡ
ሄዳችሁ ‘የቀንድ ከብቶቻችሁንና በጎቻችሁን
ሁሉ አምጡ ፤ አነርሱንም ዐርዳችሁ በዚህ
ስፍራ መመገብ አለባችሁ ፤ ደም ያለበትንም
እርጥብ ሥጋ በመብላት በእግዚአብሔር ፊት
ኃጢአት አትሥሩ’ ብላችሁ ንገሩአቸው ።” ስለ
ዚህም ሕዝቡ በዚያን ሌሊት የቀንድ ከብቶቻቸ
ውንና በጎቻቸውን ሁሉ አምጥተው በዚያ
ዐረዱ ፤ 35 ሳኦልም በዚያ ለእግዚአብሔር መሠ
ዊያ ሠራ ፤ ይህም እርሱ የሠራው መሠዊያ የመ
ጀመሪያው ነበር ።

36 ሳኦልም ወታደሮቹን “እንግዲህ እንውረ
ድና በፍልስጥኤማውያን ላይ በሌሊት አደጋ
እንጣልባቸው ፤ እስኪነጋም ድረስ ሀብታቸውን
ዘርፈን ሁሉንም እንፍጃቸው” አለ ።

እነርሱም “መልካም መስሎ የታየህን ሁሉ
አድርግ” እሉት ።

ካህኑ ግን “በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን
ፈቃድ እንጠይቅ” አለ ።

37 ሳኦልም “በፍልስጥኤማውያን ላይ እደጋ
እንጣልባቸውን? ድልንስ ለእኛ ትሰጣለህን?”
ሲል እግዚአብሔርን ጠየቀ ፤ ነገር ግን እግዚአ
ብሔር በዚያን ቀን ምንም መልስ አልሰጠም ።
38 ከዚህ በኋላ ሳኦል ለሕዝቡ መሪዎች እንዲህ
አለ ፥ “ወደዚህ ቀርባችሁ ዛሬ ምን ዐይነት
ኃጢአት እንደተሠራ መርምሩችሁ ዕወቁ ፤
39 በደል ሠርቶ የተገኘው ሰው ልጅ ፥ ዮናታን
እንኳ ቢሆን በሞት እንደሚቀጣ ለእስራኤል
ድልን ባሰጠው በሕያው እግዚአብሔር ስም
እምላለሁ ።” ነገር ግን አንዳች መልስ የሰጠው
ሰው አልተገኘም ። 40 ከዚያም በኋላ ሳኦል
“እናንተ ሁላችሁም በዚያ በኩል ቁሙ ፤ እኔና
ዮናታን ደግሞ በዚህ በኩል እንቆማለን” አላ
ቸው ።

እነርሱም “መልካም መስሎ የታየህን አድ
ርግ” አሉት ።

41 ሳኦልም የእስራኤል አምላክ ወደሆነው
ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ጸሰየ ፥ “እግዚ
አብሔር ሆይ! [ዛሬ ስለምን መልስ አልሰጠኸ
ኝም?] የእስራኤል አምላክ የሆንህ እግዚአብ
ሔር ሆይ! [በእነዚህ በተቀደሱ ድንጋዮች አማ
ካይነት መልስ ስጠኝ ፤ ይህን በደል የሠራነው
ዮናታን ወይም አኔ ከሆንን በኡራም አማካይ
ነት ፥ ይህን በደል የፈጸሙ ሕዝብህ እስራኤል
ከሆኑ በቱሚም አማካይነት መልስ ስጠኝ ።”]
መልሱም ዮናታንንና ሳኦልን ስላመለከተ ሕዝቡ
ነፃ ሆኑ ፤ 42 ከዚህም በኋላ ሳኦል “በልጄ በዮና
ታንና በእኔ መካከል ውሰኔ ስጥ” ሲል ጠየቀ ፤
መልሱም ወደ ዮናታን አመለከተ ፤ 43 ከዚህም

14፥33 ፦ ዘፍ. 9፥4 ፤ ዘሌ. 7፥26-27 ፤ 17፥10-14 ፤ 19፥26 ፤ ዘጸ. 12፥16 ፣23 ፤ 15፥23 ። 14፥41 ፦ ዘኍ. 27፥21 ፤ 1ሳሙ. 28፥6 ።

በኋላ ሳኦል ዮናታንን "ያደረግኸው ነገር ምን ድን ነው?" ሲል ጠየቀ ።

ዮናታንም "ጥቂት ማር በልቻስሁ ፥ እነሆ በዚህ አገኛስሁ ፥ ስመሞትም ዝግጁ ነኝ" አለ ።

44 ሳኦልም "እግዚአብሔር ያጥፋኝ ፥ አንተ ከሞት ቅጣት አታመልጥም" አለው ።

45 ሕዝቡ ግን ሳኦልን "ይሆን ታላቅ ድል ስእስራኤል ያስገኘ ዮናታን ይሞታልን? ከቶ አይደረግም ፥ መሞቱ ይቅርና ከራስ ጠጕሩ አን ዲቱ እንደማትወድቅ በሕያው እግዚአብሔር ስም እንምላስን ፥ ዛሬ እርሱ ያደረገው ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ረዳትነት የተፈጸመ ነው" አሉ ፥ በዚህም ሀይነት ሕዝቡ ዮናታንን ከሞት ቅጣት አዳኑት ።

46 ከዚያም በኋላ ሳኦል ፍልስጥኤማውያንን ከማሳደድ ተገታ ፥ እነርሱም ተመልሰው ወደ አገራቸው ሄዱ ።

የሳኦል ዘመነ መንግሥትና የቤተሰቡ ሁኔታ

47 ሳኦል በእስራኤል ከነገሠ በኋላ ፥ በሁሉም ስፍራ የሚገኙ ጠላቶቹን ወጋ ፥ እነርሱም የሞ አብ ፥ የዐሞንና የኤዶም ሕዝቦች ፥ የጾባ ነገሥ ታትና ፍልስጥኤማውያን ናቸው ፥ በተዋጋበት ስፍራ ሁሉ ድል አድራጊ ሆነ ፥ 48 በጀግንነ ትም ተዋግቶ የዐማሌቅን ሕዝብ እንኳ ሳይቀር ድል መታ ፥ እርሱም እስራኤላውያንን በመታ ደግ ከሚጣልባቸው አደጋ ሁሉ አዳነ ።

49 የሳኦልም ወንዶች ልጆች ዮናታን ፥ ይሽ ዊና ማልኪሹዓ ተብለው ይጠሩ ነበር ፥ ታላቋ ሌት ልጁም ሜራብ ስትሆን ፥ ታናሽዋ ሚካል ትባል ነበር ፥ 50 ሚስቱም አሒኖዓም ተብላ የምትጠራ የአሒማኣጽ ልጅ ነበረች ፥ የሠራዊ ቱም አዛዥ አበኔር ተብሎ የሚጠራው የአጐቱ የኔር ልጅ ነበር ። 51 ስለዚህም የሳኦል አባት ቂስና የአበኔር አባት ኔር የአቢኤል ልጆች ነበሩ ።

52 ሳኦል በነበረበት ዘመን ሁሉ ከፍልስጥኤ ማውያን ጋር በብርቱ ጠላትነት ሲዋጋ ኖረ ፥ ስለዚህም ብርቱ ወይም ጀግና የሆነ ሰው ሲያ ገኝ እየመለመለ በጦር ሠራዊቱ ውስጥ ያስመዘ ግበው ነበር ።

ምዕራፍ 15

ሳኦል በዐማሌቃውያን ላይ ያደረገው ጦርነት

1 ሳሙኤል ሳኦልን እንዲህ አለው ፥ "በሕ ዝቡ በእስራኤል ላይ ቀብቼ እንዳነግሥህ እግዚ አብሔር የላከኝ እኔ ነኝ ፥ አውንም ሁሉን የሚ ችል እግዚአብሔር የሚለውን ስማ ፥ 2 እግዚአብ ሔር ዐማሌቃውያንን ስመቅጣት ወስናል ፥ እስራኤላውያን ከግብጽ በወጡበት ጊዜ የእን ዚሁ የዐማሌቃውያን የቀድሞ አባቶቻቸው ተቃ ውመዋቸው ነበር ፥ 3 ሄደህ በዐማሌቃውያን ላይ አደጋ በመጣል ያላቸውን ሁሉ ደምስስ ፥ ከእነ ርሱ ምንም ነገር አታስቀር ፥ ወንዶችን ፥ ሴቶ ችን ፥ ልጆችንና ሕፃናትን ፥ ከብቶችን ፥ በጎ ችን ፥ ግመሎችንና አህዮችን ሁሉ ግደል ።"

4 ሳኦልም ሠራዊቱን በአንድነት ጠርቶ ጤሌም በሚባል ስፍራ ቈጠራቸው ፥ የወታደሮ ቹም ብዛት ከእስራኤል ሁለት መቶ ሺ ፥ ከይ ሁዳ ዐሥር ሺ ሆነው ተገኙ ፥ 5 ከዚያም እር ሱና ሠራዊቱ ወደ ዐማሌቃውያን ከተማ ሄደው በአንድ ደረቅ ጅረት ውስጥ ደፈጣ አደረጉ ፥ 6 እስራኤላውያን ከግብጽ በወጡ ጊዜ የቀድሞ አባቶቻቸው ቸርነት ወደ አደረጉላቸው ቄናው ያን ተብሎ ወደሚጠሩት ሕዝብ "ከእነርሱ ጋር አንዳሳጠፋችሁ ከዐማሌቃውያን ተለይታችሁ ወደ ሌላ ስፍራ ሂዱ" ሲል የማስጠንቀቂያ መልእክት ላከ ፥ እነርሱም ከዚያ ሰቀው ሄዱ ።

7 ሳኦል ከሐዊላ ጀምሮ በግብጽ ምሥራቅ እስከምትገኘው እስከ ሹር በሚያደርሰው መን ገድ ሁሉ በመውጋት ዐማሌቃውያንን ድል አደ ረገ ። 8 የዐማሌቅ ንጉሥ የነበረውን አጋግን በሕ ይወት ማርከ ፥ ሕዝቡን ሁሉ ፈጀ ፥ 9 ነገር ግን ሳኦልና ሠራዊቱ የአጋግን ሕይወት አተረፉ ፥ እንዲሁም ምርጥ ምርጥ የሆኑትን በጎችና የቀ ንድ ከብቶች ፥ የሰቡ ሰንጋዎችንና ጥቦቶችን ከዚህም ጋር መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ አላ ጠፉም ፥ እነርሱም ያጠፉት የማይረባውንና የማ ይጠቅመውን ነገር ብቻ ነበር ።

ሳኦል በንጉሥነት መቀጠል እንደማይችል ተነገረ

10 እግዚአብሔር ሳሙኤልን እንዲህ አለው ፥ 11 "ሳኦልን በማንገሤ ተጸጸትሁ ፥ ምክንያቱም እርሱ እኔን ትቶአል ፥ ትእዛዜንም አልጠበ ቀም ፥" ሳሙኤልም በዚህ ነገር ተቈጥቶ ሌሊ ቱን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር በመጮኽ ማሰደ ፥ 12 በማግሥቱም ማለዳ በመነሣት ሳኦልን ፊልጎ ስማግኘት ሄደ ፥ ሳኦል ስራሱ ሐውልት ወዳቆ መባት ወደ ቀርሜሎስ ከተማ ከደረሰ በኋላ ተመልሶ ወደ ጌልገላ መሄዱን ሰማ ፥ 13 ሳሙ ኤል ወደ ሳኦል ሄደ ፥ ሳኦልም አቀባበል ሲያደ ርግለት "ሳሙኤል ሆይ! እግዚአብሔር ይባር ክህ! እኔም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ፈጽሜአ ለሁ" አለው ።

14 ሳሙኤልም "ታዲያ ይኼ የምሰማው የቀ ንድ ከብትና የበግ መንጋ ድምፅ ምንድን ነው?" ሲል ጠየቀው ።

15 ሳኦልም "እነርሱ መታደሮቼ ከዐማሌቃው ያን የማረኩአቸው ናቸው ፥ ምርጥ ምርጥ የሆኑ ትን የቀንድ ከብቶችና በጎች ለአምላክህ ለእግዚ አብሔር መሥዋዕት ሰማቅረብ እምጥተዋል ፥

15:1 ፡- 1ሳሙ. 10:1 ። 15:2 ፡- ዘጸ. 17:8-14 ፤ ዘዳ. 25:17-19 ።

የቀሩትን ግን በሙሉ ደምስሰዋል” ሲል መለሰለት።

16 ሳሙኤልም “ተወው በቃ! እግዚአብሔር ትናንትና ማታ የነገረጠልኝን እነግርሃለሁ” አለው።

ሳኦልም “እሺ ንገረኝ” አለ።

17 ሳሙኤልም እንዲህ ሲል መለሰ፥ “አንተ ስለራስህ የነበረህ ግምት አነስተኛ ቢሆንም የእስራኤል ነገዶች መሪ ሆነሃል፤ እግዚአብሔርም በእስራኤል ላይ ቀብቶ እንግሥሃል፤ 18 ከዚህም በኋላ ኃጢአተኞች የሆኑትን እነዚያን የዐማሌቅ ሕዝብ እንድትደመስስ ልኮሃል፤ እስኪጠፉም ድረስ እነርሱን ግደል ብሎ ነግሮሃል። 19 ታዲያ ስለምን ትእዛዙን አልፈጸምክም? ለምርኮስ በመሳሳትና በመስገብገብ እግዚአብሔርን ደስ የማያሰኝ ነገር ስለምን እደረግህ?”

20 ሳኦልም እንዲህ ሲል መለሰ፥ “እኔ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ፈጽሜአለሁ፤ ባዘዘኝም መሠረት ዘምቻለሁ፤ ንጉሥ አጋግን ብቻ ማርኬ ሳመጣ ሌሎችን ዐማሌቃውያን ሁሉ ገድያለሁ፤ 21 ነገር ግን ወታደሮቼ የማረኩአቸው ውን ምርጥ ምርጥ የሆኑ በጎችንና የቀንድ ከብቶችን አልገደሉአቸውም፤ ይህን በማድረግ ፈንታ በጌልገላ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እድርገው ለማቅረብ አምጥተዋቸ ዋል።”

22 ሳሙኤልም እንዲህ አለ፥ “እግዚአብሔር የሚወደው የቱን ይመስልሃል? መታዘዝን ወይስ ቍርባንና መሥዋዕት ማቅረብን? ለእርሱ መታ ዘዝ ምርጥ የበግ መሥዋዕት ከማቅረብ ይበል ጣል፤ 23 በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ እንደሚር ተኛነት፥ የትዕቢት አልኸኛነትም ጣዖትን በማ ምለክ ኃጢአት እንደመሥራት ይቈጠራል፤ አንተ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለተውህ በንጉ ሥነትህ እንዳትቀጥል እርሱም አንተን ትቶ ሃል።”

24 ሳኦልም እንዲህ ሲል መለሰ፥ “እም! እኔ ኃጢአት ሠርቼአለሁ፤ የእግዚአብሔርን ትእዛ ዝና አንተ የሰጠኸኝን መመሪያ አልጠበቅሁም፤ ወታደሮቹን በመፍራት እነርሱ የፈለጉትን ሁሉ እደረግሁ፤ 25 አሁን ግን እለምንሃለሁ በደሌን ይቅር በለኝ፤ ከእኔም ጋር ወደ ጌልገላ ሂድ፤ እኔም በዚያ ለእግዚአብሔር እሰግዳለሁ።”

26 ሳሙኤልም “እኔ ከአንተ ጋር አልሄ ድም፤ አንተ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም ትተሃል፤ አንተም የእስራኤል ንጉሥ ሆነህ እን ዳትቀጥል እርሱ ትቶሃል” ሲል መለሰለት።

27 ከዚያም በኋላ ሳሙኤል ተለይቶ ለመሄድ ፊቱን መለሰ፤ ሳኦል ግን ሳሙኤል እንዳይሄድ በት የካባውን ጠርዝ ሲይዝ ተቀደደ፤ 28 ሳሙ ኤልም ሳኦልን እንዲህ አለው፥ “ዛሬ እግዚአብ ሔር የእስራኤልን መንግሥት ቀዶ ከእጅህ በመ ውሰድ ከአንተ ለተሻለ ለሌላ ሰው ሰጥቶታል፤ 29 የእስራኤል የክብር ግርማ የሆነ እግዚአብ ሔር እይዋሽም፤ አሳቡንም አይለውጥም፤ እርሱ እንደ ሰው ስላልሆነ አሳቡን አይለው ጥም።”

30 ሳኦልም “በእርግጥ በደል ሠርቼአለሁ፤ ይሁን እንጂ ሌላው ቢቀር በሕዝቤ መሪዎችና በእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ፊት አክብረኝ፤ ለአም ላክህ ለእግዚአብሔር እሰግድ ዘንድ ከእኔ ጋር አብረህ ሂድ” ሲል ለመነው። 31 ስለዚህም ሳሙኤል አብሮት ወደ ጌልገላ ሄደ፤ ሳኦልም ለእግዚአብሔር ሰገደ።

32 ሳሙኤልም “ንጉሥ አጋግን ወደዚህ አም ጣልኝ!” ሲል ትእዛዝ ሰጠ፤ አጋግም በፍርሃት እየተንቀጠቀጠ ወደ እርሱ መጣ፤ በልቡም “ሞት እንዴት መራራ ናት” እያለ ያስብ ነበር፤ 33 በዚህም ጊዜ ሳሙኤል “የአንተ ሰይፍ ብዙዎች እናቶችን ልጅ አልባ እንዳደረገ ቻቸው፤ የእንተም እናት ልጅ አልባ ሆና ትቀ ራለች” አለው። ከዚህም በኋላ በጌልገላ በሚገ ኘው በእግዚአብሔር መሠዊያ ፊት አጋግን ቈራርጦ ጣለው።

34 ከዚህም በኋላ ሳሙኤል ወደ ራማ ሄደ፤ ንጉሥ ሳኦልም ወደ ጊብዓ ተመለሰ። 35 ከዚያን ሰዓት ጀምሮ ሳሙኤል በነበረበት ጌዜ ሁሉ ንጉሥ ሳኦልን በዐይኑ አላየውም፤ ነገር ግን ለእርሱ በማዘን ያለቅስለት ነበር፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሳኦልን በእስራኤል ላይ በማን ገሡ ተጸጽቶ ነበር።

ምዕራፍ 16

ዳዊት ለንጉሥነት ተቀባ

1 እግዚአብሔር ሳሙኤልን እንዲህ አለው፥ “ለሳኦል በማዘን የምታሰቅስበት እስከ መቼ ነው? በእስራኤል ላይ ንጉሥ ሆኖ ይኖር ዘንድ እኔ እርሱን አልፈልገውም፤ አሁን ግን የወይራ ዘይት በቀንድ ሞልተህ በመያዝ በቤተልሔም ወደሚኖረው እሴይ ተብሎ ወደሚጠራው ሰው ዘንድ ሂድ፤ ምክንያቱም እኔ ከእርሱ ልጆች መካከል አንዱን ንጉሥ እንዲሆን መርጫ ለው።”

2 ሳሙኤልም “ይህን ለማድረግ እንዴት ይቻ ለኛል? ምክንያቱም ሳኦል ይህን ቢሰማ ይገድለ ኛል” ሲል ጠየቀ።

እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል መለሰለት፥ “‘ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ለማቅረብ መጥቻ ለሁ’ ብለህ ጊደር ይዘህ ሂድ፤ 3 እሴይንም ወደ መሥዋዕቱ እንዲመጣ ጥራው፤ እኔም የምታደ ርገውን ነገር እነግርሃለሁ፤ እኔ የምነግርህንም ሰው ቀብተህ ታነግሣለህ።”

15:27-28 ፦ 1ሳሙ. 28:17፤ 1ነገ. 11:30-31።

4 ሳሙኤልም እግዚአብሔር ያዘዘውን ለማድ
ረግ ወደ ቤተልሔም ሄደ ፤ አዚያም እንደደረሰ
የከተማይቱ መሪዎች በፍርሃት እየተንቀጠቀጡ
ወደ ሳሙኤል ቀርበው “ባለ ራእይ ሆይ! አመ
ጣጥህ ለሰላም ነውን?” ሲሉ ጠየቁት ።
5 እርሱም “እም ! ለሰላም ነው ፤ ለእግዚአብ
ሔር መሥዋዕት እቀርብ ዘንድ መጥቻለሁ ፤
ሁለንተናችሁን በማንጻት ወደ እኔ ኑ” ሲል
መለሰላቸው ። እሴይና ልጆቹም በሕጉ መሠረት
ሁለንተናቸውን አንጺያኑ በመንገር ወደ መሥ
ዋዕቱ እንዲመጡ ጠራቸው ።
6 እዚያም በደረሱ ጊዜ ሳሙኤል ኤሊአብ
ተብሎ የሚጠራውን የእሴይን ልጅ እይቶ “በእ
ግዚአብሔር ፊት የቆመው ይህ ሰው በእርግጥ
ለንጉሥነት የተመረጠ ነው” ሲል አሰበ ። 7 እግ
ዚአብሔር ግን “የኤሊአብን ቁመት መርዘምና
መልከ ቀናነቱን እትይ ፤ እኔ እርሱን አልፈሰግ
ሁትም ፤ ምክንያቱም እኔ የምፈርደው ሰዎች
እንደሚፈርዱት አይደለም ፤ ሰው ውጫዊ መል
ክን ያያል ፥ እኔ ግን ውስጣዊ ልብን እያሰሁ”
አለው ።
8 ከዚህ በኋላ እሴይ እሚናዳብ ተብሎ የሚ
ጠራውን ልጁን ወደ ሳሙኤል አመጣለት ፤
ሳሙኤል ግን “እግዚአብሔር ይህኛውንም አል
መረጠውም” አለ ። 9 ቀጥሎም እሴይ ሻማ
ተብሎ የሚጠራውን ልጁን አመጣ ፤ ሳሙኤል
ግን “እግዚአብሔር ይህኛውንም አልመረጠም”
አለ ። 10 በዚህም ወይነት ሁኔታ እሴይ ሰባቱንም
ልጆቹን አቅርቦ በሳሙኤል ፊት አሰለፋቸው ፤
ሳሙኤልም እሴይን “አነሆ ! ከእነዚህ መካከል
እግዚአብሔር አንዱንም አልመረጠውም ”
ካለው በኋላ ፥ 11 “ታዲያ ሌሎች ልጆች የሉህ
ምን?” ሲል ጠየቀው
እሴይም “የሁሉ ታናሽ የሆነ አንድ ልጅ
አለ ፤ እርሱ ግን ወደ በግ አረኝነት ሄዶአል”
ሲል መለሰለት ።
ሳሙኤልም “እርሱን እስጠርተህ እምጣው ፤
እርሱ ሳይመጣ መሥዋዕት እናቀርብም ”
አለው ። 12 ስለዚህም እሴይ ልኮ እስጠራው ፤
እርሱ ቀይ ፥ መልከ መልካምና ወይኖቹ የሚያ
በሩ ጤናማ ወጣት ነበር ፤ እግዚአብሔርም
ሳሙኤልን “የመረጥሁት ሰው ይህ ነውና እር
ሱን ቀባው” አለው ። 13 ሳሙኤልም በወይራ
ዘይት የተሞላውን ቀንድ ወሰዶ ዳዊትን በወንድ
ሞቹ ፊት ቀባው ፤ ወዲያውኑ የእግዚአብሔር
መንፈስ በዳዊት እደረበት ፤ ከዚያም ቀን ጀምሮ
ከእርሱ አልተለየም ፤ ከዚህም በኋላ ሳሙኤል
ወደ ራማ ተመለሰ ።

ዳዊት በሳኦል ቤተ መንግሥት

14 የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል ሰለተለየ
ከእግዚአብሔር የተላከ ክፉ መንፈስ ያሠቃየው
ነበር ፤ 15 አገልጋዮቹም እንዲህ አሉት ፥ “ከእግ
ዚአብሔር የተላከ ክፉ መንፈስ እንደሚያሠቃ
ይህ እናውቃለን ፤ 16 ስለዚህ ንጉሥ ሆይ ! በገና
መደርደር የሚያውቅ ሰው ፈልገን እንድናመጣ
ልህ እዘዘን ፤ ከዚያም በኋላ ክፉ መንፈስ በሚ
መጣብህ ጊዜ ያ ሰው በገና ይደረድርልሃል ፤
እንተም እንደገና ጤናማ ትሆናለህ ።”
17 ሳኦልም “በገና ለመደርደር የታወቀ ሰው
ፈልጋችሁ እምጡልኝ” አላቸው ።
18 ከቅርብ አገልጋዮቹም እንዱ “የቤተል
ሔም ከተማ ነዋሪ የሆነው እሴይ በገና መደር
ደር የሚችል ልጅ አለው ፤ ይህም ብቻ ሳይሆን
ጀግና ፥ መልከ ቀና ፥ ብርቱ ወታደርና ንግግር
ወዋቂ ነው ፤ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር
ነው” አለው ።
19 ስለዚህም ሳኦል ወደ እሴይ መልእክተ
ኞች ልኮ “የበጎች እረኛ የሆነውን ልጅህን ዳዊ
ትን ላከልኝ” አለው ። 20 እሴይም ዳዊትን
አንድ ትንሽ የበግ ጥቦት አሰይዞ ፥ እንጀራና
የወይን ጠጅ የተሞላበት አቁማዳ ከተጫነ
እንድ አህያ ጋር ወደ ሳኦል ላከው ። 21 ዳዊትም
ወደ ሳኦል መጥቶ ሥራውን ጀመረ ፤ ሳኦልም
በጣም ስለወደደው የእርሱ መሣሪያ ያዥ ጋሻጃ
ግሬ እደረገው ። 22 ከዚያም በኋላ ሳኦል ወደ
እሴይ መልእክት ልኮ “ዳዊትን ወድጀዋለሁ ፤
ስለዚህ እዚህ በመቆየት ያገልግለኝ” አለው ።
23 ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ከእግዚአብሔር የተላከ
ክፉ መንፈስ በሳኦል ላይ በሚመጣበት ጊዜ
ሁሉ ዳዊት በገናውን አንሥቶ ይደረድራል ፤
ከፉውም መንፈስ ለቅቆት ስለሚሄድ ሳኦል እየ
ተሻለው እንደገና ጤናማ ይሆናል ።

ምዕራፍ 17

ጎልያድ እስራኤላውያንን ተፈታተነ

1 ፍልስጥኤማውያን ሶኮ ተብላ በምትጠራው
በይሁዳ ለመርነት ተሰለፉ ፤ እነርሱም በሶኮና
ለዐዜቃ መካከል ኤፌስዳሚም ተብሎ በሚጠ
ራው ቦታ ሰፍረው ነበር ። 2 ሳኦልና እስራኤላው
ያንም ፍልስጥኤማውያንን ለመውጋት በተዘጋጁ
በት በኤላ ሸለቆ ተሰብሰበው መሸጉ ። 3 በመካከ
ላቸው አንድ ሸለቆ ሲኖር በአንድ በኩል ባለው
ኮረብታ ፍልስጥኤማውያን ፥ በሌላ በኩል ባለው
ኮረብታ እስራኤላውያን ተሰልፈው ነበር ።
4 ኪጋት ከተማ የመጣ ፥ ጎልያድ ተብሎ የሚ
ጠራ አንድ ሰው ፥ ከፍልስጥኤማውያን ሰፈር
ወጥቶ እስራኤላውያንን መፈታተን ጀመረ ፤ የዚ
ያም ሰው ቁመት ሦስት ሜትር ያህል ነበር ፤
5 ከነሐስ የተሠራና ከብደቱ ኀምሳ ሰባት ኪሎ
የሚሆን የጦር ልብስና ከነሐስ የተሠራ የራስ
ቍር ነበረው ። 6 እግሮቹም ከነሐስ በተሠራ ገን
ባሌ የተሸፈኑ ነበሩ ፤ ከነሐስ የተሠራ ጦርም
በትከሻው ነበር ፤ 7 የጦሩ ዘንግ ውፍረቱ የሸማኔ
መጠቅለያ ያህል ነበር ፤ የጦሩም ብረት ከብደቱ

ለባት ኪሎ ያህል ነበር ፤ ጋሻውንም እንድ ወታ
ደር ተሸክሞለት በፊት በፊቱ ይሄድ ነበር ።
8 ጎልያድ ተነሥቶ በመቆም በእስራኤላውያን
ሠራዊት ላይ እንዲህ እያለ ይደነፋባቸው
ነበር ፥ “አሁን በዚያ ቦታ ለጦርነት የተሰለፋች
ሁት ከቶ ምን ልታደርጉ ነው? አኔ ፍልስጥኤ
ማዊ ነኝ! እናንተ ደግሞ የሳኦል ባሪያዎች
ናችሁ! እንግዲህ ከእኔ ጋር የሚዋጋ እንድ ሰው
ከወታደሮቻችሁ መካከል ምረጡ ፤ 9 እርሱ
እኔን አሸንፎ ከገደለኝ ፥ እኛ የእናንተ ባሪያ
ዎች እንሆናለን ፤ ነገር ግን አኔ አሸንፌ ከገደል
ሁት ፥ እናንተ የእኛ ባሮች ትሆናላችሁ ።
10 እንሆ እኔ በዚህ የእስራኤልን ሠራዊት እፈታ
ተናለሁ! ከእኔ ጋር የሚዋጋ እንድ ሰው እንድ
ትመርጡ ብድፍረት እጠይቃችኋለሁ!” 11 ሳኦ
ልና ወታደሮቹም ይህን በሰሙ ጊዜ በፍርሃት
ተንቀጠቀጡ ።

ዳዊት በሳኦል ጦር ሰፈር

12 ዳዊት በይሁዳ ቤምትገኘው በቤተልሔም
የሚኖር የኤፍራታዊው የእሴይ ልጅ ነበር ፤
እሴይ ስምንት ልጆች ያሉት ሲሆን ሳኦል በነገ
ሠበት ዘመን በዕድሜ የገፋ ሽማግሌ ሰው
ነበር ። 13 ሦስቱ ታላላት ልጆቹም ከሳኦል ጋር
ወደ ጦርነት ዘምተው ነበር ፤ እነርሱም በኵሩ
ኤሊአብ ፥ ሁለተኛው እሚናዳብ ፥ ሦስተኛ
ውም ሻማ ተብለው ይጠሩ ነበር ። 14 ዳዊት
የሁሉ ታናሽ ልጅ ሲሆን ፥ ሦስት ታላላት ወን
ድሞቹ ከሳኦል ጋር በጦር ሜዳ በነበሩበት
ጊዜ ፥ 15 ዳዊት በየጊዜው ከሳኦል በመለየት በጎ
ቹን ለመጠበቅ ወደ ቤተልሔም ይሄድ ነበር ።
16 ጎልያድም እስራኤላውያንን አርባ ቀን
ሙሉ ጠዋትና ማታ ተፈታተናቸው ።
17 እንድ ቀን አሴይ ዳዊትን እንዲህ አለው ፥
“ዐሥር ኪሎ የተጠበሰ እሸትና ዐሥር የዳቦ
ሙልሙል ያዝ ፤ ፈጥነህም በመሄድ በጦር
ሰፈር ለሚገኙት ወንድሞችህ አድርስላቸው ።
18 እነዚህንም ዐሥር የአይብ ጥፍጥፎች ለጦሩ
አዛዥ ስጠው ፤ ወንድሞችህም እንዴት እንዳሉ
በዐይንህ አይተህ የደኅንነታቸውን መረጃ አምጣ
ልኝ ። 19 ምክንያቱም ንጉሥ ሳኦል ፥ ወንድሞ
ችህና መላው እስራኤላውያን በኤላ ሸለቆ ከፍ
ልስጥኤማውያን ጋር በመዋጋት ላይ ናቸው ።”
20 ዳዊትም በማግሥቱ ማልዶ ተነሣ ፤ በጎ
ቹን ለሌላ አረኛ ዐደራ በመስጠት አሴይ ባዘ
ዘው መሠረት የተብጃጀውን ምግብ ይዞ ሄደ ፤
እስራኤላውያን ጦርነት ለመግጠም ድምፃቸውን
ከፍ አድርገው በሚደነፋበት ጊዜ ዳዊት ወደ
ጦሩ ሰፈር ደረሰ ። 21 የፍልስጥኤማውያን ሠራዊ
ትና የእስራኤላውያን ሠራዊት ቦታ ቦታቸውን
ይዘው ሰጦሩ ግንባር ፊት ለፊት በመተያየት
ላይ ነበሩ ። 22 ዳዊትም የያዘውን ምግብ ለስንቅ
ጠባቂው ትቶ ወደ ጦሩ ግንባር እየሮጠ ወደ
ወንድሞቹ ሄደ ፤ ስለደኅንነታቸውም ጠየቃ
ቸው ። 23 ዳዊትም ከወንድሞቹ ጋር ሰመነጋገር
ላይ ሳለ ጎልያድ ከዚያ በፊት ያደርገው እንደነ
በር ወደፊት በማምራት እስራኤላውያንን መፈ
ታተኑን ቀጠለ ፤ ዳዊትም የእርሱን ድንፋታ
ሰማ ። 24 እስራኤላውያንም ጎልያድን ባዩ ጊዜ
በመሸበር ሸሹ ። 25 እርስበርሳቸውም እንዲህ
ይባባሉ ነበር ፥ “ተመልከቱት! በመፈታተን
የሚናገረውንም ቃል እደምጡ ፤ ንጉሥ ሳኦል
እርሱን ስሚገድልለት ሰው ብዙ ሀብት ለመሰ
ጠት ቃል ገብቶአል ፤ ሴት ልጁንም እንደሚድ
ርለትና የአባቱም ቤተሰብ ከግብር ነፃ እንደሚ
ያደርግለት ተናግሮአል ።”
26 ዳዊትም በአጠገቡ ያሉትን ሰዎች “ይህን
ፍልስጥኤማዊ ገድሎ እስራኤልን ከዚህ አሳፋሪ
ውርደት ለሚያድን ሰው ምን ይደረግለታል?
ኧረ ለመሆኑ የሕያው እግዚአብሔርን ሠራዊት
የሚፈታተን ይህ አረመኔ ፍልስጥኤማዊ ማን
ነው?” ሲል ጠየቀ ። 27 እነርሱም ጎልያድን
ለሚገድል ሰው ምን እንደሚደረግለት ነገሩት ።
28 የዳዊት ታላቅ ወንድም ኤሊአብም ዳዊት
ከሰዎቹ ጋር ሲነጋገር ሰማ ፤ እርሱም በዳዊት
ላይ ተቈጥቶ “እዚህ ምን ትሠራለህ? በዘረሓ
ያሉትንስ እነዚያን ጥቂቶች በጎችህን ለማን
ተውካቸው? እኔ ትዕቢተኛነትህንና የልብህን
ክፋት ዐውቃለሁ! አሁን የመጣኸው እኮ የጦር
ነቱን ሁኔታ ለመመልከት ነው” አለው ።
29 ዳዊትም “እሁን እኔ ምን አደረግሁ?
ለመጠየቅ እንኳ አልችልምን?” ሲል መለሰ
ለት ፤ 30 ከዚያም ወደ ሌላው ሰው መለሰ ብሎ
ያንኑ ጥያቄ አቀረበለት ፤ በጠየቀ ቍጥር የሚያ
ገኘው መልስ ተመሳሳይ ነበር ።
31 እንዳንድ ሰዎች ዳዊት የተናገረውን ቃል
ለምተው ስለነበር ፥ ሄደው ለሳኦል ነገሩት ፤ ሳኦ
ልም ልኮ ዳዊትን አስጠራው ። 32 ዳዊትም ሳኦ
ልን “ንጉሥ ሆይ! ከዚህ ፍልስጥኤማዊ የተነሣ
ማንም ሰው መፍራት የለበትም ፤ እኔ ሄጀ እር
ሱን እዋጋዋለሁ” አለው ።
33 ሳኦልም “ይህ ሊሆን አይችልም ፤ እንተ
እርሱን እንዴት መዋጋት ትችላለህ? እንተ እኮ
ትንሽ ልጅ ነህ ፤ እርሱ ግን ዕድሜውን ሙሉ
ልምምድ ያደረገ የጦር ሰው ነው” አለው ።
34 ዳዊትም እንዲህ አለ ፥ “ንጉሥ ሆይ! እኔ
የአባቴን በጎች የምጠብቅ እረኛ ነኝ ፤ አንበሳም
ሆነ ድብ መጥቶ ጥቦት በሚነጥቅበት ጊዜ ፥
35 ተከትየው ሄጀ አደጋ በመጣል የወሰደውን
ጥቦት አስጥለዋለሁ ፤ አንበሳው ወይም ድቡ
ወደ እኔ ተመልሶ በሚመጣበትም ጊዜ ጉሮሮ
ውን አንቄ በመምታት እገድለዋለሁ ። 36 ስለዚ
ዐይነት እኔ እንበሳና ድብ ገድያለሁ ፤ ይህንንም
ድርጊት የሕያው እግዚአብሔር ሠራዊት በሚገ
ዳደር በዚህ አረመኔ ፍልስጥኤማዊ ላይ እንደ
ገና እደግመዋለሁ ። 37 ከአንበሳና ድብ ያዳነኝ

እግዚአብሔር ከዚህም ፍልስጥኤማዊ እጅ ያድ
ንኛል ።”

ሳኦልም “መልካም ነው! እንግዲህ ሂድ ፣
እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር ይሁን” ሲል መሰ
ሰበት ። 38 ሳኦልም የገዛ ራሱን የጦር ልብሰ ስዳ
ዊት አለበሰው ፣ ከነሐስ የተሠራውን የራስ ቍር
በዳዊት ራስ ላይ ደፍቶ ጥሩርም አሰዘሰው ፣
39 ዳዊትም የሳኦልን ሰይፍ በጦር ልብሱ ታጥቆ
ለመሄድ ሲነሣ መራመድ አልቻለም ፣ ምክንያ
ቱም ይህን ዐይነት ልብስ ሰብሶ አያውቅም
ነበር ፣ ሰሰዚህ ዳዊት “ይህን ሁሉ ልብስ ሰብሼ
መዋጋት አልችልም ፣ ምክንያቱም ያልተሰማመ
ድሁት ነገር ነው” አለ ፣ ሰሰዚህም ያንን ሁሉ
አወለቀ ፣ 40 በትሩን አንሥቶ ፣ ከውሃ ምንጭ
አምሰት ዱቡልቡል ድንጋዮች መርጦ በመል
ቀም በእረኝነት ነረጀው ከተተ ፣ ወንጭፉንም
ይዞ መደ ጎልያድ ሄደ ።

ዳዊት ጎልያድን ድል አደረገ

41 ፍልስጥኤማዊው ጎልያድ ወደ ዳዊት ሰመ
ቅረብ መራመድ ጀመረ ፣ ጋሻጃግሬውም በፊት
በፊቱ ይሄድ ነበር ፣ ጎልያድም እየቀረበ
መጥቶ ፣ 42 ዳዊትን ትኵር ብሎ ባየው ጊዜ በን
ቀት ዐይን ተመሰከተው ፣ ምክንያቱም ዳዊት
ቀይ ፣ መልከ መልካም ፣ ትንሽ ልጅ ነበር ።
43 ሰሰዚህም ጎልያድ ዳዊትን “ይህን በትር የያ
ዝከው ምን ልታደርግበት ነው? እኔ ውሻ መሰ
ልከህ እንዴ!” ካለው በኋላ በአማልክቱ ሰም
የእርግማን መዓት አወረደበት ። 44 ቀጥሎም
“ወዲህ ና! ሥጋህን ሰስማይ እሞራዎችና ለም
ድር አራዊት እሰጣሰሁ” ሲል ተገዳደረው ።
45 ዳዊትም እንዲህ ሲል መሰሰ ፦ “አንተ
ሰይፍ ፣ ጦርና ጭሬ ይዘህ መጥተህብኛል ፣ እኔ
ደግሞ አንተ በምትገዳደረውና የእስራኤል ሠራ
ዊት አምላክ በሆነው ሁሉን በሚችል በእግዚአ
ብሔር ሰም እመጣብሃለሁ ፣ 46 በዚህች ቀን እግ
ዚአብሔር አንተን በእጄ ይጥልልኛል ፣ እኔም
እሸንፈህ ራስህን አቁርጣለሁ ፣ የፍልስጥኤማው
ያንንም ወታደሮች ሥጋ ለአሞራዎችና ለአራ
ዊት ምግብ እድርጌ አሰጣለሁ ፣ ከዚያም በኋላ
መላው ዓለም የእስራኤል አምላክ መኖሩን ያው
ቃል ፣ 47 በዚህም የሚገኝ ማንኛውም ሰው እግ
ዚአብሔር ሕዝቡን ሰማዳን ሰይፍ ወይም ጦር
እንደማያስፈልገው ማሰተዋል ይችላል ፣ እግዚአ
ብሔር በጦርነት ድል አድራጊ ነው ፣ እናንተ
ንም ሁሉ በእኛ ሥልጣን ሥር ያደርጋል ።”
48 ጎልያድም እርምጃውን በመቀጠል አንደ
ገና ወደ ዳዊት ቀረበ ፣ ዳዊትም ከፍልስጥኤማዊ
ጎልያድ ጋር ወደሚዋጋበት ጦር ግንባር ፈጥኖ
ሄደ ፣ 49 እጁንም ወደ ኮረጆው ከቶ አንዲት
ድንጋይ በማውጣት በጎልያድ ላይ ወነጨፈ ፣
ድንጋዩም ግንባሩን ፈጥርቆ ወደ ራስ ቅሉ ገባ ፣
ጎልያድም በምድር ላይ በግንባሩ ተደፋ ።
50 ሰሰዚህም ዳዊት ሰይፍ ሳይዝ ጎልያድን በወን
ጭፍና በድንጋይ ገድሎ ድል አደረገው ።
51 ወደ እርሱም ሮጦ በመሄድ በላዩ ላይ ቆመ ፣
የጎልያድንም ሰይፍ ከሰገባው በማውጣት ራሱን
ቁርጦ ገደለው ።

ፍልስጥኤማውያንም የእነርሱ ዝነኛ ተዋጊ
ጎልያድ መገደሉን ባዩ ጊዜ ሸሹ ። 52 ከዚህ
በኋላ የእስራኤልና የይሁዳ ሰዎች ድምፃቸውን
ከፍ እድርገው እየደነፉ እነርሱን በመከተል በየ
መንገዱ እስከ ጋትና እስከ ዔቅሮን የቅጽር
በሮች ድረስ አሳደዱአቸው ፣ የፍሰልጥኤማው
ያን ራሳ እስከ ጋትና እስከ ዔቅሮን ድረስ ወደ
ሻዕራይም በሚያደርስው መንገድ ሁሉ ወደቀ ።
53 እስራኤላውያንም እነርሱን አሳደው ከተመ
ለሱ በኋላ ፍልስጥኤማውያን የነበሩበትን ሰፈር
ዘረፉ ። 54 ዳዊት የጎልያድን ራስ ይዞ ወደ ኢየ
ሩሳሌም አመጣው ፣ የጎልያድን የጦር መሣሪያ
ዎች ግን በራሱ ድንኳን አሰቀመጠ ።

ዳዊት ወደ ሳኦል ቀረበ

55 ዳዊት ጎልያድን ለመውጋት በሚሄድበት
ጊዜ ሳኦል ተመልከቶ የጦሩን አዛዥ አበኔርን
“ይህ የማን ልጅ ነው?” ሲል ጠየቀው ።
አበኔርም “የማን ልጅ እንደሆነ ገና አላወቅ
ሁም” አለው ።
56 ሳኦልም “ሄደህ ይህ ወጣት የማን ልጅ
እንደሆነ አጥንተህ ዕወቅ” ሲል አዘዘው ።
57 ሰሰዚህ ዳዊት ጎልያድን ገድሎ ወደ ጦር
ሰፈር በተመለሰ ጊዜ አበኔር ተቀብሎ ወደ
ሳኦል አቀረበው ፣ በዚህን ጊዜ ዳዊት የጎልያድን
ራስ እንደያዘ ነበር ፣ 58 ሳኦልም “አንተ ወጣት
የማን ልጅ ነህ?” ብሎ ጠየቀው ።
ዳዊትም “የቤተልሔም ነዋሪ የሆነው የአገ
ልጋይህ የእሴይ ልጅ ነኝ” ሲል መለሰለት ።

ምዕራፍ 18

1 ሳኦልና ዳዊት ንግግራቸውን ከጨረሱ በኋላ
የሳኦል ልጅ ዮናታን ከዳዊት ጋር እጅግ የተቀ
ራረበ አንድነት መሠረተ ፣ እንደ ራሱም እድ
ርጎ ወደደው ፣ 2 ከዚያን ቀን ጀምሮ ሳኦል ዳዊ
ትን ከእርሱ ጋር እንዲኖር አደረገ ፣ ወደ
ቤቱም እንዲሄድ አሳሰናበተውም ፣ 3 ዮናታን
ዳዊትን እጅግ ሰሰወደደው ከእርሱ ጋር የወዳጅ
ነት ቃል ኪዳን ሰማጽናት ማለ ፣ 4 የሰበሰውንም
ካባ እውልቆ ሰዳዊት ሰጠው ፣ እንዲሁም የጦር
ልብሱን ፣ ሰይፉን ፣ ቀሰቱንና መታጠቂያውን
ጭምር ሰጠው ። 5 ሳኦል በትእዛዝ በሚያዘምት
በት ቦታ ሁሉ የዳዊት ተልእኮ የተሳካ ሆነ ፣

17፥50 ፦ 2ሳሙ. 21፥19 ። 17፥51 ፦ 1ሳሙ. 21፥9 ።

ስለዚህም ሳኦል በጦር ሠራዊቱ ውስጥ የመኰን ንነት ማዕርግ እንዲኖረው እደረገ ፥ ይህም የሳኦ ልን የጦር መኰንኖችና ወታደሮችን ሁሉ አስደ ሰተ ።

ሳኦል በዳዊት ላይ ምቀኝነትና ቅንአት አደረበት

6 ዳዊት ንልያድን ገድሎ ሲመለስና ወታደሮ ችም ወደየቤታቸው በማምራት ላይ ሳሉ ፥ በእ ስራኤል በሚገኙት ከተሞች ሁሉ የሚኖሩ ሴቶች ሳኦልን ለመቀበል ወጡ ፤ እነርሱም በእ ልልታ እየዘፈኑና እየጨፈሩ ፥ የመስንቆ ድምፅ እያሰሙ እታሞ ይመቱ ነበር ። 7 ሴቶቹም ባደረ ጉት የአቀባበል ሥርዓት ላይ “ሳኦል ሺ ገዳይ ! ዳዊት ግን ዐሥር ሺ ገዳይ !” እያሉ አሞገሡ ። 8 ሳኦልም ይህ ነገር ደስ ስላሳሰኘው በብርቱ ተቈጣ ፤ እንዲህም አለ ፥ “ዳዊትን ‘ዐሥር ሺ ገዳይ !’ ብለው ሰ,ያሞግሡ ፥ እኔን ግን ‘ሺ ብቻ ገዳይ’ አሉኝ ፤ በዚህ ወያነት ከዮነማ ወደፊት እርሱን ሲያነግሡት ነው !” 9 ከዚህም የተነሣ ከዚያን ቀን ጀምሮ በዳዊት ላይ ቅንአትና ጥር ጣሬ አደረበት ።

10 በማግሥቱም በድንገት ከእግዚአብሔር የተላከ ክፉ መንፈስ ሳኦልን ተቆራኘው ፤ በቤ ቱም ውስጥ እንደ አብድ ይሰፈልፍ ነበር ፤ ዳዊ ትም በየቀኑ ያደርግ በነበረው ዐይነት ለሳኦል በገና ይደረድርለት ነበር ፤ ሳኦልም ጦሩን በእጁ በመያዝ ፥ 11 “መትቼ ከግድግዳ ጋር አጣብቀዋ ለሁ” ብሎ በልቡ አሰበ ፤ ከዚህም በኋላ ጦሩን በዳዊት ላይ ሁለት ጊዜ ወረወረ ፤ ዳዊት ግን ሁለቱም ዞር አያለ አመለጠ ።

12 ሳኦል ዳዊትን ፈራው ፤ ምክንያቱም እግ ዚአብሔር እርሱን ትቶ ከዳዊት ጋር ስለሆነ ነው ፤ 13 ከዚህም የተነሣ ሳኦል ዳዊትን ከፊቱ ስማራቅ የሺ ወታደሮች አዛዥ አድርጎ ሳከው ፤ ዳዊትም ወታደሮቹን ወደ ጦርነት መራ ። 14 እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ስለሆነ የሚያደ ርገው ነገር ሁሉ ይሳካለት ነበር ። 15 ሳኦልም የዳዊትን ተልእኮ መሳካት እየተመለከተ በይበ ልጥ ይፈራው ጀመር ፤ 16 ነገር ግን በእስራኤ ልም ሆነ በይሁዳ የሚገኝ ሕዝብ ሁሉ ዳዊትን ይወደ ነበር ፤ ምክንያቱም ተልእኮው የሚሳካ ስት መሪ በመሆኑ ነው ።

ዳዊት የሳኦልን ልጅ አገባ

17 ከዚህ በኋላ ሳኦል ዳዊትን እንዲህ አለው ፥ “እነሆ ሜራብ ተብላ የምትጠራ ታላ ቅዋ ሴት ልጄ አስች ፤ ታማኝና ጀግና ወታደር ሆነህ የእግዚአብሔርን ጦርነት በመዋጋት ልታ ገለግለኝ ታል ብትገባልኝ እኔ እርስዋን በሚስት ነት እድርልሃለሁ ።” ሳኦል ይህን ያደረገበት ምክንያት እርሱ “ከደሙ ንጹሕ ሆኖ ፍልስጥ ኤማውያን ዳዊትን ይገድላሉ” ብሎ በማሰብ ነበር ።

18 ዳዊትም “የንጉሥ ዐማች እሆን ዘንድ እኔ ማን ነኝ ? ቤተሰቤስ በእስራኤል መካከል እምን ቊጥር ይገባል ?” ሲል መለሰለት ። 19 ነገር ግን ሜራብ ስዳዊት የምትዳርበት ጊዜ ሲደርስ ከመ ሐላ ስመጣውና ዓድሪኤል ተብሎ ስሚጠራ ለአ ንድ ሌላ ሰው ተሰጠች ።

20 ይሁን እንጂ ሚካል ትብላ የምትጠራው የሳኦል ልጅ ዳዊትን ወደደች ፤ ሳኦልም ይህን በሰማ ጊዜ ደስ አለው ፤ 21 በልቡም “ሚካልን ስዳዊት እሰጣለሁ ፥ እርስዋም ዳዊትን አንድታ ጠምድልኝ አደርጋለሁ ፤ ከዚያም በኋላ በፍልስ ዋኤማውያን እጅ ይገደላል” ሲል አሰበ ። ስለዚ ህም ሳኦል ለሁለተኛ ጊዜ ዳዊትን ጠርቶ “አሁን የእኔ ሁለተኛ ዐማች ትሆናለህ” አለው ። 22 ባለሟሎቹንም ጠርቶ “ንጉሡ በአ ንተ ተደስቶአል ፤ የእርሱ ባለሟሎች የሆኑት ባለሥልጣኖቹም ይወዱሃል ፤ ስለዚህ የእርሱን ልጅ ታገባ ዘንድ አሁን ጥሩ ጊዜ ገጥሞሃል” ብለው ስዳዊት በግል እንዲነግሩት አዘዘ ።

23 እነርሱም ይህን ሁሉ ስዳዊት በነገሩት ጊዜ እርሱ “የንጉሡ ዐማች መሆን ታላቅ ክብር ነው ፤ ይልቁንም እንደ እኔ ላለ ዝቅተኛ ድኻ ይህ ክብር ይበዛበታል” ሲል መለሰላ ቸው ።

24 ባለሟሎቹም ከዳዊት ያገኙትን መልስ ስሳኦል ነገሩት ፤ 25 ሳኦልም እንደ ገና “ንጉሡ ስለልጁ ከእንተ የሚፈልገው ዋሎሽ ጠላቶቹን መበቀል እንዲችል እንደ መቶ ፍልስጥኤማው ያን ገድለህ ሸለፈታቸውን እንድታመጣለት ብቻ ነው” ብላችሁ ንገሩት ሲል ባለሟሎቹን እዘዘ ። ሳኦል ይህን ያደረገበት ምክንያት ዳዊት በፍልስጥኤማውያን እጅ እንዲገደልለት በማ ቀድ ነበር ። 26 የሳኦል ባለሟሎችም ይህንኑ ለዳ ዊት ነገሩት ፤ ዳዊትም የንጉሡ ዐማች እንዲ ሆን በመታሰቡ ደስ አለው ። የሠርጉም ቀን ከመድረሱ በፊት ፥ 27 ዳዊትና ወታደሮቹ ዘም ተው ሁለት መቶ ፍልስጥኤማውያንን ገደሉ ፤ ዳዊትም የንጉሥ ዐማች መሆን ይችል ዘንድ ሸለፈታቸውን ወደ ንጉሡ በመውሰድ ቈጥሮ አስረከበ ። ስለዚህም ሳኦል ልጁን ሚካልን ስዳ ዊት መዳር ግድ ሆነበት ።

28 ሳኦል እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር መሆኑ ንና ልጁም ሚካል እርሱን እንደወደደችው አረ ጋገጠ ። 29 ስለዚህም ሳኦል ዳዊትን ይበልጥ ከመፍራቱ የተነሣ በኖረበት ዘመን ሁሉ የዳዊት ጠላት ሆነ ።

30 የፍልስጥኤማውያን ወታደሮች በየጊዜው እየመጡ ጦርነት ያደርጉ ነበር ፤ ይሁን እንጂ

በማናቸውም ጦርነት ሁሉ ከሳኦል የጦር መኰንኖች ይበልጥ ድል የሚሳካሰት ስዳዊት ነበር ፤ ከዚህም የተነሣ ዳዊት እጅግ ዝነኛ ሆነ ።

ምዕራፍ 19

ሳኦል ዳዊትን ያሳድድ ጀመር

[1] ሳኦል ዳዊትን ሲገድለው ማቀዱን ስልጁ ስዮናታንና ባስሚሎቹ ለሆኑት ባስሥልጣኖች ሁሉ ነገረ ፤ ነገር ግን ዮናታን ዳዊትን እጅግ ይወደው ስስነበረ ፥ [2] በእርሱ ላይ የታቀደውን ነገር ሁሉ እንዲህ ሲል ነገረው ፥ “አባቴ ሲገድ ልህ ፀቅዶአል ፤ ስስዚህ እባክህ በነገው ማስዳ ይህ እንዳይደርስብህ ተጠንቀቅ ፤ ስውር በሆነ ቦታ ተሸሽገህ ቆይ ፤ [3] አንተም ተደብቀህ ባስህ በት እርሻ ወደ አባቴ ቀርቤ ስስ አንተ እነጋግረ ዋስሁ ፤ የማገኘውንም መልስ እንድታውቀው አደርጋስሁ ።”

[4] ዮናታንም ዳዊትን በማመስገን ሰሳኦል እን ዲህ ሲል ነገረው ፥ “ጌታዬ ሆይ ! በአገልጋይህ በዳዊት ላይ ከፉ ነገር አታድርግ ፤ እርሱ ኩፉ ምንም ነገር አልበደለህም ፤ ይልቅስ እርሱ የሚ ያደርገው ነገር ሁሉ ታላቅ ጥቅም በማስገኘት ረድቶሃል ፤ [5] እርሱ ስሕይወቱ ሳይሳሳ በጦጋፊጥ ኅልያድን ገደስ ፤ እግዚአብሔርም ስእሰራኤል ታላቅ ድልን አቀዳጀ ፤ አንተም ይህን ባየህ ጊዜ ደስ ብሎህ ነበር ፤ ታዲያ አሁን አንተ በንጹሕ ስው ላይ በደል ስመሥራት ስስምን ታስባስህ? ምክንያት በሌለውስ ነገር ዳዊትን ስመግደል ስስምን ፈስግህ?”

[6] ሳኦልም ዮናታን በተናገረው ቃል ስሳመነ በት ዳዊትን እንደማይገድሰው የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ በመማል አረጋገጠ ፤ [7] ስስዚህ ዮና ታን ዳዊትን ጠርቶ ይህን ሁሉ ከነገረው በኋላ ወደ ሳኦል አቀረበው ፤ ዳዊትም ከዚያ በፊት ያደርገው እንደነበር በንጉሡ ፊት ማገልገሉን ቀጠለ ።

[8] ከፍልስጥኤማውያን ጋር ይደረግ የነበረ ውም ጦርነት እንደገና አገረሸ ፤ ሆኖም ዳዊት በእነርሱ ላይ ብርቱ አደጋ በመጣል ድባቅ ስስ መታቸው ሸሽተው ሄዱ ፤

[9] አንድ ቀን ከእግዚአብሔር የተላከ ከፉ መንፈስ ሳኦልን ተቆራኘው ፤ ስስዚህም ጦሩን በእጁ እንደያዘ በቤቱ ውስጥ ተቀምጦ ነበር ፤ ዳዊትም በዚያው በገናውን ይደረድር ነበር ፤ [10] ሳኦል ዳዊትን ወግቶ ከግድግዳው ጋር ሲያጣ ብቀው በማሰብ ጦሩን ወረወረበት ፤ ዳዊት ግን ዞር በማስቱ ጦሩ በግድግዳ ላይ ተተከስ ፤ ዳዊ ትም ከዚያ በመነሣት ሮጦ አመለጠ ።

[11] በዚያኑ ምሽት ሳኦል የዳዊትን ቤት ከበው ማስዳ እንዲገድሱት ሰዎችን ላከ ፤ የዳ ዊት ሚስት ሚካል “ዛሬ ማታ ከዚህ ካልሄድህ በቀር ነገ ጠዋት ትገደላስህ” ስትል አስጠነቀቀ ችው ፤ [12] እርስዋም በመስኮት አወረደችው ፤ ሮጦም በመሄድ አመለጠ ፤ [13] ከዚህ በኋላ ቤተ ሰብ የሚያመልከውን ጣዖት ወስዳ በአልጋ ላይ አጋደመችው ፤ ከፍየል ጠጕር የተሠራ ትራስም በራስጌው አኑራ በአልጋ ልብስ ሸፈነችው ። [14] የሳኦል ወታደሮችም ዳዊትን ስመያዝ በመጡ ጊዜ ሚካል እርሱ ታሞ ተኝቶአል አስቻቸው ። [15] ሳኦል ግን በዐይናቸው አይተው ያረጋግጡ ዘንድ መልሶ ላካቸው ፤ እንዲያውም “ከነአል ጋው ተሸከማችሁ ወደዚህ አምጡት ፤ እኔ ራሴ እገድስዋስሁ” አስ ። [16] ወደ ቤትም ውስጥ ዘል ቀው በገቡ ጊዜ ቤተሰብ የሚያመልከውን ጣዖ ትና በራስጌው ያስውን ከፍየል ጠጕር የተሠራ ውን ትራስ ብቻ አገኙ ። [17] ሳኦልም ሚካልን “ጠላቴ የሚያመልጥበትን ተንኰል በመሥራት ስለምን እንዲህ አታስልሽኝ?” ሲል ጠየቃት ።

እርስዋም “እኔ ምን ላድርግ ፥ ‘በሆነው ዘዴ ማምስጥ እንድችል ካልረዳሽኝ በቀር እገድልሻ ስሁ’ አስኝ” ስትል መሰሰችስት ። [18] ዳዊትም አምልጦ ሳሙኤል ወደነበረበት ወደ ራማ መጣ ፤ ሳኦል ያደረገበትንም በደል ሁሉ ነገ ረው ፤ ከዚህም በኋላ ሳሙኤልና ዳዊት በራማ ወደምትገኘው ወደ ናዮት ሄደው በዚያ ተቀ መጡ ፤ [19] ዳዊት በራማ በምትገኘው በናዮት መኖሩን ሳኦል ስማ ፤ [20] ስስዚህም ሳኦል ዳዊ ትን የሚይዙ ስዎች ላከ ፤ እነርሱም እዚያ በደ ረሱ ጊዜ ፥ በሳሙኤል መሪነት የተሰበሰቡ ነቢ ያት በጉባኤ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በመዘ መር ሲያሸበሽቡ አዩ ፤ በዚህን ጊዜ የእግዚአብ ሔር መንፈስ በሳኦል ሰዎች ላይ ስስወረደ እነር ሱም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በመዘመር ማሸብሸብ ጀመሩ ። [21] ሳኦል ይህን በስማ ጊዜ ሌሎች መልእክተኞችን ላከ ፤ እነርሱም እንደዚ ያው መዘመርና ማሸብሸብ ቀጠሉ ፤ ሳኦልም ሰሦስተኛ ጊዜ ሌሎች መልእክተኞችን ቢልክ ያው ነገር በእነርሱም ላይ ተደገመ ፤ [22] ከዚህ በኋላ እርሱ ራሱ ወደ ራማ ሰመሄድ ተነሣ ፤ እዚያም ሴኩ በሚባለው ስፍራ ወደሚገኘው ወደ አንድ ታላቅ ጕድጓድ በደረሰ ጊዜ “ሳሙ ኤልና ዳዊት የሚገኙት የት ነው?” ብሎ ሲጠ ይቅ ፥ በናዮት መኖራቸው ተነገረው ። [23] ወደዚ ያም በማምራት ላይ ሳስ የእግዚአብሔር መን ፈስ በእርሱም ላይ ወረደበት ፤ እስከ ናዮት በሚያደርስው መንገድ ሁሉ ድምፀን ከፍ አድ ርጎ በመዘመር ያሸበሽብ ነበር ፤ [24] ወደ ሳሙኤ ልም ፊት ሲቀርብ ልብሱን አውልቆ ዋሎ ድም ፁን ከፍ አድርጎ በመዘመር ማሸብሸቡን ቀጠለ ፤ ቀኑንም ሌሊቱንም ሁሉ ራቁቱን በዚ ያው ተጋድሞ ዋስ ፤ “ሳኦልም ከነቢያት እንደ

19፥11 ፦ መዝ. 59 ። 19፥24 ፦ 1ሳሙ. 10፥11-12 ።

አንዱ ሆኖ ተቈጠርን?” የሚሰው የምሳሌ እነ ጋገር የመነጨው ከዚህ የተነሣ ነው ።

ምዕራፍ 20

ዮናታን ዳዊትን ረዳ

1 ከዚህ በኋላ ዳዊት በራማ ከምትገኘው ከና ዮት በመሸሽ ወደ ዮናታን ሄዶ “ከቶ ምን አደ ረግሁ? ምንስ ወንጀል ፈጸምሁ? አባትህ ሰመሣ ደል የሚፈልገኝስ ምን በድየው ነው?” ሲል ጠየቀው ።

2 ዮናታንም “ሞትህንስ እግዚአብሔር ያር ቀው! አባቴ የሚያደርገውን ነገር ሁሉ በጎው ንም ክፉውንም ነገር ሁሉ ይነግረኛል፤ የአንተ ንም ጕዳይ ቢሆን ከእኔ አይበውርም፤ ስለዚህ ይህ የምትለው ነገር እውነት ሊሆን አይች ልም” አለው ።

3 ዳዊት ግን “አባትህ አንተ እኔን ምን ያህል እንደምትወደኝ በደንብ ያውቃል፤ ስለዚህም ዕቅዱን አንተ እንድታውቅበት ላለማድረግ ወስ ኖአል፤ ምክንያቱም አንተ ይህን ብታውቅ በብ ርቱ እንደምታዝን ያውቃል፤ በሕያው እግዚአ ብሔር ስምና በነፍስህ እምላለሁ፤ ከአሁን ወዲያ ወደ ሞት ሰመድረስ የቀረችኝ አንዲት እርምጃ ብቻ ናት” አለው ።

4 ዮናታንም “አንት የምትፈልገውን ሁሉ አደርጋለሁ” አለ ።

5 ዳዊትም እንዲህ ሲል መለሰ፥ “ነገ አዲስ ጨረቃ የምትታይበት በዓል ነው፤ እኔም ከን ጉሡ ጋር መብላት ይኖርብኛል፤ አንተ የምትስ ማማበት ከሆነ ሄጀ እስከ ተነገ ወዲያ ምሽት ድረስ እሸሸጋለሁ፤ 6 አባትህ በዚያ ማእድ ላይ እስመገኘቴን ቢያስታውስ ቤተሰቤ ሁሉ ዓመ ታዊ መሥዋዕት የሚያቀርብበት ዕለት ስለሆነ፥ በቤተልሔም ወደሚገኘው መኖሪያ ቤቴ ፈዋኜ እንድሄድ ከአንተ ፈቃድ የጠየቅሁ መሆኔን ንገ ረው፤ 7 ንጉሡም ‘እሺ’ ቢል፥ እኔ በሰላም እን ደምኖር ዐውቃለሁ፤ ንጉሡ ከተቈጣ ግን ጕዳት ሊያደርስብኝ የወሰነ መሆኑን ታውቃለህ፤ 8 በእ ግዚአብሔር ቃል ኪዳን ስለተማመን የሰጠኸኝን የተቀደሰ ተስፋ በመጠበቅ እባክህ ይህን መል ካም ነገር አድርግልኝ፤ ወንጀሰኛ ሆኜ ከተገ ኘሁ ግን እንተው ራስህ ግደለኝ እንጂ እንዲገድ ሰኝ ወደ አባትህ ስምን ትወስደኛለህ?”

9 ዮናታን ግን “እንዲህ ያለውን ነገር ከቶ አታስብ፤ አባቴ በእንተ ላይ ጕዳት ሰማድረስ መወሰኑን በእርግጥ ዐውቄ ቢሆንማ ኖሮ እኔው ራሴ እገልጥልህ አልነበረም እንጂ?” አለው ።

10 ዳዊትም “ታዲያ አባትህ ስለእኔ ከፉ ቃል ሲናገር ማን ያስረዳኛል?” ሲል ጠየቀ ።

11 ዮናታንም “ና ወደ ዱር እንሂድ” ሲል መለሰለት፤ አብረውም ከሄዱ በኋላ፥ 12 ዮናታን ዳዊትን እንዲህ አለው፥ “እንግዲህ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ምስክራችን ይሁን፤ ነገ በዚህን ጊዜና በሚከተሰውም ቀን አባቴን እጠያ ቀዋለሁ፤ እርሱ ስለ አንተ ያሰው አመሰካከት ጥሩ ከሆነ የቃል መልእክት እልክልሃለሁ፤ 13 እንተን ስመጕዳት የሚፈልግ ከሆነ ግን፥ ሰስ እርሱ ባልገለጥልህና አንተም በሰላም እንድት ሄድ ባላደርግ እግዚአብሔር በሞት ይቅጣኝ፤ እግዚአብሔር ከአባቴ ጋር እንደነበር ከአንተም ጋር ይሁን፤ 14 እኔ በሕይወት ብኖር የስጠኸኝን የተቀደሰ ተስፋ በመጠበቅ ለእኔ ታማኝ ሁን፤ ብሞት ግን፥ 15 ይህንኑ ለእኔ ያስህን ታማኝነት በመቀጠል ሰቤተሰቤ ዘላቂ ቸርነት አድርግ፤ እግዚአብሔር ጠሳቶችህን ሁሉ ኑቃቅሎ በሚያ ጠፋበት ጊዜም፥ 16 እኔ ሰአንተ፥ አንተም ለእኔ የገባኸው ቃል እንደተጠበቅ ይኑር፤ ይህን ቃል ኪዳን ብታፈርስ ግን እግዚአብሔር ይቀጣ ሃል ።”

17 ዮናታን ዳዊትን እንደ ራሱ አድርጎ ይወ ድደው ስለ ነበር “በእርግጥ እንደምትወደኝ ስመግለጥ እንደገና ማልልኝ” አለው ። 18 ከዚህ በኋላ ዮናታን እንዲህ አሰው፥ “ነገ አዲስ ጨረቃ የምትታይበት ቀን ነው፤ ስሰዚህ በማ እድ ላይ አስመኖርህ ይታወቃል፤ 19 ይልቁንም ተነገ ወዲያ በማእድ ላይ አስመኖርህ ይበልጥ ጎልቶ ይታያል፤ ስለዚህ ከዚህ በፊት ተሸሽገህ ወደ ነበርክበት ቦታ ሄደህ ከኤጼል ድንጋይ ከምር በስተ ደርባ ተሸሸግ፤ 20 እኔም የድንጋዮ ቹን ከምር ሊለማ በማድረግ ሦስት ፍላጻዎች እወረውርበታለሁ፤ 21 ከዚያም በኋላ አገልጋዬን ‘ሄደህ ፍላጻዎቹን ፈልገህ አግኛቸው’ እለዋ ለሁ፤ ‘ተመልከት! ፍላጻዎቹ ከአንተ ወደዚህ ስሰሆኑ ሄደህ አምጣቸው!’ ያልኩት እንደ ሆን፥ በእንተ ላይ ከፉ ነገር የማይደርስብህ መሆኑን ስሰሚያስረዳ ከተሸሸግህበት መውጣት ትችላለህ፤ ምንም ዐይነት አደጋ እንደማይደርስ ብህ በሕያው እግዚአብሔር ስም እምላለሁ፤ 22 ነገር ግን አገልጋዬን ‘ፍላጻዎቹ ከአንተ ወዲያ አልፈው ሄደዋል!’ ያልኩት እንደሆን ተነሥተህ ሂድ፤ ምክንያቱም አንተ ከዚህ ስቀህ እንድትሄድ እግዚአብሔር ራሱ ፈቅዶልሃል ። 23 እርስ በርሳችን ስለገባነው ቃል ኪዳን የሆነ እንደሆን፥ ሰዘላለም እንደምንጠብቀው እግዚአ ብሔር ምስክራችን ነው ።”

24 ስሰዚህም ዳዊት በዱር ተደብቆ ቆየ፤ አዲስ ጨረቃ በምትታይበት በዓል ሳኦል ግብሩ ወደሚበላበት አዳራሽ መጥቶ፥ 25 ከግድግዳው ጥግ በተለመደው የክብር ስፍራ ሲቀመጥ፥ አበ ኔር ከእርሱ ቀጥሎ ተቀመጠ፤ ዮናታንም በን ጉሡ ፊት ለፊት ነበር፤ በዚህ ጊዜ የዳዊት ወን በር ባዶ ነበር፤ 26 ይሁን እንጂ ሳኦል በዚያን

20፥5 ፡- ዘኍ. 28፥11 ። 20፥15 ፡- 2ሳሙ. 9፥1 ።

ቀን ምንም ቃል አልተናገረም ፤ ምክንያቱም ሳኦል ስለ ዳዊት ሲያስብ “ምናልባት እንድ ነገር ገጥሞት ይሆናል ፤ ወይም በሕጉ መሠረት በሥርዓት አልነጻም ይሆናል” በማለት ያስላስል ነበር ፤ 27 እሺህ ጨረቃ የታየችበት በዓል ካለፈ በኋላም በተከታዩ ቀን የዳዊት ወንበር ባዶ ነበር ፤ ስለዚህ ሳኦል ዮናታንን “ዳዊት ትናን ትም ፥ ዛሬም ወደዚህ ግብጥ ያልመጣው ለሰ ምንድን ነው?” ሲል ጠየቀው ።

28 ዮናታንም እንዲህ ሲል መለሰ ፥ “ወደ ቤተልሔም ይሄድ ዘንድ እንድፈቅድለት ሲለም ነኝ ፥ 29 ‘እባክህ እንድሄድ ፍቀድልኝ ፥ ምክን ያቱም ቤተሰባችን በከተማይቱ የመሥዋዕት በዓል ያከብራል ፤ ውንድሜም በዚያው እንድ ገኝ እዝዞኛል ፤ ስለዚህ የምትወደኝ ከሆንህ ቤተሰቦቼን ለማየት እንድሄድ ፍቀድልኝ’ ብሎኝ ነበር ፤ እንግዲህ በዚህ ንጉሣዊ ማእድ ላይ ያልተገኘበትም ምክንያት ይኸው ነው ።”

30 ሳኦልም በዮናታን ላይ እጅግ ተቈጥቶ እንዲህ አለ ፥ “አንተ የማትረባ ዲቃላ! አንተ የዳዊት ደጋፊው እንደሆንህ ፥ ከዚህም የተነሣ የራስህንና የወላጅ እናትህን ክብር እንዳዋረድህ አውን ዐወቅሁ! 31 የእሴይ ልጅ ዳዊት በሕይ ወት እስካለ ድረስ አንተ የዚህች አገር ንጉሥ መሆን እንደማትችል ኩዶ አታውቅምን? አሁን ሂደህ አምጣው ፤ በሞት መቀጣት አለበት ።”

32 ዮናታንም “ለምን ይሞታል? ምንስ በደል ሠራ?” ሲል መለሰ ።

33 ከዚህም የተነሣ ዮናታንን ለመግደል የያዘ ውን ጦር ወረወረበት ፤ ስለዚህም ዮናታን አባቱ ሳኦል ዳዊትን ለመግደል ቍርጥ ውሳኔ ማድረ ጉን እረጋገጠ ፤ 34 ዮናታንም በቍጣ ከማእዱ ላይ ተነሣ ፤ በዚያ ቀን ማለትም አዲስ ጨረቃ በታየችበት በዓል በሁለተኛ ቀን ምንም ምግብ አልበላም ፤ ሳኦል ዳዊትን በማዋረዱ ምክንያት ስለዳዊት ሁኔታ ዮናታን በብርቱ አዝኖ ነበር ።

35 በማግሥቱ ጠዋት በቀጠሮአቸው መሠረት ዮናታን ዳዊትን ለማግኘት ወደ ዱር ሄደ ፤ ሲሄ ድም አንድ ትንሽ ልጅ አስከትሎ ነበር ፤ 36 ልጁንም “ፈጥነህ ሂደና የምወረውራቸውን ፍላጻዎች ፈልገህ አምጣልኝ” አለው ፤ ልጁም ሲሮጥ ዮናታን ከዚያ ልጅ ፊት አሳልፎ እንድ ፍላጻ ወረወረ ፤ 37 ያም ልጅ ፍላጻው ባረፈበት ቦታ በደረሰ ጊዜ ዮናታን “ፍላጻው አልፎህ ሄዶአል ፤ 38 እዚያ ዝም ብለህ አትቁም ፤ ፈጠን በል!” ሲል ጮኸበት ፤ ልጁም የዚህን ምስ ጢር ሳያውቅ ፍላጻውን እንሥቶ ወደ ጌታው ተመለሰ ፤ 39 ይህን ምስጢር የሚያውቁት ዮናታ ንና ዳዊት ብቻ ነበሩ ፤ 40 ዮናታንም ያንን ልጅ “መሣሪያዎቼን ይዘህ ወደ ከተማ ተመለስ” አለው ።

41 ልጁም ከሄደ በኋላ ዳዊት ከድንጋዩ ከምር በስተኋላ ከተደበቀበት ስፍራ ወጥቶ በጉ ልበቱ በመንበርከክ ሦስት ጊዜ ወደ መሬት ሰገደ ፤ እርሱና ዮናታን በሚሳሳሙበት ጊዜ ሁሉ ቱም ያለቅሱ ነበር ፤ ከዮናታንም ይልቅ የዳዊት ሐዘን የበረታ ነበር ። 42 ከዚህም በኋላ ዮናታን ዳዊትን “እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሁን ፤ እኔና እንተ የአንተ ዘሮችና የእኔም ዘሮች እርስ በርሳችን በእግዚአብሔር ስም የገባነውን ቃል ኪዳን ለዘላለም ጠብቀን ስለመኖራችን እግዚአ ብሔር ምስክር ይሁን” አለው ፤ ከዚህ በኋላ ዳዊት ተነሥቶ ሄደ ፤ ዮናታንም ወደ ከተማ ተመልሶ ሄደ ።

ምዕራፍ 21

ዳዊት ከሳኦል ፊት ሸሽቶ ሄደ

1 ዳዊት በኖብ ወደሚገኘው ወደ ካህኑ አቢ ሜሌክ ዘንድ ሄደ ፤ አቢሜሌክም በፍርሃት እየ ተንቀጠቀጠ ሲቀበለው ወጥቶ “ማንም ሰው ሳይከተልህ ብቻህን ስለምን ወደዚህ መጣህ?” ሲል ጠየቀው ።

2 ዳዊትም እንዲህ ሲል መለሰ ፥ “እኔ እዚህ የመጣሁት የንጉሥ ሳኦልን ተልእኮ ለመፈጸም ነው ፤ እኔ ወደዚህ የተላከሁበትን ጕዳይ ለማ ንም ሰው እንዳልገልጥ ንጉሡ አዝዞኛል ፤ ተከ ታዮቼንም በአንድ ቦታ እንድንገናኝ አዝዣቸዋ ለሁ ፤ 3 ታዲያ አሁን ምን ምግብ ትሰጠኛለህ? እምስት እንጀራ ወይም ያለህን ሌላ ነገር ሰጠኝ ።”

4 ካህኑም “ከተቀደሰው ኅብስት በቀር ሕዝብ የሚመገበው እንጀራ የለኝም ፤ ተከታዮ ችህ በቅርቡ ሩካቤ ሥጋ ከማድረግ ተቈጥበው በንጽሕና የቆዩ ከሆኑ ፥ ይህን ኅብስት መውሰድ ይቻላል” ሲል መለሰለት ።

5 ዳዊትም “በእውነት ከዚህስ የነዱ ናቸው ፤ የእኔ ሰዎች ተራ ተልእኮ ለመፈጸም በሚወጡ በት ጊዜ እንኳ ዘወትር በሕጉ መሠረት ንጽሕና ቸውን ይጠብቃሉ ፤ ታዲያ ይህን ልዩ ተልእኮ በሚፈጽሙበት ጊዜማ እንዴት ንጽሕናቸውን አይጠብቁም?” አለው ።

6 ስለዚህም ካህኑ የተቀደሰውን ኅብስት እን ሥቶ ለዳዊት ሰጠው ፤ ምክንያቱም ካህኑ ያለው ምግብ ለእግዚአብሔር መባ ሆኖ የቀረበው ኅብ ስት ብቻ ነበር ፤ ይህም ኅብስት ከተቀደሰው ጠረጴዛ ላይ ተነሥቶ በሌላ አዲስ ኅብስት የተ ተካ ነበር ።

7 የሳኦል አረኖች አለቃ የሆነው ኤዶማዊው ዶይቅ በዚያኑ ቀን ሃይማኖታዊ ሥርዓትን ለመ ፈጸም በዚያ ተገኝቶ ነበር ።

8 ዳዊትም አቢሜሌክን “የምትሰጠኝ ጦር ወይም ሰይፍ በአንተ ዘንድ ይገኛልን? የንጉሡ

21፥1-6 ፡- ማቴ. 12፡3-4 ፤ ማር. 2፡25-26 ፤ ሉቃ. 6፡3 ። 21፥6 ፡- ዘሌ. 24፥5-9 ።

ትእዛዝ አሰቸኳይ ሰለሆነ ጦሬንም ሆነ ሌላውንም መሣሪያዬን ስመያዝ ጊዜ አላገኘሁም ነበር” አለው ።

9እሊሜሌክም “በኤላ ሸለቆ የገደልከው የፍልስጥኤማዊው የጎልያድ ሰይፍ በእኔ ዘንድ አለ ፤ እርሱም ከኤፉዱ በስተኋላ በጨርቅ ተጠቅልሎ ተቀምጠአል ፤ የምትፈልገው ከሆነ ውሰደው ፤ ምክንያቱም በዚህ የሚገኝ የጦር መሣሪያ እርሱ ብቻ ነው” አለው ።

ዳዊትም “እርሱኑ ስጠኝ! ከእርሱ የተሻለ ሰይፍ የትም አይገኝም” አለው ።

10ዳዊትም ከሳኦል በመሸሽ አኪሽ ተብሎ ወደሚጠራው ወደ ጋት ንጉሥ ሄደ ፤ 11የጎ ኑሙ ባለሟሎች የሆኑት ባለሥልጣኖች “ይህ በአገሩ የነገሠው ዳዊት አይደለምን? ‘ሳኦል ሺ ገዳይ! ዳዊት ዐሥር ሺ ገዳይ!’ እያሉ ሴቶች በዘፈን ያሞገሱትስ እርሱን አይደለምን?” ሲሉ አኪሽን ጠየቁት ።

12በእነርሱም እንጋገር የዳዊት ልብ በብርቱ ተነካ ፤ ንጉሥ አኪሽንም በብርቱ ፈራ ። 13ስለዚህ ዳዊት እነርሱ ባሉበት አካባቢ ሁሉ ያበደ ስማስመሰል ሞከረ ፤ ሊይዙት በሚሞክሩበትም ጊዜ እንደ እብድ ሆኖ አገኙት ፤ የከተማይቱን ቅጽር በሮች እየጒጠጠ ፥ ስሐጩን በጺሙ ላይ ያዝረከርክ ነበር ። 14አኪሽም ባለሟሎቹ ስሆኑት ባለሥልጣኖች “እነሆ ይህ ሰው እብድ ነው! ታዲያ ስለምን ወደ እኔ አመጣችሁት? 15ድሮውኑ እኔ እብድ መቼ እጥቼ ነው? ይህን አእምሮው የተነካ ሰው ወደቤተ መንግሥቴ ሰተት እድርጋችሁ በማሰገባት የምትበጠብጡኝ!” አለ ።

ምዕራፍ 22

የካህናት መገደል

1ዳዊት ከጋት ከተማ ሸሽቶ በዐዱላም ከተማ አጠገብ ወደሚገኘው ወደ አንድ ዋሻ ሄደ ፤ ወንድሞቹና ሌሎቹም ቤተሰቦቹ ይህን በሰሙ ጊዜ ወደዚያ ሄደው ከእርሱ ጋር ተባበሩ ፤ 2ጭቈና የደረሰባቸው ፥ ዕዳ ያለባቸው ፥ እንዲሁም ሆድ የባሰባቸው አንዳንድ ሰዎች ወደ እርሱ ስለሄዱ ብዛታቸው በድምሩ አስከ አራት መቶ ደረሰ ፤ ዳዊትም የእነርሱ መሪ ሆነ ።

3ዳዊትም ከዚያ ተነሥቶ በሞአብ ወደምትገኘው ወደ ምጽጳ ሄደ ፤ የሞአብንም ንጉሥ “እግዚአብሔር ስእኔ የሚያደርግልኝን ነገር እስካውቅ ድረስ እባክህ እባቴና እናቴ መጥተው በእንተ ዘንድ እንዲቆዩ ፍቀድላቸው” ሲል ጠየቀው ። 4በዚህም ዐይነት ሁኔታ ወላጆቹን በሞአብ ንጉሥ ዘንድ ተዋቸው ፤ እነርሱም ዳዊት በዋሻ እየተደበቅ በሚኖርበት ዘመን ሁሉ በዚያው ቆዩ ።

5ከዚህ በኋላ ነቢዩ ጋድ ወደ ዳዊት መጥቶ “በዚህ አትቆይ ፤ እሁኑኑ ፈጥነህ ወደ ይሁዳ ሂድ” ሲል ነገረው ፤ ስለዚህም ዳዊት ከዚያ ተነሥቶ ወደ ሔሬት ጫካ ገባ ።

6ከዕለታት አንድ ቀን ሳኦል ጦሩን በእጁ እንደያዘ በጊብዓ በሚገኝ ኮረብታ ላይ ታማሪ ስከ ተብሎ በሚጠራ ዛፍ ሥር ተቀምጦ ነበር ፤ ባለሟሎቹ የሆኑ ባለሥልጣኖችም በዙሪያው ቆመው ነበር ፤ በዚህን ጊዜ ዳዊትና ተከታዮቹ በአንድ ስፍራ መኖራቸው ስሳኦል ተነገረው ፤ 7ሳኦልም ባለሟሎችን እንዲህ አላቸው ፥ “እናንተ የብንያም ሰዎች እድምጡኝ! በውኑ የእሴይ ልጅ ዳዊት ስሁላችሁም ለእያንዳንዳችሁ የእርሻ መሬትና የወይን ተክል ቦታ የሚሰጣች ሁና በሠራዊቱም ውሰጥ የጦር መኰንኖች እድርጎ የሚሾማችሁ ይመስላችኋልን? 8በእኔስ ላይ ሤራ የምታካሄዱት ሰስዚህ ነውን? የገዛ ልጄ ከዳዊት ጋር መተባበሩን የነገረኝ ከእናንተ አንድ እንኳ የለም ፤ ሰስ እኔ የሚያሰብ ከቶ ማንም የለም ፤ ወይም ከእኔው ከራሴ ሰዎች እንዱ የሆነው ዳዊት በእሁኑ ወቅት እኔን ስመግደል አጋጣሚ ጊዜ እንደሚፈልግና የእኔም ልጅ እንደሚያበረታታው የሚነግረኝ የለም ።”

9በዚህን ጊዜ ከባለሥልጣኖቹ ጋር ዶይቅ እዚያ ቆሞ ስለነበር “እኔ ዳዊትን በኖብ ወደሚገኘው የእሒጡብ ልጅ ወደሆነው ወደ እቢሜሌክ በመጣ ጊዜ አይቼዋለሁ ፤ 10ዳዊትም ምን ማድረግ እንደሚገባው አቢሜሌክ እግዚአብሔርን ጠይቆለታል ፤ ከዚያም በኋላ ለዳዊት ጥቂት ምግብና የፍልስጥኤማዊውን የጎልያድን ሰይፍ ሰጥቶታል” ሲል ተናገረ ።

11ስለዚህም ንጉሥ ሳኦል ወደ ካህኑ እቢሜሌክና በኖብ ወደሚገኙት ዘመዶቹ ወደሆኑት ካህናት ሁሉ መልእክት ላከ ፤ እነርሱም መጡ ፤ 12ሳኦል ፥ እቢሜሌክን “እቢሜሌክ ሆይ! እድምጠኝ” አለው ።

እቢሜሌክም “ጌታዬ እነሆ ታዛዥ ነኝ” አለ ።

13ሳኦልም “አንተና ዳዊት በእኔ ላይ የምታሤሩት ስለምንድን ነው? ምግብና ሰይፍ ሰጥተህ እግዚአብሔርን የጠየቅህለትስ ስለምንድን ነው? እነሆ እርሱ አሁን በእኔ ላይ ተነሥቶ እኔን ስመግደል አጋጣሚ ጊዜ በመፈለግ ላይ ነው” ሲል ጠየቀው ።

14እሊሜሌክም እንዲህ ሲል መለሰ ፥ “ዳዊት ስእንተ የታመነ የጦር መኰንን ነው ፤ የእንተው የራስህ ዐማች ከመሆኑም ሌላ የክብር ዘብህ አዛዥ ነው ፤ በቤተ መንግሥትህም እደባ ባይ ሰው ሁሉ የሚያከብረው ነው ፤ 15በእርግጥ እኔም እግዚአብሔርን ጠይቄለታለሁ ፤ ይህም

21፥9 ፦ 1ሳሙ. 17፥51 ። 21፥11 ፦ 1ሳሙ. 18፥7 ፤ 29፥5 ። 21፥12 ፦ መዝ. 56 ። 21፥13 ፦ መዝ. 34 ።
22፥1 ፦ መዝ. 57 ፤ መዝ. 142 ። 22፥9-10 ፦ 1ሳሙ. 21፥7-9 ፤ መዝ. 52 ።

የመጀመሪያ ጊዜ አይደለም ፤ ንጉሥ ሆይ! በአንተ ላይ ስለሚደሙ ጕዳይ ግን አእንም ሆነ ወይም ከቤተሰቤ አንዱን መውቀስ አያገባህም ፤ ምክንያቱም እኔ ስለዚህ ጕዳይ ምንም የማውቀው ነገር የለም ።”

16 ንጉሡም “አቢሜሌክ ሆይ! አንተና ዘመዶችህ ሁሉ ሞት ይገባችኋል” አለው ። 17 ከዚህም በኋላ ሳኦል በአጠገቡ ወደቆሙት ዘብ ጠባቂዎች መለስ ብሎ “እነዚህን የእግዚአብሔርን ካህናት ግደሉ! ምክንያቱም እነርሱ ከዳዊት ጋር በእኔ ላይ ዐምፀውብኛል ፤ እንዲሁም ሁሉን ነገር እያወቁ ዳዊት መኰብለሉን እንኳ እልነገሩኝም” እላቸው ፤ ዘብ ጠባቂዎቹ ግን “የእግዚአብሔርን ካህናት እንገድልም” አሉ ። 18 ስለዚህም ሳኦል ዶይቅን “እንተው ግደላቸው” አለው ፤ ዶይቅም ተነሥቶ ሁሉንም ገደለ ፤ በዚያኑ ቀን የፈጃቸው ኤፉድ የሚለብሱ ካህናት ብዛት ሰማኒያ አምስት ነበር ፤ 19 ከዚህም በኋላ ሳኦል የካህናት ከተማ በሆነችው በኖብ የሚኖሩት ሁሉ ወንዶችና ሴቶች ፥ ልጆችና ሕፃናት ፥ የቀንድ ከብቶችና አህዮች ፥ እንዲሁም የበግ መንጋዎች ሁሉ እንዲገደሉ አደረገ ።

20 ነገር ግን አብያታር የሚባል ከአቢሜሌክ ወንዶች ልጆች እንዱ ብቻ አምልጦ በመሄድ ከዳዊት ጋር ተባበረ ፤ 21 ሳኦል የእግዚአብሔርን ካህናት እንዴት እንደፈጀም ለዳዊት ነገረው ፤ 22 ዳዊትም እብያታርን “እኔ በዚያ ቀን ዶይቅን እዚያ በየሁት ጊዜ ሁሉን ነገር ለሳኦል እንደሚነግረው ወውቄ ነበር ፤ ከዚህም የተነሣ ስለ ዘመዶችህ ሁሉ እልቂት እኔ ተጠያቂነት አለብኝ ፤ 23 እንተ ግን ከእኔ ጋር ኑር ፤ አይዞህ አትፍራ ፤ በእርግጥ ሳኦል እንተንም አኔንም ለመግደል ይፈልጋል ፤ ነገር ግን አንተ ከእኔ ጋር በሰላም ትኖራለህ” አለው ።

ምዕራፍ 23

ዳዊት የቀዒላን ከተማ ከጥፋት አዳነ

1 ፍልስጥኤማውያን በቀዒላ ከተማ ላይ እደጋ መጣላቸውንና በቅርቡ የተሰበሰበውንም የእዲሱን መከር እህል ሰርቀው መውሰዳቸውን ዳዊት ሰማ ፤ 2 ስለዚህም ዳዊት “ሄጄ በፍልስጥኤማውያን ላይ አደጋ ልጣልባቸውን?” ሲል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠየቀ ።

እግዚአብሔርም “እዎ በፍልስጥኤማውያን ላይ አደጋ በመጣል ቀዒላን ከጥፋት አድን” ሲል መለሰለት ።

3 ነገር ግን የዳዊት ተከታዮች “በዚህ በይሁዳ ስንኖር የምንፈራው ብዙ ነገር አለ ፤ አሁን ደግሞ ወደ ቀዒላ ሄደን በፍልስጥኤማውያን ሠራዊት ላይ አደጋ ብንጥል የባሰ ችግር ይገጥመናል” አሉት ። 4 ከዚህም የተነሣ ዳዊት እንደገና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠየቀ ፤ እግዚአብሔርም “እኔ በፍልስጥኤማውያን ላይ ድልን ስለማቀዳጅህ ሄደህ በቀዒላ ላይ አደጋ ጣል” አለው ። 5 ስለዚህም ዳዊትና ተከታዮቹ ወደ ቀዒላ ሄደው በፍልስጥኤማውያን ላይ አደጋ ጣሉባቸው ፤ ከእነርሱም ብዙዎቹን ገድለው የከብትና የበግ መንጋዎቻቸውን ዘርፈው ወሰዱ ፤ በዚህም ዐይነት ሁኔታ ዳዊት ከተማይቱን በመታደግ ከጥፋት አዳናት ።

6 የአቢሜሌክ ልጅ አብያታር አምልጦ በቀዒላ ከዳዊት ጋር በተባበረ ጊዜ ወደዚያ የመጣው ኤፉዱን አንደያዘ ነበር ።

7 ለሳኦልም ዳዊት ወደ ቀዒላ መምጣቱ በተነገረው ጊዜ “እግዚአብሔር እርሱን በእጄ ሊጥልልኝ ነው ፤ ዳዊት የግንብ ቅጽርና የተመሸጉ የቅጽር በሮች ወዳሉአት ከተማ በመዝለቁ ራሱን በወጥመድ ውስጥ እስገብቶአል” አለ ። 8 ስለዚህም ሳኦል ወታደሮቹን ለጦርነት ጠርቶ ወደ ቀዒላ በመዝመት ዳዊትንና ተከታዮቹን አንዲከቡ አዘዘ ።

9 ዳዊትም ሳኦል አደጋ ሊጥልበት ማቀዱን በሰማ ጊዜ ካህኑን አብያታርን “ኤፉዱን ይዘህና” አለው ። 10 ከዚህም በኋላ ዳዊት እንዲህ አለ ፥ “የእስራኤል አምላክ የሆንህ እግዚአብሔር ሆይ! እገልጋይህ በሆንኩት በእኔ ስበብ ሳኦል መጥቶ ቀዒላን ለመደምሰስ ማቀዱን ስምቻለሁ ። 11 ታዲያ የቀዒላ ከተማ ነዋሪዎች አኔን ለሳኦል እሳልፈው ይሰጡኝ ይሆን? ሳኦልስ እኔ እንደሰማሁት ወደዚህ መምጣቱ እውነት ነውን? የእስራኤል አምላክ የሆንህ እግዚአብሔር ሆይ! መልስ እንድትስጠኝ አለምንሃለሁ ።”

እግዚአብሔርም “እዎ ሳኦል በእርግጥ ይመጣል” ሲል መለሰለት ።

12 ዳዊትም “የቀዒላ ከተማ ነዋሪዎችስ ተከታዮቼንና አኔን ለሳኦል እሳልፈው ይሰጡን ይሆን?” ሲል እንደገና ጠየቀ ።

እግዚአብሔርም “አዎ አሳልፈው ይሰጡ አችኋል” ሲል መለሰ ።

13 ስለዚህም ዳዊትና ስድስት መቶ የሚሆኑ ተከታዮቹ በሙሉ ወዲያውኑ ቀዒላን ለቀው ለመሄድ ተንቀሳቀሱ ፤ ሳኦልም ዳዊት ከቀዒላ እምልጠ መሄዱን በሰማ ጊዜ የነበረውን ዕቅድ ተወ ።

ዳዊት በኮረብታማው አገር የነበረበት ሁኔታ

14 ዳዊት በዚፍ አጠንብ ባለው ምድረ በዳ ውስጥ በኮረብታማው አገር ተሸሽጎ ኖረ ፤ ሳኦልም እርሱን ለማግኘት ዘወትር ይፈልገው ነበር ፤ እግዚአብሔር ግን ዳዊትን ለሳኦል አሳልፎ አልሰጠውም ፤ 15 ዳዊትም ሳኦል ሊገድለው መምጣቱን ተመለከተ ።

ዳዊት በዚፍ አጠገብ ባለው ምድረ በዳ ውስጥ በሖሬሽ ይገኝ ነበር ፤ 16 ዮናታንም እዚ ያው ድረሰ ወደ ዳዊት ሄዶ እግዚአብሔር በአሰ ተማማኝ ሁኔታ የሚጠብቀው መሆኑን በመግ ስጥ እንዲህ እያለ አበረታታው ፤ 17 “አይዞህ አትፍራ! አባቴ ሳአል በአንተ ላይ ጕዳት ማድ ረስ ከቶ አይችልም ፤ አንተ የእስራኤል ንጉሥ እንደምትሆንና እኔም ከአንተ የምቀጥል ሁሰ ተኛ ማዕርግ እንደሚኖረኝ አባቴ በደንብ ያው ቃል ።” 18 ስለዚህ ሁሰቱም እርሰ በርሳቸው የተቀደሰ የወዳጅነት ቃል ኪዳን አደረጉ ፤ ከዚ ህም በኋላ ዳዊት በሖሬሽ መኖሩን ቀጠለ ፤ ዮና ታንም ወደ ቤቱ ተመልሶ ሄደ ።

19 ከዚፍ ነዋሪዎች አንዳንዶቹ በጊብዓ ወደ ሚገኘው ወደ ሳአል ሄደው እንዲህ አሉ ፥ “ዳዊት በእኛ ግዛት ውስጥ ከይሁዳ ምድረ በዳ በሰተ ደቡብ ባለው በሐኪላ ተራራ ላይ በምትገ ኘው በሖሬሽ ተሸሽጎአል ፤ 20 ንጉሥ ሆይ! አንተ እርሱን ስመያዝ ምን ያህል ፍላጎት እንዳ ስህ እናውቃስን ፤ ስለዚህ ወደ እኛ ግዛት ብት መጣ አኛ እርሱን አንዴት መያዝ እንደምት ችል እናረጋግጥልሃስን ።”

21 ሳአልም አንዲህ ሲል መሰሰላቸው ፥ “ስእኔ ይህን ያህል ቸርነት ሰላደረጋችሁልኝ እግዚአብሔር ይባርካችሁ ፤ 22 አሁንም እንደ ገና ሄዳችሁ አረጋግጡ ፤ ያስበትን ሰፍራ ያየ ውም ማን እንደሆነ መርምራችሁ አግኙ ፤ እኔ እርሱ ዘዴኛ መሆኑን ስምቻለሁ ፤ 23 የሚሸሸግ ባቸውን ሰፍራዎች በትክክል አግኙ ፤ ያገኛችሁ ትንም ማስረጃ ወዲያው ይዛችሁልኝ ኑ ፤ ከዚ ያም በኋላ እኔ አብራአችሁ እሄዳለሁ ፤ አሁንም በዚያው ግዛት ውስጥ የሚኖር ከሆነ መላውን የይሁዳ ግዛት ማሰስ ቢያስፈልገኝም እንኳ እር ሱን በማደን እይዘዋስሁ ።”

24 ስስዚህም እነርሱ ሳአል ከመሄዱ በፊት ወደ ዚፍ ተመስሰ ፤ በዚህን ጊዜ ዳዊትና ተከ ታዮቹ ከይሁዳ ምድረ በዳ ብሰተ ደቡብ በኩል በሚገኘው ማንም ሰው የማይኖርበት ሸለቆ በሆ ነው በማዖን በረሓ ነበሩ ፤ 25 ሳአልና ወታደሮ ቹም ዳዊትን ስማሳደድ ወጥተው ሄዱ ፤ ዳዊ ትም ይህን ስላወቀ በማዖን ምድረበዳ አስት ወደበዛበት አንድ ኮረብታ አልፎ በዚያ ተቀ መጠ ፤ ሳአልም ይህን በሰማ ጊዜ ዳዊትን የመከ ታተል ተግባሩን ቀጠለ ፤ 26 ሳአልና ወታደሮቹ ከኮረብታው በአንድ በኩል ሲሆኑ ፥ ዳዊትና ተከታዮቹም ከኮረብታው በሌላ በኩል ነበሩ ፤ ዳዊትና ተከታዮቹም ሊማርኩአቸው ከተቃረ ቡት ከሳአልና ከወታደሮቹ ስማምለጥ በመጣ ደፍ ላይ ነበሩ ። 27 ይህ በዚህ እንዳለ ወዲያ ውኑ አንድ መልእክተኛ ደርሶ ሳአልን “አሁ ኑኑ ተመልሰህ ና ፤ ምክንያቱም ፍልስጥኤማው ያን አገሪቱን በመውረር ላይ ናቸው” አለው ። 28 ስስዚህም ሳአል ዳዊትን የማሳደድ ተግባሩን አቁሞ ፍልስጥኤማውያንን ስመውጋት ሄደ ፤ ያም ቦታ “የመስያየት ኮረብታ” ተብሎ የተጠ ራበት ምክንያት ይኸው ነው ። 29 ዳዊትም ከዚያ በመነሣት ተሸሽጎ ወደቆየበት ዔንገዲ ተብሎ ወደሚጠራው በረሓማ ሰፍራ ሄደ ።

ምዕራፍ 24

ዳዊት የሳአልን ሕይወት አተረፈ

1 ሳአል ፍልስጥኤማውያንን ወግቶ ከተመስሰ በኋላ ዳዊት በዔንገዲ አጠገብ በሚገኘው ምድረ በዳ የሚገኝ መሆኑን ሰማ ፤ 2 ስስዚህም ሳአል በእስራኤል ምርጥ የሆኑትን ሦሰት ሺ ወታደሮች በማሰከተል “የሜዳ ፍየሎች አስት” ተብሎ በሚጠራው ሰፍራ በሰተ ምሥራቅ በኩል ዳዊ ትን አሳድዶ ስመያዝ ሄደ ፤ 3 በመንገድ ዳር ባሉት የበጎች ማደሪያዎች አቅራቢያ ወደሚገ ኘው ወድ አንድ ዋሻ ወገቡን ሊሞክር ወደ ውስጥ ገባ ፤ በዚያም እርሱ ከተቀመጠበት ወደ ውስጥ ገባ ብሎ ዳዊትና ተከታዮቹ ተደብቀው የሚኖሩበት ክፍል ነበር ፤ 4 ተከታዮቹም ዳዊትን “እነሆ ጥሩ አጋጣሚ ሆኖልሃል ፤ እግዚአብሔር ጠሳትህን በእጅህ እንደሚጥልልህ ነግሮሃል ፤ እነሆ አሁን በጠሳትህ ላይ የፈለግኸውን ማድረግ ትችላስህ” አሉት ፤ ዳዊትም በልቡ አየተሰበ በመቅረብ ሳአል ሳያውቅ ከልብሱ ሜፍ ላይ ቁርጦ መሰደ ፤ 5 ነገር ግን ዳዊትን የኅሊና ወቀሳ አስጨነቀው ፤ 6 ስስዚህም ተከታዮቹን “አግዚአ ብሔር ቀብቶ ባነገሠው በጌታዬ ላይ እጀን ከማን ሣት እግዚአብሔር ይጠብቀኝ ፤ እኔ በእርሱ ላይ ምንም ዐይነት ጕዳት ሳደርስበት አይገባኝም ፤ ምክንያቱም እርሱ እግዚአብሔር የመረጠው ንጉሥ ነው” አላቸው ። 7 በዚህም አባባሱ በሳ አል ላይ አደጋ እንዳይጥሱበት ዳዊት ተከታዮ ቹን አሳመናቸው ።

ሳአልም ከዚያ በመነሣት ከዋሻው ወጥቶ ሄደ ፤ 8 ዳዊትም ከዚያ ወጥቶ ሳአልን በመከተል “ንጉሥ ሆይ!” አስው ፤ ሳአልም መስሰ ብሎ ዙሪያውን ሲመስከት ዳዊት በመሬት ላይ ስጥ ብሎ እጅ ነሣውና እንዲህ አስው ፥ 9 “እኔ አን ተን ጕዳት አንደማደርስብህ አስመስለው የሚነግ ሩህን ሰዎች ቃል ሰስምን ትሰማስህ? 10 ዛሬ በዚህ ሰዓት በዋሻው ውስጥ ሳለህ እግዚአብሔር በእጄ ጥሎህ እንደነበር አንተ ራስህ ማየት ትችላ ስህ ፤ ከተከታዮቼም አንዳንዶቹ እንድገድልህ ነግረውኝ ነበር ፤ ነገር ግን እኔ ሰአንተ አዝንልህ ምንም ዐይነት ጕዳት እንደማሳደርስብህ ነገርሁ አቸው ፤ ምክንያቱም አንተ እግዚአብሔር የመረ ጠህ ንጉሥ ነህ ፤ 11 አባቴ ሆይ! እነሆ ከካባህ ላይ ቁርጡ የያዝሁትን ጨርቅ ተመልከት!

23:18 ፡- 1ሳሙ. 18:3 ። 23:19 ፡- መዝ. 54 ። 24:3 ፡- መዝ. 57 ፤ መዝ. 142 ። 24:6 ፡- 1ሳሙ. 26:11 ።

ታዳያ እኮ ልገድልህ እችል ነበር፤ ነገር ግን ይህን በማድረግ ፈንታ የልብስህን ጫፍ ቈረጥሁ፤ በእንተ ላይ ስማመፅም ሆነ ወይም በእንተ ላይ ጕዳት ላደርስብህ አለመፈለጌን በዚህ መረዳት ትችላለህ፤ አንተ ግን ምንም ነገር ሳላደርግና ሳልበድልህ እኔን ሰመግደል ትከታተለኛ ሰህ፤ 12እንግዲህ ሰሕተተኛው ማንኛችን እንደ ሆንን በመሰየት እግዚአብሔር ፍርዱን ይስጥ፤ እኔ በእንተ ላይ ምንም ዐይነት ጕዳት ላደርስብህ ስለማልፈልግ በእኔ ላይ ስሰምታደርገው ከፉ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ራሱ ይቅጣህ። 13'ከፉ ነገርን የሚያደርጉ ክፉ ሰዎች ብቻ ናቸው' የተባለውን ጥንታዊ እነ,ገር ታውቃለህ፤ ስለዚህም እኔ በእንተ ላይ ጕዳት ላደርስብህ አልፈልግም። 14እነሆ የእስራኤል ንጉሥ ማንን ሰመግደል እን ደሚዋር ተመልከት! ማንንም እንደሚያሳድድ አስተውል! የሞተ ውሻን ወይስ ቁንጫን? ማንን እንደሚያሳድድ ተመልከት! 15እግዚአብሔር ይፍረድ፤ ከሁሰታችንም ስሕተተኛው ማን እንደ ሆነ እርሱ ይወስን፤ እግዚአብሔር ይህን ጕዳይ ተመልክቶ ይከላከልልኝ፤ ከአንተም እጅ ያድ ነኝ።"

16ዳዊትም ይህን ተናግሮ እንደጨረሰ ሳአል "ልጄ ዳዊት ሆይ! በእውነት ይህ የአንተ ድምፅ ነውን?" ብሎ ማልቀስ ጀመረ፤ 17ከዚ ያም በኋላ ዳዊትን እንዲህ አሰው፥ "አንተ እውነተኛ ስው ነህ፤ እኔ ግን ስሕተተኛ ነኝ፤ ይህን የመሰለ በደል ስፈጽምብህ አንተ ሰእኔ ቸርነት አድርገህልኛል፤ 18ለእኔ በጎ አድራጊ መሆንከንም ዛሬ አስመስከረሃል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በእጅህ ቢጥሰኝም እንኳ አንተ አልገደልኸኝም፤ 19ጠላት በእጁ ገብቶለት ጕዳት ሳያደርስበት የሚሰቀው ስው ከቶ የት ይገኛል? ዛሬ ሰእኔ ስላደረግኸው መልካም ነገር እግዚአብሔር ይባርክህ! 20እነሆ አንተ የእሰራኤል ንጉሥ እንደምትሆንና የእስራኤ ልም መንግሥት በእንተ እገዛህ ሥር ጸንቶ እን ደሚኖር ዛሬ አረጋግጫለሁ። 21አንግዲህ ስሜና የቤተሰቤ ስም ተደምስሶ እንዳይረሳ ሰማ ድረግና የዘሮቼንም ሕይወት ከጥፋት ሰማትረፍ በእግዚአብሔር ስም ቃል ግባልኝ።" 22ዳዊ ትም ይህን እንደሚያደርግ ቃል ገባለት።

ከዚህ በኋላም ሳአል ወደ ቤቱ ተመልሶ ሄደ፤ ዳዊትና ተከታዮቹም ወደሚሸሸጉበት ስፍራ ተመለሱ።

ምዕራፍ 25

የሳሙኤል መሞት

1ሳሙኤል ሞተ፤ መላው እስራኤላውያንም በአንድነት መጥተው እሰቀበሩት፤ ከዚያም በኋላ በራማ በሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ቀበሩት።

ዳዊትና አቢጋይል

ከዚያም በኋላ ዳዊት ወደ ፋራን ምድረ በዳ ሄደ፤ 2-3በዚያም ቤተሰቡ ከካሌብ ጐሳ የሆነ ናባል ተብሎ የሚጠራ አንድ ስው ነበረ፤ እር ሱም የማያን ተወላጅ ሲሆን በቀርሜሎስ ከተማ አጠገብ የእርሻ መሬት ነበረው፤ ታላቅ ባለጸጋ ከመሆኑም የተነሣ ሦስት ሺ በጎችና አንድ ሺ ፍየሎች ነበሩት፤ ሚስቱ አቢጋይልም እጅግ የተዋበች አስተዋይ ሴት ስትሆን እርሱ ግን መልካም ጠባይ የጐደለው ባለጌ ስው ነበር።

ናባል በቀርሜሎስ በጎቹን ያሸልት ነበር፤ 4ዳዊትም በበረሓ ሳለ ይህንኑ ሰማ፤ 5ስለዚህም ወሥር መልእክተኞችን መርጦ ወደ ቀርሜሎሰ እንዲሄዱና ናባልን እግኝተው የእርሱን ሰላምታ እንዲያቀርቡለት አዘዛቸው፤ 6ሰናባልም ይነግ ሩት ዘንድ እንዲህ የሚል መመሪያ ሰጣቸው፥ "ዳዊት ለአንተና ሰቤተሰብህ እንዲሁም የአንተ ሰሆነው ሁሉ መልካም ምኞቱን በመግለጥ የመ ጻጅነት ስላምታ ልኮልሃል፤ 7በጎችህንም እንደ ምታሸልት ስምቶአል፤ እረኞችህ ከእኛ ጋር በነበሩበት ጊዜም ሁሉ ምንም ዐይነት ጕዳት እንዳላደረስንባቸውም እንድታውቅ ይፈልጋል፤ በቀርሜሎስ በነበሩበት ጊዜ ሁሉ ከእንስሳቶቻ ቸው አንድ እንኳ ተሰርቆ አልተወሰደባቸ ውም፤ 8እነርሱንም ብትጠይቃቸው ይህንኑ ይነግሩሃል፤ እነሆ ዛሬ እኛ የደስታ ግብዣ በሚደረግበት ቀን መጥተናል፤ እኛንም በመል ካም ሁኔታ ትቀበሰን ዘንድ ዳዊት ጠይቆአል፤ ስለዚህ ሰእኛ ሰእገልጋዮችህና ሰወዳጅህ ሰዳዊት ስትል የሚቻልህን ሰጠታ አድርግልን።"

9የዳዊት ሰዎችም ይህንኑ መልእክት በዳ ዊት ስም ሰናባል አስረክበው ይጠባበቁ ጀመር፤ 10ናባልም በመጨረሻ "ዳዊት ላላችሁኝ! እረ ሰመሆኑ እርሱ ማን ነው? እኔ ስሰ እርሱ ሰም ቹም አላውቅም፤ እነሆ በአሁኑ ጊዜ አገሪቱ ከጌቶቻቸው በኰበሰ አገልጋዮች ተሞልታ ለች! 11ስለዚህ እንጀራዬንና ውሃዬን እንዲ ሁም ሰበጎች ሸላቾቼ ያረድኋቸውን እንስሳት አንሥቼ ከወዴት እንደመጡ ሰማላውቃቸው ሰዎች የምሰጥበት ምክንያት የለም" አለ።

12መልእክተኞቹም ተመልሰው መጥተው ናባል ያሰውን ሁሉ ሰዳዊት ነገሩት፤ 13ዳዊ ትም "በሉ ሰይፋችሁን ታጠቁ!" የሚል ትእ ዛዝ ስጠ፤ እነርሱም እንደታዘዙት አደረጉ፤ ዳዊትም ራሱ ሰይፉን ታጠቀ፤ ጓዝ የሚጠብቁ ሁለት መቶ ሰዎች ወደ ኋላ ትቶ አራት መቶ ሰዎች በማሰከተል ገሥግሦ ሰመሄድ ተነሣ። 14ከናባል አገልጋዮች አንዱም የናባልን ሚስት አቢጋይልን እንዲህ አላት፥ "ይህን ታሪክ ስም ተሻልን? ዳዊት ካለበት በረሓ መልእክተኞችን

ከሰላምታ ጋር ወደ ጌታችን ልኮ ነበር ፤ እርሱ ግን በለድብ አዋረዳቸው ፤ 15 ታዲያ እኮ እነርሱ ለእኛ በጎ አድራጊዎች ነበሩ ፤ ምንም ችግር እልፈጠሩብንም ፤ ከእነርሱ ጋር በዱር በነበርን በት ጊዜ ሁሉ ከእንስሶቻችን አንድ እንኳ ተሰር ቆብን አያውቅም ፤ 16 መንጋዎቻችንን እየጠበ ቅን በቆየንበት ጊዜ ሁሉ ቀንም ሆነ በሌሊት እነርሱ ለእኛ ዘበኞች ነበሩ ። 17 እባክሽን ይህን ጉዳይ አስበ በት ና ማድረግ ስለሚገባሽ ነገር ወስኚ ፤ አለበለዚያ ለጌታችንና ለቤተሰቡ ሁሉ እደገኛ ጥፋት ይሆናል ፤ እርሱ እንደሆን የማን ንም ምክር የማይሰማ አአምሮቢስ ሰው ነው ።''

18 አቢጋይልም በፍጥነት ሁለት መቶ እን ጀራ ፥ ወይን ጠጅ የተሞላበት ሁለት የወይን አቁማዳ ፥ እምስት የተጠበሰ በጎች ፥ ፀሥራ ስባት ኪሎ የተጠበሰ እሸት ፥ እንድ መቶ ዘለላ ወይንና ሁለት መቶ የበለስ ፍሬ ጥፍጥፍ በአን ድነት ሰብስባ በአህዮች ላይ ጫነች ። 19 ከዚህም በኋላ አገልጋዮቹን “ቀድማችሁኝ ሂዱ ፤ እኔም እከተላችኋለሁ” አለቻቸው ፤ ለባልዋ ግን የነገረ ችው ቃል አልነበረም ።

20 እርስዋም በአህያ ላይ ተቀምጣ እየጋለበች በኮረብታው ጥግ በሚገኘው ጠመዝማዛ መንገድ ስትወርድ በድንገት ዳዊትና ተከታዮቹ ወደ እርስዋ ሲመጡ አገኘቻቸው ፤ 21 ዳዊትም በልቡ እንዲህ እያለ ያሰብ ነበር ፥ “ያዚያን የማ ይረባ ሰው ሀብት በዚህ በረሓ ለምን ስጠብቅ ቆየሁ? የእርሱ ከሆነው ንብረት ምንም ነገር ተሰርቆበት አያውቅም ፤ ታዲያ እኔ ስላደረግሁ ሰት መልካም ነገር እርሱ የሚከፍለኝ ወሮታ ይህ ሆኖ ቀረ! 22 ከመንጋቱ በፊት የእርሱ የሆ ኑትን ወንዶች ሁሉ አንድ እንኳ ሳላስቀር በሙሉ ሳልገድል ብቀር እግዚአብሔር እኔን በሞት ይቅጣኝ ።''

23 አቢጋይልም ዳዊትን ባየችው ጊዜ በፍጥ ነት ከአህያዋ ወርዳ በዳዊት ጫማ እጠነብ መሬት ላይ ለዋ ብላ እጅ በመንሣት እንዲህ አለችው ፥ 24 ''ጌታዬ ሆይ! እባክህ እድምጠኝ! በደሱን እኔ ልሸከም ፤ 25 የናባልን ጉዳይ ከቁም ነገር አታግባው! እርሱ ምንም የማይረባ ሰው ነው! እርሱ ልክ እንደስሙ አጠራር ስንፍና የሰፈነበት ሰው ነው ፤ ጌታዬ! የእንተ አገልጋ ዮች በመጡ ጊዜ እኔ በዚያ አልነበርኩም ፤ 26 የበቀል እርምጃ በመውሰድ ጠላቶችህን እንዳ ትገድል የጠበቀህ ራሱ እግዚአብሔር ነው ፤ እነሆ እኔ አሁን በሕያው እግዚአብሔር ስም እምልልሃለሁ ፤ ጠላቶችህና እንተን ለመጉዳት የሚፈልጉ ሁሉ እንደ ናባል ቅጣታቸውን ይቀ በሉ ፤ 27 ጌታዬ ሆይ! እባክህ ይህን እኔ ያመጣ ሁልህን ስጦታ ተቀብለህ ለተከታዮችህ አድላ ቸው ። 28 ጌታዬ! ስላደረግሁ-ትም በደል እባክህ ይቅር በለኝ ፤ እግዚአብሔር አንተንና ዘሮችህን ያነግሣል ፤ ምክንያቱም እንተ የእግዚአብሔርን ጦርነት እየተዋጋህ ነው ፤ በምትኖርበትም ዘመን ሁሉ ምንም ወይነት ክፋ ነገር ማድረግን አትፈልግም ። 29 ማንም ሰው በእንተ ላይ አደጋ ጥሎ ሊገድልህ ቢፈልግ አንድ ሰው ውድ የሆነ ሀብቱን እንደሚጠብቅ እምላክህ እግዚአብሔር እንተን በሰላም ይጠብቅሃል ፤ ስለ ጠላቶችህም የሆነ አንደሆን አንድ ሰው ድንጋዩን ከወንጭፍ እንደሚያስፈነጥር እግዚአብሔር ራሱ አሸቀን ጥሮ ይጥላቸዋል ። 30 እግዚአብሔር በሰጠህ ተሰፋ መሠረት ፥ መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ ባደረገልህና በእስራኤልም ላይ በሚያነግሥህ ጊዜ ፥ 31 ምንም ወይነት ጸጸት ወይም የኅሊና ወቀሳ አይደርስብህም ፤ ምክንያቱም ጌታዬ ሆይ! ያለ ምክንያት ወይም የበቀል እርምጃ ለመውሰድ ብለህ የገደልክው ሰው የለም ፤ ስለ ዚህ ጌታዬ ሆይ! እግዚአብሔር በሚባርክህ ጊዜ እኔንም እትርሳኝ ።''

32 ዳዊትም እንዲህ አላት ፥ “ከእኔ ጋር እን ድትገናኚ አንቺን ወደ እኔ የላከ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን! 33 ስለመል ካም አሳብሽ ፥ እንዲሁም ዛሬ የማይ ወንጀል ከመፈጸምና የራሴንም የበቀል እርምጃ ከመው ሰድ እንድቈጠብ ስላደረግሽኝ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ። 34 በአንቺ ላይ ጉዳት ከማድረስ እግዚአብሔር ጠብቆኛል ፤ ፈጥነሽ ወደ እኔ ባትመጪ ኖሮ ግን ከናባል ወንዶች አንድ እንኳ ሳላስተርፍ ከንጋት በፊት ሁሉንም እገ ድል እንደ ነበረ በሕያው እግዚአብሔር ስም ምያለሁ!” 35 ከዚያም በኋላ ዳዊት ያመጣችለ ትን ስጦታ ተቀብሎ “ወደ ቤትሽ ተመልሰሽ ሂጂ ፤ አትጨነቂ ፥ የምትፈጊውንም ሁሉ አደ ርጋለሁ” አላት ።

36 አቢጋይልም እንደ ቤተ መንግሥት ግብር ታላቅ ግብዣ በሚድረግ ላይ ወደነበረው ወደ ናባል ተመልሳ ሄደች ፤ እርሱም ሰክሮ በደስታ ይፈነድቅ ስለነበር እስከ ማግሥቱ ጠዋት ድረስ ምንም ቃል አልነገረችውም ፤ 37 ስካሩም ከበረ ደለት በኋላ ሁሉንም ነገር አስረዳችው ፤ ልቡም በድንጋጤ ስለተመታ ተዝለፍልፎ ፍጹም ሽባ ሆነ ፤ 38 ከዐሥር ቀናት በኋላም እግዚአብሔር ስለቀሠፈው ናባል ሞተ ።

39 ዳዊትም የናባልን መሞት በሰማ ጊዜ “እኔን በመስደቡ እግዚአብሔር ናባልን ስለተበ ቀለውና እኔንም ከስሕተት ስለጠበቀኝ እግዚአ ብሔር ይመስገን! እርሱ ናባልን ስለ ክፉ ሥራው ቀጥቶታል” አለ ።

ከዚህም በኋላ ዳዊት ወደ አቢጋይል መልእ ክተኛ ልኮ ሊያገባት መፈለጉን ገለጠላት ። 40 አገልጋዮቹም እርስዋ ወዳለችበት ወደ ቀር ሜሎስ ሄደው “ሊያገባሽ ስለፈቀደ ወደ ዳዊት ልንወስድሽ መጥተናል” አሉአት ።

41 አቢጋይልም ወደ መሬት ሰጥ ብላ እጅ
በመንሣት “እኔ ለእርሱ ገረዱ ነኝ፤ የአገልጋዮ
ችንም እግር ለማጠብ ዝግጁ ነኝ” አለች።
42 ፈጥናም ተነሥታ በአህያዋ ላይ ተቀመጠች፤
በእምስት ገረዶችዋም ታጅባ ከዳዊት አገልጋ
ዮች ጋር በመሄድ ሚስቱ ሆነች።

43 ዳዊት ከዚህ በፊት የኢይዝራኤል ተወላጅ
የሆነችውን አሒኖዓም አግብቶ ነበር፤ አሁን
ደግሞ አቢጋይልን አገባ፤ 44 ይህ በዚህ እንዳለ
ሳኦል የዳዊት ሚስት የነበረችውን ልጁን ሚካ
ልን የጋሊም ተወላጅ ለሆነው ለላሺሽ ልጅ
ለፓልጢ ዳረለት።

ምዕራፍ 26

ዳዊት እንደገና የሳኦልን ሕይወት አተረፈ

1 ጥቂት ሰዎች ከዚፍ ተነሥተው ሳኦል ወዳ
ለበት ወደ ጊብዓ በመምጣት “እነሆ ዳዊት ከይ
ሁዳ ምድረበዳ ዳርቻ በተለይ ሐኪላ ተብሎ
በሚጠራው ተራራ ላይ ተደብቆ ይገኛል”
ብለው ነገሩት። 2 ሳኦልም በፍጥነት ተነሥቶ
በእስራኤል ምርጥ የሆኑትን ሦስት ሺ ወታደ
ሮች በማለከተል ዳዊትን ለመፈለግ ወደ ዚፍ
ምድረ በዳ ሄደ። 3 ዳዊትም በሐኪላ ተራራ ላይ
በሚገኘው መንገድ አጠገብ ሰፍሮ ነበር፤ ዳዊ
ትም በምድረ በዳ ሳለ ሳኦል እርሱን ለመፈለግ
መምጣቱን በሰማ ጊዜ፥ 4 መልእክተኞች ልኮ
በማሰለል ሳኦል በእርግጥ እዚያ መድረሱን
ዐወቀ። 5 ከዚያም በፍጥነት ተነሥቶ በመሄድ
ሳኦልና የሠራዊቱ አዛዥ የኔር ልጅ አበኔር የሚ
ተኙበትን ቦታ አረጋገጠ፤ ሳኦል በሰፈሩ መካ
ከል ተኝቶ ሳለ ወታደሮቹ በዙሪያው ይገኙ
ነበር።

6 ከዚህም በኋላ ዳዊት ሒታዊውን አሒሜሌ
ክንና ከጸሩያ ልጆች የኢዮአብን ወንድም አቢሻ
ይን “ከእናንተ ከውስታችሁ ከእኔ ጋር አብሮ
ወደ ሳኦል ሰፈር የሚሄድ ማን ነው?” ሲል
ጠየቃቸው።

አቢሻይም “እኔ እሄዳለሁ” ሲል መለሰ።

7 ስለዚህም በዚያው ምሽት ዳዊትና አቢሻይ
ወደ ሳኦል ሰፈር ገቡ፤ ሳኦልንም በሰፈሩ መካ
ከል ተኝቶ አገኙት፤ ጦሩም በራሱጌው በኩል
መሬት ላይ ተተክሎ ነበር፤ አበኔርና ወታደሮ
ቹም በዙሪያው ተኝተዋል። 8 አቢሻይም ዳዊ
ትን “እግዚአብሔር በዛሬው ምሽት ጠላትህን
በእጅህ ጥሎልሃል፤ ስለዚህ አሁን የገዛ ጦሩን
አንሥቼ ልውጋውና ከመሬት ጋር ላጣብቀው፤
አንድ ምት ብቻ ስለሚበቃው ድጋሚ አያስፈል
ገውም” አለው።

9 ዳዊት ግን “ጉዳት ልታደርሰበት አይገባ
ም! ቀብቶ ያነገሠውን ንጉሥ የሚጐዳ ሰዎ
ችን እግዚአብሔር ራሱ ይቀጣል፤ 10 በሕያው
እግዚአብሔር ስም እምልልሃለሁ፤ እግዚአብ
ሔር ራሱ ላአልን ይገድለዋል፤ የሚሞትበት
ጊዜ ደርሶ፥ አሰበሰዚያም በጦርነት መሞቱ አይ
ቀርም፤ 11 እግዚአብሔር ቀብቶ ባነገሠው
ንጉሥ ላይ ጉዳት የማድረስ ተግባርስ ከእኔ
ይራቅ፤ ይልቅስ ጦሩንና ውሃ መቅጃውን ይዘን
በት እንሂድ” አለው። 12 ስለዚህም ዳዊት ጦሩ
ንና ውሃ መቅጃውን ከሳኦል ራስጌ አንሥቶ እር
ሱና አቢሻይ ከዚያ ሄዱ፤ ይህ ሁሉ ሲሆን
ማንም ያየና ነቅቶም ያወቀ አልነበረም። ምክን
ያቱም እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ከባድ እንቅ
ልፍ ልኮባቸው ስለነበር ተጫጭኖአቸው ተኝተ
ዋል።

13 ከዚህ በኋላ ዳዊት ነሸሰቆው ባሻገር ወደ
ሚገኘው ጠሳቶቹ ሲደርሱበት ወደማይችሉበት
ወደ ኮረብታው ጫፍ ወጣ፤ 14 ድምፁንም ከፍ
አድርጎ ወደ ሳኦል ወታደሮችና ወደ አበኔር
ዘመጮኸ “አበኔር! ትሰማኛለህን?” አለው።

አበኔርም “እንዲህ እየጮኸ ንጉሡን እንቅ
ልፍ የሚነሣ ማነ ነው?” አለ።

15 ዳዊትም “አበኔር! አንተ በእስራኤል የታ
ወቅህ ታላቅ ሰው አይደለህም እንዴ? ታዲያ
ጌታህን ንጉሡን በደንብ የማትጠብቀው ለሰምን
ድን ነው? እነሆ ከእኛ አንድ ሰው ጌታህን ለመ
ግደል ወደ ሰፈር ገብቶ ነበር፤ 16 በሥራህ ላይ
ታማኝ ሆነህ አልተገኘህም፤ አበኔር! እኔ በሕ
ያው እግዚአብሔር ስም እምላለሁ፥ ሁላችሁም
ሞት ይገባችኋል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር
ቀብቶ ያነገሠውን ጌታችሁን ንጉሡን መጠበቅ
አልቻላችሁም፤ በራስጌው የነበረው የንጉሡ
ጦርና እንዲሁም የውሃ መቅጃው አሁን የት
እንዳለ አሰቲ ተመልከት!” አለው።

17 ሳኦልም የዳዊትን ድምፅ ሰይቶ ስላወቀ
“ዳዊት ልጄ ሆይ! በእርግጥ ይህ ቃል የአንተ
ነውን?” ሲል ጠየቀ።

ዳዊትም እንዲህ ሲል መለሰ፥ “አዎ ንጉሥ
ሆይ! 18 ታዲያ አንተ ጌታዬ እኔን አገልጋይህን
ለሰምን ታሳድደኛለህ? ያደረግሁት ነገር ምን
ድን ነው? ምንስ ወንጀል ፈጸምሁ? 19 ንጉሥ
ሆይ! የምልህን አድምጠኝ! አንተን በእኔ ላይ
ያነሣሣህ እግዚአብሔር ቢሆን ኖሮ መሥዋዕት
በማቅረብ ቍጣውን እንዲመልስ ማድረግ በተ
ቻለ ነበር፤ ነገር ግን ይህን ያደረጉት ሰዎች
ከሆኑ የእግዚአብሔር መርገም በእነርሱ ላይ
ይውረድ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ከሚመስ
ከባት ምድር አስወጥተው ባዕዳን አማልክት
ወደሚመለኩበት አገር እንድሰደድ አድርገው
ኛል። 20 ከእግዚአብሔር ርቄ በባዕድ አገር እን
ድገደል አታድርግ፤ ይህን ያህል ታላቅ የሆነ
የእስራኤል ንጉሥ እንደ ቁንጫ የምቈጠረውን

25:44 :- 2ሳሙ. 3:14-16። 26:1 :- መዝ. 54። 26:11 :- 1ሳሙ. 24:6።

እኔን ስለምን ያሳድዳል? እንደ በረሓ ቆቅ የሚ
ያድነኝስ ስለምንድን ነው?”
21 ሳኦልም “በእርግጥ ተሳስቻለሁ፤ ልጄ
ዳዊት ሆይ! ተመልሰህ ወደ እኔ ና፤ ዳግመኛ
ልጐዳህ ከቶ እልፈልግም፤ ምክንያቱም በዛሬ
ይቱ ሌሊት ሕይወቴን አትርፈሃል፤ እኔ እንደ
ሞኝ ሆኜአለሁ፤ ከባድ የሆነ ስሕተትም ፈጽሜ
አለሁ!” ሲል መለሰ።
22 ዳዊትም እንዲህ ሲል መለሰ፥ “ንጉሥ
ሆይ! እነሆ ጦርህን ከመታደሮችህ አንድ ሰው
መጥቶ ይውሰድ። 23 ታማኞች ለሆኑ ለደጋግ
ስዎች የመልካም ሥራቸውን ዋጋ የሚሰጥ እግ
ዚአብሔር ነው፤ እነሆ ዛሬ እግዚአብሔር አን
ተን በእጄ ጥሎልኝ ነበር፤ እኔ ግን እግዚአብ
ሔር መርጦ ያነገሠህን አንተን ልጐዳ አልፈለግ
ሁም። 24 ዛሬ እኔ የአንተን ሕይወት እንዳከበ
ርሁ እግዚአብሔር እኔንም እንደዚሁ ከመከራ
በማውጣት ይጠብቀኝ።”
25 ሳኦልም ዳዊትን “ልጄ ሆይ! እግዚአብ
ሔር ይባርከህ፤ የምትሠራው ሁሉ ይከናወን
ልህ!” አለው።
ስለዚህም ዳዊት ወደ ፈለገበት ቦታ ሄደ፤
ሳኦልም ወደ ቤቱ ተመለሰ።

ምዕራፍ 27

ዳዊት በፍልስጥኤማውያን መካከል

1 ዳዊት ዘልቡ እንዲህ ሲል አሰበ፥ “ከእነ
ዚህ ዕለታት በአንዱ ሳኦል እኔን ይገድለኛል፤
እንግዲህ ለእኔ የሚበጀኝ ነገር አምልጩ ወደ
ፍልስጥኤም መሄድ ነው፤ ከዚያም በኋላ ሳኦል
በእስራኤል ምድር እኔን መፈለጉን ስለሚተው
በሰላም መኖር እችላለሁ።” 2 ስለዚህም ዳዊትና
ስድስት መቶ ተከታዮቹ ወዲያውኑ ተነሥተው
የጋት ንጉሥ ወደሆነው ወደ ማዖክ ልጅ ወደ
አኪሽ ሄዱ፤ 3 ዳዊትና ተከታዮቹም ከቤተሰቦቻ
ቸው ጋር በጋት ተቀመጡ፤ ከዳዊትም ጋር
ሁለቱ ሚስቶቹ አብረው ነበሩ፤ እነርሱም የኢ
ይዝራኤል ተወላጅ የሆነችው አሒኖዓምና የቀ
ርሜሎሱ ተወላጅ ናባል አግብቶአት የነበረው
አቢጋይል ነበሩ፤ 4 ሳኦልም ዳዊት ወደ ጋት
ሸሽቶ መሄዱን በሰማ ጊዜ እርሱን ፈልጎ ሰማግ
ኘት ያደርገው የነበረውን ሙከራ ሁሉ አቆመ።
5 ዳዊትም ንጉሥ አኪሽን “የምትወደኝ ከሆ
ንህ በእንድ ትንሽ ከተማ እንድኖር ፍቀድልኝ፤
ጌታዬ! እኔ ሰመናገሻ ከተማ ከእንተ ጋር
መኖር አይገባኝም አለው።” 6 ስለዚህም አኪሽ
የጺቅላግን ከተማ ለዳዊት ሰጠው፤ በዚህም
ምክንያት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጺቅላግ የይሁዳ
ነገሥታት ይዞታ እንደሆነች ቀረች። 7 ሰዚህ
ወይነት ዳዊት በፍልስጥኤም ሀሥራ ስድስት
ወር ተቀመጠ።

8 በዚያን ጊዜ ውስጥ ዳዊትና ተከታዮቹ
በዚያ ግዛት ለረዥም ዘመን ከኖሩት ከጌሹር፥
ከጊርዚና ከዐማሌቅ ሕዝብ ጋር ይዋጉ ነበር፤
ዳዊት ወደ ግብጽ እስከሚያወርደው ሹር
ተብሎ እስከሚጠራው ስፍራ ድረስ በመዝመት
ምድራቸውን ወረረ፤ 9 ወንዶችንም ሴቶችንም
ሁሉ እየገደለ፥ በጎችን የቀንድ ከብቶችን፥ አህ
ዮችን፥ ግመሎችንና ልብሱንም ሁሉ ይወስድ
ነበር፤ ከዚያም በኋላ ዳዊት ወደ አኪሽ
ሲመጣ፥ 10 አኪሽ “በዚህ ጊዜ ወረራ ያደረጋች
ሁት በየት በኩል ነው” ብሎ ሲጠይቀው
ዳዊት “እኛ የዘመትነው ከይሁዳ በስተ ደቡብ
ባለው ክፍል፥ እንደገናም በይራሕመኤል ነገድ
ግዛትና ቄናውያን በሚኖሩበት ግዛት ነው”
እያለ ይመልስለት ነበር። 11 በዚህ ሀይነት
ሁኔታ ዳዊት አደጋ የጣለባቸውን ወንዶቹንም
ሴቶቹንም ይገድል ስለነበር እርሱና ተከታዮቹ
ያደረጉትን ሁሉ ወደ ጋት ሄዶ የሚነግርበት
ማንም አልነበረም፤ ዳዊት በፍልስጥኤም በኖረ
በት ጊዜ ሁሉ ይህን ማድረጉ የተለመደ ነበር።
12 አኪሽ ግን ዳዊትን ስለሚተማመንበት በልቡ
“በወገኖቹ በእስራኤል ሕዝብ ዘንድ የተጠላ
ስለሆነ በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ያገለግለኛል”
በማለት ያስብ ነበር።

ምዕራፍ 28

1 ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፍልስጥኤማውያን እስ
ራኤልን ለመውጋት የጦር ሠራዊታቸውን ሰበ
ሰቡ፤ አኪሽም ዳዊትን “አንተና ተከታዮችህ
ከእኔ ጐን ተሰልፋችሁ መዋጋት እንደሚገባ
ችሁ በእርግጥ ታውቅ የለምን?” አለው።
2 ዳዊትም “እንዴታ! እኔ አገልጋይህ ነኝ፤
የማደርገውንም አንተ ራስህ ማየት ትችላለህ”
ሲል መለሰለት።
አኪሽም “መልካም ነው! እኔ አንተን ለዘለ
ቂታ የራሴ የክብር ዘብ አደርግሃለሁ” አለው።

ሳኦል ከሙታን ጠሪ ምክር ጠየቀ

3 እነሆ ሳሙኤል ከሞተ ቆየት ብሎአል፤
እስራኤላውያንም ሁሉ ለእርሱ በማዘን አልቅ
ሰው ሰሚኖርባት በራማ ቀብረውታል፥ ቀደም
ሲል ሳኦል ጠንቋዮችንና ሙታን ጠሪዎችን ከእ
ስራኤል ምድር እንዲባረሩ አስገድዶአቸው
ነበር።
4 የፍልስጥኤም ወታደሮች ተሰልፈው መጥ
ተው በሹነም ከተማ አጠገብ ሰፈሩ፤ ሳኦልም
እስራኤላውያንን አስልፎ በጊልቦዓ ተራራ ሳይ
መሸገ፤ 5 ሳኦልም የፍልስጥኤማውያንን ሠራ
ዊት ብዛት ባየ ጊዜ በፍርሃት ተጨነቀ፤ 6 ስለዚ
ህም ምን ማድረግ እንደሚገባው እግዚአብሔ
ርን ጠየቀ፤ እግዚአብሔር ግን በሕልም ወይም

28፥3 ፡- ዘሌ. 20፥27፤ ዘዳ. 18፥10-11፤ 1ሳሙ. 25፥1። 28፥6 ፡- ዘኍ. 27፥21።

በኡሪምና በቱሚም ወይም በነቢያት እማካይ
ነት መልስ እንዲሰጠው አልፈቀደም ። 7 ከዚህ
በኋላ ሳኦል "ሙታን ጠሪ የሆነች እንዲት ሴት
ፈልጉልኝ፣ እኔም ሄጀ ምክር እጠይቃታለሁ"
ሲል ባለሟሎቹን አዘዘ ።

እነርሱም "አንዲት ዔንዶራዊት አለች"
ሲሉ መለሱለት ።

8 ሳኦልም ልብሱን ለውጦ ማንነቱ እንዳይታ
ወቅ በማድረግ በሌሊት ሁለት ሰዎች አስከትሎ
ሴትዮዋን ለማየት ሄደ፣ እዚያም እንደደረሰ
"መናፍስትን ጠይቂኝ ወደ ፊት ስለሚሆነው
ነገር አስረጂኝ፣ ስሙንም የምጠራልሽን ሰው
መንፈስ አስነሽልኝ" አላት ።

9 ሴትዮዋም "ንጉሥ ሳኦል ያደረገውን ነገር
ሁሉ ታውቃለህ፣ እርሱ እኮ ጠንቋዮችንና
ሙታን ጠሪዎችን ከእስራኤል ምድር አጥፍቶአ
ቸዋል፣ ታዲያ አንተ እኔን አጥምደህ ልታስገድ
ለኝ የምትፈልገው ለምንድን ነው?" ስትል
መለሰችለት ።

10 ከዚያም በኋላ ሳኦል "በዚህ ነገር ምንም
ዐይነት ቅጣት እንደማይደርስብሽ በሕያው እግ
ዚአብሔር ስም ምዬ ቃል እገባልሻለሁ"
አላት ።

11 "ታዲያ ማንን ላስነግልህ?" ስትል ጠየቀ
ችው ።

እርሱም "ሳሙኤልን አስነሽልኝ" አላት ።

12 እርስዋም ሳሙኤልን ባየችው ጊዜ ድምፅ
ዋን ከፍ አድርጋ በመጮኽ "ለምን አታለል
ከኝ? እንተ ንጉሥ ሳኦል ነህ" አለችው ።

13 ንጉሡም "አይዞሽ አትፍሪ! ይልቅስ የም
ታይው ነገር ምንድን ነው?" ሲል ጠየቃት ።

እርስዋም "እኔ አንድ መንፈስ ከመቃብር
ሲወጣ አያየሁ ነኝ" አለችው ።

14 እርሱም "ምንን ይመስላል?" ሲል ጠየ
ቃት ።

እርስዋም "እነሆ ካባ የለበሰ አንድ ሽማግሌ
ሰው እየተነሣ ነው" ስትል መለሰችለት ።

ሳኦልም ያ መንፈስ ሳሙኤል መሆኑን
ዐውቆ ለስ ብብሩ በመሬት ላይ ሰግ ብሎ እጅ
ነሣ ።

15 ሳሙኤልም ሳኦልን "ዕረፍት የምትነሣኝ
ለምንድን ነው? ለምንስ ከመቃብር እንድነሣ
አስጠራኸኝ?" አለው ።

ሳኦልም "እነሆ እኔ በታላቅ ችግር ላይ ነኝ፣
ፍልስጥኤማውያን ከእኔ ጋር ጦርነት በማድረግ
ላይ ናቸው፣ እግዚአብሔርም እኔን ትቶኛል፣
በነቢይም ሆነ በሕልም መልስ ሊሰጠኝ አልፈለ
ገም ፣ ስለዚህም ምን ማድረግ እንደሚገባኝ ትነግ
ረኝ ዘንድ እንድትነግ አስጠራሁህ" ሲል መለሰ ።

16 ሳሙኤልም ሳኦልን እንዲህ አለው ፣ "እግ
ዚአብሔር ተለይቶህ ጠላትህ ከሆነ በኋላ እኔን
ስለምን ታስጠራኛለህ? 17 እግዚአብሔር በእኔ
እማካይነት የነገረህን ሁሉ እየፈጸመ ነው ፣
መንግሥቱንም ከእንተ እጅ ወስዶ ለዳዊት ሰጥ
ቶታል ፣ 18 እንተ ለእግዚአብሔር ቃል ታዛዥ
ሆነህ አልተገኘህም ፣ ዐማሌቃውያንንና የእነርሱ
የሆነውንም ሁሉ አልደመሰስክም ፣ እንግዲህ
እግዚአብሔር አሁን ይህን ሁሉ የሚያደርግብህ
በዚህ ምክንያት ነው ። 19 ስለዚህ እርሱ እንተ
ንና እስራኤልን ለፍልስጥኤማውያን አሳልፎ
ይሰጣቸዋል ፣ ነገ አንተና ልጆችህ እኔ ወዳለሁ
በት ቦታ ትመጣላችሁ ፣ እግዚአብሔርም የእስ
ራኤልን ሠራዊት ለፍልስጥኤማውያን አሳልፎ
ይሰጣል ።"

20 ሳኦልም ሳሙኤል በተናገረው ቃል ደንግጦ
በመዝለፍለፍ ወደቀ ፣ በመሬት ላይም ተዘረረ ፣
ቀኑንና ሌሊቱን ሁሉ እህል ውኃ ስላልቀመሰ
ድካም ተሰምቶት ነበር ። 21 ሴትዮዋም ቀረብ
ብላ ስትመለከተው በፍርሃት ሲንቀጠጥ አየ
ችው ፣ እንዲህም አለችው ፣ "ጌታዬ! አንተ ያል
ከውን ሰማድረግ ሕይወቴን እስከ ማለስፍ ደርሻ
ለሁ ፣ 22 አንተ ደግሞ በፊንታህ እባክህ እኔ የምጠ
ይቅህን አድርግ ፣ ጥቂት ምግብ ላቀ ጋጅልህ ጠንክ
ረህ መጓዝ እንድትችል መመገብ ይገባሃል ።"

23 ሳኦል "ምንም ነገር አልቀምስም" ብሎ
እምቢ አለ ፣ ይሁን እንጂ ባለሟሎቹም እንዲመ
ገብ አበረታቱት ፣ በመጨረሻም "እሺ" ብሎ
ከወደቀበት መሬት በመነሣት አልጋ ላይ ተቀ
መጠ ፣ 24 ሴትዮዋም ያስባቸውን ጥጃ በፍጥነት
ወረደች ፣ ጥቂት ዱቄትም ወሰዳ በማቡካት
እርሾ ያልነካው ቂጣ ጋገረች ። 25 ምግቡንም
ለሳኦልና ለባለሟሎቹ አቅርባላቸው ተመገቡ ፣
በዚያኑም ምሽት ከዚያ ተነሥተው ሄዱ ።

ምዕራፍ 29

ፍልስጥኤማውያን ዳዊትን ተቃወሙ

1 እስራኤላውያን በኢይዝራኤል ሸለቆ ውስጥ
በሚገኘው ምንጭ አጠገብ ሰፍረው ሳሉ ፍልስ
ጥኤማውያን ወታደሮቻቸውን በአንድነት ስብስ
በው በማምጣት በአፌቅ አሰለፉ ፣ 2 እምስቱም
የፍልስጥኤም ነገሥታት በመቶና ሰሺ ከተመ
ደቡ ሰልፈኞቻቸው ጋር ዘመቱ ፣ ዳዊትና ተከ
ታዮቹም የአኪሽ ደጀን ጦር ሆነው ዘመቱ ፣
3 የፍልስጥኤም ጦር አዛዦችም እነርሱን ባዩ
ጊዜ "እነዚህ ዕብራውያን እዚህ ምን ይሠ
ራሉ?" ሲሉ ጠየቁ ።

እኪሽም "ይህማ የእስራኤል ንጉሥ ባለሟል
የነበረው ዳዊት ነው ፣ እነሆ እርሱ ከእኔ ጋር
ሲኖር ብዙ ጊዜው ነው ፣ ሳኦልን ከድቶ ወደ
እኔ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ሊያሳዝነኝ የሚችል
ምንም ዐይነት በደል ሠርቶ አልተገኘም" ሲል
መለሰ ።

28:17 ፡- 1ሳሙ. 15:28 ። 28:18 ፡- 1ሳሙ. 15:3-9 ።

4 ነገር ግን የፍልስጥኤም ጦር አዛዦች
በአኪሽ ላይ ተቈጥተው እንዲህ አሉት፥
“ይህን ሰው ቀድሞ ወደሰጠኸው ከተማ መል
ሰው፤ ከእኛ ጋር አብሮ እንዲዘምት አታድ
ርግ፤ ምክንያቱም ጦርነቱ በሚፋፋምበት
ወቅት ሰእኛ ላይ ሊነሣ ይችላል፤ እርሱ ከጌ
ታው ጋር ለመስማማት የእኛን ሰዎች ከመግ
ደል ሌላ ምን አማራጭ ይኖረዋል? 5 ከዚህስ
በቀር ቀደም ሲል ሴቶች በማሸብሸብ ‘ሳኦል ሺ
ገዳይ! ዳዊት ዐሥር ሺ ገዳይ!’ እያሉ የዘመሩ
ለት ይኸው ዳዊት እይደለም እንዴ?”

6 ስለዚህም አኪሽ ዳዊትን ጠርቶ እንዲህ
አለው፥ “እንተ ለእኔ ታማኝ ስለመሆንህ
ሕያው በሆነው በእስራኤል አምላክ ስም እምላ
ለሁ፤ ወደዚህም ጦርነት ዘምተህ ብትዋጋ ደስ
ባለኝ ነበር፤ ምክንያቱም ወደ እኔ ከመጣህበት
ጊዜ ጀምሮ እኔን ማሳዘን የሚችል በደል ሠር
ተህ አላገኘሁህም፤ ነገር ግን ሌሎቹ ነገሥታት
የአንተን አብሮ መዝመት አልፈቀዱም፤ 7 ስለ
ዚህ እነርሱን ደስ የማያሰኝ ሥራ ከመሥራት
በሰላም ወደ ቤትህ ብትመለስ ይሻልሃል።”

8 ዳዊትም “ጌታዬ ምን በደል ሠራሁ?
እንተ እንደምትሰው፥ እንተን ማገልገል ከጀመ
ርሁበት ጊዜ አንሥቶ በደል ካልተገኘብኝ ጌታ
ዬና ንጉሤ የሆንከውን አንተን ተከትዬ በመዝ
መት ጠላቶችህን መውጋት የማልችለው ስለምን
ድን ነው?” አለው።

9 አኪሽም “አዬ በበኩሌ እስማማለሁ፤ ምክ
ንያቱም እንደ አግዚአብሔር መልአክ አተማመ
ንብሃለሁ፤ ነገር ግን ሌሎቹ ነገሥታት ‘ከእኛ
ጋር መዝመት አይችልም’ አሉ፤ 10 ስለዚህ ከሳ
ኦል እምልጣችሁ ወደ እኔ የመጣችሁ ሁሉ ነገ
ጠዋት ማለድ ብላችሁ በመነሣት ፀሐይ ሳት
ወጣ ወደ ሰፈራችሁ ተመለሱ” ሲል መለሰ
ለት።

11 ስለዚህም ዳዊትና ተከታዮቹ በማግሥቱ
ማለዳ ወደ ፍልስጥኤም ተመልሰው ለመሄድ
ተነሡ፤ ፍልስጥኤማውያንም ወደ ኢይዝራኤል
ዘመቱ።

ምዕራፍ 30

በዐማሌቃውያን ላይ የተደረገ ጦርነት

1 በሁለተኛው ቀን ዳዊትና ተከታዮቹ ወደ
ጺቅላግ ደረሱ፤ አኒርሱም ከመድረሳቸው በፊት
ዐማሌቃውያን የይሁዳን ደቡብ ወርረው በጺቅ
ላግ ላይ እደጋ ጥለውባት አገኙአት፤ ዐማሌቃ
ውያን ከተማይቱን ካቃጠሉ በኋላ፥ 2 ሴቶችን
ሁሉ ማርከው ወስደዋል፤ ከዚያም ለቅቀው
ሲሄዱ ያገኙትን ሁሉ ማርከው ወሰዱ እንጂ
ማንንም አልገደሉም ነበር፤ 3 ዳዊትና ተከታዮ
ቹም አዚያ በደረሱ ጊዜ ከተማይቱ ተቃጥላ፥
ሚስቶቻቸው፥ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው
ተማርከው መወሰዳቸውን ተረዱ፤ 4 ዳዊትና
ተከታዮቹም ፈጽሞ እስኪደክሙ ድረስ ባለማቋ
ረጥ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ።
5 ሌላው ቀርቶ ሁለቱ የዳዊት ሚስቶች አሒኖ
ምና አቢጋይል ተማርከው ተወስደው ነበር።

6 ከዚህም የተነሣ ዳዊት ታላቅ ሐዘን ደርሶ
በት ነበር፤ ምክንያቱም ተከታዮቹ ልጆቻቸ
ውን በማጣታቸው በመረረ ሁኔታ እዝነው በድ
ንጋይ ሊወግሩት ማስፈራራት ጀምረው ነበር፤
ነገር ግን እምላኩ አግዚአብሔር በማጽናናት
አበረታታው፤ 7 ዳዊትም የአቢሜሌክ ልጅ የሆነ
ውን ካህኑን አብያታርን “ኤፉዱን እምጣልኝ”
አለው፤ አብያታርም ኤፉዱን አመጣለት፤
8 ዳዊትም “እነዚያን ወራሪዎች ተከታትዬ በማ
ሳደድ ልያዛቸውን?” ሲል እግዚአብሔርን
ጠየቀ።

እግዚአብሔርም “ተከተላቸው! እነርሱንም
ይዘህ ምርኮኞችን በመታደግ ታድናለህ” ሲል
መለሰለት።

9 ስለዚህም ዳዊትና ስድስት መቶ የሚሆኑ
ተከታዮቹ ወጥተው ሄዱ፤ ብሦር ተብሎ በሚ
ጠራው ወንዝ አጠገብ በደረሱ ጊዜ፥ ጥቂቶቹ
በዚያ ዕረፍት በማድረግ ቆዩ። 10 ዳዊት ግን
ከአራት መቶ ተከታዮቹ ጋር ጕዞውን ቀጠለ፤
ሌሎቹ ሁለት መቶ ተከታዮቹ ግን ወንዙን ለመ
ሻገር ስለደከሙ ወደ ኋላ ቀሩ። 11 ከዳዊት ጋር
የነበሩት አራት መቶ ሰዎች እንድ ግብጻዊ
ወጣት ከበረሐ ሲመጣ እግኝተው ወደ ዳዊት
አቀረቡት፤ እነርሱም የሚመገበው ጥቂት እህል
ውሃ፥ 12 ደረቅ የበለስ ፍሬና ሁለት ጥፍጥፍ
ዘቢብ አቀረቡለት፤ ወጣቱም ከተመገበ በኋላ
እንደገና በረታ፤ ምክንያቱም ከዚያ በፊት
ሦስት ቀን ሙሉ እህል ውሃ እልቀመሰም
ነበር። 13 ዳዊትም ወጣቱን “የማን አገልጋይ
ነህ? እመጣጥህስ ከየት ነው?” ሲል ጠየቀው።

ወጣቱም “እኔ ግብጻዊ የሆንሁ የእንድ ዐማ
ሌቃዊ እገልጋይ ነኝ፤ ታምሜ ስለነበር ከሦስት
ቀን በፊት ጌታዬ ጥሎኝ ሄደ፤ 14 ይህም ከመ
ሆኑ በፊት በይሁዳ ደቡብ የምትገኘውን የክሪ
ታውያንን ግዛትና የካሌብን ጐሳ ግዛት በመው
ረር ጺቅላግን እቃጥለናታል” ሲል መለሰለት።

15 ዳዊትም “እነዚያ ወራሪዎች ወዳሉበት
ስፍራ ልትመራን ትችላለህን?” ሲል ጠየቀው።

ወጣቱም “እንደማትገድለኝና ለጌታዬም
አሳልፈህ እንደማትሰጠኝ ከማልክልኝ ላሳይህ
እችላለሁ” ሲል መለሰለት። 16 ከዚያም በኋላ
ዳዊትን ወራሪዎቹ ወዳሉበት እየመራ እደረ
ሰው።

ወራሪዎቹም በየቦታው ተበታትነው በመብላ
ትና በመጠጣት ተድላ ደስታ በማድረግ ላይ

29:5 ፡- 1ሳሙ. 18:7፤ 21:11። 30:5 ፡- 1ሳሙ. 25:42-43። 30:7 ፡- 1ሳሙ. 22:20-23።

ነበሩ ፤ ምክንያቱም ከፍልስጥኤምና ከይሁዳ
ያገኙት ምርኮ እጅግ ብዙ ነበር ፤ 17 በምሽት
ጊዜ ዳዊት በእነርሱ ላይ እደጋ ጥሎ እስከ ማግ
ሥቱ ማታ ድረስ ተዋጋቸው ፤ በግመል ላይ
ተቀምጠው እየጋለቡ ከሸሹት አራት መቶ ወጣ
ቶች በስተቀር ከነዚያ ወራሪዎች ያመለጠ አን
ድም አልነበረም ፤ 18 ዳዊትም ዐማሌቃውያን
የወሰዱበትን ማንኛውንም ሰውና ንብረት ፥ እን
ዲሁም ሁለቱን ሚስቶቹን ጭምር በመታደግ
አዳነ ፤ 19 አንድም የጐደለ ሳይኖር ዳዊት የተከ
ታዮቹን ወንዶችና ሴቶች ልጆች ፥ እንዲሁም
ዐማሌቃውያን ማርከው የወሰዱትን ምርኮ ሁሉ
እስመለሰ ፤ 20 የከብት ፥ የበግና የፍየል መንጋዎ
ችንም ሁሉ አገኘ ፤ ተከታዮቹም እንስሳቱን
በፈታቸው እየነዱ “ይህ ሁሉ የዳዊት ምርኮ
ነው!” አሉ ።

21 ዳዊትም ደክሞአቸው በብሶር ምንጭ
አጠገብ ዕረፍት በማድረግ ቆይተው ወደነበሩት
ወደ ሁለት መቶ ተከታዮቹ ተመልሶ ሄደ ። እነ
ርሱም ዳዊትንና ተከታዮቹን ሊቀበሉአቸው
መጡ ፤ ዳዊትም ወደ እነርሱ ቀረብ ብሎ ደኅን
ነታቸውን በመጠየቅ ሰላምታ አቀረበላቸው ።
22 ነገር ግን የብልሞና ጠባይ ያሰባቸው አንዳ
ንድ የማይረቡ ሰዎች “ከእኛ ጋር ወደ ጦርነቱ
ስላልሄዱ ምርኮ ልናካፍላቸው አይገባም ፤ ሚስ
ቶቻቸውንና ልጆቻቸውን ብቻ ተረከበው ወዲያ
ይሂዱ” አሉ ።

23 ዳዊትም “ወንድሞቼ ሆይ! እግዚአብ
ሔር በሰጠን ድል እናንተ ይህን ማድረግ አትች
ሉም ፤ እኛን በሕይወት ጠብቆ በወራሪዎች ላይ
ድልን የሰጠን እርሱ ነው ፤ 24 እናንተ በምት
ሉት ነገር ማንም አይሰማማበትም! ወደ ኋላ
ቀርቶ ጓዝ ሲጠብቅ የቆየውም ሆነ ወደ ጦርነት
የዘመተው ሁሉም የተገኘውን ምርኮ እኩል
መካፈል አለበት” ሲል መሰለላቸው ። 25 ዳዊ
ትም ይህን እንደ ሕግ አድርጎ በሰተጠቀመበት
በእስራኤል ምድር እስከ ዛሬ ድረስ ሲሠራበት
ይኖራል ።

26 ዳዊትም ወደ ጺቅላግ በተመለሰ ጊዜ ከምር
ኩው ከፈሉን ወዳጆቹ ለሆኑት ለይሁዳ ሽማግሌ
ዎች ላከላቸው ፤ ከላከላቸውም ምርኮ ጋር “ይህ
ከእግዚአብሔር ጠላቶች ተወስዶ የተላከላችሁ
ስጦታ ነው” የሚል መልእክት ነበር ፤ 27 ከዚያም
ምርኮ በቤትኤል ለሚገኙ ሕዝብ ፥ በደቡብ
ደቡብ በራማ ለሚገኙ ወገኖች ፥ እንዲሁም በያ
ቲር ከተሞች ለሚገኙ ሕዝብ ሁሉ ላከላቸው ፤
28 ከዚህም በቀር በዓሮዔር ፥ በሲፍሞት ፥ በኤሽተ
ሞዓና ፥ 29 በራካል ለሚገኙ ፥ እንዲሁም ለይራሕ
መኤል ጐሳ አቋኖዎያን ፥ 30 በሖርማ ፥ በቦርዓ
ሻን ፥ በዐታክና ፥ 31 በኬብሮን ከተሞች ለሚኖሩ
ሁሉ ላከላቸው ፤ ከዚህም በቀር እርሱና ተከታ
ዮቹ በተዘዋወሩባቸው ስፍራዎች ሁሉ ለሚኖሩ
ሰዎች ስጦታ ያልተላከላቸው አልነበሩም ።

ምዕራፍ 31

የሳኦልና የልጆቹ አሟሟት
(1 ዜ.መ. 10፡1-12)

1 ፍልስጥኤማውያን በጊልቦዓ ተራራ ላይ
ከእስራኤላውያን ጋር ጦርነት ገጠሙ ፤ በዚ
ያም ብዙ እስራኤላውያን ተገደሉ ፥ የቀሩትም
ንኑሥ ሳኦልና ልጆቹም ጭምር ሸሹ ፥ 2 ፍል
ስጥኤማውያን ግን ተከታትለው ሰለደረሱባቸው
ሦስቱን የሳኦልን ልጆች ዮናታንን ፥ አቢናዳብ
ንና ማልኪሹዓን ገደሉአቸው ፤ 3 በሳኦል
ዙሪያ ጦርነቱ ሰለበረታ ሳኦል ራሱ ከጠላት
በተወረወረ ፍላጻ ተመትቶ ከፉኛ ቈሰለ ፤
4 ጋሻጃግሬው የነበረውንም ወጣት “እነዚህ
ያልተገረዙ ከሐዲዎች ፍልስጥኤማውያን እኔን
ወግተው በመሳለቅ መጫወቻ እንዳያደርጉኝ
እንተ ራስህ ሰይፍህን መዝዘህ ግደለኝ”
አለው ፤ ወጣቱ ግን ይህን ለማድረግ ፈራ ፤
ስለዚህም ሳኦል ራሱ የገዛ ሰይፉን ወስዶ በሰ
ቱ ላይ ወደቀበት ፤ 5 ወጣቱም ሳኦል እንደ
ሞተ ባየ ጊዜ እርሱም በዘኩሉ በራሱ ሰይፍ
ስለት ላይ ወድቆ ከሳኦል ጋር ሞተ ። 6 እንግ
ዲህ ሳኦልና ሦስቱ ወንዶች ልጆቹ እንዲሁም
ጋሻጃግሬው የሞቱት በዚህ ዐይነት ሲሆን ፥
የሳኦልም ተከታዮች በዚያን ቀን አብረዋቸው
ሞቱ ። 7 ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅና
በኢይዝራኤል ሸለቆ ማዶ የነበሩ እስራኤላው
ያንም የእስራኤል ሠራዊት መሸሹን ፥ ሳኦልና
ልጆቹም መገደላቸውን ሰምተው ከተሞቻቸ
ውን እየጣሉ ሸሹ ፤ ፍልስጥኤማውያንም መጥ
ተው ከተሞቹን ያዙ ።

8 ከጦርነቱ ቀጥሎ ባለው ቀን ፍልስጥኤማ
ውያን የሚቾቹን ሬሳ ትጥቅ ለመግፈፍ
ሄደው ሳኦልንና ሦስቱን ልጆቹን በጊልቦዓ
ተራራ ላይ ወድቀው አገኙአቸው ። 9 የሳኦል
ንም ራስ ቈርጠው የጦር ልብሱንም ገፍፈው
በማስያዝ ለአማልክቶቻቸውና ለሕዝባቸው
የድሉን ዜና ያበሥሩ ዘንድ መልእክተኞቻቸ
ውን ላኩ ። 10 ከዚህ በኋላ ፍልስጥኤማውያን
የሳኦልን የጦር መሣሪያዎች ዐስታሮት ተብላ
በምትጠራው ሴት አምላካቸው ቤተ መቅደስ
ውስጥ አኖሩ ። የሳኦልንም ሬሳ ቤትሻን ተብላ
በምትጠራው ከተማ ቅጽር ግንብ ላይ በምስ
ማር ችንከሩት ።

11 በገለዓድ የሚኖሩ የያቢሽ ሰዎችም ፍል
ስጥኤማውያን በሳኦል ላይ ያደረጉበትን ነገር
በሰሙ ጊዜ ፥ 12 ጀግኖቻቸው በድንገት ተነሥ
ተው በመገሥገሥ በሌሊት ወደ ቤትሻን
ሄዱ ፤ የሳኦልንና የልጆቹን አስከሬን ከከተማ
ይቱ ቅጽር ግንብ ላይ አውርደው ወደ ያቢሽ
በማምጣት እቃጠሉአቸው ። 13 አጥንቶቻቸው
ንም በከተማው ውስጥ ታማሪስክ ተብሎ በሚ
ጠራ ዛፍ ሥር ቀብረው ሰባት ቀን ጾሙ ።

መጽሐፈ ሳሙኤል

ክፍል ሁለት

መግቢያ

መጽሐፈ ሳሙኤል ክፍል ሁለት ፣ የመጽሐፈ ሳሙኤል ክፍል አንድ ተከታይ ሲሆን ዳዊት በመጀመሪያ በደቡብ በኩል የይሁዳ ንጉሥ (ከም. 1-4) ፣ ዘግየት ብሎም የስሜናዊ ክፍል የሆ ነውን እስራኤልን ጨምሮ የመላዋ አገሪቱ ንጉሥ ሆኖ እንደ ገዛ የሚያስረዳ ታሪክ ነው (ከም. 5-24) ፤ መጽሐፉ ዳዊት ንጉሣዊ መንግሥቱን ለማስፋፋትና ሥልጣኑንም ለማጠናከር በአገሪቱ ውስጥና ከአገሪቱ ውጭ ከነበሩት ጠላቶቹ ጋር ያደረገውን ብርቱ ፍልሚያ ዘርዝሮ ያስ ረዳል ። ዳዊት ጠንካራ እምነት ያለውና እግዚአብሔርን የሚወድ ፣ እንዲሁም የሕዝቡን ታማኝ ነት ያተረፈ ሰው እንደነበር ተገልጦአል ፤ በተጨማሪም አንዳንድ ጊዜ የጭካኔ ሥራ ይፈጽም እንደነበረና የሥጋውን ፍላጐት ለማርካት አመቃቂ የሆኑ ኃጢአቶችን እንደ ሠራ ተዘርዝሮ አል ። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ነቢይ ናታን ወደ እርሱ ቀርቦ ስለ ኃጢአቱ ባስገነዘበው ጊዜ ፣ ኃጢአቱን ተናዝዞ የእግዚአብሔርን ቅጣት ይቀበል ነበር ።

የዳዊት ሕይወትና ያከናወናቸው ሥራዎች የእስራኤልን ሕዝብ እጅግ የማረከ በመነበር ፥ ከእ ርሱ በኋላ በነበሩት ዘመናት በአገሪቱ ላይ ችግር በደረሰ ቊጥር ሌላ ንጉሥ እንዲኖራቸው ሲፈ ልጉ ፥ የዳዊት ልጅ ወይም የዳዊት ዝርያ የሆነና ልክ እንደ ዳዊት የሚያስተዳድር ሰው ለማግ ኘት ይመኙ ነበር ።

ምዕራፍ 1

ዳዊት የሳኦልን ሞት ሰማ

1 ሳኦል ከሞተ በኋላ ዳዊት ዐማሌቃውያንን ድል አድርጎ ተመለሰ ፤ በጺቅላግም ሁለት ቀን ቆየ ፤ 2 በተከታዩ ቀን አንድ ወጣት ከሳኦል ሰፈር መጣ ፤ ሐዘኑን ለመግለጥ ልብሱን ቀዶ በራሱ ላይ ትቢያ ነሰንሶ ነበር ፤ ወደ ዳዊትም ቀርቦ በአክብሮት ወደ መሬት ለጥ ብሎ እጅ ነሣ ፤ 3 ዳዊትም “ከወዴት መጣህ?” ሲል ጠየ ቀው ።

እርሱም “ከእስራኤላውያን ሰፈር አምልጡ የመጣሁ ነኝ” ሲል መለሰ ።

4 ዳዊትም “እስቲ የሆነውን ሁሉ ንገረኝ” አለው ።

እርሱም “ሠራዊታችን ከሞር ግንባር ሸሸ ፣ ከሰዎቻችንም ብዙዎቹ ሞቱ ፤ ሳኦልና ልጁ ዮናታንም ተገደሉ” አለ ።

5 ዳዊትም “ሳኦልና ዮናታን መሞታቸውን እንዴት ዐወቅህ?” ሲል ጠየቀው ።

6 ወጣቱም እንዲህ ሲል መለሰ ፥ “እኔ በጊል በዓ ተራራ ላይ ነበርኩ ፤ ሳኦል ጦሩን ተደግፎ ሳለ የጠላት ሠረገላዎችና ፈረሰኞች ወደ እነርሱ ሲጠጉ አየሁ ፤ 7 እርሱም ወደ ኋላ መለስ ሲል እኔን አየኝና ጠራኝ ፤ እኔም ‘ጌታዬ እነሆ አለሁ’ አልሁት ፤ 8 ማን እንደሆንሁ በጠየቀኝ ጊዜም ዐማሌቃዊ መሆኔን ነገርሁት ፤ 9 እርሱም ‘ወደ እኔ ቀርበህ ግደለኝ ፤ በብርቱ ስለቈሰልሁ መሞቴ ነው’ አለኝ ፤ 10 እኔም ወደ እርሱ ቀርቤ ገደልሁት ፤ ምክንያቱም በሚወድቅበት ጊዜ እንደሚሞት ዐውቅ ነበር ፤ ከዚህ በኋላ ዘውዱን ከራሱ ላይ ፥ አንባሩንም ከክንዱ ላይ ወሰድሁ ፤ ጌታዬ ሆይ! እነሆ እነርሱን ለአንተ አመጣሁልህ ።”

11 ዳዊትም በሐዘን ልብሱን ቀደደ ፤ ከእር ሱም ጋር የነበሩ ተከታዮቹ ሁሉ እንደዚሁ አደ ረጉ ፤ 12 በጦርነቱ ብዙ ሰዎች ተገድለው ነበር ፤ ለሳኦል ፥ ለዮናታንና የእግዚአብሔር ሠራዊት ለሆኑት ለመላው እስራኤል እስከ ምሽት ድረስ በመጾም በከባድ ሐዘን አለቀሱላ ቸው ።

13 ዳዊትም ወሬውን ይዞ የመጣውን ያንን ወጣት “የየት አገር ሰው ነህ?” ሲል ጠየ ቀው ።

እርሱም “በሀገርህ ውስጥ በመጻተኛነት የሚኖር የዐማሌቃዊ ልጅ ነኝ” ሲል መለሰ ለት ።

14 ዳዊትም “ታዲያ እግዚአብሔር መርጦ የቀባውን ንጉሥ ለመግደል እንዴት ደፈርህ” ሲል ጠየቀው ። 15 ከዚህ በኋላ ዳዊት ከተከታ ዮቹ አንዱን ጠርቶ “ግደለው!” ሲል አዘዘው ፤ ሰውየውም ዐማሌቃዊውን መቶ ገደለው ፤

1፡6-10፦ 1ሳሙ. 31፡1-6 ፤ 1ዜ.መ. 10፡1-6 ።

16 ዳዊትም ዐማሌቃዊውን "ይሆን ጥፋት በራሰህ ላይ ያመጣህ እንተው ራስህ ነህ፤ እግዚአብሔር መርጦ የቀባውን ንጉሥ ገድያሰው ብለህ በተናገርህ ጊዜ በራሰህ ላይ ፈርደሃል" አለው።

ዳዊት ስለ ሳኦልና ስለ ዮናታን ሞት
የሐዘን ቅኔ በመቀኘት አለቀሰላቸው

17 ዳዊት ስለ ሳኦልና ስለ ልጁም ስለ ዮናታን ይህን የሐዘን ቅኔ ተቀኘ፤ 18 የይሁዳም ሕዝብ ያጠኑት ዘንድ አዘዘ፤ ቅኔውም በያሻር መጽሐፍ ተመዝግቦ ይገኛል፦

19 "መሪዎቻችን በእስራኤል ኮረብታዎች
ላይ ሞቱ፤
ከወታደሮቻችን ብርቱዎቹ ጀግኖች
ወደቁ፤
20 ይህን መሬ በጋት አትናገሩ፤
በአስቀሎናም መንገዶች አታውሩ፤
የፍልስጥኤማውያን ሴቶች እንዲደሰቱ፥
የአረማውያን ሴቶች ልጆችም
እንዲፈነድቁ እታድርጉ።

21 "በጊልቦዓ ኮረብታዎች ዝናምም ሆነ
ጤዛ አይውረድባቸው፤
የእርሻ መሬቶቻቸውም ምንም ነገር
አይብቀልባቸው፤
ምክንያቱም የጀግኖች ጋሻዎች እዚያ
በውርደት ወድቀዋል፤
የሳኦልም ጋሻ በዘይት መወልወሉ
ቀርቶአል።
22 የዮናታን ቀስት ሳይገድል የማይመለስ፥
የሳኦልም ሰይፍ ያለምሕረት
የሚያመስስ፥
ጎያላንን መትቶ የሚሰብር፥
ጠሳትን የሚገድል ነበር።

23 "ሳኦልና ዮናታን በአስደናቂ ፍቅር ኖሩ፤
በሕይወትም ሆነ በሞት ላለመሰያየት
ተባበሩ፤
እነርሱም ከንስር የፈጠኑ፥
ከእንበሳም የበረቱ ነበሩ።

24 "የእስራኤል ሴቶች ሰሳኦል አልቅሱለት!
ምክንያቱም እርሱ ውድ የሆነ
ሐምራዊ ቀሚስ አልብሶአችኋል፤
በዕንቍና በወርቅም አስጊጦአችኋል።

25 "ጀግኖች ወታደሮች ወድቀዋል!
ሁሉም በጦርነት ተገድለዋል!
ዮናታንም ሞቶ በኮረብታዎች ላይ
ተጋድሞአል!

26 "ወንድሜ ዮናታን ሆይ!
እኔ ስለ አንተ በመረረ ሁኔታ
አዘንሁልህ፤
አንተ እኮ ለእኔ የቅርብ ወዳጄ
ነበርህ፤
የአንተ ፍቅር ለእኔ እጅግ አስደናቂ
ነበር፤
ይሽሙም ከሴት ፍቅር የበረታ ነበር።

27 "እነሆ ብርቱዎቹ ጦረኞች ወድቀዋል፤
የጦር መሣሪያዎቻቸው ሁሉ
ከንቱ ሆነው ቀርተዋል።"

ምዕራፍ 2

ዳዊት የይሁዳ ንጉሥ ሆነ

1 ከዚህ በኋላ ዳዊት "ሄጀ ከይሁዳ ከተሞች አንዲን ልያዝን?" ሲል እግዚአብሔርን ጠየቀ።
እግዚአብሔርም "አዎ ሄደህ ያዝ" አለው።
ዳዊትም "የትኛይቱን ከተማ ልያዝ?" ሲል ጠየቀ።
እግዚአብሔርም "ኬብሮንን ያዝ" አለው።
2 ሰለዚህ ዳዊት ከሁለቱ ሚስቶቹ ጋር ወደ ኬብሮን ሄደ፤ እነርሱም የኢይዝራኤል ተወላጅ የሆነችው አሒኖዓምና የቀርሜሎስ ተወላጅ የሆነችው የሚቹ የናባል ሚስት አቢጋይል ነበሩ። 3 እንዲሁም አብረውት የነበሩት ተከታዮቹ ከነቤተሰባቸው ከእርሱ ጋር ሄዱ፤ በኬብሮን ዙሪያ ባሉትም ታናናሽ ከተሞች ተቀመጡ። 4 ከዚህ በኋላ የይሁዳ ሰዎች ወደ ኬብሮን መጡ፤ ዳዊትንም ቀብተው የይሁዳ ንጉሥ አደረጉት።
ዳዊት ገለዓዳውያን የሆኑ የያቤሽ ሰዎች ሳኦልን እንደቀበሩት በሰማ ጊዜ፥ 5 መልእክተኞች ልኮ እንዲህ አሳቸው፥ "የእርሱን አሰክሬን በመቅበር ለጌታችሁ ታማኝነታችሁን ሰላሳያችሁ እግዚአብሔር ይባርካችሁ፤ 6 ደግሞም እግዚአብሔር ቸርነቱንና ታማኝነቱን ይግለጥላችሁ፤ እናንተ ሰሰፈጸማችሁት መልካም ነገር እኔም ለእናንተ በጎ ነገር እደርግላችኋለሁ። 7 እንግዲህ ጠንክሩ፤ በርቱም፤ ጌታችሁ ሳኦል ሞቶአል፤ የይሁዳ ሕዝብ እኔን ቀብተው ንጉሣቸው አድርገውኛል።"

ኢያቡሴቱ በእስራኤል ላይ ነገሠ

8 የሳኦል ሠራዊት አዛዥ የኔር ልጅ አበኔር ከሳኦል ልጅ ከኢያቡሴቱ ጋር የዮርዳኖስን ወንዝ በመሻገር ወደ ማሕናይም ሸሽቶ ሄደ፤ 9 በዚያም አበኔር ኢያቡሴቱን በገለዓድ ግዛቶች፥

1፡18 ፦ ኢያሱ 10፡13። 2፡2 ፦ 1ሳሙ. 25፡42-43። 2፡4 ፦ 1ሳሙ. 31፡11-13።

በአሴር ፥ በኢይዝራኤል ፥ በኤፍሬምና በብን
ያም ይኸውም በመላው እስራኤል ላይ እንዲነ
ግሥ አደረገ ። 10እርሱም በነገሠ ጊዜ ዕድሜው
አርባ ዓመት ነበር ፥ ሁለት ዓመትም ገዛ ።

የይሁዳ ነገድ ግን ዳዊትን ተከተለ ፥ 11ዳዊ
ትም በኬብሮን ተቀምጦ በመላው ይሁዳ ላይ
ሰባት ዓመት ተኩል ነገሠ ።

በእስራኤልና በይሁዳ መካከል
የተደረገው ጦርነት

12አበኔርና የኢያቡስቴ ባለሟሎች የሆኑ ባለ
ሥልጣኖች ከማሕናይም ተነሥተው ወደ ገባዖን
ከተማ መጡ ፥ 13እናቱ ጸሩያ ተብላ የምትጠ
ራው ኢዮአብና ሌሎቹም የዳዊት ባለሥልጣ
ኖች ወጥተው በኩሬው ውሃ አጠገብ አገኙአ
ቸው ፥ ሁሉም በቡድን ተከፋፍለው በኩሬው
ውሃ ማዶ ለማዶ ተቀምጠው ነበር ። 14በዚህ
ጊዜ አበኔር ኢዮአብን “ከእያንዳንዳችን ወገን
ወጣቶችን መርጠን በሰር መሣሪያ ውጊያ በመ
ጣመም ይወዳደሩ” አለው ።

ኢዮአብም “መልካም ነው!” ሲል መለሰ ።
15ሰለዚህም ከብንያም ወገን የኢያቡስቴ
ተወካዮች የሚሆኑ ዐሥራ ሁለት ሰዎች ተመር
ጠው ከዳዊት ወገን ከተመረጡት በሥራ ሁለት
ሰዎች ጋር ውጊያ ገጠሙ ። 16እያንዳንዱ በው
የባለጋራውን ራስ ይዞ ሰይፉን በጉኑ ሻጠበት ፥
በዚህ ዐይነት ሃያ አራቱም ሰዎች በእንድነት
ወድቀው ሞቱ ፤ ስለዚህም በገባዖን የሚገኘው
ያ ሰፍራ “የሰይፍ ምድር” ተብሎ ተጠራ ።

17ከዚያም በኋላ ነባድ ጦርነት ተደርጎ እበ
ኔርና እስራኤላውያን በዳዊት ሰዎች ድል
ተመቱ ። 18ኢዮአብ ፥ አቢሻይ ፥ ሀማኤል ተብ
ለው የሚጠሩት ሦስቱም የጸሩያ ልጆች እዚያ
ነበሩ ፤ በሩጫ እንደ በረሓ አጋዘን ፈጣን የነበ
ረው አሳሔል ፥ 19እበኔርን እባርሮ ለመያዝ በቀ
ጥታ ወደ እርሱ ሮጠ ፤ 20እበኔርም ፥ ወደ
ኋላው መለሰ ብሎ “ዐማኤል! አንተ ነህ?”
አለ ።

ዐማኤልም “አዎ እኔ ነኝ” ሲል መለሰለት ።
21አበኔርም “እኔን ማሳደድ ተው! ይልቅስ
ከወታደሮቹ አንዱን በማሳደድ የያዘውን ምርኮ
ውሰድ” አለው ፤ ዐማኤል ግን እርሱን ማሳደዱን
ቀጠለ ፤ 22እንደገናም አበኔር “እኔን ማሳደድ
ሀን ተው! ለምን እንድገድልህ ትገፋፍኛለህ?
አንተንስ ብገድል የወንድምህን የኢዮአብን ፊት
እንዴት ማየት እችላለሁ?” አለው ። 23ዐማኤል
ግን አሁንም ማሳደዱን ሊተው አልፈቀደም ፤
ሰለዚህ አበኔር ጦሩን ወደ ኋላው ወርወር ሆዱ
ላይ ሲሸጥበት ጫፉ ዘልቆ በጀርባው ወጣ ፤
ዐማኤልም መሬት ላይ ወድቆ ሞተ ፤ ራሳው
በተጋደመበት ሰፍራ የሚያልፍ ሰው ሁሉ በአ
ጠገቡ ቆሞ ይመለከተው ነበር ።

24ኢዮአብና አቢሻይ ግን አበኔርን አሳደ
ዱት ፤ ፀሐይ ዘጠለቀች ጊዜም ከጊያሕ በስተ
ምሥራቅ ፥ ወደ ገባዖን ምድረ በዳ በሚወሰደው
መንገድ ወዳለው ወደ አማ ኮረብታ ደረሱ ።
25የብንያም ነገድ ሰዎች አንደገና ተሰብሰበው
ወደ አበኔር መጡ ፤ በአንድ ኮረብታም ጫፍ
ላይ ሰፍርነት በመዘጋጀት ተሰሰፉ ። 26አበኔ
ርም ፤ ኢዮአብን ጠርቶ እንዲህ አለው ፤ “ዘላ
ለም ስንዋጋ አንኖራለንን? በመጨረሻ ከምሬት
በቀር የምናተርፈው ምንም ነገር እንደሌለ አት
ገነዘብምን? እኛ እኮ የአንድ አገር ሰዎች ነን ፤
ሰዎችህ እኛን ከማሳደድ እንዲገቱ ትእዛዝ የማ
ትሰጣቸው እስከ መቼ ነው?”

27ኢዮአብም “እንተ ይሀን ቃል ባትናገር
ኖር የእኔ ሰዎች እስከ ነገ ጠዋት እናንተን ከማ
ሳደድ እንደማይገቱ በሕያው እግዚአብሔር
ሰም እምላለሁ” ሲል መለሰለት ። 28ከዚህ
በኋላ ኢዮአብ እስራኤላውያንን ከማሳደድ እንዲ
ገቱ ክእርሱ ጋር ላሉት ሰዎች ምልክት የሚሰጥ
መለከት ነፋ ፤ ሰለዚህም ጦርነቱ ቆመ ።

29አበኔርና ከእርሱ ጋር የነበሩት ተከታዮቹ
በሌሊት የዮርዳኖስን ሸለቆ አቋርጠው ሄዱ ፤
የዮርዳኖስንም ወንዝ ተሻገሩ ፤ በተከታዩም ቀን
በጠዋት ተጕዘው ወደ ማሕናይም ተመለሱ ።

30ኢዮአብ ማሳደዱን በተወ ጊዜ ፥ የእርሱ
ሰዎች ሁሉ በአንድነት ተሰበሰቡ ፤ ከዐማኤልም
ሌላ ዐሥራ ዘጠኝ ሰዎች የደረሱበት ያልታወቀ
መሆኑ ተረጋገጠ ። 31የዳዊት ሰዎች የብንያም
ነገድ ከሆኑት ከአበኔር ተከታዮች ሦስት መቶ
ሰልሳ ሰዎችን ገደሉ ። 32ኢዮአብና ከእርሱ ጋር
የነበሩት ተከታዮቹ የዐማኤልን አስክሬን ወሰ
ደው በቤተልሔም በሚገኘው የቤተሰቡ መቃ
ብር ውስጥ ቀበሩት ፤ ሌሊቱንም ሁሉ ሲጓዙ
ግሡ እድረው ኀሔብሮን ደረሱ ።

ምዕራፍ 3

1በዚህ ዐይነት በእንድ በኩል የሳአልን ቤተ
ሰብ ፥ በሌላ በኩል ዳዊትን ይደግፉ በነበሩት
ኀይሎች መካከል የሚካሄደው ጦርነት ለረዥም
ጊዜ ቆየ ፤ ሆኖም ዳዊት እየበረታ ሲሄድ ፥ ተቃ
ዋሚዎቹ እየደከሙ ሄዱ ።

የዳዊት ልጆች

2ዳዊት በኬብሮን ሳሰ ሰድሰት ወንዶች ልጆች
ተወለዱለት ፤ እነርሱም የኢይዝራኤል ተወላጅ
ከሆነችው ከአሒኖዓም የተወለደው አምኖን ፥
3የቀርሜሎሰ ተወላጅ የናባል ሚሰት ከነበረችው
ከአቢጋይል የተወለደው ኪልአብ ፥ ታልማይ
ተብሎ የሚጠራው የጌሹር ንጉሥ ልጅ ከሆነችው
ከማዕካ የተወለደው አቤሴሎም ፥ 4ከሐጊት የተ
ወለደው አዶኒያ ፥ ከአቢጣል የተወለደው ሸፋ
ጥያ ፥ 5ከዔግላ የተመለደው ዩትረንም ፥ እነዚህ
ሁሉ በኬብሮን የተወለዱ ናቸው ።

አበኔር ከዳዊት ጋር ተባበረ

6 በዳዊት ሠራዊትና ሰሳኦል ቤተሰብ ታማኝ
በሆኑት ሠራዊት መካከል ጦርነቱ እየቀጠለ
በሄደ መጠን አበኔር በሳኦል ተከታዮች መካከል
ይበልጥ እየበረታ ሄደ ።
7 እንድ ቀን የሳኦል ልጅ ኢያቡስቴ አበኔርን
"የአባቴ ቊባት ከነበረችው ከአያ ልጅ ከሪጽፋ
ጋር ስለምን ተኛህ?" ብሎ በመወንጀል ከሰ
ሰው ። 8 ይህም አበኔርን በብርቱ ስላስቈጣው
በማግረር እንዲህ አለው ፥ "እኔ ሳኦልን ከድቼ
ይሁዳን የማገለግል ይመስልሃልን? ከመጀመሪ
ያው እንሥቶ አባትህ ሳኦል ፥ ወንድሞቹና ወዳ
ጆቹ ሰቆሙለት ዓላማ ታማኝ ነበርሁ ፤ እንተ
ንም ሰዳዊት አሳልፌ አልሰጠሁህም ፤ ይህ ሁሉ
ከሆነ በኋላ አንተ ዛሬ ስለ ሴት ጕዳይ በእኔ ላይ
ወንጀል ትፈልጋለህ ። 9-10 መንግሥቱን ከሳኦ
ልና ከዝርያዎቹ እንደሚወስድና ዳዊትንም በእ
ስራኤልና በይሁዳ ላይ በእገሪቱ ዳር አስከዳር
እንደሚያነግሠው ቀደም ሲል እግዚአብሔር
ሰዳዊት ቃል ገብቶለታል ፤ እንግዲህ ይህን ቃል
እውነት ባላደርገው እግዚአብሔር በሞት ይቅሠ
ፈኝ!" 11 ኢያቡስቴም እጅግ ፈርቶ ስለነበር
ለአበኔር እንድ ቃል እንኳ ሲመልስለት አልቻ
ለም ።
12 አበኔር በዚያን ጊዜ በኬብሮን ወደነበረው
ወደ ዳዊት መልእክተኞች ልኮ "የዚህች
ምድር ገዥ ለመሆን በመዘጋጀት ላይ ያለው
ማን ነው? እንግዲህ ከእኔ ጋር ስምምነት አድ
ርግ ፤ እኔም መላው እስራኤል በእንተ ቍጥጥር
ሥር እንዲሆን ለማድረግ እረዳሃለሁ" አለው ።
13 ዳዊትም "መልካም ነው ፤ ከእንተ ጋር
ስምምነት አደርጋለሁ ፤ ነገር ግን እንተ በቅድ
ሚያ የምትፈጽምልኝ ነገር አለ ፤ ይኸውም
ወደ አኔ በምትመጣበት ጊዜ የሳኦልን ልጅ
ሚካልን ይዘህልኝ ና" ሲል መለሰለት ። 14 እን
ዲሁም ዳዊት ወደ ኢያቡስቴ መልእክተኞች
ልኮ እንዲህ አለው ፥ "ሚስቴን ሚካልን መልስ
ልኝ ፤ እኔ እርስዋን ለማግባት የእንድ መቶ ፍል
ስጥኤሜውያን ሸለፈት ከፍያለሁ" አለው ።
15 ስለዚህም ኢያቡስቴ መልእክተኛ በመላክ
ሚካልን የላዊሽ ልጅ ከሆነው ከባልዋ ከፓልጢ
ኤል ልጅ አስወሰዳት ፤ 16 ባልዋ ፓልጢኤልም
እያለቀሰ እስከ ባሑሪም ከተማ ድረስ ተከተ
ላት ፤ ነገር ግን አበኔር "ወደ ቤትህ ተመለስ!"
ባለው ጊዜ ተመለሰ ።
17 አበኔር ወደ እስራኤል መሪዎች ሄዶ እን
ዲህ አላቸው ፥ "ዳዊት የእናንተ ንጉሥ እንዲ
ሆን ለብዙ ጊዜ ተመኝታችሁ ነበር ፤ 18 እነሆ
አሁን ጥሩ አጋጣሚ አግኝታችኋል ፤ ደግሞም
እግዚአብሔር 'በአገልጋዬ በዳዊት አማካይነት
ሕዝቤን እስራኤልን ከፍልስጥኤማውያንና ከሌ
ሎቹም ጠላቶቻቸው እጅ በመታደግ አድናለሁ'
ሲል ተናግሮ እንደነበር አስታውሱ ። 19 አበኔር
ሰብንያም ነገድ ሕዝብም ይህንኑ ተናገረ ፤ ከዚ
ያም በኋላ የብንያምና የእስራኤል ሕዝብ ሰማ
ድረግ የተስማሙበትን ጕዳይ ሰዳዊት ለመንገር
ወደ ኬብሮን ሄደ ።
20 አበኔር ሃያ ሰዎችን አስከትሎ ዳዊት ወዳ
ሰበት ወደ ኬብሮን በመጣ ጊዜ ዳዊት ግብዣ
አደረገላቸው ፤ 21 አበኔርም ዳዊትን "እነሆ
አሁን ሄጀ መላው እስራኤል የእንተ ደጋፊዎች
እንዲሆኑ አደርጋለሁ ፤ ሁሉም የእንተን ንጉሥ
ነት እምነው ይቀበላሉ ፤ አንተም የፈለግኸውን
ሁሉ ታገኛለህ ፤ በምድሪቱ ሁሉ ላይ ገዥ ትሆ
ናለህ" አለው ፤ ዳዊትም ለአበኔር አስተማማኝ
ዋስትና ከሰጠው በኋላ እንዲሄድ አሰናበተው ።

አበኔር ተገደለ

22 ጥቂት ዘግየት ብሎ ኢዮአብና የቀሩት የዳ
ዊት ባልሟሎች የሆኑ ባለሥልጣናቸው ብዙ
ምርኮ ካገኙበት ወረራ ተመለሱ ፤ ይሁን እንጂ
አበኔር በዚያን ጊዜ ከዳዊት ጋር በኬብሮን አል
ነበረም ፤ ምክንያቱም ዳዊት አስተማማኝ ዋስ
ትና ሰጥቶ ልኮት ነበር ፤ 23 ኢዮአብና ተከታ
ዮቹ በደረሱም ጊዜ አበኔር ወደ ንጉሥ ዳዊት
መጥቶ አስተማማኝ ዋስትና ካገኘ በኋላ ተመ
ልሶ መሄዱ ለኢዮአብ ተነገረው ። 24 ስለዚህም
ኢዮአብ ወደ ንጉሡ ቀርቦ እንዲህ አለው ፥
"ይህ ያደረግኸው ነገር ምንድን ነው? አበኔር
ወደ አንተ መጥቶ ሳለ እንዲሁ በቀላሉ ያሰናበ
ትከው ስለምንድን ነው? 25 እርሱ ወደዚህ የመ
ጣው አኮ አንተን ለማታለልና ምን እንደምት
ሠራ ፥ የት እንደምትሄድ ለመስለል ነው ፤ አን
ተም ይህን በአርግጥ ታውቃለህ!"
26 ኢዮአብ ከዳዊት ፌት ወጥቶ ከሄደ በኋላ
አበኔርን ያመጡት ዘንድ መልእክተኞች ላከ ፤
እነርሱም ከሲራ የውሃ ጕድጓድ አጠገብ መል
ስው አመጡለት ፤ ዳዊት ግን ስለዚህ ጕዳይ
ምንም የሚያውቀው ነገር አልነበረም ። 27 አበ
ኔር ወደ ኬብሮን በደረሰ ጊዜ ኢዮአብ በግል
ሊያነጋግረው የፈለገ በመምሰል ወደ ቅጽሩ በር
ገለል አድርጎ ወሰደው ፤ አዚያም ሆዱን ወግቶ
ገደለው ፤ ኢዮአብ ይህን ያደረገበት ምክንያት
አበኔር ቀደም ብሎ ወንድሙን አሣሄልን ስለገ
ደለበት ስመበቀል አሰቦ ነበር ። 28 ዳዊትም የአ
በኔርን መገደል በሰማ ጊዜ እንዲህ አለ ፥ "እኔና
በንጉሣዊ ግዛቴ ውስጥ ያሉት ሕዝብ ለዘ አበ
ኔር መገደል ከደሙ ንጹሓን መሆናችንን እግዚ
አብሔር ያውቃል ። 29 ስለዚህም ቅጣቱ በኢዮ
አብና በቤተሰቡ ላይ ይውረድ! በዘመናት ሁሉ
ከቤተሰቡ የአባለ ዘር ወይም አሥቃቂ የሆነ

3:9-10 ፡- 1ሳሙ. 15:28 ። 3:14 ፡- 1ሳሙ. 18:27 ።

የቆዳ በሽታ ያለበት ሰው አይጥፋ! እንዲሁም አካለ ስንኩል የሆነ ሰው፥ በጦር ሜዳ የሚሞት ወይም የሚበላው አጥቶ የሚራብ ሰው አይ ታጣ!” 30በዚህ ዐይነት ኢዮአብና ወንድሙ አቢሻይ ወንድማቸውን ሀማሄልን በገባዖን በተደ ረገው ጦርነት ስለገደለ በአበኔር ላይ የበቀል እርምጃ ወሰዱበት።

አበኔር ተቀበረ

31ከዚህ በኋላ ዳዊት በሐዘን ልብሳቸውን ቀደው፥ ማቅ ለብሰው ለአበኔር እንዲያለቅሱ ኢዮአብንና የእርሱ ተከታዮች የሆኑትን ሰዎች አዘዘ፤ በቀብር ሥነ ሥርዓቱም ላይ ንጉሥ ዳዊት ራሱ እስከሬኑን ተከትሎ ሄደ፤ 32አበኔር በኬብሮን ተቀበረ፤ በመቃብሩም ላይ ንጉሡ ድምፁን ከፍ አድርጎ አለቀሰ፤ ሕዝቡም ሁሉ እርሱን በማየት በመረረ ሁኔታ አለቀሱ፤ 33ዳዊ ትም ለአበኔር ሐዘኑን በቅኔ ሲገልጥ እንዲህ አለ፥

“አበኔር ስለምን እንደሞኝ ሰው ሞተ?
34እጆቹ አልታሰሩም፤
እግሮቹም አልታበቱም፤
ታዲያ በዚህ ሁኔታ ሳለ
በወንጀለኞች እጅ እንደሚገደል
እንዴት ተገደለ?”

ሕዝቡም ሁሉ ስለ እርሱ እንደገና አለቀሱ።

35ሕዝቡም ቀኑን ሙሉ ዳዊት እህል ይቀ ምስ ዘንድ ለማግባባት ምክሩ፤ እርሱ ግን “የዛ ሬያቱ ጀንበር ሳትጠልቅ እህል ብቀምስ እግዚ አብሔር በሞት ይቅጣኝ!” ሲል ማለ። 36ሕዝ ቡም ይህን ነገር ተመልክተው ደስ አላቸው፤ በእርግጥም ንጉሡ ያደረገው ነገር ሁሉ ሕዝ ቡን ደስ አሰኛቸው። 37የዳዊት ሰዎችና መላው የእስራኤል ሕዝብ በእበኔር ሞት ንጉሥ ዳዊት ምንም ያልተባበረ መሆኑን ተገነዘቡ። 38ንጉሡም ባለሟሎቹ ለሆኑት ባለሥልጣኖች እንዲህ አለ፥ “በዛሬው ቀን በእስራኤል ታላቅ መሪ አንደሞተ አታስተውሱምን? 39ምንም እንኳ እኔ እግዚአብሔር መርጦ የሾመኝ ንጉሥ ብሆንም ዛሬ ደካማነት ተሰምቶኛል፤ እነዚህ የጸሩያ ልጆች በእኔ ላይ እጅግ የበረቱ ፀመፀ ኞች ሆነውብኛል፤ እነዚህን ነፍሰ ገዳዮች አግ ዚአብሔር ራሱ የሚገባቸውን ቅጣት ይሰጣ ቸው።”

ምዕራፍ 4

ኢያቡስቴ ተገደለ

1የሳኦል ልጅ ኢያቡስቴ አበኔር በኬብሮን መገደሉን በሰማ ጊዜ እጅግ ፈራ፤ የእስራኤ ልም ሕዝብ ሁሉ በድንጋጤ ተሸበሩ፤ 2ኢያቡ ስቴ የወራሪ ጭፍራ ቡድን መሪዎች የሆኑ ሁለት መኰንኖች ነበሩት፤ እነርሱም ክብንያም ነገድ የበኤሮት ተወላጆች የሆኑት የሪሞ ልጆች በዓንና ሬካብ ነበሩ፤ በኤሮት የብንያም ክፍል እንደሆነች ይታሰብ ነበር፤ 3የበኤሮት የመጀመ ሪያዎቹ ነዋሪዎችም ወደ ጊታይም ተሰደው ከዚያን ዘመን ጀምሮ የሚኖሩት በዚያው ነበር።

4ሴላው የሳኦል ዘር የዮናታን ልጅ መፊቦ ሼት ሲሆን፥ እርሱ ሳኦልና ዮናታን በተገደሱ ጊዜ ገና የአምስት ዓመት ልጅ ነበር፤ የእነር ሱን ሞት የሚገልጠው ወሬ ከኢይዝራኤል ከተማ በተነገረ ጊዜ ሞግዚቱ እርሱን ይዛ ሸሸች፤ ነገር ግን በጥድፍያ በምትሸሽበት ጊዜ ከእጅዋ ወደቀ፤ ከዚህም የተነሣ ሽባ ሆነ።

5ሬካብና በዓና ወደ ኢያቡስቴ ቤት በመ ሄድ እኩለ ቀን ላይ ደረሱ፤ እርሱም በዚያን በዓት የቀትር ጊዜ ዕረፍት በማድረግ ላይ ነበር፤ 6ስንዴ እያበጠሪች በሸር ላይ ተቀምጣ የነበረች እንዲት ሴት ታንቀላፋ ነበር፤ ስለዚ ህም ሬካብና በዓና በቀስታ አልፈው ገቡ፤ 7ከገ ቡም በኋላ ወደ ኢያቡስቴ መኝታ ክፍል ዘለቁ፤ እርሱም በአልጋ ላይ ተኝቶ ሳለ ወግ ተው ገደሉት፤ ራሱንም ቈርጠው ወሰዱ፤ ሴሊ ቱንም ሁሉ በመንዝ የዮርዳኖስን ሸለቆ አል ፈው ሄዱ፤ 8የኢያቡስቴንም ራስ በኬብሮን ለን በረው ለንጉሥ ዳዊት ካቀረቡ በኋላ እንዲህ አሉ፥ “ሊገድልህ ይመኝ የነበረው የጠላትህ የሳኦል ልጅ የኢያቡስቴ ራስ ይኸውልህ! ንጉሥ ሆይ! ዛሬ በሳኦልና በቤተሰቡ ላይ የበ ቀል እርምጃ እንድትወስድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖአል።”

9ዳዊትም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፥ “ከልዩ ልዩ እደጋ ባዳነኝ በሕያው እግዚአብ ሔር ስም እምላለሁ! 10በጺቅላግ ወደ እኔ መጥቶ ስለ ሳኦል ሞት የነገረኝ መልእክተኛም እንደዚሁ መልካም ዜና ያመጣልኝ መስሎት ነበር፤ እኔ ግን እርሱን ይዤ አሰገደልሁት፤ መልካም ዜና ነው ብሎ ላመጣውም ወሬ የከፈ ልሁት ዋጋ ይኸው ነበር! 11ታዲያ በገዛ ቤቱ ተኝቶ የነበረውን ንጹሕ ሰው ለገደሉት ሰዎ ችማ የሚከፈላቸው የበቀል ዋጋ ምን ያህል የከፋ ይሆን! ስለዚህም እርሱን በመግደላችሁ ምክንያት እኔ በእናንተ ላይ የበቀል እርምጃ በመውሰድ ከምድር ላይ ጠራርጌ አጠፋችኋ ላሁ!” 12ወዲያውም ዳዊት እንዲገድሉአቸው ለመታደሮቹ ትእዛዝ አስተላለፈ፤ ወታደሮቹም ሬካብንና በዓናን ገደሉአቸው፤ እጃቸውንና እግ ራቸውንም ቈርጠው በኬብሮን በሚገኘው ኩሬ አጠገብ እንጨት ላይ ሰቀሉአቸው፤ የኢያቡስ ቴንም ራስ ወስደው በዚያው በኬብሮን በሚገ ኘው በአበኔር መቃብር ውስጥ ቀበሩት።

4፥4 ፤ 2ሳሙ. 9፥3። 4፥10 ፤ 2ሳሙ. 1፥1-16።

ምዕራፍ 5

ዳዊት የእስራኤልና የይሁዳ ንጉሥ ሆነ
(1 ዜ.መ. 11፡1-9፡ 14፡1-7)

1 ከዚህ በኋላ የእስራኤል ነገዶች ሁሉ በኬ
ብሮን ወደንዘረው ወደ ዳዊት ሄደው እንዲህ
አሉት ፡ "እነሆ እኛ የአጥንትህ ፍላጭ ፡ የሥ
ጋህ ሥራው የሆንን ወገኖችህ ነን ፤ 2 ከአሁን
በፊት ሳኦል የእኛ ንጉሥ በነበረ ጊዜ እንኳ
በሠርነት እስራኤልን የምትመራ እንተ ነበርክ ፤
እንዲሁም ሕዝቡን እስራኤልን እንድትመራና
በእስራኤልም ላይ እንድትነግሥ እግዚአብሔር
ቃል ገብቶልሃል ።" 3 እንግዲህ የእስራኤል መሪ
ዎች ሁሉ በኬብሮን ወደ ነበረው ወደ ዳዊት
የመጡት በዚህ ዐይነት ሁኔታ ነበር ፤ እርሱም
ከእነርሱ ጋር በእግዚአብሔር ፊት የቃል ኪዳን
ስምምነት አደረገ ፤ እነርሱም ቀብተው በእስራ
ኤል ላይ እንዲነግሡት ። 4 ዳዊት በነገሠበት ጊዜ
ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ነበር ፤ ለሰቅላላ የነገሠ
በት ዘመን አርባ ዓመት ነበር ። 5 ይኸውም በኬ
ብሮን ሳለ በይሁዳ ላይ ሰባት ዓመት ተኩል ፡
በኢየሩሳሌም ሆኖ በይሁዳና በመላው እስራኤል
ላይ ሠላሳ ሦስት ዓመት ነገሠ ።

6 ንጉሥ ዳዊትና ተከታዮቹ በኢየሩሳሌም
ላይ አደጋ የሚጥሉበት ጊዜ ደረሰ ፤ በዚያ የሚ
ኖሩ ኢያቡሳውያን ግን ዳዊት በሠርነት ድል
ነሥቶ ከተማይቱን የሚይዝ አልመሰላቸውም
ነበር ፤ ስለዚህም ዳዊትን "ከቶ ወደዚህ አትገ
ባም ! ዐይነ ስውሮችና እንካሶች እንኳ ወደ ከተ
ማይቱ እንዳትገባ ሊያደርጉህ ይችላሉ" አሉት ፤
7 ዳዊት ግን በጽዮን የሠሩትን ምሽጋቸውን ያዘ ፤
እርስዋም "የዳዊት ከተማ" ተብላ ተጠራች ።

8 በዚያን ቀን ዳዊት ተከታዮቹን እንዲህ
አለ ፡ "እኔ የምጠላቸውን ያህል ከእናንተ መካ
ከል ኢያቡሳውያንን የሚጠላ ይኖራልን? ዋላቻ
ውስ እንርሱን ለመግደል ያበቃዋልን? እንግዲያ
ውስ በውሃው መተላለፊያ በኩል ሄዳችሁ እንዚ
ያን ምስክን የሆኑ ዐይነ ስውሮችና እንካሶች
ግደሉ ፡" በዚህም ምክንያት "በይነ ስውሮችና
እንካሶች ወደ እግዚአብሔር ቤተ መግባት አይ
ፈቀድላቸውም" ተባለ ።

9 ዳዊት ምሽጉን ከያዘ በኋላ መኖሪያውን
በዚያው ስፍራ አደረገ ፤ እርስዋንም "የዳዊት
ከተማ" ብሎ ጠራት ፤ ከኮረብታው በስተ ምሥ
ራቅ በኩል በወፊር ከተደለደለው ስፍራ አን
ሥቶ በኮረብታው ዙሪያ ከተማይቱን ሠራ ።
10 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር
ስለነበር ዳዊት በየጊዜው እየበረታ ሄደ ።

11 ኪራም ተብሎ የሚጠራው የጢሮስ
ንጉሥ መልእክተኞችን ወደ ዳዊት ላከ ፤ ከእነ
ርሱም ጋር ለዳዊት ቤተ መንግሥት የሚሠሩ
ለት የዝግባ ግንድ የያዙ እናጢዎችና ግንበኞች
ነበሩ ፤ 12 ከዚህም ሁሉ የተነሣ እግዚአብሔር
የእስራኤል ንጉሥ አድርጎ እንዳጸናውና ሰሕዝ
ቡም ሲል መንግሥቱን እንዳበለጸገለት ዳዊት
ተገነዘበ ።

13 ዳዊት ከኬብሮን ወደ ኢየሩሳሌም ከተዛ
ወረ በኋላ ከሆፊት ይልቅ ብዙ ቍባቶችና ሚስ
ቶች ነበሩት ፤ ብዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆችም
ተወልደውለት ነበር ፤ 14 በኢየሩሳሌምም የተወ
ለዱት ልጆች ፡ ሻሙዓ ፡ ሾባብ ፡ ናታን ፡ ሰሎ
ሞን ፤ 15 ይብሐር ፡ ኤሊሹዓ ፡ ኔፌግ ፡ ያፊዓ ፡
16 ኤሊሻማዕ ፡ ኤልያዳዕና ኤሊፌሌት ነበሩ ።

ዳዊት ፍልስጥኤማውያንን ድል አደረገ
(1 ዜ.መ. 14፡8-17)

17 ዳዊት በእስራኤል ላይ መንገሡን ፍልስጥ
ኤማውያን ሰሙ ፤ ስለዚህም ሠራዊታቸው ዳዊ
ትን ለመማረክ ገሥግሦ ሄደ ፤ ዳዊት የእነርሱን
መምጣት በሰማ ጊዜ ወደ ተመሸገ ስፍራ
ወረደ ፤ 18 ፍልስጥኤማውያንም ደርሰው የራፋ
ይምን ሸለቆ በቍጥጥራቸው ሥር አደረጉ ፤
19 ዳዊትም "በፍልስጥኤማውያን ላይ አደጋ
ልጣልባቸውን? ድልንስ ትሰጠኛለህን?" ሲል
እግዚአብሔርን ጠየቀ ።

እግዚአብሔርም "አዎ በእነርሱ ላይ አደጋ
ጣልባቸው ፤ እኔ በእነርሱ ላይ ድልን እሰጥ
ለሁ" ሲል መለሰለት ።

20 ስለዚህም ዳዊት ወደ ባዓል ፈራጺም*
ወርዶ ፍልስጥኤማውያንን ድል ካደረገ በኋላ
"እግዚአብሔር በጠላቶቼ መካከል እንደጉርፍ
ሰባብሮ ገባ" አለ ፤ ስለዚህም የዚያ ስፍራ ስም
"ሳዓል ፈራጺም" ተብሎ ተጠራ ። 21 ፍልስጥ
ኤማውያን በሸሹ ጊዜ ጣዖቶቻቸውን ጥለው
ሄዱ ፤ ዳዊትና ተከታዮቹም ማርከው ወሰዱአ
ቸው ።

22 ከዚህ በኋላ ፍልስጥኤማውያን ወደ ራፋ
ይም ተመልሰው እንደገና ያዙአት ፤ 23 ዳዊትም
እንደገና እግዚአብሔርን ጠየቀ ፤ እርሱም እን
ዲህ ሲል መለሰለት ፡ "አሁን ካለህበት በኩል
በእነርሱ ላይ አደጋ አትጣል ፤ ነገር ግን ከወዲያ
ብኩል በስተ ኋላ በመዞር ከሾላ ዛፎች አጠገብ
ሆነህ በእነርሱ ላይ አደጋ ስመጣል ተዘጋጅ ።
24 በዛፎቹ ጫፍ ላይ የሰልፍ ጉዞ የመሰሰ ድምፅ
በምትሰማበት ጊዜ አደጋ ጣልባቸው ፤ ምክንያ
ቱም እኔ የፍልስጥኤማውያንን ሠራዊት ድል
ስመንሣት ቀድሜ በእንተ ፊት አልፋለሁ ፡"
25 ዳዊትም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ ፤
ፍልስጥኤማውያንንም ከጌባዕ እንሥቶ እስከ
ጌዜር ድረስ በመመለስ ስማቸውር ቻለ ።

1* 5፡20 ባዓል ፈራጺም ፡- በዕብራይስጥ "ሰባብር የገባ ጌታ" ማለት ነው ።
5፡4-5 ፡- ነገ. 2፡11 ፤ 1ዜ.መ. 3፡4 ፤ 29፡27 ። 5፡6 ፡- ኢያሱ 15፡63 ፤ መሳ. 1፡21 ።

ምዕራፍ 6

የቃል ኪዳኑ ታቦት ከአቢናዳብ
ቤት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ
(1 ዜ.መ. 13፥1-14፤ 15፥25–16፥6,43)

1 ዳዊት ከመላው እስራኤል የተመረጡ ፴ ሺ
ምሩ ሠላሳ ሺ የሚሆኑ ምርጥ ወታደሮች በአን
ድነት አሰባሰበ። 2 ዙፋኑ በኪሩቤል ላይ የሆ
ነው የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ስም ያለበ
ትን የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ያመ
ጡም ዘንድ በይሁዳ ወደሚገኘው ወደ በዓላ
ይዘአቸው ሄደ፤ 3 እነርሱም የቃል ኪዳኑን
ታቦት በኮረብታ ላይ ከሚገኘው ከአቢናዳብ
ቤት አመጥተው በአዲስ ሠረገላ ላይ አኖሩት፤
ዑዛና አሒዮ ተብለው የሚጠሩት የአቢናዳብ
ልጆች ሠረገላውን እየመሩ በሚጓዙበት ጊዜ፥
4 እሕዮ ከታቦቱ ፊት ቀድሞ ይሄድ ነበር።
5 ዳዊትና እስራኤላውያን ሁሉ የበገና፥ የመሰ
ንቆ፥ የከበሮ፥ የጸናጽልና የቃሎም ድምፅ እያ
ሰሙ ለእግዚአብሔር ክብር በመዘመር በሙሉ
ኀይላቸው ያሸበሽቡ ነበር።

6 ናኮን ተብሎ ወደሚጠራውም አውድማ
በደረሱ ጊዜ ሠረገላውን የሚሰቡት በሬዎች
ተደናቀፉ፥ ዑዛም እጁን ዘርግቶ የቃል ኪዳኑ
ታቦት እንዳይወድቅ ደገፈ፤ 7 እግዚአብሔር
አምላክም ወዲያውኑ ተቈጥቶ ስለ ድፍረቱ
ዑዛን ገደለው፤ ስለዚህም ዑዛ በዚያው በቃል
ኪዳን ታቦት አጠገብ ሞተ፤ 8 ከዚያን ጊዜ ጀም
ሮም የዚያ ሰፍራ ስም "ፌሬጽዑዛ"* እየተባለ
ሲጠራ ይኖራል፤ እግዚአብሔር በቍጣ ተነሣ
ሥቶ ዑዛን በመግደሉ ዳዊት እጅግ ተበሳጨ።

9 ከዚያም በኋላ ዳዊት እግዚአብሔርን ስለ
ፈራ "እንዲህ ከሆነማ የቃል ኪዳኑን ታቦት እን
ዴት ልወስደው እችላለሁ?" አለ። 10 ስለዚህም
ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም ላለመውሰድ ወሰነ፤
ይህንንም በማድረግ ፈንታ ከመንገድ መልሶ
የጌት ኩጥማ ነዋሪ ወደሆነው ዖቤድኤዶም
ተብሎ ወደሚጠራው ሰው ቤት አስገባው፤
11 እዚያም ሦስት ወር ተቀመጠ፤ እግዚአብሔ
ርም ዖቤድኤዶምንና ቤተሰቡን ባረከ።

12 በቃል ኪዳኑ ታቦት ምክንያት እግዚአብ
ሔር የዖቤድኤዶምን ቤተሰብና ያለውን ነገር
ሁሉ እግዚአብሔር የባረከለት መሆኑን ንጉሥ
ዳዊት ሰማ፤ ስለዚህም የቃል ኪዳኑን ታቦት
በታላቅ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ሊወስደው በማ
ሰብ ወደ ዖቤድኤዶም ቤት ሄዶ አመጣው።
13 የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙት ሰዎች
ስድስት እርምጃ በተራመዱ ቍጥር ዳዊት እንደ
ገና እያሰቆመ አንድ ኮረማና አንድ የሰባ ጥጃ
ለእግዚአብሔር መሥዋዕት በማድረግ ያቀርብ
ነበር፤ 14 ዳዊት ከበፍታ የተሠራ ተሣጭን ሐር
በወገቡ ዙሪያ ታጥቆ እግዚአብሔርን በማክበር
በሙሉ ኀይሉ ይጨፍር ነበር፤ 15 በዚህም ዐይ
ነት ዳዊትና መላው እስራኤል በደስታ እልል
እያሉና የመለከት ድምፅ እያሰሙ፥ የቃል ኪዳ
ኑን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም ይዘው ሄዱ።

16 ታቦቱን ይዘው ወደ ከተማ በሚገቡበት
ጊዜ የሳኦል ልጅ ሚካል በመስኮት ተመለከ
ተች፤ ንጉሡ ዳዊት እየዘለለ ሲያሸበሽብ አይ
ታም ናቀቸው፤ 17 ታቦቱንም አምጥተው ዳዊት
ባዘጋጀለት ድንኳን ውስጥ በተመደበለት ስፍራ
አኖሩት፤ ከዚህም በኋላ ዳዊት የሚታጠለውን
መሥዋዕትና ለደኅንነት የሚሆነውንም የኅብ
ረት መሥዋዕት ሁሉ ለእግዚአብሔር አቀረበ።
18 መሥዋዕት ማቅረቡንም በፊጸመ ጊዜ የሠራ
ዊት ጌታ በሆነው በእግዚአብሔር ስም ሕዝቡን
ባረከ፤ 19 ለሁሉም ምግብ አደላቸው፤ በእስራ
ኤል ለሚገኘው ለእያንዳንዱ ወንድና ሴት አን
ዳንድ ኅብስት፥ እንዳንድ ቍራጭ የተጠበሰ
ሥጋና እንዳንድ የዘቢብ ጥፍጥፍ ሰጠ፤ ከዚ
ያም በኋላ ሁሉም ወደየቤታቸው ሄዱ።

20 ዋቂት ዘማየት ብሎም ዳዊት ቤተሰቡን
ሰላም ለማለት ወደ ቤት ገባ፤ የሳኦል ልጅ
ሚካልም ልትቀበለው ወጣችና "የእስራኤል
ንጉሥ ዛሬ ትልቅ ስም አግኝቶአል! በመኳን
ንቱ ገረዶች ፊት እንደ አበደ ሰው እርቃኑን
ገልጦአል!" አለችው።

21 ዳዊትም እንዲህ ሲል መለሰላት፥ "እኔ
የጨፈርሁት የሕዝብ የእስራኤል መሪ ያደርገኝ
ዘንድ በአባትሽና በቤተሰቡ ፈንታ ለመረጠኝ
እግዚአብሔር ክብር ነው፤ አሁንም ቢሆን እር
ሱን ለማክበር ከመጨፈር አልገታም፤ 22 ከዚ
ህም የባሰ ራሴን አዋርዳለሁ፤ ለአንቺ እንደሚ
መስልሽ በወይንሽ ፊት የተናቅሁ ብሆንም በእነ
ርሱ ፊት ራስህን አዋረደህ ብለሽ በተናገርሽባ
ቸው ልጃገረዶች ዘንድ እጅግ የተከበርኩ እሆና
ለሁ።"

23 ከዚህም የተነሣ የሳኦል ልጅ ሚካል
ምንም ልጅ ሳትወልድ መካን ሆና ቀረች።

ምዕራፍ 7

ናታን ለዳዊት የተናገረው ቃል
(1 ዜ.መ. 17፥1-15)

1 እግዚአብሔር ከጠላቶቹ ሁሉ ሰለጠበቀው
ንጉሥ ዳዊት በዚታ መንግሥቱ ተደላድሎ በሰ
ላም ይኖር ነበር። 2 ከዚህም በኋላ ንጉሡ ነቢዩ
ናታንን "እነሆ እኔ ከዝግባ እንጨት በተሠራ
ቤት ውስጥ እየኖርሁ፥ የእግዚአብሔር የቃል
ኪዳን ታቦት ግን በድንኳን ውስጥ ይኖራል!"
አለው።

2* 6፥8 ፌሬጽ ዑዛ፦ በዕብራይስጥ "የዑዛ በሳራት" ማለት ነው።
6፥2፦ ዘጸ. 25፥22። 6፥3፦ 1ሳሙ. 7፥1-2። 6፥11፦ 1ዜ.መ. 26፥4-5። 6፥19-20፦ 1ዜ.መ. 16፥43።

3 ናታንም “እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ስለ
ሆነ በልብህ ያሰብኸውን ሁሉ አድርግ” ሲል
መለሰለት። 4 ነገር ግን በዚያን ሌሊት እግዚአብ
ሔር ናታንን እንዲህ አለው፥ 5 “ሂድና ለአገል
ጋዬ ለዳዊት እኔ ስለአርሱ የምለውን እንዲህ
ብለህ ንገረው፥ ‘እኔ የምኖርበትን ቤተ መቅደስ
የምትሠራልኝ አንተ አይደለህም፤ 6 የእስራኤ
ልን ሕዝብ ከግብጽ በመታደግ ካዳንኩበት ጊዜ
አንሥቶ እስከ አሁን ድረስ በድንኳን ውስጥ
ሆኜ በየስፍራው ስዘዋወር ኖርሁ እንጂ በቤተ
መቅደስ ውስጥ አልኖርሁም፤ 7 ከእስራኤል
ሕዝብ ጋር በተንቀሳቀስኩበት ጊዜ ሁሉ ከሾምሁአ
ቸው መሪዎች መካከል ማንንም ከዝግባ እን
ጨት ቤተ መቅደስ እንዲሰራልኝ አልጠየቅ
ሁም።’

8 “ስለዚህም ለአገልጋዬ ለዳዊት እኔ የሠራ
ዊት ጌታ እግዚአብሔር የምለውን እንዲህ
ብለህ ንገረው፥ ‘እኔ አንተን የበግ መንጋ ከምት
ጠብቅበት መስክ እንሥቼ የሕዝቤ የእስራኤል
መሪ እደረግሁህ፤ 9 በሄድህበት ስፍራ ሁሉ እኔ
ከአንተ ጋር ነበርሁ፤ ወደፊትም በተራመድህ
መጠን ጠላቶችህን ድል አደረግሁልህ፤ ገና
ደግሞ በዓለም እንደታወቁት ታላላቅ መሪዎች
ዝነኛ አደርግሃለሁ። 10 ለሕዝቤ ለእስራኤል
እንድ ሰፍራ መርጫ በዚያ እንዲኖሩ አድርጌአ
ለሁ፤ በዚያም ሲኖሩ ከእንግዲህ ወዲህ ጭቈና
አይደርሰባቸውም፤ 11 ወደዚህች ምድር ገብ
ተው የሚያስተዳድሩአቸውን መሳፍንት ከሾም
ሁላቸው ጊዜ አንሥቶ ጨካኞች የሆኑ አሕዛብ
በየጊዜው እደጋ ይጥሉባቸው ነበር፤ ከአንግ
ዲህ ወዲህ ግን እንዲህ አይሆንም፤ ከጠላቶችህ
ሁሉ ሰለሳም ልጠብቅህና ቤትህን ሰማጽናት
ተተኪ ዘር ልሰጥህ ቃል አገባለሁ፤ 12 አንተም
ሞተህ ሥጋህ በቀድሞ አባቶችህ መካነ መቃ
ብር በሚያርፍበት ጊዜ ከልጆችህ አንዱን አነ
ግሣለሁ፤ መንግሥቱንም አጸናለታለሁ፤
13 ቤተ መቅደስ የሚሠራልኝም አርሱ ነው፤
ሥረወ መንግሥቱም ሳይቋረጥ ስዘላለም የሚቀ
ጥል እንዲሆን አደርጋለሁ፤ 14 እኔ አባት እሆን
ዋለሁ፤ አርሱም ልጄ ይሆናል፤ ስሕተት በሚ
ፈጽምበትም ጊዜ አባት ልጁን እንደሚቀጣ
እቀጠዋለሁ፤ 15 ይሁን እንጂ በአርሱ ቦታ
እንተ ትነግሥ ዘንድ ባስወገድሁት በሳኤል ላይ
እንዳደረግሁ ዘላለማዊ ፍቅሬን ከአርሱ አላር
ቅም። 16 ምን ጊዜም ቢሆን የዙፋንህ ወራሽ
የሚሆን ዘር አታጣም፤ መንግሥትህንም ስዘላ
ስም እጸናዋለሁ፤ ሥረወ መንግሥትህም ስዘላ
ስም ይጸናል።’”

17 በዚህ ዐይነት ናታን እግዚአብሔር የነገረ
ስትን ሁሉ ስዳዊት ነገረው።

ዳዊት ለእግዚአብሔር ያቀረበው የምስጋና ጸሎት
(1 ዜ.መ. 17፥16-27)

18 ከዚህ በኋላ ንጉሥ ዳዊት እግዚአብሔር
ወደሚመለከበት ድንኳን ሄደ፤ ተቀምጦም እን
ዲህ ሲል ጸለየ፥

“ልዑል እግዚአብሔር ሆይ! እኔ ይህን
ሁሉ ነገር ታደርግልኝ ዘንድ የሚገባኝ ሰው
እይደለሁም፤ ቤተሰቤም ስዚህ የበቃ አይደ
ለም፤ 19 ልዑል እግዚአብሔር ሆይ! እነሆ አሁ
ንም እንደገና የበለጠ ነገር እያደረግህ ነው፤
በሚመጡት ዘመናት ስሚኖሩትም ስዘሮቼ
ሁሉ ብዙ የተስፋ ቃል ሰጥተሃል፤ ልዑል እግ
ዚአብሔር ሆይ! እነሆ ሰብአዊ ፍጡር ይህን
ሁሉ እንዲያስተውል ፈቃድህ ሆኖአል! 20 እን
ግዲህ ስአንተ ከዚህ በላይ ምን መናገር አችላ
ለሁ? እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! አንተ አእን
አገልጋይህን ታውቀኛለህ፤ 21 ይህን ታደርግ
ዘንድ ፈቃድህና ዕቅድህ ሆኖአል፤ ይህን ሁሉ
ታላቅ ነገር ያደረግኸው አእን ስማስተማር
ነው። 22 ልዑል እግዚአብሔር ሆይ! አንተ እን
ዴት ታላቅ ነህ! ከቶም አንተን የሚመስል
የለም፤ ምን ጊዜም አንተ ብቻ አምላክ እንደሆ
ንህ አናውቃለን። 23 ወገኖችህ ታደጋቸው
ዘንድ ከባርነት እንደዋጀሃቸው እንደ አስራኤል
ያለ ሕዝብ ከቶ የለም፤ ለአገርህ ሰሳደረግህላ
ቸው ታላቅና አስደናቂ ነገሮች ገናናነትህ በዓ
ለም ሁሉ ተሰምቶአል። ወገኖችህ ይሆኑ ዘንድ
ከግብጽ ነፃ ያወጣሃቸው ሕዝብህ ወደ ፊት በተ
ራመዱ መጠን ሌሎችን ሕዝቦችና አማልክቶች
ቸውን ጭምር ከፈታቸው ኃይልህ አስረርህ።
24 አስራኤልንም ስዘላለም ሕዝብህ አደረግህ፤
ጌታ ሆይ! አንተም አምላካቸው ሆንህ።

25 “አሁንም አግዚአብሔር አምላክ ሆይ!
ስስ አእና ስስ ዘሮቼ የተናገርከውን የተሰፋ ቃል
ሁሉ ፈጽም፤ አደርጋለሁ ያልከውንም ሁሉ
አድርግ። 26 ስምህ ታላቅ ይሆናል፤ ሕዝብም
ሁሉ ስዘላለም ‘የሠራዊት ጌታ አግዚአብሔር
የአስራኤል አምላክ ነው’ ይላሉ፤ ሥረወ መንግ
ሥቴንም ስዘላለም ታጸናዋለህ፤ 27 የአስራኤል
አምላክ የሆንህ የሠራዊት ጌታ ሆይ! አገልጋ
ይህ ስሆንሁት ለእኔ ይሆን ሁሉ ስስገነዮኸልኝና
ዘሮቼንም እንደምታነግሣቸው ስስነገርከኝ ይህን
የምስጋና ጸሎት ወደ አንተ ስማቅረብ ድፍረት
አግኝቻለሁ።

28 “አሁንም ልዑል እግዚአብሔር ሆይ!
አንተ አምላክ ነህ፤ የሰጠኸውንም የተሰፋ ቃል
ዘወትር ትፈጽማለህ፤ እነሆ አሁንም ይህን አሰ
ደናቂ የተስፋ ቃል ለእኔ ሰጥተኸኛል፤

7፥12 ፦ መዝ. 89፥3-4፤ 132፥11፤ ዮሐ. 7፥42፤ ሐ.ሥ. 2፥30። 7፥14 ፦ መዝ. 89፥26-27፤ 2ቆር. 6፥18፤ ዕብ. 1፥5።
7፥16 ፦ መዝ. 89፥36-37። 7፥23 ፦ ዘዳ. 4፥34።

29 በለማቅረጥ የአንተን ሞገስ ያገኙ ዘንድ ዘሮቹን እንድትባርክ እስምንሃለሁ ፤ ልውል እግዚአ
ብሔር ሆይ! አንተ ይህን የተሰፋ ቃል ሰጥተኸ
ኛል ፤ በረከትህም በዘሮቼ ላይ ለዘላለም ይኖ
ራል ።”

ምዕራፍ 8

ዳዊት በጦርነት የተቀዳጃቸው ድሎች
(1 ዜ.መ. 18፥1-17)

1 ጥቂት ዘግየት ብሎም ንጉሥ ዳዊት በፍል
ስጥኤማውያን ላይ አንደገና እደጋ በመጣል
ድል እደረጋቸው ፤ “ሜቴግ እማ” የተባለችው
ንም ከተማ ከእነርሱ ቍጥጥር ሥር ነፃ እንድት
ሆን አደረገ ።

2 ቀጥሎም ንጉሥ ዳዊት ሞአባውያንን ድል
አደረገ ፤ እስረኞቹ በመሬት ላይ እንዲጋደሙ
እድርጎ ከየሦስቱ ሰዎች ሁለት ሁለቱ በሞት
እንዲቀጡ አደረገ ። ስለዚህም ሞአባውያን የእ
ርሱ ተገዥዎች በመሆን ያገብሩለት ነበር ።

3 ከዚያም በኋላ ዳዊት የሶርያ ግዛት የሆነችው
የጾባ ንጉሥ የሆነውን የረሐብን ልጅ ሀዳድዔዜ
ርን ድል አደረገ ፤ ሀዳድዔዜር ድል በተመታበ
ትም ጊዜ በሳይኛው ኤፍራጥስ ወንዝ የሚገኘ
ውን ግዛቱን ለማሰመለስ በጉዞ ላይ ነበር ። 4 ዳዊ
ትም ከሀዳድዔዜር አንድ ሺ ሰባት መቶ ፈረሰኞች
ንና ሃያ ሺ አግረኛ ወታደሮችን ማረከበት ፤ ሠረ
ገላ ለመሳብ የሚያገለግሉ አንድ መቶ ፈረሶችን
አሰቀርቶ ፥ የቀሩትን ፈረሶች በሙሉ ቋንጃቸውን
ቈርጦ ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆኑ እደረገ ።

5 በደማስቆ የሚኖሩ ሶርያውያንም ንጉሥ
ሀዳድዔዜርን ለመርዳት ሠራዊት በላከ ጊዜ
ዳዊት አደጋ ጥሎ ሃያ ሁለት ሺ ጭፍሮቸን
ገደለ ። 6 ከዚያም በኋላ በግዛታቸው ውስጥ
የጦር ሰፈሮችን አቋቋመ ፤ ሶርያውያንም ለአ
ርሱ ተገዥዎች ሆነው ገብሩለት ፤ እግዚአብሔ
ርም ዳዊትን በሄደበት ሰፍራ ሁሉ ድልን እንዲ
ቀዳጅ አደረገው ። 7 ዳዊት የሀዳድዔዜር መኳን
ንት ያነገቡአቸውን ከወርቅ የተሠሩ ጋሻዎችን
ማርኮ ወደ ኢየሩሳሌም መሰዳቸው ፤ 8 እንዲ
ሁም ሀዳድዔዜር ከሚያስተዳድራቸው ቤጣሕና
ቤሮታይ ተብለው ከሚጠሩት ከተሞች እጅግ
ብዙ የሆነ ነሐስ ወሰደ ።

9 የሐማት ንጉሥ ቶዒ ዳዊት የሀዳድዔዜርን
ሠራዊት በሙሉ ድል ማድረጉን ሰማ ። 10 ስለዚ
ህም ንጉሥ ሀዳድዔዜርን ድል በመንሣቱ ሰላም
ታና የደስታ መግለጫ ያቀርብለት ዘንድ ልጁን
ዮራምን ወደ ንጉሥ ዳዊት ላከው ፤ ቀደም
ሲልም ቶዒ በሀዳድዔዜር ላይ ጦርነት ሲያካ
ሄድ የነበረ ነው ፤ ዮራምም ከወርቅ ፥ ከብርና
ከነሐስ የተሠሩ ልዩ ልዩ ሰጦታዎችን ለዳዊት
ይዞለት ሄደ ። 11-12 ንጉሥ ዳዊትም ድል ካደረ
ጋቸው ከኤዶም ፥ ከሞአብ ፥ ከአሞን ፥ ከፍልስ
ጥኤምና ከአማሌቅ ከወሰደው ብርና ወርቅ ፥
እንዲሁም ከሀዳድዔዜር ከወሰደው ምርኮ ከፊ
ሉን ለይቶ ለእግዚአብሔር አገልግሎት እንዲ
ውል አደረገው ።

13 ዳዊት የጨው ሸለቆ ተብሎ በሚጠራው
ስፍራ ወሥራ ሰምንት ሺ ኤዶማውያንን ገድሎ
በተመለሰ ጊዜ ከምንጊዜውም ይበልጥ ዝናው
ገነነ ፤ 14 በመላው ኤዶም ብዙ የጦር ሰፈሮችን
አቋቋመ ፤ በዚያም የሚኖሩ ሕዝብ የእርሱ ተገ
ዥዎች ሆኑ ፤ እግዚአብሔር ዳዊትን በሄደበት
ሰፍራ ሁሉ ድልን እንዲቀዳጅ አደረገ ።

15 በዚህ ሀይነት ዳዊት የመላው አሰራኤል
ንጉሥ ሆኖ ሕዝቡ ዘወትር ትክክለኛ ፍትሕ
ማግኘት እንዲችሉ ጥረት ያደርግ ነበር ፤ 16 የጸ
ሩያ ልጅ ኢዮአብ የሠራዊቱ አለቃ ሲሆን የአ
ሒሉድ ልጅ ይሆሻፋጥ ታሪክ ጸሐፊ ነበር ፤
17 የአሒጦብ ልጅ ሳዶቅና የአብያታር ልጅ
አሒሜሌክ ካህናት ነበሩ ፤ ሠራያ ደግሞ የቤተ
መንግሥቱ ጸሐፊ ነበረ ፤ 18 የዮዳሄ ልጅ በናያ
የዳዊት ከብር ዘብ አዛዥ ነበር ፤ የዳዊትም
ልጆች አማካሪዎቹ[ነ] ነበሩ ።

ምዕራፍ 9

ዳዊትና መፊቦሼት

1 አንድ ቀን ዳዊት “ከሳኦል ቤተሰብ ከሞት የተረፈ ሰው አለን? ምናልባት ያለ እንደሆን ሰለ ዮናታን ሰል ቸርነት እደርግለታለሁ” አለ ።

2 ከሳኦል ቤተሰብ ጸባ የሚባል አንድ አገል
ጋይ ነበረ ፤ እርሱም ወደ ዳዊት እንዲሄድ ተነገ
ረው ፤ ዳዊትም “እንተ ጸባ ነህን?” ሲል ጠየ
ቀው ።

ጸባም “ጌታ ሆይ! እነሆ አገልጋይህ ነኝ” ሲል መለሰ ።

3 ንጉሡም “ለእግዚአብሔር ቃል በገባሁት መሠረት ቸርነት የማሳየው ከሳኦል ቤተሰብ ከሞት የተረፈ ሰው አለን?” ሲል ጸባን ጠየ
ቀው ።

ጸባም “ከዮናታን ወንዶች ልጆች አንዱ አሁንም በሕይወት አለ ፤ እርሱም እግሩ ሽባ ነው” ሲል መለሰ ።

4 ንጉሡም “የት ነው ያለው?” ሲል ጠየቀ ።

ጸባም “በሎዶባር በዓሚኤል ልጅ በማኪር ቤት ይገኛል” ሲል መለሰ ። 5 ስለዚህም ንጉሥ ዳዊት መፊቦሼትን ከሎዶባር አስመጣው ።

6 የሳኦል የልጅ ልጅ ፥ የዮናታን ልጅ መፊቦ
ሼት በመጣ ጊዜ በዳዊት ፊት ወደ መሬት ሰዋ
ብሎ እጅ በመንሣት አክብሮቱን ገለጠ ።

[ነ] 8፥18 አማካሪዎቹ ፦ አንዳንድ የጥንት ቅጂዎች “ካህናት ነበሩ” ይላሉ ።

8፥13 ፦ መዝ. 60 ። 9፥1 ፦ 1ሳሙ. 20፥15-17 ። 9፥3 ፦ 2ሳሙ. 4፥4 ።

ዳዊትም "መፊቦሼት!" ሲል ጠራው።
መፊቦሼትም "ጌታ ሆይ! እነሆ እገልጋይህ ነኝ!" ሲል መለሰ።
7ዳዊትም "አይዞህ አትፍራ! ስለ አባትህ ስለ ዮናታን ስል ቸርነት አደርግልሃለሁ፤ የአያ ትህ የሳኦል ይዞታ የነበረውን መሬት ሁሉ እመ ልስልሃለሁ፤ ዘወትርም በማእዴ ተቀምጠህ ትመገባለህ" አለው።
8መፊቦሼት እንደገና ወደ መሬት ሰጥ ብሎ እጅ በመንሣት "ጌታዬ ሆይ! እኔ እኮ ከሞተ ውሻ የምሻል አይደለሁም፤ ታዲያ የማይገባኝን ይህን ያህል ቸርነት የምታደርግልኝ ለምንድን ነው?" አለው።
9ከዚህ በኋላ ንጉሡ የሳኦልን አገልጋይ ጺባን ጠርቶ እንዲህ አለው፤ "የሳኦልና የቤተ ሰቡ ንብረት የነበረውን ማናቸውንም ነገር የጌ ታህ የልጅ ልጅ ለሆነው ለመፊቦሼት አሰጣ ለሁ፤ 10እንተ፥ ወነዶች ልጆችህና አገልጋዮ ችህ ሰጌታህ ሰሳኦል ቤተሰብ ምድሪቱን አርሰው ምግብ ይሆናቸው ዘንድ መከሩን ያግቡላቸው፤ መፊቦሼት ግን የእኔ እንግዳ በመሆን ዘወትር በገበታዬ የሚቀርብ ተመጋቢ ይሆናል፤" ጺባ ዐሥራ አምስት ወንዶች ልጆችና ሃያ አገልጋ ዮች ነበሩት።
11ጺባም "ንጉሥ ሆይ! አንተ የምታዝዘ ውን ማናቸውንም ነገር እፈጽማለሁ" ሲል መለሰ።
በዚህ ዐይነት መፊቦሼት ከንጉሡ ልጆች እንደ አንዱ ተቈጥሮ በንጉሥ ገበታ እየቀረበ ይመገብ ነበር፤ 12መፊቦሼት ሚኳ የተባለ ወጣት ልጅ ነበረው፤ የጺባ ቤተሰብ አባሎች በሙሉ የመፊቦሼት አገልጋዮች ሆኑ፤ 13ስለ ዚህ ሁሉቱም አሞሮቹ ሽባ የሆኑት መፊቦሼት በንጉሡ ገበታ እየቀረበ በመመገብ የኢየሩሳ ሌም ነዋሪ ሆነ።

ምዕራፍ 10

ዳዊት ዐሞናውያንንና ሶርያውያንን ድል አደረገ
(1 ዜ.መ. 19፡1-19)

1ከጥቂት ጊዜ በኋላ የዐሞን ንጉሥ ናያስ ስለሞተ፥ ልጁ ሐኑን በእርሱ እግር ተተክቶ ነገሠ፤ 2ንጉሥ ዳዊትም "እሱም ናያስ ለእኔ እንዳደረገልኝ ሁሉ እኔም ለልጁ ለሐኑን ታማኝ ወዳጅ በመሆን ውለታውን እከፍላለሁ" አለ። ስለዚህም ዳዊት የሐዘን ተካፋይነቱን ለመግለጥ መልእክተኞች ላከ።
መልእክተኞቹም ዐሞን በደረሱ ጊዜ፥ 3ዐሞናውያን መሪዎች ንጉሡን እንዲህ አሉት፥ "ዳዊት እነዚህን ሰዎች የላከው እባት ህን በማክበር የሐዘንህ ተካፋይ ለመሆን ይመስ ልሃልን? ከቶ እንዳይመስልህ! እርሱ እነዚህን መልእክተኞች የላካቸው በከተማይቱ ሳይ አደጋ ለመጣል ያመች ዘንድ እንዲሰልሱለት ነው።"
4ሐኑን የዳዊትን መልእክተኞች ይዞ በእንድ በኩል ጺማቸውን ላጨ፥ ልብሳቸውንም በመቀረጥ እስከ ወገባቸው አሳጥሮ እባረራ ቸው፤ 5እነርሱም ወደ ቤታቸው ለመመለስ አፈሩ፤ ዳዊት ለሰሆነው ነገር በሰማ ጊዜ መል እክተኞች ልኮ በኢያሪኮ እንዲቆዩና ጺማች ውም እንደገና እስኪያድግ እንዳይመለሱ ነገ ራቸው።
6ዐሞናውያን ዳዊትን በገዛ እጃቸው ጠላት እንዳደረጉት ተገነዘቡ፤ ለሰዚህም ከቤትረሐብና ከጸባ ሃያ ሺ ሶርያውያንንና ከጦብ ዐሥራ ሁለት ሺ ሰዎችን ቀጠሩ፤ እንዲሁም ንጉሥ ማዕካ አንድ ሺ ሠራዊት አሰከትሎ እንርሱን ለመር ዳት መጣ፤ 7ዳዊትም ለሰዚህ ጉዳይ ሰምቶ ከመላው ሠራዊት ጋር ኢዮአብን በእነርሱ ላይ እዘመተ፤ 8ዐሞናውያን ተሰልፈው ወጥተው የእነርሱ ዋና ከተማቸው ለሆነችው በራባ መግ ቢያ በር አጠገብ ሰፍራቸውን ያዙ፤ ሌሎቹ ሶርያውያን፥ ከጦብና ከማዕካ የመጡት ጦረኞች በእንድ ሜዳማ ቦታ ሰፍራቸውን ያዙ።
9ኢዮአብ የጠላት ሠራዊት ከፊትና ከኋላ በኩል እደጋ እንደሚጥልበት ተመለከተ፤ ለሰ ዚህ ከእሰራኤል ወታደሮች ጀግኖች የሆኑትን መርጦ በሶርያውያን ፊት ለፊት አመች በሆነ ሰፍራ መደባቸው፤ 10ከሠራዊቱ ቀሪውን ክፍል በወንድሙ በአቢሻይ ትእዛዝ ሥር አደረገ፤ አቢሻይም እነርሱን በዐሞናውያን ፊት ለፊት አሰለፋቸው፤ 11ኢዮአብም አቢሻይን እንዲህ አለው፥ "ሶርያውያን ድል ሲያደርጉኝ መቃረ ባቸውን በምታይበት ጊዜ መጥተህ እርዳኝ፤ እኔም ዐሞናውያን አንተን ድል ሲያደርጉህ በሚቃረቡበት ጊዜ መጥቼ እረዳሃለሁ። 12እንግ ዲህ አይዞህ በርታ! ለሕዝባችንና ለአምላካችን ከተሞች ስንል በርትተን እንዋጋ! እንግዲህ ሁሉ ነገር እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን!"
13ኢዮአብና ሠራዊቱ አደጋ ለመጣል ወደ ፊት በገሠገሡ ጊዜ ሶርያውያን ሸሹ፤ 14ዐሞና ውያንም የሶርያውያንን መሸሽ ባዩ ጊዜ እነር ሱም ከአቢሻይ ፊት ሸሽተው ወደ ከተማይቱ አፈገፈጉ። ከዚህ በኋላ ኢዮአብ ዐሞናውያንን መውጋት አቁሞ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ።
15ሶርያውያን በእስራኤላውያን ድል እንደተ መቱ በተገነዘቡ ጊዜ ሠራዊታቸውን ሁሉ በአን ድነት አሰባሰቡ፤ 16የደባው ንጉሥ ሀዳድዔዜር ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ ወደሚገኙት ሶርያውያን መልእክት ላከ፤ እነርሱም የሀዳድ ዔዜር የሠራዊት አለቃ በሆነው በሾባክ መሪነት ወደ ሔላም መጡ። 17ዳዊትም ይህን በሰማ ጊዜ የእሰራኤላውያንን ወታደሮች ሁሉ በእንድ ነት አሰባስቦ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻገረ፤ ከዚ ያም ሶርያውያን ወደሰፈሩበት ወደ ሔላም

ሄደ ፤ ሶርያውያንም በሰልፍ ወጥተው በዳዊት ላይ ጦርነት ከፈቱ ፤ 18እስራኤላውያን ሶርያውያንን መልሰው እላደዱአቸው ፤ ዳዊትና ሠራዊቱ ስባት መቶ የሶርያውያንን የሠረገላ ነጂዎች ንና ፥ አርባ ሺ ፈረሰኞችን ገደሉ ፤ አንዲሁም የጠላት ሠራዊት አለቃ የነበረውን ሾባክን መት ተው አቊሰለውት ስሰነበር እዚያው በጦር ሜዳው ላይ ሞተ ። 19በሀዳድዓዜር ሥልጣን ሥር የነበሩት ነገሥታት በእስራኤላውያን ድል መመታታቸውን በተገነዘቡ ጊዜ ከእነርሱ ጋር የሰላም ስምምነት አድርገው የእስራኤላውያን ተገዥዎች ሆኑ ፤ ከዚያም በኋላ ሶርያውያን ስለ ፈሩ ዳግመኛ ዐሞናውያንን ላለመርዳት ወሰኑ ።

ምዕራፍ 11

ዳዊትና ቤርሳቤህ*

1የዓመት መጀመሪያ በሆነው ዘጻደይ ወራት ፥ በተሰምዶ ነገሥታት ወደ ጦርነት በሚዘምቱበት ጊዜ ፥ ዳዊት ኢዮአብን ከሦር መኰንኖቹና ከመላ እስራኤል ሠራዊት ጋር አዘ መተው ፤ እነርሱም ዐሞናውያንን ድል ነሥ ተው ራባ ተብላ የምትጠራውን ከተማ ከበቡ ፥ ዳዊት ግን በኢየሩሳሌም ቆየ ።

2አንድ ቀን ከቀትር በኋላ ዘማየት ብሎ ዳዊት ከቀን እንቅልፉ ነቅቶ ወደ ቤተ መንግ ሥቱ ሰገነት ወጣ ፤ እዚያም ወዲያና ወዲህ ሲመላለስ ገላዋን የምትታጠብ አንዲት ሴት አየ ፤ ሴትዮዋም በጣም ውብ ነበረች ፤ 3ስለዚህ ማንነትዋን ለማወቅ ዳዊት እንድ መልእክተኛ ልኮ ቤርሳቤህ ተብላ የምትጠራው የኤሊዓም ልጅ ፥ የሒታዊው የአርዮን ሚስት መሆንዋን ተረዳ ። 4እርስዋንም ሄደው ያመጡለት ዘንድ ዳዊት መልእክተኞችን ላከ ፤ እነርሱም ሄደው እመጡለትና ከእርሰዋ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙ ነት እደረገ ፤ በዚህም ጊዜ ሴትዮዋ ወርሐዊ የመንጻት ሥርዓትዋን የፈጸመች ጥብቅ ነበረች ፤ ከዚህ በኋላ ሴትዮዋ ወደ ቤትዋ ተመልሳ ሄደች ። 5ከጥቂት ጊዜ በኋላም መፅነስዋን ስለ ተገነዘበች መልእክት ልካ ለዳዊት ነገረችው ።

6ከዚህ በኋላ ዳዊት “ሒታዊውን አርዮንን ወደ እኔ ላከው” ሲል ወደ ኢዮአብ መልእክት ሰደደ ፤ ስለዚህም ኢዮአብ አርዮንን ወደ ዳዊት ላከው ፤ 7አርዮን በደረሰ ጊዜ ዳዊት “ኢዮአ ብና ሠራዊቱ ሁሉ እንዴት ናቸው ፤ የጦርነቱስ ሁኔታ እንዴት ነው?” ሲል ጠየቀው ፤ 8ከዚ ህም በኋላ ዳዊት አርዮንን “እንግዲህ ወደ ቤትህ ሂድና ዕረፍት አድርግ” አለው ፤ አርዮ ንም ከዳዊት ፊት ወጥቶ ሄደ ፤ ዳዊትም ወዲያ ውኑ ስጦታ ላከለት ፤ 9አርዮን ግን ወደ ቤቱ ሳይሄድ ከንጉሡ ከብር ዘበኞች ጋር በቤተ መን ግሥቱ የችጽር በር አጠገብ ተኝቶ አደረ ፤ 10አርዮን ወደ ቤቱ አለመሄዱን ዳዊት በሰማ ጊዜ “ብዙ ጊዜ ከቤተሰብህ ተሰይተህ እንሆ አሁን ገና መመለስህ ነው ፤ ታዲያ ወደቤትህ ያልሄድከው ስለምንድን ነው?” ሲል ጠየ ቀው ።

11አርዮንም እንዲህ ሲል መልስ ሰጠ ፥ “የእስራኤልና የይሁዳ ሰዎች በድንኳን ሰፍረው በሦር ሜዳ ይገኛሉ ፥ የቃል ኪዳኑም ታቦት ከእነርሱ ጋር ነው ፤ የሦር አለቃዬ ኢዮአብና የአርሱም የጦር መኰንኖች በሜዳ ሰፍረዋል ፥ ታዲያ እኔ ወደ ቤቴ ሄጀ መብላት ፥ መጠ ጣት ፥ ከሚስቴም ጋር መተኛት እንዴት ይቻለ ኛል? ይህን የመሰለ ነገር ከቶ እንደማላደርግ በእንተ ሕይወት እምላለሁ ።”

12ዳዊትም “በል እንግዲህ የዛሬን እዚህ ዋል ፤ ነገ ግን መልሼ አልክሃለሁ” አለው ፤ ስለ ዚህ አርዮን በዚያን ቀንና በሚቀጥለው ቀን በኢየሩሳሌም ቆየ ፤ 13ዳዊትም አርዮንን ራት ጋበዘውና እስኪሰክር ድረስ የወይን ጠጅ እንዲ ጠጣ እደረገው ፤ በዚያም ሴሊት አርዮን ወደቤተ መንግሥቱ ዘበኞች ቤት ብርድ ልብሱን በማን ጠፍ ተኝቶ አደረ እንጂ ወደ ቤቱ እልሄደም ።

14በማግሥቱም ጧት ዳዊት ለኢዮአብ ደብ ዳዜ ጻፈና በአርዮን እጅ ላከው ፤ 15የጻፈውም ቃል “አርዮንን ጦርነቱ በተፋፋመበት ግንባር እሰልፈው ፤ ከዚያም እንተ ወደ ኋላ አፈግፍገህ እርሱ እንዲገደል እድርገው” የሚል ነበር ። 16በዚህ ወይነት ኢዮአብ ከተማይቱን ከቦ በመ ያዝ ላይ ስለ ጠላት ማየሱን በሚያውቅበት ስፍራ አርዮንን አሰለፈው ። 17የጠላት ወታደ ሮች ከከተማይቱ ወጥተው የኢዮአብን ሠራዊት ወጉ ፤ ከዳዊት የጦር መኰንኖች ጥቂቶቹ ሞቱ ፤ አርዮንም አብሮ ሞተ ።

18ከዚህ በኋላ ኢዮአብ ስለ ጦርነቱ የሚያስ ረዳ መልእክት ወደ ዳዊት ላከ ፤ 19ሰመልእክተ ኛውም እንዲህ የሚል መመሪያ ስጠው ፥ “ስለ ጦርነቱ ሁሉን ነገር ለንጉሡ ካስረዳህ በኋላ ፥ 20ንጉሡ ተቈጥቶ እንዲህ ይልህ ይሆናል ፥ ‘እነርሱን ለመውጋት ወደ ከተማይቱ ለምን ተጠጋችሁ? በግንብ ላይ ሆነው ፍላጻዎችን እን ደሚወረውሩባችሁ አላወቃችሁምን? 21የጌዴ ዎን ልጅ አቢሜሌክ እንዴት እንደሞተ አታስ ታውሱምን? እርሱን ቴቤጽ ተብሎ በሚጠራ ሰፍራ አንዲት ሴት ከግንብ ላይ የወፍጮ ድን ጋይ ናዳ በመጣል ገደሰችው ፤ ታዲያ እናንተ ወደ ግንብ የተጠጋችሁት ለምንድን ነው?’ ንጉሡ ይህን ዋያቱ ቢያቀርብልህ ፥ ‘የሦር መኰንንህ አርዮንም ተገድሎአል’ ብለህ ንገ ረው ።”

4* 11፡1 ቤርሳቤህ ፦ በዕብራይስጥ መጠሪያ ስሟ “ባትሼባ” ነው ።
11፡1 ፦ 1ዜ.መ. 20፡1 ። 11፡21 ፦ መሳ. 9፡53 ።

22 ስለዚህም መልእክተኛው ወደ ዳዊት ሄዶ
ኢዮአብ ያዘዘውን ሁሉ እንዲህ ሲል ነገረው ፥
23 "ጠላቶቻችን ስለበረቱብን እኛን ለመውጋት
ከከተማይቱ ወጥተው ወደ ሜዳ መጡ ፤ እኛ
ግን አሳድደን ወደ ኩተማይቱ ቅጽር ሸር መለስ
ናቸው ። 24 ከዚያም በኋላ በግንብ ላይ ሆነው
ፍላጻዎችን ወረወሩብን ፤ ንጉሥ ሆይ! ከሦር
መኰንኖችህ ጥቂቶቹ በዚያን ጊዜ ሞቱ ፤ አገል
ጋይህ ኦርዮንም ተገደለ ።"
25 ዳዊትም መልእክተኛውን "በጦርነት ላይ
ግን እንደሚሞት በቅድሚያ ስለማይታወቅ
ኢዮአብን 'እይህህ በርታ' በለው ፤ ብሰጭት እን
ዳያድርበትም ንገረው ፤ ይልቁንም ጎይሉን አጠ
ናክሮ አደጋ በመጣል ከተማይቱን እንዲይዝ
አስጠንቅቀው ።"
26 ቤርሳቤህ ባልዋ እንደተገደለ በሰማች ጊዜ
በማልቀስ አዘነችለት ፤ 27 የሐዘንዋም ጊዜ ሲፈ
ጸም ዳዊት ሰው ልኮ ወደ ቤተ መንግሥት አስ
መጣት ፤ ለእርሱም ሚስት ሆና ወንድ ልጅ
ወለደችለት ፤ ነገር ግን ዳዊት ያደረገው ነገር
እግዚአብሔርን አሳዘነ ።

ምዕራፍ 12

የናታን ትንቢታዊ ምሳሌና የዳዊት ንስሐ

1 እግዚአብሔር ነቢዩ ናታንን ወደ ዳዊት
ላከው ፤ ናታንም ወደ ዳዊት ሄዶ እንዲህ
አለው ፥ "በአንድ ከተማ የሚኖሩ ሁለት ሰዎች
ነበሩ ፤ ከእነርሱ አንዱ ሀብታም ሲሆን ሁለተ
ኛው ደግሞ ድኻ ነበር ፤ 2 ሀብታሙ ሰው ብዙ
የቀንድ ከብቶችና የበግ መንጋ ነበሩት ፤
3 ድኻው ግን በገንዘቡ የገዛት አንዲት የበግ
ጥቦት ብቻ ነበረችው ፤ እርስዋን እየተከባከበ
ከልጆቹ ጋር በቤቱ ውስጥ ያሳድጋት ነበር ፤
ከሚመገበው ይመግባት ፥ ከሚጠጣውም ያጠ
ጣት ነበር ፤ ስትተኛም ያቅፋት ነበር ፤ ያችም
ጥቦት ልክ እንደ ልጁ ነበረች ፤ 4 አንድ ቀን
ወደ ሀብታሙ ሰው ቤት እንድ መንገደኛ
መጣ ፤ ሀብታሙ ሰው ለእንግዳው የሚሆን
ምግብ ለማዘጋጀት ከእንሰሶቹ አንዱን ማረድ
አልፈለገም ፤ ይህንንም በማድረግ ፈንታ የድኻ
ውን ሰው ጥቦት ወስዶ በማረድ ለእንግዳው
ምግብ አዘጋጀ ።"
5 ዳዊት በሀብታሙ ሰው ታሪክ እጅግ ተቈ
ጥቶ "ይህን ያደረገው ሰው ሞት እንደሚገባው
በሕያው እግዚአብሔር ስም እምላለሁ ፤ 6 ይህን
የመሰለ የጭካኔ ሥራ በመፈጸሙ ከዚያ ሰው
የወሰደበትን አራት እጥፍ አድርጎ መመለስ አለ
በት" አለ ።
7 ናታንም ዳዊትን እንዲህ አለው ፥ "ያ ሰው
አንተ ራስህ ነህ! የእስራኤል አምላክ የሆነ እግ
ዚአብሔር እንዲህ ይላል ፥ 'እኔ ንጉሥ አደረግ
ሁህ ፤ ከሳኦልም እጅ ስመታደግ አዳንሁህ ፤
8 መንግሥቱንና ሚስቶቹን ሰጠሁህ ፤ በእስራኤ
ልና በይሁዳ ላይ አነገሥሁህ ፤ ይህም ሁሉ
እንኳ የማይበቃህ ቢሆን ኖሮ በተጨማሪ እጥፍ
አድርጌ በሰጠሁህ ነበር ፤ 9 ታዲያ ትእዛዜን የና
ቅኸው ስለምንድን ነው? ይህንንስ ክፉ ነገር
ለምን አደረግህ? እርዮንን በሦር ሜዳ አስገደል
ከው ፤ ንጹሑን ሰው ዐሞናውያን እንዲገድሉት
አደረግህ ፤ ሚስቱንም ወሰድህ ፤ 10 እንተ እኔን
ስላልታዘዝህና የኦርዮንን ሚስት ስለወሰድህ ፥
እነሆ በየትውልዱ ከዘሮችህ አንዳንዶቹ በማፍ
ይገደላሉ ፤ 11 ከቤተሰብህ አንዱ ተነሥቶ ችግር
እንዲፈጥርብህ የማደርግ መሆኔን በመሐላ አረጋ
ግጥልሃለሁ ፤ ሚስቶችህን ወስጀ ለሌላ ሰው
በምሰጥበት ጊዜ ይህ ነገር እንደሚፈጸም ትገነዘ
ባለህ ፤ እርሱም ከሚስቶችህ ጋር በቀን ብርሃን
በግልጥ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያደርጋል ፤
12 አንተ ይህን ኃጢአት በስውር ሠርተሃል ፤ እኔ
ግን እስራኤል ሁሉ ይመለከቱ ዘንድ ይህን ነገር
የቀን ብርሃን ባለበት በግልጥ አደርጋለሁ ።'"
13 ዳዊትም "ኃጢአት በመሥራት እግዚአብ
ሔርን አሳዝኛለሁ" አለ ።
ናታንም እንዲህ ሲል መለሰለት ፥ "እግዚአ
ብሔር ይቅር ስለሚልህ አትሞትም ፤ 14 ነገር
ግን ይህን በደል በመፈጸም በዚህ ሁኔታ እግዚ
አብሔርን ስለናቅህ ልጅህ ይሞታል ።" 15 ከዚህ
በኋላ ናታን ወደ ቤቱ ሄደ ።

የዳዊት ልጅ ሞተ

የእርዮን ሚስት ለዳዊት የወለደችለትን ልጅ
እግዚአብሔር በከባድ ሕመም ቀሠፈው ፤
16 ዳዊትም ሕፃኑን እንዲፈውስለት በጾምና በጸ
ሎት እግዚአብሔርን ለመነ ፤ ሰየሌሊቱም ወደ
መኝታ ክፍሉ እየገባ በመሬት ላይ ይተኛ
ነበር ፤ 17 የቤተ መንግሥቱ ባለሟሎች ወደ
እርሱ ቀርበው ከመሬት ላይ ሊያስነሡት
ሞከሩ ፤ እርሱ ግን ከመሬት ላለመነሣትና ከእነ
ርሱም ጋር ምንም ነገር ላለመቅመስ ወሰነ ፤
18 ከአንድ ሳምንትም በኋላ ሕፃኑ ሞተ ፤ የዳ
ዊት ባለሟሎችም መርዶውን ለመንገር ፈር
ተው "ሕፃኑ በሕይወት በነበረበት ጊዜ እንኳ
ዳዊት ስንመክረው አልሰማንም ፤ ታዲያ አሁን
የልጁን መሞት እንዴት አድርገን ልንነግረው
እንችላለን? ምክንያቱም በራሱ ላይ አንዳች
ጕዳት ማድረስ ይችል ይሆናል" አሉ ።
19 ዳዊት እርስ በርሳቸው ሲያንሾካሹኩ
በሰማ ጊዜ ሕፃኑ መሞቱን ተረዳ ፤ ስለዚህም
"ሕፃኑ ሞተ እንዴ?" ሲል ጠየቃቸው ።
እነርሱም "አዎ ሞቶአል" ሲሉ መለሱ
ለት ።

12፥1 ፦ መዝ. 51 ። 12፥11-12 ፦ 2ሳሙ. 16፥22 ።

20 ዳዊትም ከተኛበት መሬት ተነሥቶ ሰውነቱን ታጠበ፤ ቅባት ተቀባ፤ ልብሱንም ቀየረ፤ ከዚያም ወደ እግዚአብሔር ቤት ሄዶ ሰገደ፤ ወደ ቤተ መንግሥቱም ሲመለስ ምግብ እንዲያ ቀርቡለት ጠየቀ፤ እንደቀረበለትም ወዲያውኑ ተመገበ፤ 21 ባለሟሎቹም “ይህ ነገር ምን አን ደሆነ ሰማወቅ አልቻልንም፤ ሕፃኑ በሕይወት በነበረበት ጊዜ በመጾም አለቀስክለት፤ እርሱ ከሞተ በኋላ ግን ወዲያውኑ ተነሥተህ ተመገ ብህ” አሉት።

22 ዳዊትም እንዲህ ሲል መለሰ፥ “ሕፃኑ በሕይወት ሳለ መጾሜና ማልቀሴ እርግጥ ነው፤ እግዚአብሔር ምሕረት አድርጎልኝ ሕፃኑ እንዳ ይሞት ያደርግ ይሆናል ብዬ አስቤ ነበር፤ 23 አሁን ግን ከሞተ በኋላ ስለምን እጾማለሁ? ሕፃኑን እንደገና በሕይወት እንዲኖር ማድረግ ይቻለኛልን? እኔ እንድ ቀን ወደ እርሱ እሄዳ ለሁ እንጂ እርሱ ወደ እኔ ተመልሶ አይመ ጣም።”

የሰሎሞን መወለድ

24 ከዚህ በኋላ ዳዊት ሚስቱን ቤርሳቤህን አጽናናት፤ ከእርስዋም ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙ ነት አደረገ፤ እርስዋም ወንድ ልጅ ወለደች ለት፤ ዳዊትም የልጁን ስም “ሰሎሞን” ብሎ ጠራው፤ እግዚአብሔር ሕፃኑን ስለወደደው፥ 25 “ይዲድያ” የሚል ሰም እንዲያወጣለት ነቢዩ ናታንን አዘዘው፤ ይህም “በእግዚአብሔር የተወደደ” ማለት ነው።

ዳዊት በድል አድራጊነት ራባ ተብላ የምትጠራውን ከተማ ያዘ
(1 ዜ.መ. 20፥1-3)

26 በዚያን ጊዜ ኢዮአብ ራባ ተብላ የምትጠ ራውን የዐሞናውያንን ከተማ ለመያዝ የሚያደር ገውን ዘመቻ በመቀጠል ሊይዛት ተቃርቦ ነበር፤ 27 መልእክተኞችንም ልኮ ለዳዊት እን ዲህ ብሎው እንዲነግሩት አደረገ፥ “በራባ ላይ አደጋ ጥዬ የውሃ ማከፋፈያ ለፍራዋን ይገርአ ለሁ፤ 28 እንሆ አሁን ከሠራዊትህ ቀሪውን ከፍል አሰባስብና በከተማይቱ ላይ አደጋ በመ ጣል እንተው ራስህ ያዛት፤ አሰበለዚያ እኔ ከተ ማይቱን ይገር በስሜ እንድትጠራ እደርጋ ለሁ።” 29 ስለዚህም ዳዊት ሠራዊቱን ሁሉ እሰ ባስቦ ወደ ራባ በመዝመት አደጋ ጥሎ ያዛት፤ 30 ዳዊት የዐሞናውያን አምላክ ከሆነው ሚል ኮም ተብሎ ከሚጠራው ጣዖት[5*] ራስ ላይ ሠላሳ አምስት ኪሎ ግራም የሚመዝነውንና በውስጡም የከበረ ዕንቁ ያሰበትን ዘውድ ወስዶ በራሱ ላይ ደፋው፤ እንዲሁም ከከተማይቱ ብዙ ምርኮ ወሰደ፤ 31 ሕዝቡም በመጋዝ፥ በብ ረት ዶማና በብረት መጥረቢያ እንዲሠሩ አደረ ጋቸው፤ ጡብ እንዲሠሩበትም አስገደዳቸው፤ በሌሎቹ የዐሞን ከተሞች ሁሉ ያሉትን ሕዝ ብም እንዲሁ በዚሁ ዐይነት እንዲሠሩ አደረጋ ቸው፤ ከዚህ በኋላ እርሱና ሠራዊቱ ወደ ኢየሩ ሳሌም ተመለሱ።

ምዕራፍ 13
አምኖንና ታማር

1 የዳዊት ልጅ አቤሴሎም ውብ የሆነች ታማር ተብላ የምትጠራ፥ ገና ባል ያላገባች እኅት ነበረችው፤ አምኖን ተብሎ የሚጠራው ከዳዊት ልጆች አንዱ ትዕማርን ወደዳት፤ 2 እር ስዋንም እጅግ ከማፍቀሩ የተነሣ ታመመ፤ ድን ግል እንደመሆንዋ መጠን ከወንዶች ጋር አንዳ ትገናኝ ተጠብቃ ስለነበር አርስዋን ማግኘት ከቶ እልተቻለውም። 3 ነገር ግን በጣም ዘዴኛ የሆነ፥ ዮናዳብ ተብሎ የሚጠራ ወዳጅ ነበ ረው፤ እርሱም የዳዊት ወንድም የሻማ ልጅ ነበር፤ 4 ዮናዳብ አምኖንን “አንተ የንጉሥ ልጅ ሆነህ ሳለ በየቀኑ በውነትህ ጠውልጎ የማ ይህ ስለምንድን ነው? አሰቲ ንገረኝ” ሲል ጠየ ቀው።

አምኖንም “የወንድሜን የአቤሴሎምን እኅት ታማርን ስለወደድሁ ነው” ሲል መለሰ ለት።

5 ዮናዳብም እንዲህ አለው፥ “ይህ ከሆነ አን ግዲህ የታመምህ መስለህ አልጋህ ላይ ተኛ፤ አባትህ ሊጠይቅህ ሲመጣ፥ ‘እኅቴ ታማር መጥታ እንድታስታምመኝ እባክህ ንገራት፤ እዚህ በእጠገቤ እያየኋት ምግብ አዘጋጅታ እር ስዋ ራስዋ እንድታጐርሰኝ አፈልጋለሁ’ በለው።” 6 ስለዚህም አምኖን የታመመ በመም ስል በአልጋው ላይ ተኛ።

ንጉሥ ዳዊትም ሊጠይቀው ወደ እርሱ በሄደ ጊዜ አምኖን “ታማር እዚህ በእጠገቤ እያየኋት ሁለት እንጀራ ጋግራ እርስዋ ራስዋ እንድታቀርብልኝ ፍቀድላት” አለው።

7 ስለዚህም ዳዊት በቤተ መንግሥት ለምትገ ኘው ለታማር “ወደ አምኖን ቤት ሄደሽ ምግብ አዘጋጂለት” የሚል ትእዛዝ ላከ። 8 እርስዋም ወደ አምኖን ቤት በሄደች ጊዜ አልጋ ላይ ተኝቶ አገኘችው፤ ዋቂት ሊጥ ወስዳ በማቅለ ንም አምኖን እያያት እንጀራ ጋገረች፤ 9 የጋገረ ችውንም እንጀራ ከመጋገሪያው አውጥታ እንዲ በላ አቀረበችለት፤ እርሱ ግን መመገቡን እምቢ ብሎ “ሰዎቼን ሁሉ አስወጡልኝ” አለ፤ ሁሉም ወጡ፤ 10 ከዚያም በኋላ “እንጀራውን ወደዚህ ወደ አልጋዬ አምጥተሽ እንቺው ራስሽ አጉርሺኝ” አላት፤ እርስዋም እንጀራውን ይዛ ወደ እርሱ ሄደች፤ 11 በምታቀርብለትም ጊዜ

5* 12፥30 ሚልኮም ተብሎ ከሚጠራው ጣዖት ፡- ወይም “ከዐሞናውያን ንጉሥ”

አፈፍ በማድረግ ይዞ “ነይ አብረን እንተኛ” አላት ።

12እርስዋም “አይሆንም! ወንድሜ ሆይ! እባክህ አታዋርደኝ! የዚህ ዐይነቱ አሳፋሪ ተግባር በእስራኤል ተፈጽሞ አያውቅም ፥ ስለዚህ ይህን ትልቅ ብልግና እትፈጽም! 13እንደዚህ ካዋረድሽኝ በኋላ በሕዝብ ፊት ራሴን ቀና አድርጌ ስመሄድ እንዴት እችላለሁ? አንተም ብትሆን በእስራኤል እጅግ የተዋረድህ ትሆናለህ ፥ ይልቅስ ስንጉሡ ብትነግረው እኔን ስለንተ ዐሚ ስትነት እንደሚሰጥህ እርግጠኛ ነኝ” አለችው ። 14እርሱ ግን ሊያዳምጣት አልፈቀደም ፥ እርስዋንም በኀይል አስገድዶ ከብረ ንጽሕናዋን ደፈረ ።

15ከዚያም በኋላ እምኖን እጅግ አድርጎ ጠላት ፥ እንዲያውም ቀድሞ ካፈቀራት ይበልጥ አሁን በእርስዋ ላይ ያለው ጥላቻ ስለባሰ “ከዚህ ውጪልኝ!” አላት ።

16እርስዋም “አይሆንም! እኔን እንደዚህ አድርገህ ብታባርረኝ አሁን ከፈጸምከው በደል ይልቅ የከፋ ኃጢአት ትፈጽማለህ” አለችው ።

አምኖን ግን ሊያዳምጣት አልፈቀደም ፥ 17የግል አገልጋዩንም ጠርቶ “ይህችን ሴት ከፊቴ ወዲያ አስወግድልኝ! እርስዋንም ወደ ውጭ አስወጥተህ በሩን ዝጋ!” አለው ። 18-19አገልጋዩም እርስዋን አስወጥቶ በሩን ዘጋ ።

ታማርም በዚያን ዘመን ያሳዝቡ ሴቶች ይለብሱት የነበረውን እጅጌ ረዥም የሆነውን ትልቅ መጐናጸፊያዋን ቀደደች ፥ ፊትዋንም በእጅዋ ሸፍና እያስቀሰች ሄደች ። 20ወንድምዋ አቤሴሎም ባያት ጊዜ “እምኖን አስነዋሪ ነገር ፈጸመ ብሽን? እኅቴ ሆይ! እባክሽ እንደዚህ አትበሳጪ ፥ እርሱ ወንድምሽ ስለሆነ ለማንም አትናገሪ” አላት ። ስለዚህ ታማር በአቤሴሎም ቤት ሐዘንተኛና ብቸኛ ሆና ተቀመጠች ።

21ንጉሥ ዳዊት የሆነውን ነገር በሰማ ጊዜ በብርቱ ተቈጣ ፥ 22የእኅቱን የታማርን ክብረ ንጽሕና በመድፈሩም ምክንያት አቤሴሎም አምኖንን እጅግ ጠላው ፥ ዳግመኛም ከፉም ሆነ ደግ ሊያነጋግረው አልፈለገም ።

አቤሴሎም የወሰደው የበቀል እርምጃ

23ከሁለት ዓመት በኋላ አቤሴሎም በኤፍሬም ክተማ አጠገብ ሐጾር ተብሎ በሚጠራው ስፍራ በጎቹን ይሸልት ነበር ፥ ስለዚህም የንጉሡን ወንዶች ልጆች ሁሉ ሰግብጣ ወደዚያ ጠራ ። 24ወደ ንጉሥ ዳዊትም ሄዶ “ንጉሥ ሆይ! በጎቼን እየሸለትሁ ነው ፥ ሰለዚህ አንተና መኳንንትህ መጥታችሁ የግብጣው ተካፋዮች እንድትሆኑልኝ ትፈቅዳለህን?” አለው ።

25ንጉሡም “ልጄ ሆይ! መምጣት አያስፈልገንም ፥ ምክንያቱም እኛ ሁላችን ከመጣን መስተንግዶው ይከብድብሃል” ሲል መለሰለት ፥ አቤሴሎምም አጥብቆ ጠየቀ ፥ ንጉሡ ግን አሳቡን መለወጥ ስላልፈቀደ አቤሴሎምን መርቆ አሰናበተው ።

26አቤሴሎም ግን “መልካም ነው! እንተ መምጣት ካልፈቀድህ ወንድሜ አምኖን እንዲመጣ እትፈቅድለትምን?” ሲል ጠየቀ ።

ንጉሡም “እርሱስ ቢሆን ለምን ይመጣል?” ሲል ጠየቀው ። 27አቤሴሎም አጥብቆ በለመነው ዳዊት ፥ አምኖንና የቀሩትም ወንዶች ልጆቹ ሁሉ እንዲሄዱ ፈቀደ ።

አቤሴሎም ስንጉሥ የሚገባ ግብዣ አዘጋጅቶ ነበር ፥ 28አገልጋዮቹንም “አምኖን ብዙ ጠጥቶ መስከሩን ተመልከቱ ፥ እኔም ትእዛዝ በምሰጣችሁ ጊዜ ግደሉት ፥ እኔ ራሴ ስለ እርሱ ሞት ኀላፊ ስለምሆን ከቶ አትፍሩ ፥ ደፋሮች ሁኑ ፥ ምንም አታመንቱ” አላቸው ። 29ስለዚህ አገልጋዮቹ አቤሴሎም በነገራቸው መመሪያ መሠረት አምኖንን ገደሉ ፥ የቀሩትም የዳዊት ወንዶች ልጆች በበቅሎዎቻቸው ተቀምጠው እየጋለቡ ሸሹ ።

30ወደ ቤታቸው ስመድረስ ገና በመንገድ ላይ ሳሉ “አቤሴሎም ልጆችህን ሁሉ ገደላቸው ፥ አንድ እንኳ የቀረ የለም” የሚል ወሬ ሰዳዊት ደረሰው ። 31ንጉሡ ከተቀመጠበት በመነሣት በሐዘን ልብሱን ቀድዶ በመሬት ላይ ተዘረረ ፥ በዚያ ከእርሱ ጋር የነበሩ አገልጋዮቹም በሐዘን ልብሳቸውን ቀደዱ ። 32የዳዊት ወንድም የሻማ ልጅ ዮናዳብ ግን እንዲህ አለ ፥ “ንጉሥ ሆይ! የተገደሉት ልጆችህ በሙሉ አይደሉም ፥ የተገደለው አምኖን ብቻ ነው ፥ አቤሴሎም ይህን ስማድረግ ያቀደው አምኖን የእኅቱን የታማርን ክብረ ንጽሕና ከደፈረበት ጊዜ አንሥቶ እንደነበር ፊቱን አይተህ መረዳት ትች ሳስህ ። 33ስለዚህ ልጆችህ በሙሉ እንደተገደሉ ሆኖ የተነገረህን ወሬ አትመን ። የተገደለው አምኖን ብቻ ነው ።”

34በዚህም ጊዜ አቤሴሎም ሸሽቶ አምልጠ ነበር ፥ ስዘብ ጥበቃ ተረኛ የነበረውም ወታደር ልክ በዚያን ስዓት ከሖሮናይም ወደዚህ በሚመጣው መንገድ ላይ ኰረብታ ብዙ ሕዝብ ወደ ታች ሊወርድ አየ ፥ ወደ ንጉሡም ቀርቦ ያየውን ሁሉ ተናገረ ፥ 35ዮናዳብም ዳዊትን “ልክ እኔ እንዳልኩህ እነሆ ልጆችህ በመምጣት ላይ ናቸው” አለው ። 36እርሱ ይህን ተናግሮ እንዳበቃ የዳዊት ልጆች ገብተው መላቀስ ጀመሩ ፥ ዳዊትና መኳንንቱም በመረረ ሁኔታ አለቀሱ ።

37-38አቤሴሎምም ሸሽቶ የገሹር ንጉሥ ወደሆነው ወደ ዓሚሁድ ልጅ ወደ ታልማይ

ሄደ ፤ ዘዚያም ሦስት ዓመት ቆየ ፤ ዳዊት ስለ ልጁ ስለ አምኖን ሞት ለረኽም ጊዜ በማዘን አሰቀሰ ፤ 39 ነገር ግን ስለ አምኖን ሞት የነበረ በት ሐዘን እየተረሳ ዘሄደ ጊዜ ልጁን አቡሴሎ ምን መናፈቅ ጀመረ ።

ምዕራፍ 14

ኢዮአብ ስለ አቡሴሎም መመለስ ያወጣው ዕቅድ

1 ንጉሡ ዳዊት አቢሴሎምን እንደናፈቀ ኢዮአብ ተረዳ ፤ 2 ስለዚህም በተቆሳ የምትኖረ ውን አንዲት ብልህ ሴት አስመራ ፤ እርስዋም በደረሰች ጊዜ “ሐዘንተኛ ለመምሰል ሞከሪ ፤ የሐዘን ልብስሽን ልበሺ ፤ ቅቤም አትቀቢ ፤ ለብዙ ጊዜ በሐዘን ላይ የቈየሽ ሴት ለመም ሰል ተዘጋጂ ፤ 3 ከዚያም በኋላ ወደ ንጉሡ ቀርበሽ እኔ የምነግርሽን ንገሪው” አላት ፤ ከዚህ በኋላ እርስዋ ልትናገረው የሚገባትን ሁሉ ኢዮአብ ነገራት ።

4 ሴቲቱም ወደ ንጉሡ ቀርባ ወደ መሬት ለጥ ብላ እጅ ነሣችና “ንጉሥ ሆይ ! እባክህ እርዳኝ” አለችው ።

5 ንጉሡም “የምትፈልጊው ነገር ምንድን ነው ?” አላት ፤ እርስዋም እንዲህ ስትል መለ ሰች ፥ “እኔ ባሌ የሞተብኝ ምስኪን ሴት ነኝ ፤ 6 ንጉሥ ሆይ ! ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሩኝ ፤ አንድ ቀን ገላጋይ በሌለበት ስፍራ ሁለቱ ልጆቼ እርስ በርሳቸው ተጣሉ ፤ አንዱም ሌላ ውን ገደለው ፤ 7 ንጉሥ ሆይ ! እነሆ አሁን ዘመ ዶቹ ሁሉ በእኔ ላይ ተነሥተው ‘ወንድሙን ስለገደለ አንገድለው ዘንድ ልጅሽን አሳልፈሽ ስጭን’ አያሉ አስቸገሩኝ ፤ ታዲያ እንዲህ የሚ ያደርጉ ከሆነ ያለ ልጅ መቅረቴ ነው ፤ የቀረ ኝን አንድ የመጨረሻ ተስፋ ሊያጠፉት ይፈል ጋሉ ፤ ባሌንም ያለ ልጅ በማስቀረት ስሙ ሕያው ሆኖ እንዳይኖር ሊያደርጉት ነው ።”

8 ንጉሡም “ወደ ቤትሽ ተመልሰሽ ሂጂ ፤ እኔም ጕዳዩን እመረምርልሻለሁ” አላት ።

9 እርስዋም “ንጉሥ ሆይ ! አንተ ስለምታደ ርገው ነገር ሁሉ እኔና ቤተሰቤ እንወቀስበታ ለን ፤ አንተና ንጉሣዊ ቤተሰብህ ግን ንጹሓን ትሆናላችሁ” አለችው ።

10 ንጉሡም “ማንም ሰው ሊያስቸግርሽ ወደ እኔ እንዲቀርብ አድርጊው ፤ ዳግመኛ ሊያስቸግ ርሽም ከቶ አይችልም” አላት ።

11 እርስዋም “ንጉሥ ሆይ ! የልጁን ሞት ለመበቀል ጎሣፊነት የተቀበለው ዘመዱ ሌላውን ልጁን በመግደል የባሰ ወንጀል እንዳይፈጽም ታደርገው ዘንድ በእግዚአብሔር ስም ማል ልኝ” አለችው ።

ንጉሡ ዳዊትም “በልጅሽ ላይ ጕዳት መድ ረስ ይቅርና ከራስ ጠጕሩ እንኳ እንዲቴ መሬት ላይ እንደማትወድቅ በሕያው እግዚአብሔር ስም ቃል እገባልሻለሁ ።” አላት ።

12 ሴቲቱም “ንጉሥ ሆይ ! እንደገናም እንድ ነገር እንድናገር ፍቀድልኝ” አለችው ።

እርሱም “እሺ ተናገሪ !” አላት ።

13 እርስዋም እንዲህ አለችው ፥ “በእግዚአብ ሔር ሕዝብ ላይ ይህን የመሰለ በደል የፈጸም ከው ስለምንድን ነው ? ልጅህ ከተሰደደበት አገር ተመልሶ እንዲመጣ አልፈቀድህለትም ፤ ስለዚህ አሁን በተናገርከው ቃል በራስህ ላይ ፈርደሃል ፤ 14 እኛ ሁላችን መሞታችን የማይ ቀር ነው ፤ እኛ በመሬት ላይ እንደፈሰሰና ተመ ልሶም ሊታፈስ እንደማይችል ውሃ ነን ፤ እግዚ አብሔር ግን በስደት ላይ የሚገኝ ሰው ከእርሱ እንደራቀ እንዳይቀር የሚመለስበትን መንገድ ያዘጋጅለታል እንጂ ሕይወቱ በከንቱ እንድት ጠፋ አይፈቅድም ። 15 አሁንም ንጉሥ ሆይ ! እኔ ወደ አንተ የመጣሁት ፥ በዚህ ነገር ሰዎች ያስቸገሩኝ መሆኑን ልነግርህ ነው ፤ ‘የጠየቅሁ ትን ሁሉ ያደርግልኛል’ በሚል ተስፋም በፈ ትህ ቀርቤአለሁ ፤ 16 የምንግርህን አድምጠህ ልጂንና እኔን በማጥፋት እግዚአብሔር ለሕዝቡ ከሰጠው ምድር ሊያስወግደን ከሚፈልገው ሰው ታድነኛለህ ብዬ አሰብሁ ነው ። 17 እንዲሁም ንጉሥ ሆይ ! የተሰሩ ቃልህ በሰላም እንድኖር ይረዳኛል ብዬ አሰብሁ ነው ምክንያቱም ንጉሥ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ስለሆነ መልካ ሙን ከክፉው ለይቶ ያውቃል ፤ እንግዲህ እምላ ክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሁን ።”

18 ንጉሡም “እንድ ዋያቴ እጠይቅሻለሁ ፤ አንቺም እውነቱን በሙሉ ንገሪኝ” አላት ።

እርስዋም “ንጉሥ ሆይ ! የፈለግኸውን ጠይ ቀኝ” አለችው ።

19 እርሱም “ይህን እንድታደርጊ ያዘዘሽ ኢዮአብ ነውን ?” ሲል ጠየቃት ።

እርስዋም እንዲህ ስትል መልስ ሰጠች ፥ “ንጉሥ ሆይ ! አንተ ከምትሰው ሁሉ ፈጽሞ ሊወጣ የሚችል እንደሌለ በእንተ ስም እምላ ለሁ ፤ በእርግጥም ምን ማድረግና ምን ማለት እንዳለብኝ የመከረኝ የአንተ የጦር አዛዥ የሆ ነው ኢዮዓብ ነው ። 20 እርሱም ይህን ያደረገው ነገሮችን ሁሉ ለማስተካከል በማሰብ ነው ፤ ንጉሥ ሆይ ! እንተ ግን እንደ እግዚአብሔር መልአክ ዋበበኛ ነህ ፤ የሚሆነውንም ነገር ሁሉ ታውቃለህ ።”

21 ንጉሡም ዘማየት ብሎ ኢዮአብን “አንተ የምትፈልገውን ለማድረግ ወስኛለሁ ፤ ሂድና ያንን ወጣት አቤሴሎምን ፈልገህ ወደዚህ አም ጣው” አለው ።

14፥17 ፡- 2ሳሙ. 19፥27 ።

22 ኢዮአብም በዳዊት ፊት ወደ መሬት ሰጥ
ብሎ እጅ በመንሣት “ንጉሥ ሆይ! የእግዚአብ
ሔር በረከት በአንተ ላይ ይሁን፤ የፈሰግሁትን
እንዳደርግ በመፍቀድህ በፊትህ ምገሰ ማግኝ
ቴን አውን ተረዳሁ” አሰ። 23 ተነሥቶም ወደ
ገሹር ሄደ፤ አቢሴሎምንም ወደ ኢየሩሳሌም
መልሶ አመጣው፤ 24 ይሁን እንጂ ንጉሥ፥
አቢሴሎም በቤተ መንግሥት ውስጥ እንዳይኖር
ትእዛዝ ሰጠ፤ ደግሞም ንጉሡ “ከቶ እርሱን
ማየት አልፈልግም” አሰ። ሰሰዚህ አቢሴሎም
በራሱ ቤት ኖረ፤ ወደ ንጉሡም ፊት ቀርቦ
አልታየም።

አቢሴሎም ከዳዊት ጋር ታረቀ

25 የአቢሴሎምን ያህል በመልክ መልካምነቱ
የታወቀ ሰው በእስራኤል ምድር ከቶ አልነበ
ረም፤ አቢሴሎም ከራስ ጠጕሩ እስከ እግር
ጥፍሩ ምንም እንከን የሌሰበት በው ነበር፤
26 የራሱ ጠጕር እጅግ ብዙ ነበር፤ ሰሰሚረዝም
በትና ሰሰሚከብደው በዓመት አንድ ጊዜ ይቈር
ጠው ነበር፤ የጠጕሩም ክብደት በቤተ መንግ
ሥት ሚዛን ሲለካ ከሁሰት ኪሎ በሳይ ነበር።
27 አቢሴሎም ሦሰት ወንዶች ልጆችና አንዲት
ሴት ልጅ ነበሩት፤ የሴት ልጁም ሰም ታማር
ሲሆን እርስዋም እጅግ ውብ ነበረች።
28 አቢሴሎም ንጉሡን ሳያይ በኢየሩሳሌም
ሁሰት ዓመት ኖረ፤ 29 ከዚያን በኋላ ወደ
ንጉሡ ቀርቦ እንዲጠይቅሰት ኢዮአብን አሰ
ጠራ፤ ኢዮአብ ግን መምጣት አልፈቀደም፤
አቢሴሎም እንደገና ኢዮአብ እንዲመጣሰት
መልእክት ላከ፤ ኢዮአብ ግን አሁንም ሳይመጣ
ቀረ፤ 30 ሰሰዚህም አቢሴሎም አገልጋዮቹን
“ተመልከቱ! የኢዮአብ እርሻ ከእኔ እርሻ
ቀጥሶ ሲሆን የገብሰ ሰብል ይገኝበታል፤ ሰሰዚ
ህም ሂዱና በእሳት አቃጥሉት” ሲል አዘዛ
ቸው፤ እነርሱም ሄደው ሰብሉን በእሳት አቃ
ጠሉ።
31 ኢዮአብም ወደ አቢሴሎም ቤት ገሥግሦ
ሄደና “አገልጋዮችህ የእርሻዬን ሰብል ያቃጠ
ሱት ሰሰምንድን ነው?” ሲል ጠየቀው።
32 አቢሴሎምም “አንተ እኔ ስጠራህ ስላል
መጣህ ነው፤ ወደ ንጉሡ ሄደህ ካገሹር ወጥቼ
ወደዚህ ሰምን መጣሁ? እዚያው ቆይቼ ብሆን
ኖሮ በተሻለኝ ነበር’ ብለህ ሰሰ እኔ ሁኔታ ጠይ
ቅልኝ፤ እንዲሁም ከንጉሡ ጋር መገናኘት
እችል ዘንድ ሁኔታዎችን አመቻችልኝ፤ እኔ
በደለኛ ሆኜ ከተገኘሁ ሞት ይፍረድብኝ”
አሰው።
33 ስሰዚህም ኢዮአብ ወደ ንጉሥ ዳዊት
ሄደና አቢሴሎም ያሰውን ሁሱ ነገረው፤ ንጉ
ሡም አቢሴሎምን አስጠራ፤ አቢሴሎምም ሄዶ
በንጉሡ ፊት ወደ መሬት ሰጥ ብሎ እጅ ነሣ፤
ንጉሡም ሰሞ ተቀበሰው።

ምዕራፍ 15

አቢሴሎም ሰግሞዕ ዐቀደ

1 ከዚህ በኋላ አቢሴሎም አንድ ሠረገሳና ፈረ
ሶች ሰራሱ አደራጀ፤ እንዲሁም ጎምሳ ጋሻ
ጃግሬዎች እንዲኖሩት አደረገ፤ 2 በማሰዳ እየተ
ነሣ በመሄድ ወደ ከተማይቱ ቅጽር በር በሚያ
ስገባው መንገድ ዳር ይቆም ነበር፤ ንጉሡ ጕዳ
ዩን እንዲያይሰት የሚፈልግ ጠብ ከርከር ያሰ
በት በው ሁሱ ወደዚያ ሲመጣ አቢሴሎም
ጠርቶ ከወዴት እንደመጣ ይጠይቀዋል፤ ሰው
የው ከየትኛው ነገድ መሆኑን ከነገረው በኋላ፥
3 አቢሴሎም “ተመልከት! ሕግ እንተን ይደግፍ
ሃል፤ ነገር ግን የንጉሡ እንደራሴ በመሆን ጕዳ
ዩን በትክክል የሚያይልህ የሰም” ይሰዋል፤
4 ንግግሩንም በመቀጠል “እኔ ዳኛ ብሆን እን
ዴት በወደድሁ ነበር! ከርከር ወይም አቤቱታ
ያሰበት ሰው ወደ እኔ ሲመጣ እኔ ትክክሰኛውን
ፍርድ እሰጠው ነበር” ይሰዋል። 5 ሰውየው
በፊቱ ሰጥ ብሎ እጅ ሰምንሣት በሚቀርብበት
ጊዜ አቢሴሎም እጁን ዘርግቶ በማቀፍ ይስመ
ዋል። 6 አቢሴሎም ፍርድ ሰማግኘት ወደ
ንጉሡ ሰሚመጡት ሁሱ እንደዚህ ያደርግ ስሰ
ነበር የእነርሱን ልብ ሰመማረክ ቻሰ።
7 ከአራት ዓመት በኋላ አቢሴሎም ንጉሥ
ዳዊትን እንዲህ አሰው፥ “ንጉሥ ሆይ! ሰእግዚ
አብሔር የተሳልሁትን ሰእሰት ሰመፈጸም ወደ
ኬብሮን እንድሄድ ፍቀድልኝ፤ 8 ምክንያቱም
በሶርያ ሰምትገኘው በገሹር በኖርኩበት ጊዜ
‘ወደ ኢየሩሳሌም ብትመልሰኝ መሥዋዕት አቀ
ርብልሃሰሁ’ ብዬ ሰእግዚአብሔር ሰእሰት ተሰዬ
ነበር።”
9 ንጉሡም “በሰላም ሂድ” አሰው፤ ሰሰዚ
ህም አቢሴሎም ወደ ኬብሮን ሄደ፤ 10 “ነገር
ግን ወደ እስራኤል ነገዶች ሁሱ መልእክተኞ
ችን ልኮ የመሰከት ድምፅ በምትሰሙበት ጊዜ
ድምፃችሁን ከፍ በማድረግ ‘አቢሴሎም የኬብ
ሮን ንጉሥ ሆኗል!’ ብላችሁ ጩኹ” ብሰው
እንዲነግሩአቸው አደረገ። 11 በአቢሴሎም ጋባ
ዥነት ከእርሱ ጋር ከኢየሩሳሌም የሄዱ ሁሰት
መቶ ሰዎች ነበሩ፤ እነርሱም ተከትሰውት የሄ
ዱት ሰሰ ሄራው ምንም ነገር ሳያውቁ በቅንነት
ነበር። 12 አቢሴሎም መሥዋዕት በሚያቀርብበት
ጊዜ ከንጉሥ ዳዊት አማካሪዎች አንዱ የሆነውን
አኪጦፌል ተብሎ የሚጠራውን ሰው መልእክ
ተኛ በመላክ ከጊሎ ከተማ አስጠራ፤ በንጉሡ
ላይ የተጠነሰሰው ሤራ እየጠነከረ፥ የአቢሴሎ
ምም ተከታዮች ቍጥር እየጨመረ ሄደ።

ዳዊት ከኢየሩሳሌም ሸሸ

13 አንድ መልእክተኛ ዳዊትን “እስራኤሳው
ያን ታማኝነታቸውን ሰአቢሴሎም በመግሰጥ
ሳይ ናቸው” አሰው።

14 ስለዚህም ዳዊት ከአርሱ ጋር በኢየሩሳ
ሌም ለሚገኙት መኳንንቱ ሁሉ "ከአቤሴሎም
አጅ ማምለጥ ከፈለግን በፍጥነት ከዚህ ሸሽተን
እንውጣ! እንግዲህ ፍጠኑ! አለበለዚያ በፍጥ
ነት መጥቶ ድል ይመታናል፤ በከተማይቱ ያገ
ኘውንም ሁሉ ይገድላል" አላቸው።

15 እነርሱም "እሺ ንጉሥ ሆይ! አንተ ያል
ከውን ሁሉ ለመፈጸም ዝግጁዎች ነን" ሲሉ
መለሱለት። 16 ስለዚህ ንጉሡ ቤተ መንግሥቱን
ይጠብቁለት ዘንድ ካስቀራቸው ዐሥር ቊባቶች
በቀር ቤተሰቡንና መኳንንቱን ሁሉ በማስከተል
ሸሽቶ ሄደ።

17 ንጉሡና ተከታዮቹ ሁሉ ከከተማይቱ ወጥ
ተው በሚሄዱበት ጊዜ በከተማይቱ መጨረሻ
ላይ በሚገኘው አንድ ቤት አጠገብ ቆሙ፤
18 የከብር ዘቦቹም በንጉሡ ፊት በሚያልፉበት
ጊዜ መኳንንቱ ሁሉ በንጉሡ አጠገብ ቆመው
ነበር፤ ኪጋት የተከተሉት ስድስት መቶ ወታደ
ሮችም በፊቱ አለፉ፤ 19 ንጉሡም ኢታይ
ተብሎ የሚጠራውን አዝማቻቸውን እንዲህ
አለው፥ "ከእኛ ጋር ለምን ትሄዳለህ? ተመል
ሰህ ከአዲሱ ንጉሥ ጋር ቆይ፤ አንተ ከአገርህ
ወጥተህ ሰሰደተኛነት እዚህ የምትኖር የውጭ
አገር ሰው ነህ፤ 20 በዚህ አገር የኖርከውም ለአ
ጭር ጊዜ ነው፤ ታዲያ አንተ ከእኔ ጋር የምት
ንከራተተው ለምንድን ነው? እኔ የት እንደም
ሄድ እንኳ አላውቅም፤ ስለዚህ የአገርህን ሰዎች
ይዘህ ተመለስ፤ እግዚአብሔር ቸርነቱንና እውነ
ተኛነቱን ይግለጥልህ።"

21 ኢታይ ግን "ንጉሥ ሆይ! ሞትን የሚያስ
ከትልብኝ ቢሆን እንኳ ወደምትሄድበት ሁሉ
ዘወትር አብሬህ እንደምሄድ በእግዚአብሔር
ሰም እምልልሃለሁ" ሲል መለሰ።

22 ዳዊትም "መልካም ነው! እንግዲህ ገሥ
ሀን ቀጥል" አለው፤ ስለዚህም ኢታይ ከወታደ
ሮቹ ሁሉና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ጕዞውን
ቀጠለ፤ 23 የዳዊት ተከታዮች ወጥተው በሄዱ
ጊዜ ሕዝቡ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አለ
ቀሱ፤ ንጉሡ ከተከታዮቹ ጋር የቄድሮንን
ወንዝ ተሻገረ፤ በአንድነትም ሆነው ወደ በረ
ሓው አመሩ።

24 ካህኑ ሳዶቅም እዚያው ነበር፤ የተቀደሰ
ውን የቃል ኪዳን ታቦት የሚሸከሙት ሌዋውያ
ንም ከእርሱ ጋር ነበሩ፤ እነርሱም ታቦቱን አስ
ቀመጡ፤ ሕዝቡ ሁሉ ከተማውን ለቀው እስኪ
ወጡ ድረስ አላኑሡትም ነበር፤ ካህኑም አብያ
ታር ደግሞ እዚያው ነበር፤ 25 ከዚህ በኋላ
ንጉሡ ሳዶቅን እንዲህ አለው፥ "የቃል ኪዳኑን
ታቦት ወደ ከተማይቱ መልሰህ ውሰድ፤ በእግዚ
አብሔር ፊት ሞገስ ያገኘሁ እንደሆን አንድ
ቀን ታቦቱንና ማደሪያውን እንዳይ ይፈቅድልኝ
ይሆናል፤ 26 በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ባላገኝ
ግን በእኔ ላይ የወደደውን ያድርግ።" 27 ንግግ
ሩንም በመቀጠል ሳዶቅን እንዲህ አለው፤
"ተመልከት! ልጅህን አሒማዓጽንና የአብያታ
ርንም ልጅ ዮናታንን ይዘህ ወደ ከተማይቱ በሰ
ላም ሂድ፤ 28 እኔም ከአንተ ወሬ አስከማገኝ
ድረስ በበረሓው ውስጥ በሚገኘው በወንዙ
መሻገሪያ ላይ አጠባበቃለሁ።" 29 ስለዚህም
ሳዶቅና አብያታር የቃል ኪዳኑን ታቦት ወደ
ኢየሩሳሌም መልሰው ወሰዱ፤ በዚያም ቆዩ።

30 ዳዊትም ሐዘኑን በመግለጥ ጫማ ሳያደርግ
ራሱን ተከናንቦ የደብረ ዘይትን አቀበት እያለ
ቀሰ ወጣ፤ የተከተሉትም ሁሉ ደግሞ ራሳቸ
ውን ተከናንበው ያለቅሱ ነበር። 31 ዳዊት፥
አኪጦፌል ከአቤሴሎም ጋር በዐመፅ መተባበ
ሩን በሰማ ጊዜ "እግዚአብሔር ሆይ! የአኪጦፌ
ልን ምክር ወደ ክንቱነት እንድትለውጥበት እለ
ምንሃለሁ" ሲል ጸለየ።

32 ዳዊት የሚምለክ ያ ስፍራ ወዳለበት ወደ
ኮረብታው ጫፍ በደረሰ ጊዜ ታማኝ ጓደኛው
የሆነው አርካዊው ሑሻይ ልብሱን ቀዶና በራሱ
ላይ ትቢያ ነስንሶ የተከተለው መሆኑን ተረዳ።
33 ዳዊትም እንዲህ አለው፥ "አንተ እኔን ተከት
ለህ ብትሄድ ምንም ልትረዳኝ አትችልም፤
34 አንተ እኔን ልትረዳኝ የምትችለው ግን ወደ
ከተማይቱ ተመልሰህ አቤሴሎምን፦ አባትህን
እንዳገለገልሁ እንተንም በታማኝነት አገለግላ
ለሁ ብለህ ብትነግረውና እንዲሁም አኪጦፌል
የሚሰጠውን ምክር ሁሉ ብትቃወምልኝ ነው፤
35 ካህናቱ ሳዶቅና አብያታርም በዚያው ይገ
ኛሉ፤ በቤተ መንግሥት የምትሰማውን ነገር
ሁሉ ለእነርሱ ትነግራቸዋለህ፤ 36 ከእነርሱም
ጋር ልጆቻቸው አሒማዓጽና ዮናታን ይገኛሉ፤
የምታገኘውንም ወሬ ሁሉ በእነርሱ በኩል
ልትልክብኝ ትችላለህ።"

37 ስለዚህም የዳዊት ወዳጅ ሑሻይ ወደ ከተ
ማይቱ ተመለሰ፤ አቤሴሎምም ወዲያውኑ
አዚያ ደረሰ።

ምዕራፍ 16

ዳዊትና ጺባ

1 ዳዊት ከኮረብታው ጫፍ፥ ባሻገር ገና ጥቂት
እንደሄደ ጺባ ተብሎ የሚጠራው የመፊቦሼት
አገልጋይ በድንገት አገኘው፤ አርሱም ሁለት
መቶ ሙልሙል ዳቦ፥ አንድ መቶ የዘቢብ ጥፍ
ጥፍ፥ አንድ መቶ እሰር ፍራፍሬና በወይን
ጠጅ የተሞላ አንድ አቁማዳ የተጫኑ ሁለት
አህዮች ይነዳ ነበር፤ 2 ንጉሥ ዳዊትም "ይህ
ሁሉ ምንድን ነው?" ሲል ጠየቀው።

ጺባም "ንጉሥ ሆይ! አህዮቹን ያመጣኋ
ቸው ቤተሰብህ እንዲቀመጡባቸው፥ ዳቦውና

ፍራፍሬውም ለተከታዮችህ ስንቅ እንዲሆኑና የወይን ጠጁም በምድረ በዳ በሚደክመውበት ጊዜ እንዲጠጡት ነው” ሲል መለሰ ።

3 ንጉሡም “የጌታህ የሳኦል የልጅ ልጅ መፊቦሼት የት ነው?” ሲል ጠየቀው ።

ጺባም “እስራኤላውያን የአያቱን የሳኦልን መንግሥት መልሰው እንደሚሰጡት ስለተማመነ እርሱ እሁን የሚገኘው በኢየሩሳሌም ነው” ሲል መለሰ ።

4 ንጉሡም ጺባን “የመፊቦሼት የነበረው ንብረት ሁሉ ከእንግዲህ የአንተ ነው” አለው ።

ጺባም “ንጉሥ ሆይ! እኔሆ እኔ አገልጋይህ ነኝ ፤ ዘወትር እንተን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ለመ ሥራት እተጋለሁ” ሲል መለሰ ።

ዳዊትና ሺምዒ

5 ንጉሥ ዳዊት ወደ ባሑሪም በደረሰ ጊዜ ከሳኦል ዘመዶች አንዱ የሆነው የጌራ ልጅ ሺምዒ ሊገናኘው ወጥቶ እየተራገመ ወደ እርሱ ቀረበ ፤ 6 ዳዊት በሠራዊቱና በከብር ዘበኞቹ መካከል እያለ ሺምዒ በዳዊትና በመኳንንቱ ላይ ድንጋይ መወርወር ጀመረ ። 7 ዳዊት ንም በመራገም የተናገረው ቃል እንዲህ የሚል ነው ፥ “እንተ ነፍሰ ገዳይ! እንተ ወንጀለኛ! ከዚህ ውጣ! 8 እንተ የሳኦልን መንግሥት ወሰድህ ቤተሰቡንም ሁሉ ገደልህ ፤ እነሆ እሁን ደግሞ እግዚአብሔር አንተን በመቅጣት ላይ ነው ! እግዚአብሔር መንግሥትን ለልጅህ ለአቤሴሎም አሳልፎ ሰጥቶታል ፤ እንተ ነፍሰ ገዳይ! እነሆ የእንተ መዋረያ ደርሶአል ።”

9 በዚህ ጊዜ የጸሩያ ልጅ አቢሻይ ንጉሡን “ንጉሥ ሆይ! ይህ ከሞተ ውሻ የማይሻል ሰው ጌታዬን ንጉሡን እንዴት ይራገማል? እኔ ሄጄ ራሱን ልቍረጠው” አለው ።

10 ንጉሡም አቢሻይንና ወንድሙን እዮአ ብን “ይህ እናንተን አይመስክታችሁም ፤ እግዚ አብሔር እዝዞት ቢረግመኝ ‘ለምን እንዲህ ታደ ርጋለህ?’ ብሎ ለመጠየቅ መብት የሚኖረው ማን ነው?” አላቸው ። 11 ቀጥሎም ዳዊት ለእ ቢሻይና ለመኳንንቱ ሁሉ እንዲህ አለ ፥ “የራሴ ልጅ ሊገድለኝ ይፈልጋል ፤ ታዲያ በዚህ ብንያ ማዊ ሰው ሰለምን ትደነቃላችሁ? እኔን እንዲረ ግመኝ እግዚአብሔር ነግሮታል ፤ ሰለዚህ ተዉት ፥ የእሰበውን ያድርግ ፤ 12 ምናልባት እግ ዚአብሔር መከራዬን እይቶ በእርሱ እርግማን ፈንታ በረከትን ይሰጠኝ ይሆናል ።” 13 ከዚህ በኋላ ዳዊትና ሠራዊቱ ባመሩበት መንገድ ተጓዙ ፤ ሺምዒም በኮረብታው ጥግ እንርሱን ተከትሎ እየሄደ በመራገም ድንጋይና ዐፈር በእ ነርሱ ላይ ይወረውር ነበር ። 14 ንጉሡና ተከታ ዮቹ ሁሉ ወደሚሄዱበት ሰፍራ በደረሱ ጊዜ በጣም ደክሞአቸው ሰለነበር በዚያ ዕረፍት አደ ረጉ ።

አቤሴሎም በኢየሩሳሌም

15 አቤሴሎምና ከእነርሱ ጋር የነበሩት እሰራ ኤላውያን በሙሉ ወደ ኢየሩሳሌም ገቡ ፤ አኪ ጦፌልም ከእነርሱ ጋር ነበር ፤ 16 የዳዊት ታማኝ ወዳጅ ሑሻይ አቤሴሎምን ባገኘው ጊዜ “ንጉሡ ለዘላለም ይኑር! ንጉሡ ለዘላለም ይኑር!” አያሰ ጮኸ ።

17 አቤሴሎምም “ለወዳጅህ ለዳዊት የነበረህ ታማኝነት እንደዚህ ነበርን? እርሱንስ ተከትለህ ለምን አልሄድህም?” ሲል ጠየቀው ።

18 ሑሻይም እንዲህ ሲል መለሰለት “እን ዴት እኔ ይህንን አደርጋለሁ? እኔ ምንግዜም በዚህ ሕዝብና በመላው እሰራኤል እንዲሁም በእግዚአብሔር የተመረጠው ሰው ወገን ነኝ ፤ አሁንም ከእንተ ጋር እኖራለሁ ፤ 19 ለመሆኑ የጌታዬን ልጅ ካሳገለገልሁ ማንን ላገለግል ነው? ለሰዚህ አባትህን እንዳገለገልሁ አሁንም ደግሞ እንተን አገለግላለሁ ።”

20 ከዚህ በኋላ አቤሴሎም ወደ አኪጦፌል መለሰ ብሎ “እነሆ እኛ አሁን በዚህ ተገኝተ ናል ፤ ታዲያ ምን እንድናደርግ ትመክረናለህ?” ሲል ጠየቀው ።

21 አኪጦፌልም “እንግዲህ ሄደህ አባትህ ቤተ መንግሥቱን ይዋብቁሰት ዘንድ ካሰቀራ ቸው ከእባትህ ቍባቶች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙ ነት አድርግ ፤ ከዚያም በኋላ በእሰራኤል የሚ ኖር ማንኛውም ሰው አባትህን እንደ ብርቱ ጠላት የቈጠረህ መሆኑን ያውቃል ፤ የተከታዮ ችህም ወኔ ይቀሰቀሳል” ሲል መለሰለት ። 22 ሰለዚህ በቤተ መንግሥቱ ጣራ ላይ ለአቤሴ ሎም ድንኳን ተከሰለት ፤ ሰውም ሁሉ እየተመ ለከተው ወደ ድንኳኑ ገብቶ ከአባቱ ቍባቶች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገ ።

23 በዚያን ጊዜ አኪጦፌል የሚሰጠው ማንኛ ውም ምክር ልክ እንደ እግዚአብሔር ቃል ተቀባይነት እግኝቶ ነበር ፤ ቀድሞ ዳዊት አሁን ደግሞ አቤሴሎም የእርሱን ምክር ይከተሉ ነበር ።

ምዕራፍ 17

ሑሻይ አቤሴሎምን አዘናጋ

1 ከዚህ በኋላ ብዙም ሳይቆይ አኪጦፌል አቤሴሎምን እንዲህ አለው “ዛሬ ማታ ዳዊትን አሳድጀ ለመያዝ እችል ዘንድ ዐሥራ ሁለት ሺ ሰዎች እንድመርጥ ፍቀድልኝ ፤ 2 ደክሞት ተሰፋ በመቊረጥ ላይ ሳለ ድንገተኛ እደጋ እጥ ልበታለሁ ፤ በዚያን ጊዜ እርሱ ድንጋጤ ላይ ይወድቃል ፤ ተከታዮቹም ጥሰውት ይሸሻሉ

ንኑሩን ለብቻው ገደዬ ፥ 3 ሙሽራ ወደ ባልዋ እንደምትመለስ ተከታዮቹ በሙሉ ወደ አንተ ተመልሰው እንዲመጡ እደርጋለሁ ፥ እንግዲህ አንተ የምትፈልገው አንድ ሰው ብቻ መሣደልን ነው ፥ የቀረው ሌላው ሕዝብ ግን በሰላም ይኖራል ።” 4 ይህም ለአቤሴሎምና ለእስራኤል መሪዎች ሁሉ ጥሩ ምክር መስሎ ታያቸው ።

5 አቤሴሎምም “አሁን ደግሞ ሑሻይን ጥሩ ትና እርሱ የሚለውን እንስማ” አለ ። 6 ሑሻ ይም ባደረሰ ጊዜ አቤሴሎም “አኪጦፌል የሰ ጠን ምክር ይህ ነው ፥ ይህንኑ ምክር እንከተል ወይስ ምን ማድረግ እንደሚገባን አንተም የም ትነግረን አለ ይሆን” ሲል ጠየቀው ።

7 ሑሻይም እንዲህ ሲል መለሰ ፥ “በአሁኑ ሰዓት አኪጦፌል የሰጣችሁ ምክር ጥሩ አይደ ለም ፥ 8 አባትህ ዳዊትና ተከታዮቹ ብርቱ ጦረ ኞች እንደሆኑና ግልገሎችዋ እንደተነጠቁባትም ድብ አስፈሪዎች መሆናቸውን ታውቃለህ ፥ አባ ትህ በጦር ልምድ የተፈተነ ወታደር በመሆኑ ሌሊቱን ከሠራዊቱ ጋር አያድርም ፥ 9 ምናልባት አሁን እንኳ በዋሻ ውስጥ ወይም በሌላ ሰፍራ ተሸሽጎ ሊሆን ይችላል ፥ ዳዊት በአንተ ሠራዊት ላይ አደጋ እንደጣለባቸው የሚሰማ ሰው ሁሉ ወዲያውኑ ወታደሮችህ እንደተሸነፉ አድርጎ ያወ ራል ። 10 አባትህ ታላቅ ጦረኛ መሆኑንና የእር ሱም ተከታዮች ብርቱ ተዋጊዎች መሆናቸውን ዘእስራኤል የሚኖር ሁሉ ስለሚያውቅ እንደ አን በሳ ደፋሮች የሆኑት ወታደሮችህ እንኳ ልባቸው በፍርሃት ሊቀልጥ ይችላል ። 11 ስለዚህ እኔ የም መክርህ ፥ ከአገሪቱ አራት ማእዘኖች ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ያሉትንና ብዛታቸው እንደ ባሕር ዳር አሸዋ የሆነው እስራኤላውያን ሁሉ በእንድነት ሰብስበህ አንተው ራስህ አዛዥ በመሆን ወደ ጦር ነቱ እንድትመራቸው ነው ። 12 የትም ስፍራ ቢደ በቅ ዳዊትን ፈልገን እናገኘዋለን ፥ በረዶ በምድር ላይ እንደሚወርድ እንወርድበታለን ፥ እርሱም ሆነ ከተከታዮቹ አንድ ሰው እንኳ በሕይወት የሚ ተርፍ አይኖርም ። 13 ሸሽቶ ወደ ከተማም ቢገባ ሕዝባችን በሙሉ ገመድ አምጥተው ከተማይቱን በመሳብ በእርስዋ ሥር ወደሚገኘው ሸለቆ እሽቀ ንዋረው ይጥሉአታል ፥ በነረብታውም ላይ አንድ ድንጋይ እንኳ አይቀርም ።”

14 አቤሴሎምና እስራኤላውያን በሙሉ “ከአ ኪጦፌል ምክር ይልቅ የሑሻይ ምክር ይበል ጣል” አሉ ፥ በእቤሴሎም ላይ ጥፋት ይመጣ በት ዘንድ እግዚአብሔር የአኪጦፌል መልካም ምክር ተቀባይ እንዳይኖረው አደረገ ።

ዳዊት በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስለተሰጠው አመለጠ

15 ከዚህ በኋላ እርሱና አኪጦፌል ለአቤሴሎ ምና ለእስራኤላውያን መሪዎች የሰጡትን ምክር ሑሻይ ለካህናቱ ለሳዶቅና ለአብያታር ነገራቸው ፥ 16 ከዚህም ጋር “እንግዲህ ዛሬ ሌሊት በበረሓ ውስጥ በሚገኘው በወንዙ መሻገ ሪያ ላይ እንዳያድር በፍጥነት መልእክተኛ ልካ ችሁ ለዳዊት ንገሩት ፥ ነገር ግን እርሱና ተከታ ዮቹ ተያዘው እንዳይገደሉ በፍጥነት የዮርዳኖ ስን ወንዝ ይሻገሩ” አላቸው ።

17 የአብያታር ልጅ ዮናታንና የሳዶቅ ልጅ አሒማዓጽ ወደ ከተማይቱ ሲገቡ ማንም እንዳያ ያቸው ስለፈሩ ፥ ከኢየሩሳሌም አካባቢ ባለችው በዔንሮጌል ምንጭ አጠገብ ይጠባበቁ ነበር ፥ አንዲት ልጃገረድ አገልጋይም ዘወትር ወደዚያ እየሄደች የሚሆነውን ነገር ሁሉ ትነግራቸው ነበር ፥ ከዚያም በኋላ እነርሱ ሄደው ለንጉሥ ዳዊት ይነግሩት ነበር ፥ 18 ነገር ግን አንድ ቀን አንድ ልጅ እንርሱን በላያቸው ሄዶ ለአቤሴ ሎም ነገረው ፥ ስለዚህ እነርሱ በባሔሪም በሚገ ኘው በአንድ ሰው ቤት ሰመሸሸግ ሮጠው ሄዱ ፥ ሰውየው በቤቱ አጠገብ የውሃ ጕድጓድ ስለነበረው ወደዚያ ውስጥ ገቡ ። 19 የዚያም ሰው ሚስት በጕድጓዱ አፍ ላይ የእህል ማስ ጪያ ሰሌን ዘርግታ ማንም ሰው እንዳይጠረጥር እህል አሰጣችበት ። 20 የአቤሴሎም ባለማዕሮች ወደዚያ ቤት መጥተው ሴቲቱን “አሒማዓጽና ዮናታን የት ናቸው?” ሲሉ ጠየቁአት ።

እርስዋም “ወንዙን ተሻግረው ሄደዋል” ስትል መለሰች ።

ሰዎቹም ፈልገው ሊያገኙአቸው ስላልቻሉ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ። 21 እነርሱም ከሄዱ በኋላ አሒማዓጽና ዮናታን በፍጥነት ከጕድጓዱ ወጥተው በመሄድ የሆነውን ሁሉ ለንጉሥ ዳዊት ነገሩት ፥ አኪጦፌል በእነርሱ ላይ ዐቅ ዶት የነበረውን ካስረዱት በኋላም “ፈጥነህ ወን ዙን ተሻገር” አሉት ። 22 ስለዚህም ዳዊትና ተከታዮቹ የዮርዳኖስን ወንዝ መሻገር ጀመሩ ፥ በማለዳ ጊዜ ሁሉም ወንዙን ተሻግረው ነበር ።

23 አኪጦፌል የሰጠው ምክር ተቀባይነት እንዳላገኘ በተረዳ ጊዜ አህያውን ጭኖ ወደ መኖሪያ ከተማው ተመልሶ ሄደ ፥ ሁሉን ነገር መልክ በማስያዝ ካስተካከለም በኋላ ተሰቅሎ ሞተ ፥ በዚህ ሰበቡም መቃብር ተቀበረ ።

24 አቤሴሎምና እስራኤላውያን ሁሉ የዮርዳ ኖስን ወንዝ በተሻገሩ ጊዜ ዳዊት ማሕናይም ተብላ ወደምትጠራው ትንሽ ከተማ ደርሶ ነበር ። 25 አቤሴሎም በእዮአብ ምትክ ዐማሳ ተብሎ የሚጠራውን ሰው የጦር አዛዥ አድርጎ ሾመ ፥ ዐማሳ የእስራኤላዊው የዬቴር ልጅ ነበር ፥ እናቱም አቢጋይል ተብላ የምትጠራ የና ሐሽ ልጅ ስትሆን ለእዮአብ አናት ለጸሩያ እኅት ነበረች ። 26 አቤሴሎምና ሠራዊቱም በገለ ዓድ ምድር ሰፈሩ ።

27 ዳዊት ማሕናይም በደረሰ ጊዜ ሰዐሞን ግዛት ራባ ተብላ ከምትጠራው ከተማ የመጣ

ውን የናያስን ልጅ ቦቢን ፥ ከሎደባር ከተማ የመጣውን የዓሚኤልን ልጅ ማኪርንና ከገለዓድ ግዛት ሮገሊም ተብላ ከምትጠራው ከተማ የመጣውን ባርዚላይን አገኘ ። 28-29እነርሱም ምን ችቶችንና የሸክላ ማሰሮዎችን ፥ የመኝታ አልጋዎችንም ይዘው መጡ ፤ እንዲሁም ሰዳዊትና ሰተከታዮቹ የሚሆን ስንዴ ፥ ገብስ ፥ ዱቄት ፥ የተጠበሰ እሸት ፥ ባቄላ ፥ አተር ፥ ማር ፥ አይብ ፥ እርጎና በጎችን አመጡ ፤ ይህንንም ያደረጉበት ምክንያት ዳዊትና ተከታዮቹ በበረሓ ኑሮ እንደሚርባቸው ፥ እንደሚጠማቸውና እን ደሚደክማቸው በማሰብ ነው ።

ምዕራፍ 18

አቤሴሎም ድል ተመቶ ሞተ

1ንጉሥ ዳዊት ተከታዮቹን ሁሉ በእንድነት ከሰበሰበ በኋላ በሺና በመቶ መድቦ ሰእያንዳንዱ ቡድን የጦር መኰንን ሾመ ፤ 2ከዚህም በኋላ ሦስት ክፍል አድርጎ ላካቸው ፤ ኢዮአብና የአ ርሱ ወንድም አቢሻይ ፥ እንዲሁም የጋት ተወ ላጅ የሆነው ኢታይ አያንዳንዳቸው የአንዳንድ ክፍል አዛዦች ሆኑ ፤ ንጉሡም ተከታዮቹን “እኔም ራሴ አብሬአችሁ እሄዳለሁ” አላቸው ።

3እነርሱም “አንተ ከእኛ ጋር መሄድ የለብ ህም ፤ ዋቂቶቻችን ወደ ኋላ ተመልሰን ብንሄድ ወይም ግማሾቻችን ብንገደል ጠላት ምንም እይ ገደውም ፤ አንተ ግን ከእኛ ዐሥሩን ሺ ትበልጣ ለህ ፤ ስለዚህ አንተ እዚሁ በከተማይቱ ውስጥ ቆይተህ አስፈላጊውን ዕርዳታ ብትልክልን ይሻ ላል” አሉት ።

4ንጉሡም “እናንተ መልካም መስሎ የታያ ችሁን ሁሉ አደርጋለሁ” ሲል መለሰላቸው ። ከዚህ በኋላም በቅጽር በሩ አጠገብ ቆሞ በሺና በመቶ የተመደቡት ሠራዊት ተሰልፈው ሲወጡ ተመለከተ ። 5ሰኢዮአብ ፥ ሰአቢሻይና ሰኢታ ይም “ሰእኔ ስትሉ በወጣቱ በአቤሴሎም ላይ ሰሞት የሚያደርስ ጉዳት እንዳታደርሱበት” የሚል ትእዛዝ ሰጣቸው ፤ ዳዊት ይህን ትእዛዝ ሰጦር አዛዦቹ በሰጠ ጊዜም ወታደሮቹ ሁሉ ይሰሙ ነበር ።

6የዳዊት ሠራዊት ወደ ገጠር ወጥተው አሰ ራኤላውያንን በኤፍሬም ደን ውስጥ ተዋጉአ ቸው ፤ 7አሰራኤላውያንም በዳዊት ተከታዮች ድል ተመቱ ፤ የመሸነፋቸውም ሁኔታ እጅግ አሠቃቂ ነበር ፤ ምክንያቱም በዚያን ቀን የሞቱ ባቸው ሰዎች ቍጥር ሃያ ሺ ያህል ነበር ። 8ጦርነቱም በየገጠሩ ስለተሰፋፋ በጦርነት ከሞ ቱት ሰዎች ይልቅ በደን ውስጥ ያሰቁት ቍጥራ ቸው በዛ ።

9በድንገት ፥ አቤሴሎም ከዳዊት ተከታዮች ዋቂቱን አገኘ ፤ አቤሴሎም በዚያን ጊዜ በበቅሎ ላይ ተቀምጦ ይጋልብ ስለነበር በቅሎዋ ዘእንድ ትልቅ የወርካ ዛፍ ሥር ስታልፍ ሳሰ የዛፉ ቅር ንጫፍ የአቤሴሎምን የራስ ጠጕር ያዘበት ፤ በቅ ሎዋም በእግሮቹ መሐል ሾልካ ስትሄድ አቤሴ ሎም በዐየር ላይ ተንጠልጥሎ ቀረ ። 10ከዳዊት ወታደሮችም አንዱ ይህን አይቶ ሰኢዮአብ “ጌታዬ! አቤሴሎምን በወርካ ዛፍ ላይ ተንጠል ጥሎ አየሁት” ብሎ ነገረው ።

11ኢዮአብም “ታዲያ ካየኸው ሰምን ወዲያ ውኑ አልገደልኸውም? ይህን አድርገህ ሲሆን ኖሮ እኔ ራሴ ዐሥር ጥሬ ብርና አንድ ዙር ዝናር በሸለምኩህ ነበር” ሲል መለሰለት ።

12ሰውየው ግን እንዲህ ሲል መለሰ ፥ “አንድ ሺ ጥሬ ብር አንኳ ብትሰጠኝ በንጉሡ ልጅ ላይ እጀን አላነሣም ፤ ንጉሡ ሰአንተ ፥ ሰአቢሻይና ሰኢታይ ‘ሰእኔ ስትሉ በወጣቱ አቤ ሴሎም ላይ ሰሞት የሚያደርስ ጉዳት እንዳታደ ርሱበት’ ሲል የሰጣችሁን ትእዛዝ ሁላችንም ሰምተናል ፤ 13ታዲያ እኔ የንጉሡን ትእዛዝ በመጣስ አቤሴሎምን ገድዬ ቢሆን ኖሮ ፥ ንጉሡ ሁሉን ነገር እንደሚሰማ ይህንንም መስ ማቱ አይቀርም ፤ አንተም እኔን ሰማዳን አትከላ ከልልኝም ።”

14ኢዮአብም “እኔ አሁን ከአንተ ጋር ጊዜ ማባከን አልፈልግም” አለውና ሦስት ጦሮችን ወሰዶ አቤሴሎም በወርካው ዛፍ ላይ ተንጠል ጥሎ ገና በሕይወት ሳለ በደረቱ ተከሰበት ። 15ከዚያም በኋላ የኢዮአብ አጫቢዎች ከሆኑ ወታደሮች ዐሥሩ ወደ አቤሴሎም ሄደው ዙሪያ ውን በመከበብ በጦር መግሪያ ገደሉት ።

16ኢዮአብ ጦርነቱ ይቆም ዘንድ መለከት እንዲነፉ አዘዘ ፤ ወታደሮቹም አሰራኤላውያንን ከማሳደድ ተመልሰው መጡ ፤ 17የአቤሴሎም ንም ሬሳ ወስደው በደን ውስጥ በሚገኘው ጥልቅ ጕድጓድ ውስጥ ጣሉት ፤ በእርሱም ላይ ብዙ ትልልቅ ድንጋይ ከምረው እንዲሸፈን አደ ረጉት ፤ እሰራኤላውያንም ሁሉ ሸሽተው እያን ዳንዱ ሰው ወደየቤቱ ገባ ።

18አቤሴሎም ስሙን የሚያስጠራለት ወንድ ልጅ አልነበረውም ፤ ስለዚህም በሕይወት በነበ ረበት ዘመን “የንጉሥ ሸለቆ” ተብሎ በሚጠ ራው ስፍራ ሰራሱ ሐውልት አሠርቶ ነበር ፤ በራሱም ስም ሰይሞት ስለነበር እስከ ዛሬ ድረስ “የአቤሴሎም ሐውልት” እየተባለ ይጠራል ።

ዳዊት የአቤሴሎምን መሞት ሰማ

19ከዚህ በኋላ የሳዶቅ ልጅ አሒማዓጽ ኢዮ አብን “እግዚአብሔር ከጠላቶቹ እንዳዳነው የሚገልጠውን መልካም ወሬ ይገር ወደ ንጉሡ ልሩጥ” አሰው ።

20ኢዮአብም “አይሆንም! ዛሬ አንተ ይዘ ኸው የምትሄድ ምንም ዐይነት መልካም ወሬ የለም ፤ ምናልባት ሌላ ቀን ይህን ልታደርግ ትችላለህ ፤ ዛሬ ግን የንጉሡ ልጅ ስለሞተ ይህን

ባታደርግ ይሻላል” አለው ። 21 ከዚህም በኋላ
ኢዮአብ አገልጋዩ የነበረውን አንድ ኢትዮጵያዊ
ጠርቶ “ያየኸውን ሁሉ ሄደህ ለንጉሡ ንገር”
አለው ፤ አገልጋዩም እጅ ነሥቶ ሮጠ ።
22 አሒማዓጽም “የፊለገው ነገር ቢሆን ግድ
የለኝም ፤ ስለዚህ እኔም ወሬውን እንዳደርስ
ፍቀድልኝ” አለ ።
ኢዮአብ ግን “ልጄ ሆይ! ስለምን ይህን
ማድረግ ፈለግህ? ይህን ስላደረግህ ምንም ሽል
ማት አታገኝም እኮ” አለው ።
23 አሒማዓጽም እንደገና “የፈለገው ነገር
ቢሆን ግድ የለኝም ፤ እኔ መሄድ እፈልጋለሁ”
አለ ።
ኢዮአብም “እንግዲያውስ ሂድ” አለው ፤
ስለዚህም አሒማዓጽ በዮርዳኖስ ሸለቆ በሚያመ
ራው መንገድ ሲሮጥ ሄዶ ወዲያውኑ አገልጋዩን
ቀደመው ።
24 ዳዊት በከተማይቱ ውስጣዊና ውጫዊ
በሮች መካከል ባለው ግልጥ ቦታ ተቀምጦ
ነበር ፤ ከተማ ጠባቂውም ቃፈር በቅጽሩ ግንብ
አናት ላይ ወጥቶ በበሩ ጣራ ላይ ቆሞ ሰለነበር
ቀና ብሎ ሲመለከት አንድ ሰው ብቻውን እየ
ሮጠ ሲመጣ አየ ፤ 25 ድምፁንም በማሰማት ያየ
ውን ለንጉሡ ነገረው ፤ ንጉሡም “ብቻውን
ከሆነ መልካም ወሬ ይዞ የመጣ መሆን አለ
በት” አለ ፤ ያም ሯጭ ሰው እየቀረበ መጣ ።
26 ቃፈሩም እንደገና አንድ ሌላ ሰው እየ
ሮጠ ሲመጣ አይቶ ፥ የቅጽር በር ጠባቂውን
በመጣራት “ተመልከት! ሌላም አንድ ሰው እየ
ሮጠ በመምጣት ላይ ነው” አለው ።
ንጉሡም “ይህኛውም መልካም ወሬ ይዞ
የሚመጣ ሊሆን ይችላል” ሲል መለሰ ።
27 ቃፈሩም “የመጀመሪያው ሰው የሚሮ
ጠው ልክ አንደ አሒማዓጽ ነው” አለ ። ንጉ
ሡም “እርሱ ጥሩ ሰው ነው ፤ መልካም ወሬ
ይዞ ይመጣል” አለ ።
28 አሒማዓጽም ድምፁን ከፍ አድርጎ ለን
ጉሡ ሰላምታ ሰጠ ፤ በንጉሡም ፊት በግንባሩ
መሬት ላይ ተደፍቶ “ንጉሥ ሆይ! በአንተ ላይ
በዐመፅ የተነሣሡትን ድል እንድታደርግ ስለረ
ዳህ እግዚአብሔር የተመስገነ ይሁን!” አለ ።
29 ንጉሡም “ወጣቱ አቢሴሎም ምንም
ጕዳት አልደረሰበትምን?” ሲል ጠየቀ ።
አሒማዓጽም “ጌታዬ ሆይ! የጦር አዛዥህ
ኢዮአብ ወደ አንተ በላከኝ ጊዜ ታላቅ ሁካታ
ሆኖ አየሁ ፤ ነገር ግን ምን እንደሆነ መናገር
አልችልም” ሲል መለሰ ።
30 ንጉሡም “አልፍ ብለህ ቁም!” አለው ።
31 ቀጥሎም ኢትዮጵያዊው አገልጋይ እዚያ
ደረሰና ንጉሡን “ንጉሥ ሆይ! የምሥራች ቃል
ይዤልህ መጥቼአለሁ ፤ በአንተ ላይ በዐመፅ የተ
ነሣሡብህን ድል እንድታደርግ ዛሬ እግዚአብ
ሔር ረድቶሃል” አለው ።
32 ንጉሡም “ወጣቱ አቢሴሎም ምንም
ጕዳት አልደረሰበትምን?” ሲል ጠየቀ ።
አገልጋዩም “ጌታዬ ሆይ! በእርሱ ላይ የደ
ረሰ ነገር በጠላቶችህና በአንተ ላይ በዐመፁት
ሁሉ ላይ ይድረስ!” ሲል መለሰ ።
33 ንጉሡም እጅግ አዘነ ፤ በቅጽር በሩ አናት
ላይ ወደሚገኘውም ከፍል ወጥቶ አለቀሰ ፤ ወደ
ዚያም ሲመጣ “ልጄ ሆይ! ልጄ አቢሴሎም!
አቢሴሎም ልጄ! ምንኩሙ በአንተ ምትክ እኔ
በሞትሁ! ልጄ ሆይ! አቢሴሎም ልጄ!” እያለ
በመጮኽ ያለቅስ ነበር ።

ምዕራፍ 19

ኢዮአብ ዳዊትን ወቀሰ

1 ንጉሥ ዳዊት ስለ ልጁ ስለ አቢሴሎም
ሞት በብርቱ አዝኖ በማልቀስ ላይ መሆኑን
ኢዮአብ ሰማ ፤ 2 እንዲሁም ንጉሡ በልጁ ምት
ምክንያት በሐዘን ላይ መሆኑን ሰለሰሙ ወታደ
ሮቹ ያገኙት የድል አድራጊነት ደስታ በዚያ
ቀን ወደ ሐዘን ተለወጠባቸው ። 3 ስለዚህ ከሠር
ግንባር ተመልሰው ወደ ኋላ እንደሚሸሹ ወታ
ደሮች ድምፃቸውን አጥፍተው በጸጥታ ወደ
ከተማይቱ ገቡ ፤ 4 ንጉሡም ፊቱን ሸፍኖ
“ልጄ ሆይ! ልጄ አቢሴሎም! አቢሴሎም
ልጄ!” እያለ ድምፁን ከፍ አድርጎ ያለቅስ
ነበር ።
5 በዚህ ጊዜ ኢዮአብ ወደ ንጉሡ ቤት ሄዶ
እንዲህ አለው ፥ “የአንተን ፥ የወንዶችና የሴ
ቶች ልጆችህን ፥ የሚስቶችህንና የቊባቶችህን
ሕይወት ያዳኑትን ሰዎች ዛሬ አሳፍረሃቸዋል ፤
6 አንተ የሚወዱህን ትጠላለህ ፤ የሚጠሉህን ግን
ትወዳለህ ፤ ስለ ጦር መኰንኖችህና ስለ ወታደሮ
ችህ ሁሉ ምንም የማይገድህ መሆኑን በግልጥ
አሳይተሃል ፤ አቢሴሎም በሕይወት ቢኖርና እኛ
ሁላችን ብንጠፋ ኖሮ እጅግ እንደምትደሰት
ተገንዝቤአለሁ ፤ 7 ይልቅስ አሁን ተነሥና ወታ
ደሮችህን አበረታታ ፤ ይህንን ባታደርግ ግን ነገ
ጠዋት ከአነርሱ አንዱ እንኳ ከአንተ ጋር እንደ
ማይሆን በእግዚአብሔር ስም እምልልሃለሁ ፤
ይህም በሕይወትህ ከደረሰብህ መከራ ሁሉ
እጅግ የከፋ ይሆንብሃል ።” 8 ከዚህ በኋላ
ንጉሡ ከተቀመጠበት ተነሥቶ በመሄድ በከተማ
ይቱ ቅጽር በር አጠገብ ተቀመጠ ፤ ተከታዮ
ቹም እዚያ መሆኑን ሰምተው ሁሉም በዙሪ
ያው ተሰበሰቡ ።

ዳዊት ወደ ኢየሩሳሌም
ለመመለስ ጉዞ ጀመረ

በዚህን ጊዜ እስራኤላውያን ሁሉ ሸሽተው
አያንዳንዱ ወደየቤቱ ሄዶ ነበር ፤ 9 በመላ አገሪ
ቱም ሕዝቡ እርስ በርስ መጣላት ጀመረ ፤
እርስ በርሳቸውም እንዲህ ተባባሉ ፥ “ንጉሥ

ዳዊት ከጠላቶቻችን እጅ በመታደግ አድኖናል፥ ከፍልስጥኤማውያንም እጅ ታድነናል፥ አሁን ግን ከአቤሴሎም ፊት በመሸሽ አገራቱን ትቶ ሄዶአል። 10 መሪያችን ይሆን ዘንድ እቤሴሎ ምን ቀብተን እንሾነው ነበር፥ ነገር ግን እርሱ በሞርነት ላይ ተገደለ፥ ታዲያ ንጉሥ ዳዊትን መልሶ ስማምጣት የሚሞከር ሰው እን ዴት ታጣ?"

11 ንጉሥ ዳዊትም አሰራኤላውያን እርስ በር ሳቸው የተናገሩትን ሰማ፥ ሰዶቅንና አብያታርን በመሳክ የይሁዳን መሪ ዎች እንዲህ ብሎው እንዲጠይቁአቸው አዘዘ፥ "ንጉሡን ረድታችሁ ወደ ቤተ መንግሥቱ ስመመስስ ሰለምን እናንተ የመጨረሻዎቹ ትሆ ናሳችሁ? 12 እናንተ እኮ ሰእኔ የሥጋ ዘመዶቼ ናችሁ፥ ታዲያ እኔን መልሶ ስመውሰድ የመጀ መሪያዎቹ በመሆን ፈንታ ሰለምን የመጨረሻ ዎቹ ትሆናላችሁ?" 13 እንዲሁም ሰዐማሳ ሲና ገር "እንተም ለእኔ የሥጋ ዘመድ ነህ፥ ከሁን ጀምሮ በኢዮአብ ምትክ የሠራዊቴ አዛዥ አደር ማሃለሁ፥ ይህንንም ባላደርግ እግዚአብሔር በሞት ይቅጣኝ" ብላችሁ ንገሩት ሲል እዘዛ ቸው። 14 የዳዊት እንጋገር የይሁዳ ሕዝብ ሁሉ ሰእርሱ ታማኞች እንዲሆኑ እደረጋቸው፥ ሰሰዚ ህም ከመኳንንቱ ሁሉ ጋር ተመልሶ እንዲመጣ ሳኩበት።

15 ዳዊት በመመስስ ላይ እንዳለም የይሁዳ ሰዎች እስከ ዮርዳኖስ ወንዝ ድረስ ሄደው ተቀ በሉት፥ እጅበውም ወንዙን ሰማሻገር እሰበው እስከ ጌልገላ ድረስ መጡ፥ 16 በዚያኑ ጊዜም የባሑሪም ተወላጅ የሆነው የጌራ ልጅ ብንያማ ዊው ሺምዒ ከይሁዳ ሰዎች ጋር ንጉሥ ዳዊትን ለመቀበል ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ፈጥኖ ሄደ፥ 17 ከእርሱም ጋር የብንያም ነገድ የሆኑ አንድ ሺ ሰዎች ነበሩ፥ የሳኦል ቤተሰብ አገልጋይ የነ በረው ጺባም ከዐሥራ አምስት ወንዶች ልጆ ቹና ከሃያ አገልጋዮቹ ጋር መጣ፥ ወደ ዮርዳና ሰም ወንዝ እየተጣደፉ ደርሰው በንጉሡ ፊት ቀረቡ። 18 እነርሱም ንጉሡንና ተከታዮቹን በጀልባ አጅበው ወደ ማዶ ለማድረስና ንጉሡ የሚፈልገውን ሁሉ ለማድረግ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻገሩ።

ዳዊት ለሺምዒ ይቅርታ አደረገለት

ንጉሡ ወንዙን ለመሻገር ሲዘጋጅ ሳለ ሺምዒ መጥቶ በፊቱ ተዘረጋና እንዲህ አለ፥ 19 "ንጉሥ ሆይ! ከኢየሩሳሌም ወጥተህ በሄድህ በት ቀን ያደረግሁትን በደል አባክህ ይቅር በለኝ፥ ቂም በቀልም አትያዝብኝ፥ ዳግመኛም ስለ እርሱ አታሰብ፥ 20 ጌታዬ ሆይ! ኃጢአት እንደሠራሁ ዐውቃለሁ፥ ዛሬ ግን ከሰሜን የአሰ ራኤል ነገዶች የመጀመሪያው በመሆን አንተን ለመቀበል መጥቼአለሁ።"

21 የጸሩያ ልጅ አቢሻይም "እግዚአብሔር ቀብቶ ያነገሠውን ሰለተሳደበ ሺምዒ በሞት መቀጣት ይገባዋል" ሲል ተናገረ።

22 ዳዊት ግን አቢሻይንና ወንድሙን ኢዮአ ብን "ይህን አሳብ እንድታቀርቡ የጠየቃችሁ ማን ነው? ችግር ልታመጡብኝ ትፈልጋላች ሁን? እነሆ አሁን የእስራኤል ንጉሥ እኔ ነኝ፥ ደግሞም በዛሬው ዕለት ማንም እስራኤላዊ በሞት አይቀጣም" አላቸው። 23 ሺምዒንም "በሞት እንደማትቀጣ ቃል እገባልሃለሁ" አለው።

ዳዊት ለመፊቦሼት ይቅርታ አደረገለት

24 ከሺህ በኋላ የሳኦል የልጅ ልጅ መፊቦ ሼት ንጉሡን ለመቀበል ወረደ፥ ንጉሡ ከእያሩ ሳሌም ከመጣበት ጊዜ አንሥቶ አሁን በድል አድራጊነት እስከተመለሰበት ጊዜ ድረስ መፊቦ ሼት እግሩን አልታጠበም፥ ጢሙን አልተላ ጨም፥ ልብሱንም አላጠበም። 25 መፊቦሼት ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ ንጉሡን በሚቀበልበት ስፍራ በደረሰ ጊዜ ንጉሡ "መፊቦሼት ሆይ! ስለምን ከእኔ ጋር ሳትሄድ ቀረህ?" አለው።

26 መፊቦሼትም እንዲህ ሲል መለሰ፥ "ንጉሥ ሆይ! እንደምታውቀው እኔ ሽባ ነኝ፥ ከአንተ ጋር ለመሄድ ፈልጌ አገልጋዬን 'በቅሎ ዬን ጫንልኝ' ብለው ከድቶኝ ሄደ፥ 27 ንጉሥ ሆይ! እንዲያውም ስለእኔ ስውሸት ለአንተ የነገ ረህ ጉዳይ አለ፥ ነገር ግን አንተ እንደ እግዚአ ብሔር መልአክ ስለሆንክ መልካም መስሎ የታ የህን አድርግ። 28 ንጉሥ ሆይ! የአባቴ ቤተሰብ ሁሉ በሞት መቀጣት የሚገባው ነበር፥ ንጉሥ ሆይ! አንተ ግን በገበታህ ቀርቤ እንድመገብ መብት ስጠኸኝ፥ ከዚህ የበለጠም ቸርነት እን ዲደረግልኝ መጠየቅ አይገባኝም።"

29 ንጉሡም "ከዚህ በላይ ብዙ መናገር አያ ስፈልግህም፥ አንተና ጺባ የሳኦል ንብረት ስሁ ስት እንድትካፈሉ ወስኛለሁ" ሲል መለሰ።

30 መፊቦሼትም "ንጉሥ ሆይ! ሁሉንም ሀብት ጺባ ይውሰደው፥ ለእኔ እንተ በሰላም ወደ ቤትህ መመለስህ ብቻ ይበቃኛል" አለ።

ዳዊት ለባርዚላይ ቸርነት አደረገለት

31 ገለዓዳዊው ባርዚላይ ንጉሡን አጅቦ የዮር ዳኖስን ወንዝ ለመሻገር ከሮገሊም መጣ፥ 32 ባርዚላይ ስማንያ ዓመት የሞላው ሽማግሌ ሰው ነበር፥ በጣም ሀብታም ከመሆኑም የተነሣ ንጉሥ ዳዊት በማሕናይም በነበረበት ጊዜ

19፥16 ፡- 2ሳሙ. 16፥5-13። 19፥24 ፡- 2ሳሙ. 9፥1-13፤ 16፥1-4። 19፥31 ፡- 2ሳሙ. 17፥27-29።

ይኸው ባርዚላይ ምግብ ያቀርብለት ነበር፤
33 ንጉሡም ባርዚላይ “ከእኔ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ና፤ እኔም በተድላና በደስታ እንድትኖር አደርግሃለሁ” አለው።
34 ባርዚላይ ግን እንዲህ ሲል መለሰ፥ “ንጉሥ ሆይ! ከእንግዲህ ወዲያ ብዙ ዘመን አልኖርም፤ ታዲያ ከአንተ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ ምን ያስፈልገኛል? 35 እነሆ እኔ አሁን የሰማኒያ ዓመት ሰው ነኝ፤ ከእንግዲህ ወዲያ የሚያስደስተኝ ነገር የለም፤ የምበላውም ሆነ የምጠጣው ጣዕም አይሰጠኝም፤ ጆሮዬም የዘፋኞችን ድምፅ አይሰማም፤ ንጉሥ ሆይ! በአንተ ላይ ሸክም ከመሆን በቀር ሌላ የማደርገው ነገር የለም። 36 ያማሞም ንጉሡ ይህን ያህል ታላቅ ወሮታ ሊከፍለኝ የሚገባኝ ሰው አይደለሁም፤ ስለዚህ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግሬ ከአንተ ጋር ጥቂት መንገድ ብቻ እሄዳለሁ። 37 ከዚያም በኋላ ወደ ቤቱ ተመልሼ አንድሄድና በወላጆቼ መቃብር አጠገብ እንዳርፍ ፍቀድልኝ፤ እነሆ ይህ ልጄ ኪምሃም ያገለግልሃል፤ ንጉሥ ሆይ! እርሱን ይዘኸው ሂድ፤ የወደድከውንም ለእርሱ አድርግለት።”
38 ንጉሡም “እርሱን ይገዜ አሄዳለሁ፤ እንዳ ደርግለት የምትፈልገውንም ሁሉ እደርግለታለሁ፤ ለአንተም ቢሆን የምትጠይቀውን ሁሉ እፈጽማለሁ” አለው። 39 ከዚህ በኋላ ዳዊትና ተከታዮቹ ሁሉ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻገሩ፤ ዳዊትም ባርዚላይን ሳመውና ባረከው፤ ባርዚላ ይም ወደ ቤቱ ተመልሶ ሄደ።

የይሁዳና የእስራኤል ሕዝብ ሰለ ንጉሥ ዳዊት ተከራከሩ

40 ንጉሥ ዳዊት በይሁዳ ሕዝብ ሁሉና በከፊል የእስራኤል ሕዝብ ታጅቦ ወንዙን ከተሻገረ በኋላ ወደ ጌልገላ አቀና፤ ኪምሃምም አብሮት ሄደ፤ 41 ከዚህ በኋላ እስራኤላውያን ሁሉ ወደ ንጉሡ ቀርበው “ንጉሥ ሆይ! ወንድሞቻችን የይሁዳ ሰዎች አንተን ወስደው የራሳቸው ለማ ድረግ፥ እንዲሁም አንተንና ቤተሰብህን፥ ተከ ታዮችህንም ሁሉ አጅበው የዮርዳኖስን ወንዝ ለማሻገር መብት እንዳላቸው ስለምን ያስባሉ?” ሲሉ ጠየቁት።
42 የይሁዳም ሰዎች “እኛ ይህን ያደረግነው ንጉሡ የእኛ ወገን ስለሆነ ብቻ ነው፤ ታዲያ እናንተስ በዚህ ነገር ስለምን ትቈጣላችሁ? እርሱ ለምግባችን ምንም የከፈለን ነገር የለም፤ ሌላም ምንም ነገር አልሰጠንም” ሲሉ መለሱላ ቸው።
43 እስራኤላውያንም “ምንም እንኳ እርሱ የእናንተ ወገን ቢሆን እናንተ ከምትፈልጉት ይበልጥ እኛ እንፈልገዋለን፤ ምክንያቱም ከመን ግሥቱ ዐሥሩ እጅ የሚገባው ለእኛው ነው፤ እናንተ እኛን የምትንቁት ስለምንድን ነው? ንጉሡን ስለመመለስ በመጀመሪያ ጥያቄ ያቀረ ብነው እኛ መሆናችንን ልትዘነጉ እይገባም” አሉአቸው።
ነገር ግን ከእስራኤል ሰዎች ይልቅ የይሁዳ ሰዎች ዳዊትን የራሳቸው ለማድረግ በብርቱ ተከራከሩ።

ምዕራፍ 20

ሼባዕ የፈጸመው ዐመፅ

1 በዚያን ጊዜ ሼባዕ ተብሎ የሚጠራ ጠባዩ የተበላሸ የማይረባ አንድ ሰው በጌልገላ ይኖር ነበር፤ እርሱም ትውልዱ ክብንያም ነገድ ሲሆን አባቱ ቢክሪ ይባላል፤ ይህም ሼባዕ መለ ከት ነፍቶ “ከዳዊት ጋር ምንም ድርሻ የለ ንም! ከእሴይ ልጅ ጋር ምንም ዕድል ፈንታ የለንም! የእስራኤል ሕዝብ ሆይ! እያንዳንድህ ወደ ቤትህ ግባ!” ሲል ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ። 2 ስለዚህም እስራኤላውያን ዳዊትን ከድተው ከሼባዕ ጋር ሄዱ፤ የይሁዳ ሕዝብ ግን ታማኝነታቸውን በማጽናት ከዮርዳኖስ እስከ ኢየሩሳሌም ዳዊትን ተከትለው ሄዱ።
3 ዳዊት በእየሩሳሌም ወደሚገኘው ቤተ መንግሥቱ በደረሰ ጊዜ፥ ቤተመንግሥቱን እን ዲጠብቁለት ትቶአቸው የነበሩትን ዐሥር ቊባ ቶቹን ወስዶ በዘበኛ አንዲጠበቁ አደረገ፤ የሚያ ስፈልጋቸው ነገር ሁሉ እንዲሰጣቸው አዘዘ፤ ይሁን እንጂ ከእነርሱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙ ነት አልፈጸመም፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞታቸው በዚት ተወሰነው እንደመበለ ቶች በመሆን ኖሩ።
4 ንጉሡም ዐማሳን “የይሁዳን ሰዎች ሁሉ ጠርተህ በአንድነት ሰብስብና ከነገ ወዲያ ይዘሃ ቸው ወደዚህ ተመለስ” አለው። 5 ዐማሳም ሊጠራቸው ሄደ፤ ነገር ግን ንጉሡ በቀጠረው ቀን ተመልሶ ሊመጣ አልቻለም። 6 ስለዚህ ንጉሡ አቢሻይን “ሼባዕ ከአቤሴሎም ይበልጥ የከፋ ችግር ይፈጥርብናል፤ ወታደሮቼን ይዘህ ተከታተለው፤ አለበለዚያ የተመሸጉ ከተሞቼን ይዞ ከእኛ እጅ ሊያመልጥ ይችላል” አለው።
7 ስለዚህ የኢዮአብ ወታደሮች፥ የንጉሡ የክ ብር ዘበኞችና ሌሎች ወታደሮችም ከአቢሻይ ጋር ከኢየሩሳሌም ወጥተው ሼባዕን በመከታተል አሳደዱት። 8 በገባዖን ወደሚገኘው ወደ ትልቁ ድንጋይ በደረሱ ጊዜ ዐማሳ አገኛቸው፤ በዚህን ጊዜ ኢዮአብ ስይፉን በስገባው ኩቶ፥ ስገባው ንም በመታጠቂያው ላይ አሰሮ ስመርነት ተዘጋ ጅቶ ነበር፤ እየተራመደ ወደ ፊት ሲሄድ ሳለም

ስይሱ ወደቀ ፤ 9 ኢዮአብም ዐማሳን “ወዳጄ ሆይ! እንደምንደን ነህ?” አለውና የሚስመው በማስመስል ረዙን በቀኝ እጁ ያዘ ፤ 10 ኢዮአብ በሌላው እጁ የያዘውን ስይፍ ስላላየ ዐማሳ አል ተጠነቀቀም ነበርና ኢዮአብ በሆዱ ሻጠበት ፤ የሆድ ዕቃውም መሬት ላይ ተዘረገፈ ፤ ወዲያ ውኑ ስለሞተም ኢዮአብ በድጋሚ አልወጋ ውም ።

ከዚህ በኋላ ኢዮአብና ወንድሙ አቢሻይ ሼባዕን ማሳደዳቸውን ቀጠሉ ። 11 ከኢዮአብ ወታደሮች አንዱ በዐማሳ ሬሳ አጠገብ ቆሞ “ኢዮአብንና ዳዊትን የምትከተሉ ሁሉ ኢዮአ ብን ተከተሉ!” ሲል ድምፁን ከፍ አድርጎ ተና ገረ ። 12 የዐማሳ ሬሳ በደም እንደተበከለ በመን ገዱ መካከል ተዘርሮ ነበር ፤ ያም ሰው የኢዮ አብ ወታደር ሁሉ ቆሞ ሲመለከት አይቶ ሬሳ ውን በመጐተት ወደ እርሻ ወሰደውና በልብስ ሸፈነው ። 13 ሬሳው ከመንገዱ መካከል ከተነሣ በኋላ ጭፍራ ሁሉ ሼባዕን ለማሳደድ ኢዮአብን ተከትለው ሄዱ ።

14 ሼባዕ በእስራኤል ነገዶች ግዛት ሁሉ አልፎ በመሄድ አቤልቤትማዕካ ወደተባለች ከተማ ደረሰ ፤ የቢክሪ ጐሳ አባሎች የሆኑ ሁሉ ተሰብስበው ሼባዕን በመከተል ወደ ከተማይቱ ገቡ ፤ 15 የኢዮአብ ወታደሮች ሼባዕ አዚያ መሆ ኑን ሰለሰሙ ሄደው ከተማይቱን ከበቡ ፤ በስተ ውጭ በኩል ቅጽሩን አስደግፈው የወሬር ቍልል ሠሩ ፤ ቀጥሎም ቅጽሩ እንዲወድቅ ከሥሩ መቈፈር ጀመሩ ፤ 16 በከተማይቱ ውስጥ የምትኖር አንዲት ብልህ ሴት በቅጽሩ ላይ ሆና ድምፅዋን ከፍ በማድረግ “ስሙ! ስሙ! ኢዮ አብ ወደዚህ ይመጣ ዘንድ ንገሩት ፤ እኔ ሳነጋግ ረው እፈልጋለሁ” አለች ። 17 ኢዮአብ ወደዚያ በሄደ ጊዜም ሴትዮዋ “ኢዮአብ የምትባለው አንተ ነህን?” ስትል ጠየቀችው ።

እርሱም “አዎ እኔ ነኝ!” አላት ።

እርስዋም “ጌታዬ! አሰቲ አድምጠኝ” አለ ችው ፤

እርሱም “እነሆ አዳምጥሻለሁ” አላት ።

18 እርሰዋም እንዲህ አለችው “በድሮ ዘመን ‘ወደ አቤል ከተማ ሄዳችሁ የጥያቄአችሁን መልስ ከዚያ ታገኛላችሁ’ ይባል ነበር ፤ ሰዎ ችም የሚያደርጉት ይህንኑ ነበር ። 19 የእኔ ከተማ ግን ታላቅ ከተማ ናት ፤ በእስራኤል ስላም የሰፈነባትና ታማኝ ከተማ እርስዋ ናት ፤ ታዲያ አንተ ይህችን ከተማ ለመደምሰስ ሰምን ታቅዳለህ ፤ የእግዚአብሔር ንብረት የሆነውን ነገር ለማፍረስ ትፈልጋለህን?”

20 ኢዮአብም እንዲህ ሲል መለሰ ፦ “እኔ ከተማችሁን አልደመሰስም ፤ ከቶም አላፈር ስም ፤ 21 የአኛ ዕቅድ ይህ አይደለም ፤ የተራራ ማው የኤፍሬም አገር ተወላጅ የሆነ ሼባዕ ተብሎ የሚጠራ የቢክሪ ልጅ በንጉሥ ዳዊት ላይ ዐመፅ አስነሥቶአል ፤ ብቻ ይህ ሰው ይስ ጠኝ እንጂ እኔ ከተማይቱን ለቅቄ አሄዳለሁ ።”

እርስዋም “ራሱን ቈርጠን በግንብ ላይ እን ወረውርልሃለን” አለችው ። 22 ይህንንም ዕቅድ በተግባር ለመግለጥ ወደ ከተማይቱ ሕዝብ ሄደች ፤ እነርሱም የሺባዕን ራስ ቈርጠው በግ ንቡ ላይ ለኢዮአብ ወረወሩለት ፤ እርሱም ወታ ደሮቹ ከተማይቱን ለቅው ይወጡ ዘንድ ምል ክት እንዲሆን ቀንደ መለከት ነፋ ፤ እነርሱም ወደየቤታቸው ተመለሱ ፤ ኢዮዓብም ንጉሡን ለማግኘት ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ።

የዳዊት ባለሟሎች

23 ኢዮአብ የእስራኤል ሠራዊት አዛዥ ሲሆን ፥ የዮዳሄ ልጅ በናያ የዳዊት ክብር ዘብ ጎላፊ ነበር ፤ 24 አዶኒራም ነፃ አገልግሎት የሚ ሰጡ ገባሮች ጎላፊ ሲሆን ፥ የአሒሉድ ልጅ ይሆሽፋጥ ታሪክ ጸሐፊ ነበር ፤ 25 ሱሳ የቤተ መንግሥት ጸሐፊ ሲሆን ፥ ሳዶቅና አብያታር ካህናት ነበሩ ፤ 26 አንዲሁም የያኢር ከተማ ተወላጅ የሆነው ዒራ ክዳዊት ካህናት አንዱ ነበር ።

ምዕራፍ 21

የሳኦል ዝርያዎች በሞት መቀጣት

1 በዳዊት ዘመነ መንግሥት ሦስት ዓመት ሙሉ ጽኑ ረሀብ ነበር ፤ ዳዊትም ስለዚህ ጒዳይ የእግዚአብሔርን ፊቃድ በጠየቀ ጊዜ እግዚአብ ሔር “ሳኦልና ቤተሰቡ ግድያ በመፈጸም በደል ሠርተዋል ፤ ሳኦልም የገባዖንን ሰዎች ፈጅቶ አል” ሲል መለሰለት ። 2 እንደሚታወቀው ሁሉ የገባዖን ሰዎች እስራኤላውያን አልነበሩም ፤ እነ ርሱ እስራኤላውያን ሊጠብቁአቸው ቃል ስለገ ቡላቸው ከአሞራውያን ተከፍለው ብቻቸውን የሚኖሩ ነበሩ ፤ ሳኦል ግን ለእስራኤልና ለይ ሁዳ ሕዝብ በነበረው ቅንአት ሊያጠፋቸው ዐቅዶ ነበር ። 3 ስለዚህም ዳዊት የገባዖንን ሰዎች በአንድነት ጠርቶ “የእግዚአብሔርን ሕዝብ ትመርቁ ዘንድ ቀድሞ በተፈጸመባችሁ ግፍ ፈንታ ካሣ የሚሆን አንድ ነገር ላደርግላችሁ አፈልጋለሁ ፤ ታዲያ ምን ላድርግላችሁ?” አላ ቸው ።

4 እነርሱም “ከሳኦልና ከቤተሰቡ ጋር ያለን ጥል በብርና በወርቅ የሚገታ አይደለም ፤ ከዚ ህም በቀር እኛ ከእስራኤል ወገን ማንንም መግ ደል አንፈልግም” ሲሉ መለሱለት ።

ዳዊትም “ታዲያ ምን እንዳደርግላችሁ ትፈ ልጋላችሁ?” ሲል ጠየቃቸው ።

21፡2 ፦ ኢያሱ 9፡3-15 ።

5እነርሱም “ሳኦል በሙሉ ሊያጠፋንና
ከእኛ መካከል ማንም ሰው በእስራኤል ምድር
በየትኛውም ስፍራ በሕይወት እንዳይኖር ፈልጎ
ነበር፤ 6ስለዚህ ከሳኦል ዝርያዎች ሰባት ወንዶ
ችን ለእኛ አሳልፈህ ስጠን፤ እኛም እነርሱን
እግዚአብሔር መርጦ በነገሠው በንጉሥ ሳኦል
ከተማ በጊብዓ በእግዚአብሔር ፊት እንሰቅላቸ
ዋለን” ሲሉ መለሱ።

ንጉሥ ዳዊትም “እነርሱን አሳልፌ እሰ
ጣችኋለሁ” አላቸው።

7ነገር ግን ዳዊትና ዮናታን እርስበርሳቸው
በገቡት የተቀደሰ ቃል ኪዳን ምክንያት ዳዊት
የሳኦልን የልጅ ልጅ የዮናታንን ልጅ መፊቦሼ
ትን አሳልፎ አልሰጣቸውም። 8ይሁን እንጂ
ዳዊት የአያ ልጅ ሪጽፋ ለሳኦል የወለደቻቸውን
ሁለቱን ወንዶች ልጆች እርሞኒንና መፊቦሼትን
ወሰደ፤ እንዲሁም የሳኦል ልጅ ሜራብ የመሖ
ላን ተወላጅ ለሆነው ለባርዚላይ ልጅ ለዐድሪ
ኤል የወለደችለትን አምስት ወንዶች ልጆች
ጨምሮ ወሰደ። 9ዳዊት እነዚህን ሁሉ ለገባዖን
ሰዎች አሳልፎ ሰጠ፤ እነርሱም በእግዚአብሔር
ፊት በተራራው ላይ ሰቀሉአቸው፤ ሰባቱም በአ
ንድነት ሞቱ፤ እነርሱም የተገደሉት በጸደይ
ወራት ማለቂያና በገብስ መከር መጀመሪያ ላይ
ነበር።

10ከዚህ በኋላ የሳኦል ቊባት የነበረችው
የአያ ልጅ ሪጽፋ ሬሳዎቹ ባሉበት ስፍራ እጠ
ገብ በሚገኘው ቋጥኝ ድንጋይ ላይ ማቅ ዘርግታ
ከሥሩ ተቀመጠች፤ እርስዋም ከመከር ጊዜ
መጀመሪያ እንሥቶ ዝናም እስከሚዋልበት ጊዜ
ድረስ እዚያ ቆየች፤ ቀን ቀን ወፎች በሬሳዎቹ
ላይ እንዳያርፉ፤ እየተከላከለች፥ ሌሊትም ሌሊ
ትም አውሬ እንዳይበላቸው ትጠብቃቸው
ነበር።

11ዳዊት ሪጽፋ ያደረገችውን በሰማ ጊዜ፥
12በገለዓድ ምድር ወደምትገኘው ወደ ያቤሽ
ሕዝብ ሄዶ የሳኦልንና የልጁን የዮናታንን ዐፅም
አመጣ፤ የያቤሽ ሕዝብ ዐፅሙን ያገኙት ፍልስ
ጥኤማውያን ሳኦልን በጊልቦዓ በገደሉበት ቀን
ሬሳዎችን ከሰቀሉበት ከቤትሻን አደባባይ በመስ
ረቅ ነበር። 13ዳዊት የሳኦልንና የዮናታንን
ዐፅም ወሰደ፤ እንዲሁም ተሰቅለው የነበሩትን
የሰባቱን ሰዎች አጽከሬን ሰበሰበ፤ 14ከዚህ በኋላ
የሳኦልንና የዮናታንን ዐፅም ወስደው በብንያም
ጼላዕ ተብሎ በሚጠራ ስፍራ በሳኦል አባት
በቂስ መቃብር ውስጥ በንጉሡ ትእዛዝ መሠ
ረት ቀበሩ፤ ይህ ሁሉ ከተፈጸመም በኋላ
ሕዝቡ ስለ አገራቸው ያቀረቡትን ጸሎት እግዚ
አብሔር ሰማ።

ከፍልስጥኤማውያን ጎያላን ጋር የተደረገ ጦርነት
(1 ዜ.መ. 20፡4-8)

15በፍልስጥኤማውያንና በእስራኤላውያን
መካከል የተደረገ ሌላም ጦርነት ነበር፤ ስለዚ
ህም ዳዊትና ተከታዮቹ ዘምተው ፍልስጥኤማ
ውያንን ወጉ፤ ከውጊያዎቹም በአንዱ ዳዊት
ደክሞት ነበር፤ 16ሦስት ኪሎ ተኩል የሚመ
ዝን ከነሐስ የተሠራ ጦር የያዘና አዲስ ሰይፍ
የታጠቀ ዩሽቢቦናብ ተብሎ የሚጠራ አንድ
ጎያል ሰው ዳዊትን ሰመግደል አስቦ ነበር፤
17ነገር ግን የጸሩያ ልጅ አቢሻይ ዳዊትን ሰመር
ዳት መጥቶ በዚያ ጎያል ሰው ላይ አደጋ በመ
ጣል ገደለው፤ ከዚያን በኋላ የዳዊት ተከታዮች
ዳግመኛ ከእነርሱ ጋር ወደ ጦርነት እንዳይሄድ
ዳዊትን ቃል በማስገባት “አንተ እኮ የእስራ
ኤል ተስፋ ነህ፤ ስለዚህ አንተን ማጣት አንፈል
ግም” አሉት።

18ከዚህ በኋላ ጎብ ተብሎ በሚጠራ ስፍራ
ከፍልስጥኤማውያን ጋር ጦርነት ተደረገ፤ በዚ
ህን ጊዜ የሑሻ ተወላጅ የሆነው ሲብካይ፥ ሳፍ
ተብሎ የሚጠራውን ጎያል ሰው ገደለ።

19ቀጥሎም በጎብ ሌላ ጦርነት ከፍልስጥኤ
ማውያን ጋር ተደረገ፤ በዚህም ጊዜ የቤተል
ሔም ተወላጅ የሆነው የያዒር ልጅ ኤልሐናን
የጋት ተወላጅ የሆነውንና የጦሩ ዘንግ እንደ
ሽማኔ መጠቅለያ የሆነውን ጎልያድ ተብሎ የሚ
ጠራውን ሌላ ፍልስጥኤማዊ ገደለ።

20ከዚህም በኋላ በጋት ላይ ጦርነት ተደ
ረገ፤ በዚያም ሥ ጦርነት የሚወድ አንድ ጎያል
ሰው ነበረ፤ ያም ጎያል ሰው በእጅቹና በእግ
ሮቹ ስድስት ስድስት ጣቶች ነበሩት፤ 21እር
ሱም እስራኤላውያንን በብርቱ ተፈታተነ፤
ይሁን እንጂ እርሱን የዳዊት ወንድም የሻማ
ልጅ ዮናታን ገደለው።

22እነዚህ አራቱ የጋት ጎያላን ሰዎች ዝርያ
ዎች ሲሆኑ ሁሉንም ዳዊትና አገልጋዮቹ ገደሉ
አቸው።

ምዕራፍ 22
የዳዊት የድል መዝሙር
(መዝ. 18)

1እግዚአብሔር ዳዊትን ከሳኦልና ከሌሎቹም
ጠላቶቹ እጅ በመታደግ ባዳነው ጊዜ ይዘን
መዝሙር ለእግዚአብሔር ከብር ዘመረ፦

2 እግዚአብሔር መጠጊያዬ፥
ጠንካራ ምሽጌና ታዳጊዬ ነው፤

21፡7 ፦ 1ሳሙ. 20፡15-17፤ 2ሳሙ. 9፡1-7። 21፡8 ፦ 1ሳሙ. 18፡19። 21፡12 ፦ 1ሳሙ. 31፡8-13።
21፡17 ፦ 1ነገ. 11፡36፤ መዝ. 132፡17።

3 እምላኬ መጠጊያዬ ሰሰሆነ
ከአርሱ ጋር በደኅንነት እኖራለሁ ፤
አርሱ እንደ ጋሻ ይከላከልልኛል ፤
ረዳቴም ሆኖ በሰላም ያኖረኛል ፤
እርሱ አዳኜ ሰለሆነ
ከችግር ይጠብቀኛል ፤ ያድነኛል ።
4 ምሰጋና የሚገባውን እግዚአብሔርን
እጠራለሁ ፤
እርሱም ከጠላቶቼ ያድነኛል ።

5 የሞት ጣር ከበበኝ ፤
የጥፋት ጕርፍም እጥለቀለቀኝ ፤
6 ሲኦል እንደ ገመድ ተጠመጠመብኝ ፤
ሞትም እንደ ወጥመድ ያዘኝ ፤
7 መከራ በደረሰብኝ ጊዜ
እግዚአብሔርን ጠራሁት ፤
እንዲረዳኝም አምላኬን ጠየቅሁት ፤
በመቅደሱ ሆኖ ድምጼን ሰማ ፤
የልመናዬንም ጩኸት አደመጠ ።

8 እግዚአብሔር ሰስተቈጣ
ምድር ተናወጠች ፤ ተንቀጠቀጠችም ፤
የሰማያት መሠረቶች ተናጉ ፤
ተነቃነቁም ፤
9 ከአፍንጫው የቊጣ ጢስ ወጣ ፤
ከአፉም የሚባላ የእሳት ነበልባልና
የሚያቃጥል ፍም ወጣ ።
10 ሰማይን ሰንጥቆ ወደ ታች ወረደ ፤
ከእግሩም በታች ጥቅጥቅ ያለ ደመና
ነበረ ፤
11 ኪሩቤል ተብለው በሚጠሩ መላእክት
ከንፍ ላይ
ተቀምጦ በረረ ፤
በነፋሰም ክንፎች ሳይ ሆኖ ወደ ላይ
መጠቀ ።
12 ሁሰንተናውን በጨለማ ሸፈነ ፤
በውሃ የተሞላ ጥቅጥቅ ያለ ደመና
ከበባቸው ፤
13 በፊቱ ካለው መብረቅ
የእሳት ነበልባል ወጣ ።

14 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር
አንደ ነጐድጓድ የሆነ ድምፁን
ከሰማይ አሰማ ፤
የልዑል እግዚአብሔር ድምፅ ተሰማ ።
15 ፍላጻውን ከቀሰቱ አሰፈነጠረ ፤
ጠላቶቹንም በተናቸው ፤
በመብረቁም ብልጭታ አሳደዳቸው ።
16 እግዚአብሔር ሆይ ! ጠላቶችህን በገሠጽህ
ጊዜ
የቊጣ ድምፅህንም ባሰማሃቸው ጊዜ ፥
የውቅያኖስ ወለል ታየ ፤
የምድርም መሠረት ተገለጠ ።

17 እግዚአብሔር ከላይ ሆኖ እጁን
በመዘርጋት ያዘኝ ፤
ከጥልቅ ውሃም ውስዞ ሰቦ አወጣኝ ።
18 በጣም በርትተውብኝ ከነበሩት
ከጎይለኞች ጠላቶቼና
ከሚጠሱኝ ሰዎች ሁሉ እጅ
እግዚአብሔር አዳነኝ ።
19 እኔ በተቸገርሁ ጊዜ በጠላትነት
ተነሡብኝ ፤
እግዚአብሔር ግን ጠበቀኝ ።
20 እግዚአብሔር ረድቶ ከአደጋ አወጣኝ ፤
በእኔ ደስ ስለተሰኘም
ከአደጋ የሚመልጥበትን ሰፊ መንገድ
ከፈተልኝ ።

21 እኔ መልካም ነገር ሰለማደርግ
እግዚአብሔር ዋጋዬን ይከፍለኛል ፤
ታማኝ በመሆኔም ያክሰኛል ።
22 እኔ የእግዚአብሔርን መንገድ
ተከትያለሁ ፤
ከአምላኬ የሚለየኝንም በደል
አልፈጸምኩም ።
23 የእግዚአብሔርን ሕግ ሁሉ ፊጽሜአለሁ ፤
ሥርዓቱንም አክብሬአለሁ ፤
24 እኔ ከበደል ነፃ መሆኔንና
ከፉ ነገር አለማድረጌን
እግዚአብሔር ያውቃል ።
25 እግዚአብሔር በፊቱ ያደረግሁትን
መልካም ነገርና ታማኝነቴን
ሰለሚያውቅ
ዋጋዬን ይከፍለኛል ።
26 አምላኬ ሆይ !
ታማኞች ለሆኑት ታማኝ ነህ ፤
ቅኖች ለሆኑት ቅን ነህ ።
27 ለንጹሐች ንጹሕ ነህ ፥
ለጠማሞች ጠማማ ነህ ።
28 ትሑቶችን ታድናለህ
ትዕቢተኞችን ግን ታዋርዳለህ ።

29 እግዚአብሔር ሆይ !
እንተ ለእኔ ብርሃኔ ነህ ፤
በእኔም ያለውን ጨለማ
ታስወግድልኛለህ ።
30 ጠላቶቼን የምቋቋምበትን ብርታት
ትሰጠኛለህ ፤
ወደ ምሽጋቸውም ዘልዬ እንድገባ
ኀይልን ትሰጠኛለህ ።

31 እግዚአብሔር በሥራው አንዴት ፍጹም
ነው !
ቃሉ እንዴት የታመነ ነው ፤
አርሱን መጠጊያ ለሚያደርጉት ሁሉ
ጋሻቸው ነው ።

32 ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ
የለም ፤
ከአርሱም በቀር መጠጊያ የሚሆን
የለም ።
33 ብርታትን የሚሰጠኝና
መንገዴን የሚያቃናልኝ እግዚአብሔር
ነው ።
34 አርሱ እግሮቼን እንደ ብሔር እግሮች
ያጠነክራል ፤
በከፍታ ቦታዎችም ላይ በሰላም
ያኖረኛል ።
35 እጆቼን ለሙርነት ያሠለጥናል ፤
የነሐስን ቀስት መሳብ እንዳችሉ
ክንዶቼን ያበረታል ።

36 አምላኬ ሆይ!
የምከላከልበትን ጋሻ ትሰጠኛለህ ፤
የአንተም ከብካቤ ታላቅ አድርጎኛል ።
37 በጠላት እንዳልማረክ
እርምጃዬን አስፋተሃል ፤
ዙሪያም በመሸነፍ ወድቄ አላውቅም ።
38 ጠላቶቼን አሳድጄ እይዛቸዋለሁ ፤
ሳላጠፋቸውም ወደ ኋላ አልመለስም ፤
39 ዳግመኛ እንዳይነሡ አድርጌ
እመታቸዋለሁ ፤
ተሸንፈውም በእግሬ ሥር
ይወድቃሉ ፤
40 ለሙርነት ኀይልን ትሰጠኛለህ ፤
በጠላቶቼ ላይ ድልን ታጐናጽፈኛለህ ፤
41 ጠላቶቼ ከፊቴ ወደ ኋላ እንዲሸሹ
ታደርጋለህ ፤
የሚጠሉኝንም ሁሉ ታጠፋቸዋለህ ።
42 የሚረዳቸውን በመፈለግ ይጮኻሉ ፤
ነገር ግን ማንም አያድናቸውም ፤
እግዚአብሔርንም ይጠሩታል ፤
እርሱ ግን አይመልስላቸውም ።

43 ትቢያ እስኪሆኑ ድረስ አደቃቸዋለሁ ፤
በመንገድ ላይ እንዳለ ጭቃም
እረግጣቸዋለሁ ።
44 ከዐመፀኛ ሕዝብ አዳንኸኝ ፤
በመንግሥታትም ላይ ገዥነቴን
አጸናህልኝ ፤
የማላውቀውም ሕዝብ ይገዛልኛል ።
45 ባዕድ የሆነ ሕዝብ
ዝናዬን ሰምቶ ይታዘዝልኛል ፤
በአህበሮችም እጅ ይንሣኛል ።
46 መኼኤቸው ጠፍቶ በፍርሃት ይጨነቃሉ ፤
በመንቀጥቀጥም ከምሽጋቸው እየወጡ
ወደ እኔ ይመጣሉ ።

47 እግዚአብሔር ሕያው ነው!
መጠጊያ የሆነኝ አምላክ ይመስገን ፤
ያዳነኝም ጎያል አምላክ ከፍ ከፍ
ይበል ።
48 እርሱ ጠላቶቼን ይበቀልልኛል ፤
መንግሥታትንም ከበታቼ አድርጎ
ያስገዛልኛል ።
49 ከጠላቶቼም ያድነኛል ።

እግዚአብሔር ሆይ!
በጠላቶቼ ላይ ድልን ታጐናጽፈኛለህ ፤
ከሚፈጽሙብኝም ታድነኛለህ ።
50 ስለዚህ በሕዝቦች መካከል
አመሰግንሃለሁ ፤
ስምህንም በዝማሬ አወድሳለሁ ።
51 መርጠህ ለቀባኸው ንጉሥ ለዳዊትና ለዘሩ
እግዚአብሔር ድልን በድል ላይ
ይሰጠዋል ፤
የማያቋርጥ ፍቅሩንም ለዘላለም
ያሳየዋል ።

ምዕራፍ 23

ዳዊት በመጨረሻ የተናገረው ቃል

1 የእሴይ ልጅ ዳዊት እግዚአብሔር ታላቅ
ያደረገው ፥ የያዕቆብ አምላክ ለንጉሥነት የመረ
ጠውና ውብ የሆኑ መዝሙሮችን ለእስራኤል
የተቀኘ ሰው ነበር ። ዳዊትም በመጨረሻ የተና
ገረው ቃል ይህ ነው ፤
2 የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ አማካይነት
ይናገራል ፤
ቃሉም ከከንፈሮቼ ይወጣል ፤
3 የእስራኤል አምላክ ይህን ተናግሮአል ፤
የእስራኤል ጠባቂ እንዲህ ብሎኛል ፤
“በፍትሕና አግዚአብሔርን በመፍራት
የሚያስተዳድር ንጉሥ ፥
4 ደመና በሌለበት ንጋት እንደሚያበራ ፥
ከዝናም በኋላ ሣሩን እንደሚያደምቅ
ፀሐይ ነው ።”

5 እግዚአብሔር ቤቴን (ዝርያዎቼን)
የሚባርከው
በዚህ ዐይነት ውኔታ ነው ፤
ምክንያቱም እርሱ ከእኔ ጋር የዘላለም
ቃል ኪዳን ገብቶአል ፤
የማይለወጥም የተስፋ ቃል ሰጥቶኛል ፤
እኔም የምመኘው ይህንኑ ብቻ ነው ፤
ይህም ለእኔ ድል ይሆንልኛል ፤
እግዚአብሔርም ይህን በእርግጥ
ይፈጽመዋል ።

22፡34 ፦ ዘዳ. 3፡19 ። 22፡50 ፦ ሮም 15፡9 ።

[6] ከሐዲዎች ግን እንደተጣለ እሾህ
ናቸው፤
ማንም በእጁ ሊዳሰሳቸው
አይደፍርም፤
[7] እነርሱን ለመዳሰስ የብረት ልብስ ወይም
ጦር ያስፈልጋል፤
በዚያን ጊዜ ፈጽመው ይቃጠላሉ።

ዝነኞች የሆኑ የዳዊት ወታደሮች
(1 ዜ.መ. 11፥10-41)

[8] ዝነኞች የሆኑት የዳዊት ወታደሮች ስም ዝርዝር ከዚህ በታች እንደተመለከተው ነው፤ የመጀመሪያው የታሕከሞን ተወላጅ ዮሼብ ባሼ ቤት የተባለው ሲሆን እርሱም ከሦስቱ ጎያላን ብልጫ ያለው ተቀዳሚ ነው፤ ይህ ሰው በአንድ ውጊያ ላይ ጦሩን አንሥቶ ስምንት መቶ ጎያላን ሰዎችን ገደለ።

[9] ከሦስቱ ጎያላን ሁለተኛው ከአሖሕ ጉሳ የሆነው ዝነኛው የዶዶ ልጅ ኤልዓዛር ነበር፤ አንድ ቀን እርሱና ዳዊት ለጦርነት ተሰልፈው የነበሩትን ፍልስጥኤማውያን ተገዳደሩ፤ እስራኤላውያን ወደ ኋላቸው አፈገፈጉ፤ [10] ይህ ሰው ግን ባለበት ጸንቶ በመቆም እጁ ዝሎ በሰይፉ ላይ እስኪጣበቅ ድረስ ፍልስጥኤማውያንን ወጋ፤ በዚያን ቀን እግዚአብሔር ታላቅ ድልን አደረገ፤ ጦርነቱም ከቆመ በኋላ እስራኤላውያን ኤልዓዛር ወደነበረበት ስፍራ ተመልሰው ከሞቱት ፍልስጥኤማውያን ብዙ የጦር ልብስ ማረኩ።

[11] ከሦስቱ ጎያላን ሦስተኛው ደግሞ የሃራር ተወላጅ የሆነው ዝነኛው የአጌ ልጅ ሻማ ነበር፤ አንድ ቀን ፍላጥኤማውያን የአተር ማሳ ባለበት በሌሒ ተሰልፈው ነበር፤ እስራኤላውያንም ከፍልስጥኤማውያን ፊት ሸሹ፤ [12] ሻማ ግን በዚያው በማሳው ውስጥ ጸንቶ ቆመ፤ በመከላከልም ፍልስጥኤማውያንን ገደለ፤ በዚያም ቀን እግዚአብሔር ታላቅ ድልን አደረገ።

[13] በመከር ጊዜ መጀመሪያ ላይ ከሠላሳው ጎያላን ቢተለይ ሦስቱ ዳዊት ወዳለበት ወደ ዐዱላም ዋሻ ወረዱ፤ ከፍልስጥኤማውያን ሠራዊት ጥቂቱ ከፍል በራፋይም ሸለቆ ሰፍሮ ነበር፤ [14] ዳዊት በዚያን ጊዜ በተመሸገ ኮረብታ ላይ ነበር፤ ከፍልስጥኤማውያን ሠራዊት አንድ ቡድን ቤተልሔምን በመውረር ያዘ፤ [15] ዳዊትም አገሩን በመናፈቅ "በቤተልሔም ቅጽር በር አጠገብ ካለው የውሃ ጕድጓድ የምጠጣው ውሃ የሚያመጣልኝ ሰው ምነው ባገኘሁ!" አለ። [16] ስለዚህ ዝነኞች የሆኑት ሦስቱ ጎያላን ወታደሮች የፍልስጥኤማውያንን ሰፈር በድፍረት ጥሰው በማለፍ ከጕድጓዱ ውሃ ቀድተው ለዳዊት ይዘውለት መጡ፤ ዳዊት ግን ሊጠጣ አልወደደም፤ ይህንንም በማድረግ ፈንታ ለእግዚአብሔር መባ አድርጎ ካፈሰሰው በኋላ፥ [17] "እግዚአብሔር ሆይ! ይህን ውሃ ከቶ ልጠጣው አልችልም! እኔ እርሱን ብጠጣ፤ በነፍሳቸው ቈርጠው የሄዱትን የእነዚህን ጎያላን ሰዎች ደም እንደጠጣሁ ይቈጠራል" አለ፤ ውሃውንም መጠጣት እምቢ አለ።

ዝነኞች የሆኑት ሦስቱ ጎያላን ወታደሮች የፈጸሙአቸው የጀግንነት ተግባሮች እነዚህ ናቸው።

[18] የጸሩያም ልጅ የኢዮአብ ወንድም አቢሻይ ዝነኞች የሆኑት የሠላሳዎቹ ወታደሮች አለቃ ነበር፤ እርሱም ጦሩን አንሥቶ ከሦስት መቶ ሰዎች ጋር በመዋጋት ሁሉንም ገደለ፤ ስለዚህም እንደ ሦስቱ ዝነኛ ሆነ። [19] ከሠላሳዎቹ መካከል እጅግ ዝነኛ በመሆኑም የእነርሱ አለቃ ሆነ፤ ይሁን እንጂ የሦስቱን ጀግኖች ያህል ዝነኛ አልነበረም።

[20] ሌላው ዝነኛ ወታደር የቃብጽኤል ተወላጅ የነበረው የይዖያዳዕ ልጅ በናያ ነበር፤ እርሱም ሁለት የታወቁ ሞአባውያን ወታደሮችን ከመግደሉም ሌላ ብዙ የጀግንነት ሥራ ፈጽሞ አል፤ አንድ ጊዜ በምድር ላይ ዐመዳይ በወረደበት ቀን ወደ አንድ ዋሻ ወርዶ አንበሳ ገደለ፤ [21] እንዲሁም ጦር ይዞ የነበረውን አንድ ጎያል ግብጻዊ ገድሎአል፤ ይኸውም በናያ በእጁ ከበትር በስተቀር ሌላ የጦር መሣሪያ ሳይዝ ወደ ግብጻዊው ቀርቦ የገዛ ጦሩን በመቀማት በዚያው ጦር ግብጻዊውን ገደለው። [22] እንግዲህ እንደ ሦስቱ ጎያላን ዝነኛ የሆነው በናያ የፈጸማቸው የጀግንነት ሥራዎች እነዚህ ናቸው፤ [23] ከሠላሳዎቹ መካከል እጅግ ታዋቂ ቢሆንም በዝነኛነቱ ከሦስቱ ጎያላን ደረጃ አልደረሰም፤ ዳዊትም በናያን የከብር ዘቡ አዛዥ አድርጎ ሾሞት ነበር።

[24-39] ከሠላሳዎቹ መካከል የሌሎቹ ሰዎች ስም ዝርዝር የሚከተለው ነው፦

የኢዮአብ ወንድም ዐሣሄል፤
የቤተልሔሙ ተወላጅ የዶዶ ልጅ
ኤልሐናን፤
የሐሮድ ተወላጆች የሆኑት ሻማና
ኤሊቃ፤
የፈሌጥ ተወላጅ የሆነው ሔሌጽ፤
የተቆዓ ተወላጅ የሆነው የዒቋሽ ልጅ
ዒራ፤
የዐናቶት ተወላጅ የሆነው አቢዔዘር፤
የሑሻ ተወላጅ የሆነው መቡናይ፤
የአሖሕ ተወላጅ የሆነው ጻልሞን፤
የነጦፋ ተወላጅ የሆነው ማህራይ፤
የነጦፋ ተወላጅ የሆነው የባዕና ልጅ
ሔሌብ፤
በብንያም ግዛት የምትገኘው የጊብዓ
ተወላጅ የሆነው የሪባይ ልጅ
ኢታይ፤

የጦርናዥን ተወላጅ የሆነው በናያ ፥
በጋዓሽ ሸለቆ አጠገብ የተወለደው
ሂዳይ ፥
የዓርባ ተወላጅ የሆነው አቢዓልቦን ፥
የባርሑም ተወላጅ የሆነው ዓዝማዌት ፥
የሻዓልቦን ተወላጅ የሆነው ኤልያሕባ ፥
የያሼን ልጆች ፥
ዮናትን ፥
የሃራር ተወላጅ የሆነው ሻማ ፥
የአራር ተወላጅ የሆነው የሻራር ልጅ
አሒአም ፥
የማዕካ ተወላጅ የሆነው የአሐስባይ ልጅ
ኤሊፌሌጥ ፥
የጊሎ ተወላጅ የሆነው የአኪጦፌል ልጅ
ኤሊዓም ፥
የቀርሜሎስ ተወላጅ የሆነው ሔጽሮ ፥
የአረብ ተወላጅ የሆነው ፓዓራይ ፥
የጸባ ልጅ የሆነው የናታን ልጅ ዑግአል
የጋድ ተወላጅ የሆነው ባኒ ፥
የዐሞን ተወላጅ የሆነው ጼሌቅ ፥
የኢዮአብ ጋሻ ጃግሬ የነበረውና የበኤሮት
ተወላጅ የሆነው ናሕራይ ፥
የያቲር ተወላጆች የሆኑት ዒራና ጋሬብ ፥
ሒታዊው ኦርዮን ።
ዝነኞች የሆኑት ጎያላን ወታደሮች ጠቅላላ
ድምር ሠላሳ ሰባት ነበር ።

ምዕራፍ 24

ዳዊት የሕዝብ ቈጠራ አደረገ
(1 ዜ.መ. 21፥1-27)

1 እግዚአብሔር እንደገና በእስራኤል ላይ
ስለተቈጣ በዳዊት አማካይነት መከራ እንዲመ
ጣባቸው አደረገ ፤ እግዚአብሔር ዳዊትን
“ሂድህ የእስራኤልንና የይሁዳን ሕዝብ
ቍጠር” አለው ፤ 2 ስለዚህም ዳዊት የጦሩ
አዛዥ የሆነውን ኢዮአብን “የጦር መኰንኖች
ሀን በማስከተል ከአገሩቱ ዳር እስከ ዳር ማለ
ትም ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ወዳሉት የእስራኤል
ነገዶች ሁሉ ሂደህ ሕዝቡን ቍጠር ፤ ምን
ያህል ሕዝብ እንዳለ ማወቅ እፈልጋለሁ” ሲል
አዘዘው ።

3 ኢዮአብ ግን “ንጉሥ ሆይ! አምላክህ እግ
ዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ አሁን ካሉት
ይልቅ ስሙቶ እጅ ያብዛልህ ፤ ይህንንም ሲያደ
ርግ ሰማየት እንድትበቃ ዕድሜህን ያርዝም
ልህ ፤ ነገር ግን ንጉሥ ሆይ! ይህን ለማድረግ
ስለምን ፈለግህ?” አለው ፤ 4 ንጉሡ ግን ኢዮአ
ብና የጦር መኰንኖቹ ትእዛዙን እንዲፈጽሙ
ስላስገደዳቸው ከፊቱ ወጥተው የእስራኤልን
ሕዝብ ለመቍጠር ሄዱ ።

5 ዮርዳኖስንም ተሻግረው በጋድ ውስጥ በሚ
ገኘው ሸለቆ መካከል ባለችው በዓሮዔር ከተማ
በስተ ደቡብ ሰፈሩ ፤ ከዚያም ወደ ሰሜን አምር
ተው ወደ ያዕዜር ደረሱ ፤ 6 ቀጥለውም ወደ ገለ
ዓድና በሐታውያን ግዛት ውስጥ ወዳለው ወደ
ቃዴስ ዘለቁ ፤ ከዚያም በኋላ ወደ ዳን ፥ ከዳንም
ወደ ምዕራብ ታጥፈው ወደ ሲዶና ሄዱ ፤ 7 ቀጥ
ሎም በደቡብ በኩል ወደተመሸጉትም ወደ
ጢሮስ ከተማና አንዲሁም ወደ ሒዋውያንና
ወደ ከነዓናውያን ከተሞች ሁሉ ሄዱ ፤ በመጨ
ረሻም በይሁዳ ወደምትገኘው ወደ ቤርሳቤህ
ዘለቁ ፤ 8 በዚህ ዐይነት በመላ ሀገሪቱ ሲዘዋወሩ
ቆይተው ዘጠኝ ወር ከሃያ ቀን ከሆናቸው በኋላ
ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ፤ 9 በእስራኤል ስም
ንት መቶ ሺ ፥ በይሁዳ አምስት መቶ ሺ በውት
ድርና ለማገልገል ብቃት ያላቸው ሰዎች መኖ
ራቸውንም ለንጉሡ አሳወቁ ።

10 ነገር ግን ዳዊት ሕዝቡን ከቈጠረ በኋላ
የሕሊና ወቀሳ ስላሰጨነቀው እግዚአብሔርን
“እኔ ይህን በማድረጌ ታላቅ በደል ፈጽሜአ
ለሁ ፤ የሞኝነት ሥራ ስለሠራሁም እባክህ
ይቅር በለኝ” ሲል ለመነ ።

11-12 እግዚአብሔርም የዳዊትን ነቢይ ጋድን
“ሂደህ ዳዊትን ‘እንሆ ሦስት ምርጫ ስጥቼሃ
ለሁ ፤ እኔም አንተ የምትመርጠውን እደርጋ
ለሁ’ ይላል” ብለህ ንገረው ፤ በማግሥቱ ጠዋት
ዳዊት ከእንቅልፉ ከተነሣ በኋላ ፥ 13 ጋድ ወድ
እርሱ ቀርቦ እግዚአብሔር ስለ እርሱ ያለውን
ነገረው ፤ ቀጠል አድርጎም “በምድርህ ሦስት
ዓመት ረሀብ ከሚሆን ፥ ለሦስት ወር ጠላቶችህ
ከሚያሳድዱህ በምድርህ ላይ ለሦስት ቀን የቸ
ነፈር መቅሠፍት ከሚሆን የትኛውን ትመርጣ
ለህ? እንግዲህ በብርቱ አስብበትና ወደ እግዚአ
ብሔር የማቀርበውን መልስ ስጠኝ” ሲል ጠየ
ቀው ።

14 ዳዊትም “እንሆ እኔ ለምርጫ በሚያስቸ
ግር ውጌታ ላይ ነኝ ፤ ይሁን እንጂ በሰው እጅ
መውደቅ አልፈልግም ፤ እግዚአብሔር መሐሪ
ስለሆነ እርሱ ራሱ ይቅጣኝ” አለ ። 15 ስለዚህ
እግዚአብሔር ከዚያን ጠዋት ጀምሮ እስከወሰ
ነው ቀን ድረስ በእስራኤል ላይ ቸነፈር
አመጣ ፤ በዘገሪቱ ዳር እስከ ዳር ማለትም ከዳን
እስከ ቤርሳቤህ ድረስ ሰባ ሺ እስራኤላውያን
አለቁ ። 16 የእግዚአብሔር መልአክ ኢየሩሳሌ
ምን ለመደምሰስ በሚዘጋጅበት ጊዜ እግዚአብ
ሔር ሕዝቡን ስለመቅጣት ያለውን ውሳኔ
ለውጦ ይቀሥፋቸው የነበረውን መልአክ
“በቃህ! አቁም!” አለው ፤ በዚህንም ጊዜ መል
አኩ በኢያቡሳዊው በአርና አውድማ ላይ ቆሞ
ነበር ።

17 ዳዊትም ሕዝቡን ይቀሥፍ የነበረውን
መልአክ አይቶ እግዚአብሔርን “በደል የፈጸም
ሁት እኔ ነኝ ፤ እኔም ራሴ ክፉ ነገርን አደረ
ግሁ ፤ ታዲያ ይህ ምስኪን ሕዝብ ምን በደለህ?
ይህ መቅሠፍት በእርሱ ላይ ከሚወርድ ይልቅ
በእኔና በቤተሰቤ ላይ ይሁን” ሲል ጠየቀ ።

[18] በዚያው ዕለት ነቢዩ ጋድ ወደ ዳዊት ሄዶ “ወደ አርና አውድማ ሄደህ ለእግዚአብሔር መሠዊያውን ሥራ” አለው፤ [19] ዳዊትም ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ጋድ እንደነገረው አደረገ፤ [20] አርናም ወደ ታች ሲመለከት ንጉሥ ዳዊትና ባለሟሎቹ የሆኑት ባለሥልጣኖች ወደ እርሱ ሲመጡ አየ፤ እርሱም በዳዊት ፊት ሰግዶ ብሎ እጅ በመንሣት፥ [21] “ንጉሥ ሆይ! ሰለምን ወደዚህ መጣህ?” ሲል ጠየቀው።

ዳዊትም “እግዚአብሔር የቸነፈሩን መቅሠፍት እንዲመልስ የአንተን አውድማ ለመሣዘትና በዚያውም ላይ መሠዊያ ለመሥራት ነው የመጣሁት” አለው።

[22] አርናም “ንጉሥ ሆይ! አውድማውን ወስደህ በፈቀድከው ዐይነት ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቅርብበት፤ በመሠዊያውም ላይ የሚቃጠል መሥዋዕት ሆነው ይቀርቡ ዘንድ እነሆ እነዚህ በሬዎች አሉ፤ ስለ ማገዶም ጕዳይ እንርሱ የሚጠመዱበት ቀንበርና የእህል መውቂያው እንጨት ሁሉ አለ” አለው። [23] አርናም “ይህን ሁሉ ለንጉሡ ሰጥቶ እግዚአብሔር መሥዋዕትህን ይቀበልልህ” አለው።

[24] ንጉሥ ዳዊት ግን “ይህስ አይሆንም፤ ዋጋውን መክፈል አለብኝ፤ እኔ ምንም ዋጋ ያላ ወጣሁበትን ነገር ለአምላኬ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጌ ማቅረብ አይገባኝም” አለው፤ ከዚህም በኋላ ዳዊት አውድማውንና በሬዎቹን በጎምሳ ዋሬ ብር ገዛ፤ [25] ለእግዚአብሔርም መሠዊያ ሠርቶ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና ለደኅንነት የሚሆነውን የኅብረት መሥዋዕት ሁሉ አቀረበ፤ እግዚአብሔርም የዳዊትን ጸሎት ሰማ፤ በእስራኤል ላይ የወረደውም የቸነፈር መቅሠፍት ከዚህ በኋላ ቆመ።

መጽሐፈ ነገሥት

ክፍል አንድ

መግቢያ

መጽሐፈ ነገሥት ክፍል አንድ፣ በሁለቱ የሳሙኤል መጻሕፍት ተጀምሮ የነበረው የእስራኤል ንጉሣዊ አገዛዝ ታሪክ ተከታይ ነው። መጽሐፉ በሦስት ዋና ዋና ከፍሎች ሊመደብ ይች ላል፦

1. በሰሎሞን በአባቱ በዳዊት እግር ተተክቶ የእስራኤልና የይሁዳ ንጉሥ ስለ መሆኑና ስለአ ባቱም ስለ ዳዊት ሞት የሚተርክ ነው።
2. የሰሎሞን መንግሥት አጭምና ያከናወናቸውን ሥራዎች የሚገልጥ ታሪክ ሲሆን ከእነዚ ህም ሥራዎች ጕላ ያለው በኢየሩሳሌም የተገነባው ቤተ መቅደስ ነው።
3. እስራኤል የሰሜንና የደቡብ መንግሥት ተብላ በመጠራት ስሁለት ስለ መከፈልዋና እያ ንዳንዱንም መንግሥት ከክርስቶስ ልደት በፊት እስከ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት ስላስቡዳ ደሩ ነገሥታት የሚተርክ ነው።

በእነዚህ በሁለቱ መጻሕፍት እያንዳንዱ መሪ የሚፈረድበት ለእግዚአብሔር በሚያሳየው ታማኝነት ደረጃ መጠን ነበር፤ እንዲሁም የየአገሩም ዕድገትና መሳካት የሚለካው በዚሁ መሪ ዎቹ በሚያሳዩት ታማኝነት መጠን ነበር፤ በሌላ በኩል የባዕድ አምልኮን መከተልና እለመታ ዘዝ፥ መሪዎቹንም ሆነ ሕዝቡን ወደ ጥፋት ይመራቸው ነበር። የሰሜኑ መንግሥት ነገሥታት በሙሉ በፈተና የወደቁ ሲሆኑ፥ የይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ግን ስለክፉዎቹም፣ ስለደኅኖቹም የሚ ያወሳ ነው።

በመጽሐፈ ነገሥት ክፍል አንድ ውስጥ በጣም ታዋቂ የሆኑት፥ እነዚያ እግዚአብሔርን ወክ ሰው የትንቢት ቃል የሚያስተላልፉትና ሕዝቡም የጣዖት አምልኮ እንዳይከተሉና እግዚአብሔ ርንም መታዘዝ እምቢ እንዳይሉ ያሰጠነቅቁአቸው የነበሩ ቈራጮች ነቢያት ነበሩ፤ ከእነርሱም በጣም ታዋቂ የነበረው ኤልያስ ሲሆን፥ እርሱ ከባዓል ካህናት ጋር ያደረገው ተጋዳድሮት ሥምር ተገልጦአል (ም. 18 ተመልከት)።